መስከረም



የማርክሲስት ሌኒኒስት ርዕዮተ ዓለም መጽሔት

ቅጽ 1 ቁጥር 3
መጋቢት 1973

INFINIX HOT 8 | 13MP
AI TRIPLE CAMERA

መስከረም

ቅጽ 1 ቁጥር 3
መጋቢት 1973

የማርክሲስት ሌኒኒስት ርዕዮተ ዓለም መጽሔት

ማ ው ጫ

ገጽ

- የዝግጅት ገፅ - - - - - - - - - - - - - - - - - 3
- ኮምኒስት ማለት ምን ማለት ነው? - - - - - - - - - - 7
  - ገዛኸኝ ገብሬ
- ማርክሳዊ የፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ግንዛቤ - - - - - - - - - - - - 27
  - አምሃ ዳኘው
- የኢትዮጵያ ሕዝብ የነፃነት ትግልና የኢጣልያን ፋሽሽት ወረራ - - - - 37
  - በኢሠፓኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ የርዕዮተ ዓለም መምሪያ
  — የአብዮት ታሪክ ክፍል —
- የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም በቀድመ አብዮት ኢትዮጵያ - - - - 55
  - ለገሠ ለማ
- የጊዜያችን ፀረ-ኢምፔሪያሊስት ትግል
  — የላቲን አሜሪካ ሕዝብ የብሔራዊ አርነት ንቅናቄ - - - - 70
  - ብርሃኑ ዘሪሁን
- የነጋድራስ ገ/ሕይወት ባይከዳኝ የፖለቲካዊ ኢኮኖሚ አስተሳሰብ - - - - 84
  - አየለ ዘውገ

በኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ

ርዕዮተ ዓለም መምሪያ እየተዘጋጀ በየሦስት ወር የሚወጣ ፡፡

አድራሻ

የፖስታ ሣጥን ቁጥር — 80001
የስልክ ቁጥር — 113000

INFINIX HOT 8 | 13MP
AI TRIPLE CAMERA

ያለ አብዮቲዊ ንድፈ ሃሳብ
አብዮታዊ እንቅስቃሴ ሊኖር አይችልም !

INFINIX HOT 8 | 13MP
AI TRIPLE CAMERA

የዝግጅት ገፅ

ለዘላቂው ድል አስተማማኝ መሠረት

በማናቸውም አገር አብዮታዊ ሂደት ውስጥ የአብዮቱን ዓላማዎች እግብ ለማድረስና የሶሺያሊስት ኅብረተሰብ መመሥረትን ለማረጋገጥ የማሌ ንድፈ ሐሳብን የተገባር መመሪያው ያደረገ ፓርቲ አመራር ወሳኝነት ተደጋግሞ የተረጋገጠ ሐቅ ነው ፡፡ በኢትዮጵያም አብዮት ሂደት ውስጥ የዚህ የፓርቲ አስፈላጊነት በተደጋጋሚ ሲስተጋባ ቆይቷል፡፡

የሶሺያሊስት አብዮት በማካሄድ የሶሺያሊስት የኢኮኖሚ ግንባታቸውን ካከናወኑና በማከናወንም ላይ ከሚገኙ የሶሺያሊስት ሀገሮች ተጨባጭ ልምድ እንደምንረዳው ፤ ለፍትህ ለእኩልነትና ለሶሺያሊዝም የሚታገል ማናቸውም አብዮት ውስብስብ በሆነው የመደብ ትግል አቀራርጦ የሠራተኛውን መደብ የበላይነት ሊያሰፍን የሚችለው በማሌ የሠራተኛው መደብ ፓርቲ ሲመራ ብቻ ነው ፡፡

የሶሺያሊስቱን የእድገት ፈለግ በሚከተሉ ሀገሮች ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮቱን ወደ ሶሺያሊስት አብዮት ለማሸጋገርና ውስብስብና ከባድ የሆነውን የሶሺያሊስት የኢኮኖሚ ግንባታ ለማከናወን የማኅበራዊ የእድገት ሕግጋትን ፤ በተለይም ደግሞ የሽግግር ወቅት ሕግጋትን በሚገባ መገንዘብን ይጠይቃል ፡፡ ይህ ዓይነት ሳይንሳዊ ግንዛቤ ያለውና ፤ ግንዛቤውንም ለሰፊው ሕዝብ በማስታጠቅ ተግባራዊ እንዲሆን ሊያደርግ የሚችለው ደግሞ የማ.ሌ. የሠራተኛ መደብ ፓርቲ ብቻ ነው ፡፡ ፓርቲው በሳይንሳዊ የማሌ ንድፈሃሳብ መመራቱም በኅብረተሰቡ ውስጥ የግንባር ቀደም ሚናውን የተረጋገጠ ያደርገዋል ፡፡ ሌኒን ይህን በማስመልከት ሲፅፍ «የግንባር ቀደም ተዋጊነት ሚናውን ሊያሟላ የሚችለው ፓርቲው በአብዮታዊ ንድፈሃሳብ የታጠቀ እንደሆነ ብቻ ነው ፤» ይላል ፡፡

ያለ አብዮታዊ ንድፈሃሳብ አብዮታዊ እንቅስቃሴ ሊኖር እንደማይችል፤ የአብዮታዊ ንድፈሃሳብ ኃያልነት ሊረጋገጥ የሚችለው ደግሞ ርእዮተዓለማዊ አንድነት በድርጅታዊ አንድነት ሲደገፍ ብቻ ነው ፡፡ ይህ የርእዮተዓለማዊና የድርጅታዊ አንድነት የሚከሰትበትም የሠርቶ-አደሩ መደብ የማሌ ፓርቲው ነው ፡፡ ሠርቶ-አደሩ ሕዝብ ከሳይንሳዊ ሶሺያሊዝም ጋር የሚዋሃድበትና ለነቃ የመደብ ትግል የሚበቃበት ፤ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ጥቅሙን ለዘለቄታው ሊያስከብር የሚችልበት በአብዮታዊ ፓርቲው ሲመራ ብቻ ነው ፡፡

የኢትዮጵያ አብዮት ለፍትህ ለእኩልነትና ለሶሺያሊዝም የሚታገል አብዮት ነው ፡፡ አብዮቱ ባለፉት ስድስት መራራ የትግል ዓመታት ከፍተኛ ድሎች ተጐናጽፏል ፡፡ ለሶሺያሊስት አብዮቱ ጥርጊያ መንገድ በመክፈት ላይ ያለው የብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮቱ እየጐለበተ በመምጣት ላይ ይገኛል ፡፡ ሆኖም ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮቱን ወደ ሶሺያሊስት አብዮቱ ለማሸጋገር አብዮቱ የፓርቲ አመራርን ማግኘቱ ወሳኝ ነው ፡፡

የኢትዮጵያ አብዮታውያን በአብዮታዊው መንግሥት መሪነት አንድወጥ የፖለቲካ ፓርቲ ለማስገኘት እስከ ዛሬ ያደረጉት ትግል ከፍተኛ ነው ፡፡ ይህን ዓይነት አንድ ወጥና መሪ የፖለቲካ ፓርቲ ለማስገኘት የተካሄደው ትግል ቀላል ባይሆንም ፤ ትግሉ ፍሬ አፍርቶ ፓርቲውን የሚያደራጅ ኮሚሽን ማለትም ኢሠፓአኮ ተቋቁሟል ፡፡

ለአዲስ ሥርዓት ምሥረታ ቅድመ ሁኔታ የሆነውን ፓርቲ ለማስገኘት ፤ ፓርቲውን በማዋቀሩ ሂደት የመጀመሪያው ጥንስስ የተጣለው በኢሠፓአኮ አንደኛ ጠቅላላ ጉባኤ በመሆኑ ፤ ይህ ጉባኤ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ አዲስ ምዕራፍ ከፋች ነው ፡፡

INFINIX HOT 8 | 13MP
AI TRIPLE CAMERA

ይህን ዓይነት አብዮታዊ ፓርቲ ለመመሥረት በኢሠፓአኮ አማካይነት የሚካሄደው ዝግጅትና የሚመሠረተውን ፓርቲ ጥንካሬና ጥራት ለመጠበቅ የሚካሄደው ትግል ለኢትዮጵያ አብዮት ዋስትና የሚሰጥ መሆኑ እሙን ነው ። ጓድ ሊቀመንበር መንግሥቱ ኃይለማርያም ለኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ ሁለተኛ መደበኛ ስብሰባ በአቀረቡት ማዕከላዊ ሪፖርት ላይ ይህን በማስመልከት «የአንድ የፖለቲካ ድርጅት ጥንካሬ የሚወሰነው በአባላቱ ቁጥር ብዛት ወይንም ማነስ ብቻ ሳይሆን ይበልጡኑ በይዘታቸው ማለትም ለድርጅታዊ መርሆዎች ባላቸው ተገዥነት በርእዮተዓለማዊና ድርጅታዊ አንድነት ላይ በመመሥረትና ባላቸው ዲሲፕሊን ነው» በማለት አስገንዝበዋል ።

የማ.ሌ የፖለቲካ ድርጅት የግንባር ቀደም መሪነቱን ሚና በሚገባ ሊወጣ የሚችለው ትክክለኛ የሆነ የርእዮተዓለም ግንዛቤ ሲኖረውና በዚህም ላይ ተመሥርቶ ትክክለኛ የፖለቲካ መስመር ሲቀይስ ብቻ ነው ። ኢሠፓአኮ ካሉት ተቀዳሚ ዓላማዎች መካከል አንደኛው ማ.ሌን በሰፊው ሕዝብ ውስጥ ማሠራጨት እንደሆነ ግልፅ ነው ። በመደብ ትግሉም ሆነ በግንባታው ሂደት የነቃ ተሳትፎ እንዲኖረው በሰፊው ሕዝብ መካከል ፣ በተለይም በሠራተኛው መደብ ውስጥ የማ.ሌ ንድፈ ሐሳብን ማሠራጨትና ርእዮተዓለሙን የማስታጠቁ ተግባር ወሳኝ ነው ።

ሠርቶ-አደሩን ሕዝብ በወዝአደሩ ርእዮተዓለም የማስታጠቁ ያላሰለሰ ተግባር በተገቢው ሊሳካ የሚችለው ደግሞ የኢሠፓአኮ አባላት በርእዮተዓለም ብስለታቸውም ሆነ በድርጅታዊ ሥራቸው ከመላው ሠራተኛ ሕዝብ በእርግጥም ግምባር ቀደም ሆነው የተገኙ እንደሆነ ብቻ ነው ። የኢሠፓአኮ አባላት በዚህ ረገድ የሚጠበቅባቸው ኃላፊነት እጅግ ከባድ ነው ።

በተያያዝነው የግንባታና የፓርቲ ምሥረታ ወቅት የኢሠፓአኮ አባላት የማ.ሌ ንድፈ ሐሳብን በሚገባ መጨበጥ ተቀዳሚ ተግባራቸው መሆኑን የኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ ውሳኔ አስረድቷል ። በተጨማሪም በአሁኑ ጊዜ የመደብ ትግሉ ለደረሰበት የእድገት ደረጃና ፊታችን ላይ ለተደቀነው ውስብስብ የግንባታ ጥያቄ ፣ የርእዮተዓለም ግንዛቤያችንን ይበልጥ ማሳደግ አስፈላጊ በመሆኑ ፣ በርእዮተዓለም ሥራችን አንጻር እመርታ ማሳየት እንዳለብን ተጠቁሟል ።

በኢኮኖሚው ግንባታ ሂደት ለምርት ኃይሎች ፈጣን እድገትና ለዚህም አስፈላጊ የሆነውን የጥሪት ክምችት ለማስገኘት ፣ በተለያዩ ክፍላተ ኢኮኖሚዎች በአጠቃላይ ፣ በእርሻው ክፍለ ኢኮኖሚ ውስጥ በተለይ ፣ የሶሺያሊስት የምርት ግንኙነትን ለማስፈን መታገል አስፈላጊ መሆኑን ይጠቁማል ። የኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ ሁለተኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔ ይህን አስመልክቶ «በገጠር የሶሺያሊስት የምርት ግንኙነትን ለመገንባት፣ የካፒታሊዝምን ማቆጥቆጥ ለመከላከልና የሶሺያሊዝምን ድል አድራጊነት ለማረጋገጥ ለአምራቾች የኅብረት ሥራ ማኅበራት መስፋፋትና መጠናከር ከፍተኛ ትኩረት እንዲሰጥ፣» በማለት አስገንዝቧል ።

የኢትዮጵያን የውጭ ፖሊሲ በሚመለከት የኢትዮጵያ አብዮት ከዓለም ሶሺያሊስት ካምፕ ፣ ከሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ፓርቲዎችና አገሮች ፣ ጸረ ኢምፔሪያሊስት ትግል ከሚያካሂዱ አገሮችና የአርነት ንቅናቄዎች ፣ በካፒታሊስት አገሮች ከሚገኙ ኮሚኒስት ፓርቲዎችና በአጠቃላይ ለሰላም ፣ ለዲሞክራሲና ለሶሺያሊዝም ከቆሙ ኃይሎች ጋር ያለውን ፣ በወዝ-አደራዊ ዓለምአቀፋዊነት መርህ ላይ የተገነባውን የትግል አንድነት ይበልጥ እንደሚያጠናክር የማዕከላዊ ኮሚቴው ውሳኔ ጠቅሶአል ።

በሌላ በኩል ፣ የማናቸውም ለፍትህ ለእኩልነትና ለሶሺያሊዝም የቆመ አብዮት ተቀዳሚ ተግባር እራሱን መከላከል መቻሉ ነው ። አሁን በደረስንበት ወሳኝ የትግል ምዕራፍ የኢትዮጵያ እውነተኛ ነጻነት ከአብዮታችን ህልውና ጋር ጠርሶ የተቆራኘ መሆኑ እሙን ነው ። የኢትዮጵያ አብዮት አሁን ከደረሰበት አስተማማኝ ደረጃ ላይ ሊደርስ የቻለውም ፣ በሰፊው ሕዝብ ጠንካራ ክንድና በአብዮታዊ ጦሩ ተጋድሎ ፣ እንደዚሁም በሶሺያሊስት አገሮች በተለይም በሶቭዬት ኅብረት ድጋፍ ነው ።

INFINIX HOT 8 | 13MP
AI TRIPLE CAMERA

በቅርቡ ደግሞ ከየካቲት ፩—፭ የተካሄደው የኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ ሁለተኛ መደበኛ ስብሰባ በአብዮቱ ሂደት ውስጥ ከፍተኛ ስፍራ የሚይዝ ነው ። ምክንያቱም ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከዘመናት አኩሪ የነጻነት ተጋድሎው ጋር እንደ ሙጫ ተጣብቆ ተጋድሎውን በማዳፈን ፤ ለረሃብ ፤ ለእርዛት ፤ በአጠቃላይም ለኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ኋላቀርነት የዳረገውን አስከፊ ሥርዓት አንኮታኩቶ ፤ ፍትህና እኩልነት የሰፈነበት አዲስ የሶሺያሊስት ሥርዓት ለመገንባት የሚያካሂደው ትግል ወሳኝ ምዕራፍ ላይ በደረሰበት በአሁኑ ጊዜ የተካሄደ በመሆኑ ነው ።

አብዮቱ አሁን በደረሰበት የእድገት የደረጃ አሮጌውን የምርት ግንኙነት ቅሪቶች በማፈራረስ አዲስ የምርት ግንኙነት የማበልፀን ትግሉን የሚያጠናክርበት ፤ ለሶሺያሊስት የኢኮኖሚ ግንባታ የማቴሪያልና የቴክኒክ መሠረት ለመጣል ቀርጦ የተነሳበት ወቅት ነው ። ከዚህም በተጨማሪ የወቅቱን ተጨባጭ ሁኔታ ፤ በሀገር ውስጥና በዓለምአቀፍ ደረጃ ያለውን የኃይል አሠላለፍ ፤ በአብዮቱ ሂደት የታዩ ድክመቶችንና የሚወገዱበትን መንገድ ለመቀየስ ፤ አብዮቱን ዘለቄታዊ ድል ለማጐናጸፍ አስፈላጊውን ስትራቴጅና ታክቲክ ለመንደፍ የአብዮታዊ ፓርቲ አመራር ወሳኝነት ከምንግዜውም ይልቅ እየጐላ የመጣበት ወቅት ነው ።

በሌላ በኩል ዓለምአቀፍ ኢምፔሪያሊዝም ሶሺያሊዝም በዓለም ውስጥ እንዳይስፋፋ በፅኑ ሲዋጋውና ሲጻረረው በቀየባቸው ባለፉት ስልሳዎቹ ዓመታት ውስጥ በየጊዜው ድል እየተመታ ፤ የሶሺያሊስቱ ዓለም እየተጠናከረ መምጣቱ ግልፅ እየሆነ ሄዶአል ። በመሆኑም በተለይ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ኢምፔሪያሊዝም የጠብ አጫሪነት ባህርዩ እየጐላ ዓለምን ወደ ከፍተኛ ጦርነት ለመግፋት እየተሯሯጠ ነው ።

የዓለምአቀፍ የኃይል አሠላለፍ ሚዛን ወደ ሶሺያሊዝም እያዘነበለ መሄዱ በገሃድ በተከሰተበት በአሁኑ ጊዜ ኢምፔሪያሊዝም እንደ አበደ ውሻ ሁሉንም ለመልከፍ በመቅበዝበዝ ላይ ይገኛል ። በተለያዩ የዓለም ክፍሎች የሚካሄደውን ጸረ ኢምፔሪያሊስት ትግል ለማፈን በሚያደርገው ጥረት «የፈጣን ጣልቃ ገብ ጦር»፤ስትራቴጅክ ናቸው ብሎ በሚመለከታቸው ቦታዎች በማስፈር ፤ በአካባቢ ያሉ ተራማጅና አብዮታዊ እንቅስቃሴዎችን ለማጨናገፍ በመዘጋጀት ላይ ይገኛል ።

ኢትዮጵያም ስርነቀል የሆነ አብዮት በማካሄድ ላይ ያለችና ስትራቴጅካዊ በሆነ አካባቢ የምትገኝ በመሆኗ ፤ የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም ከአብዮቱ ፍንዳታ ጀምሮ አብዮቱን ለመቀልበስ ያላደረገው ሙከራ የለም ። አብዮቱን ከውስጥ ለማስቦርቦርና የሀገራችንንም ዳርድንበርና ነጻነት ለማስደፈር የውስጥ ጸረ አብዮተኞችንና የአካባቢ አድሃሪ ኃይሎችን ኃይል በበላይነት በማስተባበርና በማቀናጀት ከፍተኛ የአብዮት ቅልበሳ ሤራ ሲያካሂድ ቆይቷል ። ይህ በእጅ አዙር የኢትዮጵያን አብዮት ለማስቀልበስ እስካሁን ያደረገው ሙከራ አለመሳካቱን በመገንዘብ ፤ የአካባቢ አድሃሪ ኃይላትን በማስታጠቅና በድንበራቸውም ውስጥ ጣልቃ ገብ ጦሩን በማስፈር አብዮታችንን ለማፈን በመቅበዝበዝ ላይ ይገኛል ።

የኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ ሁለተኛ መደበኛ ስብሰባ በአብዮቱ ሂደት ውስጥ ከፍተኛ ስፍራ የያዘ ነው የተባለውም ቀደም ሲል በተጠቀሰው መሠረት ከባድና ውስብስብ የሆነ ፤ በሀገር ውስጥና በዓለምአቀፍ ደረጃ የተፋፋመ ትግል በሚካሄድበት በአሁኑ ወቅት የተከናወነ በመሆኑ ነው ።

የኢሠፓአኮ አንደኛው ዓላማ ለኢትዮጵያ አብዮት ዘላቂ ዋስትና የሚሰጠውን የሠራተኛ መደብ ፓርቲ ማደራጀት እንደመሆኑ መጠን ፤ የኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ ሁለተኛ መደበኛ ስብሰባ ባስተላለፈው ውሳኔ የአብዮቱን ግስጋሴ በማፋጠኑ ረገድ ወሳኝ የሆነውን የፓርቲውን ምሥረታ ጥራት ማረጋገጥ አስፈላጊ መሆኑን አስገንዝቧል ።

የኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ ሁለተኛ መደበኛ ስብሰባ የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም የኢትዮጵያን አብዮት ለመቀልበስ በአካባቢው የሚያደርገውን ዝግጅት በጥልቀት ከመረመረ በኋላ ባስተላለፈው ውሳኔ ፤ የአብዮቱን ህልውና ለመጠበቅ የመከላከያ ኃይላችንን ይበልጥ ማጠናከርና ምንጊዜም ዝግጁ ሆነን መጠበቅ እንዳለብን አስገንዝቧል ። ራሱን ከውስጥም ሆነ ከውጭ ጸረ አብዮት ሤራ ለመጠበቅና ለመከላከል የማይችል አብዮት ለአደጋ የተጋለጠ መሆኑ ግልፅ ነው ። ስለሆነም የመከላከያ ኃይላችን አብዮቱን ለመጠበቅ የሚችል ፤ ለሶሺያሊዝም ህልውና የሚጋደልና በዚህም ረገድ ሰፊ ሕዝባዊ መሠረት እንዲኖረው ተደርጉ የመጠናከሩ ጉዳይ ወቅታዊና ወሳኝም ነው ።

በአጠቃላይ የኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ ሁለተኛ መደበኛ ስብሰባ በጓድ ሊቀ መንበር መንግሥቱ ኃይለማርያም የቀረበውን ማዕከላዊ ሪፖርት ፤ በኢሠፓአኮ የተለያዩ መምሪያዎች በቀረቡ ሪፖርቶችና የሥራ እቅዶች ላይ በመመሥረት ፤ ብሔራዊ ፤ የፖለቲካ ፤ የኢኮኖሚ ፤ የማኅበራዊ ፤ የወታደራዊ ሁኔታዎችን በማጤንና ከዓለምአቀፍ ሁኔታዎች ጋር በማገናዘብ ወቅታዊና መሠረታዊ በሆኑ የአብዮቱ ጥያቄዎች ላይ በዛ ያሉ ውሳኔዎችን አስተላልፏል ።

እነዚህ ውሳኔዎች የነገው ፓርቲ የሚገኝበትን ጊዜ በማፋጠን ረገድ አስተዋፅኦ የሚያደርጉ ከመሆናቸውም በላይ ፤ በውሳኔዎቹ የተገለጸው የፖለቲካ መስመር አብዮቱን ወደፊት ለማራመድ የሚረዳ መሆኑ እሙን ነው ። የማዕከላዊው ኮሚቴ ስብሰባ ያፀደቀው የፖለቲካ መስመር ፤ የኢትዮጵያ አብዮት ጥራት በይበልጥ የተንጸባረቀበት ፤ የወደፊቱ ፓርቲ ይዘት በጉልህ የተከሰተበት ፤ አብዮታችን ከዓለም የሶሺያሊስት ካምፕ በተለይም የዚህ ካምፕ መከታ ከሆነውና ከተፈጥሮ አጋራችን ከታላቁ የሶቭዬት ኅብረት ኮምኒስት ፓርቲና መንግሥት ጋር በወዝአደራዊ ዓለምአቀፋዊነት መርህ ላይ የተገነባው የትግል አንድነታችን ይበልጥ የጐለበተበት መስመር ነው ። በተጨማሪም የተቀየሰው የፖለቲካ መስመር በኢምፔሪያሊስቶች ርካሽ ፕሮፓጋንዳ በመነዳት ለኮምኒዝም ያላቸውን ጥላቻ ፤ መናኛ አሉባልታ በማናፈስ ለማርካት የሚቀበዘበዙ አድሃሪያንን ቅስም የሰበረ ነው ። ስለሆነም የኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ የሁለተኛ መደበኛ ስብሰባ ውጤት የመደብ ትግሉን ይበልጥ የሚያፋፍም ፤ በኢትዮጵያ ለሶሺያሊዝም ድል አድራጊነት አስተማማኝ መንገድ የሚቀይስ ፤ አብዮታውያን ኃይሎችን የሚያሰባስብና የሚያጠናክር ፤ አብዮታችንን ከዓለም የሶሺያሊስት ኅብረተሰብ ጋር በይበልጥ የሚያስተሳስር መሆኑ ግልፅ ነው ።

በኢሠፓአኮ አማካይነት አብዮቱ የፖለቲካ መስመር የሚቀይስለትን የፖለቲካ ድርጅት አግኝቷል ። በኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ ሁለተኛ መደበኛ ስብሰባ የተላለፉት ውሳኔዎችም ለዘለቄታው ድል አስተማማኝ መሠረት ጥለዋል ። በተነደፈው የፖለቲካ መስመር ጀርባ ሰፊውን ሕዝብ በማስተባበር ተግባራዊ እንዲሆን ለማድረግ የሚቻለው ግን ፤ የኢሠፓአኮ አባላትና በአብዮቱ ጉን የተሠለፉ ሁሉ የኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ ሁለተኛ መደበኛ ስብሰባ ያስተላለፋቸውን ውሳኔዎች በሚገባ በማጥናት በሰፊው ሕዝብ ውስጥ እንዲሰርፅ ለማድረግ ሲችሉ ነው ። ማርክስም ሆነ ሊኒን በመደጋገም እንዳስገነዘቡት ንድፈሃሳብና ከሱም የሚመነጨው የፖለቲካ መስመር ማቴሪያላዊ ኃይል ሊሆን የሚችለው በሠራተኛው ሕዝብ ውስጥ ሰርጾ ሲገባና ሲዋሃደው ብቻ ነው ።

INFINIX HOT 8 | 13MP
AI TRIPLE CAMERA

ኮምኒስት ማሰት ምን ማሰት ነው?

ገዛኸኝ ገብሬ

ማርክሲስት ሌኒኒስት ፓርቲ የሠራተኛው መደብ እውነተኛ ግንባር ቀደም መሪ የፖለቲካ ድርጅት ነው ። የሠራተኛው መደብ በካፒታሊዝም ላይ ድልን ለመቀዳጀትና መላውን ሠርቶአደር ሕዝብ ከብዝበዛና ጭቆና ነጻ ለማውጣት የሚችለው በዚህ መሪ ድርጅት በመመራት በሚያካሂደው መራራ ትግል ብቻ ነው ። ይህ ፓርቲ በመሠረቱ የሠራተኛው መደብ የነቃና የተደራጀ ከፍተኛው አካል ቢሆንም ከመደቡም ውጭ በንቃታቸውና በታጋይነታቸው የላቁትን ታጋዮች በማቀፍ ለሶሻሊዝም ብሎም ለኮሚዩኒዝም ግንባታ የሚያሰልፍ የመላው ሠርቶ አደር ሕዝብ አደራጅና መሪ ነው ። በዚህ ትግሉም ርዕዮተዓለማዊ መመሪያው ለአያሌ ዓመታት በተግባር የተፈተነው የማርክሲዝም ሌኒኒዝም ንድፈ ሐሳብ ነው ። ማርክሲዝም ሌኒኒዝም በተጨባጭ እንደሚያስተምረን ሠራተኛው መደብ ራሱን ነጻ ለማውጣት በሚያካሂደው ረጅምና ውስብስብ የትግል ሂደት ውስጥ በመደብ የተከፋፈለን ኅብረተሰብ ጨርሶ በማጥፋት መላ ኅብረተሰቡን በማንኛውም መልኩ ካለ ምዝበራና ተፅዕኖ ማላቀቅ ይሆናል ።

ኅብረተሰብን በመጨረሻ ለዚህ ድል ለማብቃት በሚደረገው አብዮታዊ ትግል ሰፊውን ሕዝብ ባለመሰልቸት በማንቃት ፤ በማደራጀትና ለመደብ ፍልሚያው በማዘጋጀት ፤ እንዲሁም በቀጥታ በትግሉ እሳት ውስጥ በመማገድ ግንባር ቀደም ሚና የሚጫወቱት በፓርቲው የተደራጁት ኮሚዩኒስቶች ናቸው ። የኮሚዩኒስቶች ዓላማ ሰው በሰው የማይበዘበዝበትን መደብ አልባ ኅብረተሰብ መገንባት ነው ። ይህ የሠራተኛው መደብና የግንባር ቀደም ታጋይ አካሎች ኅብረተሰብን ፍጹም ነጻ የማውጣት ተግባር በማንኛውም ኅብረተሰብ ፤ ማለትም የሠራተኛው ቁጥር ከፍ ወይም ዝቅ ባለበት ሁሉ ተፈጻሚነት ያለው ነው ። ይህ የሚሆን በትም ምክንያት ኮሚዩኒስቶች የኅብረተሰብን እድገት ደረጃ ወደ ሶሻሊዝም ሊያሸ

INFINIX HOT 8 | 13MP
AI TRIPLE CAMERA

ጋግር የሚችል ሳይንሳዊ አመራር ለመስ
ጠት የሚችሉ በመሆናቸው ነው ።

ኅብረተሰብን ከብዝበዛና ጭቆና ፍጹም
ነጻ የማውጣትንና የሰውን ልጅ ክብርና ሰብ
ዓዊ ልዕልና በተሟላ መልኩ እውን ለማ
ድረግ የሚቻለው በዚህ የመደብ ትግል
ሂደት ውስጥ ብቻ ነው ።

ርዕሳችን የኮሚዩኒስትን ምንነት ግንዛቤ
የሚመለከት ቢሆንም ከላይ እንደተመለከ
ተው ኮሚዩኒስቶች ከሚደራጁበት መሪ
አካል ማለትም ከሠራተኛው መደብ ማርክ
ሲስት ሌኒኒስት ፓርቲ ውጭ ስለኮሚዩኒስ
ታዊነት መናገር ስለማይቻል፤ይህንኑ በአ
ጭሩ ለማብራራት በቅድሚያ የሠራተኛውን
መደብ ባህሪያት ፤ ታሪካዊ ተልዕኮውን ፤
መመሪያውንና ድርጅታዊ አሠራሩን ፤ እን
ዲሁም የፓርቲው አባላት በትግሉ ሂደት
በኅብረተሰቡ ሕይወት ውስጥ የሚያደርጉ
ትን ተሳትፎና የሚጫወቱትን ሚና መመ
ልከቱ ተገቢ ይሆናል ።

የሠራተኛው መደብ ልዩ ባህሪያት

የጭቆናና የብዝበዛ ሥርዓትን ጨርሶ
በመደምሰስ መደብ አልባ የኮሚዩኒስት
ሥርዓትን የመመሥረት ታሪካዊ ተልዕኮ
የሠራተኛው መደብ መሆኑን መጥቀስ ብቻ
ጉዳዩን ግልጽ ሊያደርግ አይችልም ። ከዚህ
አባባል ጀርባ ተጨባጭ የሆኑ ምክንያቶች
እንዳሉም መገንዘቡ አስፈላጊ ነው ። የሠራ
ተኛው መደብ በመሠረቱ ምንም የማምረቻ
መሣሪያ ባለቤትነት የሌለውና ከዚህም
የተነሣ ከግል ሀብት ስሜት ጋር ያልተቆራኘ
ነው ። ኅብረተሰብን ከሥረ መሠረቱ በመ
ለወጥ ጭቆናን የማጥፋት ኀላፊነት በሱ
ትከሻ ላይ የሚወድቅበትም ምክንያት የሚ
መነጨው ከዚህ ዋና ባህሪይው ነው ።

ሠራተኛው ምንም የግል ሀብት የሌለው
በመሆኑ የሥራ ኃይሉን የማምረቻ መሣሪ
ያዎች ባለቤት ለሆነው የካፒታሊስቱ መደብ
በመሸጥ የሚተዳደር ተበዝባዥና ተጨቋኝ
መደብ ነው ። የግል ሀብት የሠራተኛው
መደብ ለሥልጣን ከመብቃቱም በፊት ሆነ
ለሥልጣን ከበቃ በኋላ ለሕልውናው አስፈ
ላጊ አይደለም ። ስለዚህ ለግል ሀብት ሕል
ውና ማክተምና ለብዝበዛ መጥፋት እስከ
መጨረሻው ለመታገል የሚችለው ኃይል
እርሱ ብቻ ነው ።

የሠራተኛው መደብ ሕይወት እጅግ
በጣም ከዳበረው ዘመናዊ የካፒታሊስት
የማምረቻ መሣሪያዎች ጋር በቅርብ የተ
ሣሠረ በመሆኑ ይህ መደብ የተራመደ የአሠ
ራር ዘዴና ጥበብ ልምድ ያለው ነው ። ከዘ
መናዊ የሳይንስና የቴክኖሎጂ ዕውቀት ጋር
ትውውቅ ያለው ከመሆኑም በላይ ኢንዱ
ስትሪዎችና ፋብሪካዎች እየተስፋፉ ሲሄዱ
በቁጥሩም ሆነ በሚያደርገው ፀረ ካፒታል
ትግል እየጐለበተ የሚሄድ ነው ። ከዚህ
የተነሳም ካሉት መደቦች ሁሉ እጅግ አብዮ
ታዊ ፥ ታዳጊና ዋናው የኅብረተሰቡ አምራች
ኃይል ነው ። ይህ በኅብረተሰቡ የያዘው ታሪ
ካዊ ቦታ በጋራ የማምረት ሰፊ ልምድና
ጠንካራ ዲስፕሊን ስለሚያጐናጽፈው ለመ
ደራጀትም አመቺ ሁኔታ አለው ። በአንድ
ላይ የተሰበሰበ ኃይል በመሆኑም የአንድነት
ስሜቱ ጠንካራ ነው ።

ሠራተኛው መደብ ትግሉን በሳይን
ሳዊ መንገድ ለማቀነባበርና ለማደራጀት
የመጀመሪያውና ብቸኛው መደብ ነው ።
ለዚህ ሊበቃ የቻለውም የማርክሲዝም ሌኒኒ
ዝምን መመሪያ ንድፈ ሐሳብ በመጨበጡ
ነው ። በግብታዊነት የጀመረውን የሠራተ
ኛውን እንቅስቃሴና ከሠራተኛው መደብ
እንቅስቃሴ ውጭ የተነደፈውን የሳይንሳዊ
ሶሻሊዝም ንድፈ ሐሳብ የሚያስተሳስረውና
የሚያዋህደው ማርክሲስት ሌኒኒስት ፓር
ቲው ነው። በመደብ ትግሉ ውስጥ የሠራተ
ኛው መደብ ሥልጣን ለመጨበጥና የተገ
ኘውንም ሥልጣን ለማጠናከር በሚያደር
ገው እንቅስቃሴ ፓርቲው ብቻ ሳይሆን
የመደቡ ሰፊ የሙያና ሕዝባዊ ድርጅቶች
የሠራተኛው የሶሻሊዝም ትምህርት ቤቶች
ናቸው ። በታሪክ የመደብ ምንጩንና ተል
ኮውን በሚገባ የተረዳው ሠራተኛው
መደብ ብቻ ነው ። በተለይ በሶሻሊስት
ኅብረተሰብ ይህ መደብ ዋናው አምራች
ኃይልና የፖለቲካ ባለቤት በመሆኑ ጥንድ
ተግባር የሚያከናውን፤ ፖለቲካዊና ማህበ
ራዊ ኃይል ነው ። በአምራችነቱም የኅብረ
ተሰቡ ሕልውናና የዕድገቱ ወሳኝ ኃይል
ነው ። የሶሻሊስት ሥርዓት ለመመሥረት
በሚያደርገው ትግልም ሆነ ሥርዓቱን ከመ
ሠረተ በኋላ ከአጋሮቹ ጋር የሚፈጥረውን
ግንኙነት ለጠባብ የመደብ ፍላጐት የማያ
ውል ፥ ሌሎችን የማይበዘብዝና የማይጫን
ብቸኛ መደብ ነው ። እንዲያውም ከዚያም
አልፎ እኩልነትና ፍትህ የሰፈነበትን መደብ

አልባ ሥርዓት ለማምጣት በግንባር ቀደም ትነት የሚጋፈጥ ነው ።

በሶሻሊስት ሁኔታ ውስጥም የሠራተኛው መደብ ከሶሻሊስት ንብረት ጋር በጥብቅ የተሳሰረ በመሆኑ የኅብረተሰቡን የጋራ ንብረት በማሳደግ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል። እጅግ ከባድና ውስብስብ በሆነው የሶሻሊስት የሽግግር ወቅት ውስጥ የተቀሩትን ጭቁን መደቦችና የኅብረተሰብ ክፍሎች በማስተባበርና በመምራት ግንባታውን ያከናውናል ። ስለሆነም የመሪነት ቦታ የሚይዘውም ከሚደርስበት የከፋ ጭቆና ለመላቀቅ በሳይንሳዊ ርዕዮተዓለም በመታጠቁ ፤ የሳይንስና የቴክኖሎጂ ዕውቀት ባለቤት በመሆኑና ኮሚዩኒዝምን ለመገንባት ካለው ጽኑ ዓላማና ችሎታ ነው ።

ኮሚዩኒስት ኅብረተሰብን መገንባት የሠራተኛው መደብ ታሪካዊ ተልዕኮ ነው

ሳይንሳዊ ሶሻሊዝም የካፒታሊዝም የኢኮኖሚ ዕድገት ሕግ ራሱ ሥርዓቱን ወደ ውድቀት እንደሚያመራና አዲስ የሶሻሊስት ሥርዓት እንደሚመሠረት ያስተምረናል።የሶሻሊዝም መመሥረት የማይቀር የኅብረተሰብ ዕድገት ሕግ ነው ። የካፒታሊዝም ወደሞኖፖል ካፒታሊዝም ወይም ኢምፔሪያሊዝም ደረጃ ማደግ በራሳቸው በካፒታሊስት አገሮች የምርት ኃይሎችን በከፍተኛ ደረጃ በማሳደግ ፤ በቅኝ ግዛትና ከፊል ቅኝ ግዛት አገሮች እና በኢምፔሪያሊስት አገሮች መካከል ያለውን ቅራኔ በማባባስ ለሶሻሊስት አብዮት ሁኔታዎችን አመቻችቷል ። ሌኒን እንዳለው ኢምፔሪያሊዝም የሶሻሊስት አብዮት ዋዜማ ነው ። በመሆኑም የካፒታሊስቱን ሥርዓት በመጣል የሶሻሊስት ኅብረተሰብን የመመሥረቱ ታሪካዊ ተልዕኮ ራሱ ካፒታሊዝም «ያስተማረውና ያሰለጠነው» የሠራተኛው መደብ ነው ።

የሠራተኛው መደብ በከበርቴው ሥርዓት ላይ የሚያደርገው ትግል በተለያዩ ጊዜያት የተለያየ ቅርፅ የሚይዝ ቢሆንም በፀረ ካፒታሊስት ይዘቱ አንድ ነው ። የዚህ ትግል ውጤት በአንድ በኩል የቡርዧው መንግሥት መውደቅ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ የሠራተኛው የበላይ ገዢነት ሕልውና ማግኘት ይሆናል ። የማምረቻ መሣሪያዎች የኅብረተሰቡ የጋራ ንብረት ወደ መሆን ይሸጋገራሉ ። በዚህም የካፒታሊስቱ የምርት ግንኙነት ጠፍቶ በቦታው የሶሻሊስት የምርት ግንኙነት ይመሠረታል ። የሶሻሊስት የምርት ግንኙነት መፈጠር አዳዲስ ሁኔታዎች እንዲከሰቱ ያደርጋል ። የሠርቶ አደሩ ሕዝብ ምርታማነት ማደግ ፤ የሥራ ሰዓት መቀነስ ፤ የቀድሞው ሥርዓት የተበታተኑና ኋላ ቀር ትናንሽ የማምረቻ ድርጅቶች በአዲስ መልክ መደራጀትና በተሻሻለ የማምረት ዘዴና ቴክኒክ በኅብረት በመሥራት ከቀድሞው የበለጠ ፍሬያማ ውጤት ማስገኘት የዚህ ለውጥ ውጤቶች ናቸው ።

ሶሻሊዝም በሰዎች ንቁ ተሳትፎ የሚገነባ ሥርዓት በመሆኑ የኅብረተሰቡ የኢኮኖሚ ፤ የፖለቲካና የሶሻል ተግባሮች ሁሉ በዕቅድ ላይ የተመረኮዙና ግልፅ ዓላማ ያላቸው ናቸው ። በዚህ አሠራር ሶሻሊዝም በከተማና በገጠር የተመዛዘነ እድገት እንዲኖር በማድረግ የገጠሩን ኋላ ቀርነትና ብቸኝነት ያስቀራል።ይህም የሰውን ልጆች በዘር፤ በቀለም በብሔርና በመሳሰሉት የመለያየትንና፤የጾታ ጭቆናን መጥፋት ጥርጊያ መንድን ያዘጋጃል ።

ሶሻሊዝም ለብቻው ያለ፣አንድ ራሱን የቻለ ሥርዓት ማህበር ሳይሆን ለኮሚዩኒዝም ቁሳዊና ቴክኒካዊ መሠረት የሚጣልበት ፤ ከካፒታሊዝም ወደ ኮሚዩኒዝም ሽግግር የሚደረግበትና የኮሚዩኒስት ኅብረተሰብ የመጀመሪያው ደረጃ ነው ። ይህንን ማርክስ እንደሚከተለው ይገልጸዋል ፤

«በካፒታሊስትና በኮሚዩኒስት ኅብረተሰብ መካከል አንዱ ወደ ሌላው አብዮታዊ ሽግግር የሚያደርግበት ወቀት ይገኛል ከዚህ ጋር የሚሄደው ሊላው ደግሞ የወዝ አደሩ የበላይ ገዥነት የሚመሠረትበት የፖለቲካ ሽግግር ወቀት ነው ።»[1]

ካፒታሊዝም ወደ ሶሻሊዝም ሽግግር በሚያደርግበት ወቅት ሰፊውን ሕዝብ በሚወክለው የሠራተኛው መደብ መንግሥት መሣሪያነት የሠርቶ አደሩ ሕዝብ ዲሞክራሲያዊ መብት ሲከበር ከሥልጣን የወረዱት የቡርዧው መደብ አባሎችና ተባባሪዎቻቸው ይህንን መብት ይነፈጋሉ ። ሶሻሊዝም ሠራተኛው የሥራ ኃይሉን ተገቢ ዋጋ ለማግኘት ያስችለዋል ። የዚህ የሽግግር ወቅት መሠረታዊው የምርት ክፍያ መርህ ፤

INFINIX HOT 8 | 13MP
AI TRIPLE CAMERA

«ከእያንዳንዱ እንደችሎታው ፤ ለእያን ዳንዱ እንደሥራው» የሚል ይሆናል ። ሆኖም ሶሻሊዝም ከካፒታሊዝም ለጥቆ የሚመጣ ስልተምርት በመሆኑ አንዳንድ የወደቀው ሥርዓት ቅሪት አስተሳሰቦች ተጽዕና ይታይበታል ። ተጻራሪ ባይሆኑም የሠራተኛውና የገበሬው መደቦችም በው ስጡ ይገኛሉ ። የአሮጌው ሥርዓት ቅሪቶች ጨርሰው የሚጠፉት የግል ሀብትና መደቦ ች ሲጠፉ እንዲሁም ከነዚሁ ጋር ተያይዞ የሚመጣው መንግሥት እየከሰመ በሚሄድ ወደ ኮሚዩኒዝም ሽግግር ሲደረግ ነው ።

ሠራተኛው መደብ የሚታገልለት ኅብ ረተሰብ ይህን የመሰለ ነው ። የኮሚዩኒስት ኅብረተሰብ የሰው ልጅ ፍላጎት የሚያሟላ በትና ሙሉ ሰብዓዊ ነጻነቱን የሚያገኝበት ነው ። ሰው ያለ አንዳች የውጭ ግፊት ቁጥ ጥርና ተመልካችነት በራሱ ከፍተኛ ንቃት ፤ ግንዛቤና ፈቃደኝነት የሚሠራበትና ራሱን የሚመራበት ሕዝባዊ ሥርዓት ነው ። የመመ ራመርና የፈጠራ ችሎታው ምጥቀት የተፈ ጥሮን ሕጐች የበለጠ ለመገንዘብ ስለሚያስ ችለው ምርት ይትረፈረፋል ። እያንዳንዱ ሰው እንደ ችሎታው ሠርቶ እንደፍላጐቱ የሚያገኝበት ሁኔታም ይፈጠራል ። በዚ ያው መጠን መንፈሳዊ ሕይወቱም የተሟላ ይሆናል ። ማርክስ አሁንም ቀደም ሲል በተጠቀሰው መጽሐፉ የኮሚዩኒስት ሥርዓ ትን እንደሚከተለው ገልጾታል ፤

«የቡርዣው መብት ጠባብ አድማስ ሙሉ በሙሉ ተሠርዞ ኅብረተሰብ ከእያንዳንዱ እንደ ችሎታው ፤ ለእያንዳንዱ እንደ ፍላ ጐቱ የሚለውን መርህ ከፍ አድርጐ የሚ ያውለበልበው በኮሚዩኒስት ኅብረተሰብ ከፍ ተኛ ደረጃ ፤ የግለሰቡ በሥራ ክፍፍል የባር ነት ቀንበር ሥር መውደቁና ከዚሁ ጋር ተያይዞ በአዕምሮ ሥራና በጉልበት ሥራ መካከል ያለው ቅራኔ ሲጠፋ ፤ ሥራ ለዕለት ጉርስ ማግኛ ብቻ ሳይሆን የመጀመሪያው የሕይወት አስፈላጊ ነገር ሲሆን ፤ ከግለሰብ የተሟላ ዕድገት ጋር የምርት ኃይሎች ሲጠ መሩና ከኅብረተሰቡ የጋራ ጥሪት የሚገ ኘው ሀብት በጣም ሲዳብር ብቻ ነው ።»[2]

ሠራተኛው መደብ በነቂ ግንባር ቀደም ታጋይ መሪዎቹ አደራጅነትና መሪነት እንዲ ሁም በሰፊው ሠርቶ አደር ሕዝብ ተባባሪ ነትና ተሳትፎ የሚያደርገው ትግል የሩቅ ዓላማው የዚህ ዓይነቱን ኅብረተሰብ በመመ ሥረት የሠራተኛውን መደብ ብቻ ሳይሆን መላውን ሠርቶ አደርና የሰው ልጅ ከምዝ በራና ጭቆና ለአንዴና ለሁሌም ነጻ ማውጣት ነው ።

የሠራተኛው መደብና የሌሎች ኃይ ሎች ኅብረት አስፈላጊነት

የሠራተኛው መደብ ፍላጎትና ዓላማ ከኅብረተሰብ ነባራዊ የዕድገት ሕጎች የሚ መነጭ ነው ። ይህም ፍላጎትና ዓላማው ከብዙሀኑ ፍላጎትና ዓላማ ጋር የሚሄድ ነው ። መሠረታዊ ዓላማው የሰውን ልጅ ከመደባዊ ጭቆና ፤ ከተፈጥሮ ተገዢነት በማውጣት እጅግ በላቀ ተፈጥሮን የመቆ ጣጠር ችሎታው የራሱ ጌታ እንዲሆን ማድ ረግ ነው ። በመሆኑም የሠራተኛው መደብ ከሌሎች ከርሱ ውጭ ከሚገኙትና ለነጻነት ፤ ለሰላም ፤ ለዲሞክራሲና ለሶሻሊዝም ከሚ ታገሉት ተራማጅና ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች ጋር ኅብረት ለመፍጠር የሚከተለው ፖሊሲ ከዚህ የሠራተኛው መደብና ሌሎች ጭቁን መደቦችና የኅብረተሰብ ክፍሎች ፍላጎት መጣጣም የሚመጣ ነው ።

ሠራተኛው መደብ ቀደም ሲል እንደ ተጠቀሰው በኅብረተሰብ ውስጥ ካለው ልዩ ቦታና ባህሪይ ፤ ከዚህም በመነሳት በሳይን ሳዊ መንገድ ኅብረተሰቡን በአብዮታዊ ጎዳና ለመምራት ካለው ችሎታ የተነሳ ቅራ ኔዎችን እንደቦታውና ወቅቱ በማቻቻል ሌሎች ኃይሎችን አስተባብሮ ለትግል ለማ ሰለፍ የሚችል ኃይል ነው ። እነማርክስ ከመጀመሪያው የሳይንሳዊ ሶሻሊዝምን ንድፈ ሐሳብ መሠረት ሲጥሉ ይህ መደብ ካፒታሊዝምን ደምስሶ የራሱን የሶሻሊስት ሥርዓት ለመመሥረት በሚቀይሰው ስት ራቴጂና ታክቲክ በተለያዩ ወቅቶች እንደ ተጨባጭ ሁኔታው በተለይ ከገበሬውና ከሌሎችም እንደመካከለኛው መደብ ተራ ማጅ ክፍልና ሌሎች ተራማጅነት ካላቸው ኃይሎች ጋር ጊዜያዊም ሆነ ዘላቂ ኅብረት መፍጠር እንደሚገባው አስገንዝበዋል ። ሌላው ቀርቶ በአንድ በተወሰነ ታሪካዊ ወቅት ፤ ለምሳሌ ፊውዳሊዝምን ለመዋጋት ከቡርዧውም ጋር ጊዜያዊ ኅብረት ለመፍ ጠር የሚገደድበትም ሁኔታ ሊኖር እንደ ሚችልም ተናግረዋል ። ይህም በተለያዩ

አገሮች በተካሄዱት ቡርዧ አብዮቶችና የብሔራዊ አርነት ትግሎች በተጨባጭ ታይቶ አል። ታላቁ ሌኒንም ወዝ አደራዊው አብዮት ያለዚህ ሰፊ ኅብረትና የአብዛኛው የሥርቶ አደሩ ሕዝብ ድጋፍ ሊካሄድ እንደ ማይችል ሲናገር እንዲህ ብሏል ፤

«አብዛኛው ሠርቶ አደሩ ሕዝብ ግንባር ቀደም መሪው ለሆነው ለሠራተኛው መደብ ድጋፉን ካልሰጠ ወዝ አደራዊ አብዮት ፍፁም ሊታሰብ አይችልም ----»[3]

የሶሻሊስት አብዮት በግንባር ቀደሙ ክፍል ብቻ ሊካሄድ አይችልም ማለት ነው ። ይህም ኅብረት በአንዴ የሚገኝ ሳይሆን በረዥምና እጅግ አድካሚ በሆነ የትግል ሂደት ውስጥ የሚመጣ ነው ። ኅብረቱ አስ ፈላጊ ቢሆንም በኅብረቱ ውስጥ አመራሩ የኮሚዩኒስቶች መሆን አለበት ። ኅብረቱ እንዲጠናከርና ዘላቂው የሥርቶ አደሩ ሕዝብ ዓላማ ወደ ጐን እንዳይገፋ ኮሚዩኒስቶች ምን ጊዜም ቢሆን በአድርባይነት የሌሎች ኃይ ሎች ጭራ በመሆን አብዮታዊ ማዕከልነታ ቸውን ማላላት የለባቸውም ። በጊዜያዊ ሁኔታ ብቻ ተገደው ከነሱ ጋር ኅብረት በመ ፍጠር ለአድሀሪው ሥርዓት መመለስ የሚታ ገሉትን ጊዜያዊ ወዳጆች ለመለየትና አብ ዮት እንዳይቀለበስ በዓላማ ጸንቶ ለየወቅቱ የሚበጅ ታክቲክ በመቀየስ ምንጊዜም ጠላ ትን ነቅቶ መጠበቅ እጅግ አስፈላጊ ነው ።

በመሠረቱ የሠራተኛው መደብ ትግል ዓለም አቀፋዊ ነው ። በመሆኑም በአንድ አገር የሚካሄደው በሠራተኛው መደብ የሚ መራ ሕዝባዊ ትግል ከሌሎች አገሮች ተራ ማጅና አብዮታዊ ኃይሎች ጋር የጠበቀ ግን ኙነት መፍጠር አለበት ። በዓለም አቀፍ ኢምፔሪያሊዝም የሚመራው የአድሀሮት ኃይሎች ፀረ ሕዝብና ፀረ ሰላም እንቅስቃሴ ዓለም አቀፍ በመሆኑ ለሕዝባዊ ትግል መሳ ካት የዚህ ዓይነቱ ኅብረት በጣም አስፈላጊ ነው ። በዚህም በኩል ትክክለኛ አመራር በመስጠት ትግሉን ወደ ፊት የሚያራም ደው በፓርቲው የሚመራውና የሰፊው ሕዝብ ድጋፍ ያለው ሠራተኛው መደብ ነው ።

በአጠቃላይ ሠራተኛው መደብ ራሱንና ኅብረተሰቡን ነጻ የሚያወጣው ብቻውን ሳይሆን በሠርቶ አደሩ ሕዝብ ኅብረት ፤ ድጋፍና አብዮታዊ ተሳትፎ ነው ። የሠራ ተኛው መደብ ትግልም ጭቁኖችንና ምዝብ ሮችን ሁሉ ነጻ ማውጣት ነው ። ይህን በማ ስመልከት ማርክስ የሚከተለውን ተናግ ሯል ፤

«የሠራተኛው መደብ ነጻነት በራሱ በሠራ ተኛው መደብ መገኘት አለበት ። ለሠራተ ኛው መደብ ነጻነት የሚደረገው ትግል ለጠ ባብ የመደብ ጥቅምና ሁሉን ነገር ለሠራ ተኛው መደብ ለማድረግ ሳይሆን ለእኩል መብትና ግዴታ ፤ እንዲሁም ማንኛውንም የመደብ አገዛዝ ለማጥፋት ነው ።»[4]

ይህም የሠራተኛው መደብ ዓላማ የመ ላው ሠርቶ አደር ሕዝብ ዓላማ ፤ የሱም ነጻ ነት የሁሉም ምዝብሮች ነጻነት መሆኑን ያሳያል ።

ለሠራተኛው መደብ ድል የኮሚኒ ስቶች አብዮታዊ መመሪያና ድርጅት ወሳኝነት

ሳይንሳዊ ሶሻሊዝም የሠራተኛው መደብ አብዮታዊ የትግል መመሪያ ነው ። ይህ ንድፈ ሐሳብ ከሰዎች ጭፍን ፍላጎትና ምኞት ወይም ልዩ ተሰጥኦ ባላቸው ጠቢባን በጎ ፈቃድ የመጣ ሳይሆን የኅብረተሰብ ነባ ራዊ የእድገት ሂደትና የመደብ ትግል ታሪክ ውጤት ነው ። በተለይ ከካፒታሊዝም እድ ገት ጋር የሠራተኛው የፖለቲካ እንቅስቃሴ እየሰፋና ጥልቀት እያገኘ መምጣት ለሳይን ሳዊ ሶሻሊዝም መነደፍ አመቺ ሁኔታን ፈጥሯል ።

በመጀመሪያ ደረጃ ለሳይንሳዊ ሶሻሊ ዝም ሳይንሳዊነት መሠረቱ ከሐሳባዊነት የጸዳው ቁስአካላዊ ይዘቱ ነው ። ቁስ አካላዊ ፍልስፍና የአድሀሪ መደቦችን ሐሊ ናዊ አመለካከትና ሜታፊዚካዊ የአሠራር ዘዴ በመዋጋት ኅብረተሰብንና የሰውንም አስተሳሰብ ጨምሮ ለአጠቃላዩ ዓለም ሕል ውናናእድገት መሠረቱቁስአካል መሆኑንና፤ ሕሊና ወይም ሐሳብ ራሱ የቁስአካል ከፍ ተኛ የእድገት ደረጃ ውጤት መሆኑን ያረ ጋግጣል ። የዚህ ፍልስፍና ሌላው ገጽታ በለውጥ ፤ በእንቅስቃሴና በእድገት ማመኑ ነው ። እድገት ከዝቅተኛ ወደ ከፍተኛ ፤

ከቀላል ወደ ውስብስብ ፤ ከመጠን ወደ ዓይነት የሚሸጋገርና ለዚህም መነሻው በነገሮች ውስጥ ያሉ የተቃራኒ ኃይሎች ትግል ነው ።

በተለይ ኅብረተሰብን በሚመለከት የታሪክ ቁስአካልነት ፅንሰ ሐሳብ መሠረቱ ኢኮኖሚው ወይም በማህበራዊ የምርት ተግባር ሂደት ውስጥ በሰዎች መካከል የሚፈጠረው የምርት ግንኙነት ነው። መሠረታዊና ለሰው ሕይወት አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች የሚገኙት በማህበራዊ የምርት እንቅስቃሴ በመሆኑ ለኅብረተሰብ ሕልውና ማግኘትና ማደግ ፤ እንዲሁም በአንድ ታሪካዊ ወቅት ላለው አስተሳሰብ ፤ አመለካከትና እምነት መሠረቱ ይኸው የኅብረተሰቡ የኢኮኖሚ መሠረት የሆነው የምርት ግንኙነት ነው ። የፖለቲካ ሥልጣን ቅርጽና ይዘትም የሚወሰነው በዚሁ ነው ። በመሆኑም በታሪክ በተለያዩ ወቅቶች የተለያዩ ኃይሎች የወሳኝነት ሚና ሊኖራቸው ቢችልም በመጨረሻ ግን ወሳኙ ምርት ማለትም የሠርቶ አደሩ ሕዝብ የማምረት ተግባርና የሰው ልጅ በዚህም ሕልውናውን ለመጠበቅ መቻል ነው ።

ከዚህ መሠረታዊና አጠቃላይ ሳይንሳዊ አመለካከት በመነሳት ማርክስና ኤንግልስ ኅብረተሰብ በመደብ ከተከፋፈለበት ጊዜ ጀምሮ የኅብረተሰብ ታሪክ የመደብ ትግል ታሪክ መሆኑን ፤ በካፒታሊስቱም ሥርዓት ውስጥ አዳዲስ መደቦች መከሰታቸውንና ይህም በዝባዥ ሥርዓት በሠራተኛው መደብ በሚመራው ሶሻሊስት አብዮት የሚወገድ መሆኑን ይገልጻሉ ። ማርክስ የመደቦች ሕልውና ማግኘት ከኅብረተሰብ የተወሰነ የምርት እድገት ደረጃ ጋር የተያያዘ መሆኑን ፤ የመደብ ትግል በመጨረሻው የግድ ወደ ሠራተኛው መደብ የበላይ ገዥነት የሚያመራ መሆኑንና፤ መደብ የሚጠፋውና ብዝበዛና ጭቆና የሌለበት የኮሚዩኒስት ሥርዓት የሚመሠረተውም በዚሁ በሠራተኛው መደብ የበላይ ገዥነት አማካይነት መሆኑን ጥርት ባለ ሁኔታ ገልጾታል ።

በዚሁ ትግሉ ሠራተኛው መደብ ስትራቴጂና ታክቲክ በመቀየስ ትግሉን የሚያቀነባብርለት ፤ በጠራ ርዕዮተዓለም መስመር የሚመራው ፤ ሰፊውን ሕዝብ በማስተባበር የሚያታግልና የሚታገል ፤ ከብረት የጠነከረ ዲስፕሊን ያለው የራሱ የመደብ የፖለቲካ ድርጅት ወይም ፓርቲ ያስፈልገዋል ። በፓርቲው የሚደራጁት የሠራተኛው መደብ ግንባር ቀደም አካል የሆኑት ኮሚዩኒስቶች ቆራጥ ፤ ይበልጥ የነቁ ፤ የትግሉን አቅጣጫ በትክክል የተረዱ ፤ አርቀው የሚያስቡ ፤ የመጨረሻ ግባቸውን ጠንቅቀው የሚያውቁና በቆሙለት ዓላማ እስከመጨረሻው በመጽናት ለዓላማቸው ግብ መምታት ለመስዋዕትነት ዝግጁ የሆኑ ናቸው ።

ኮሚዩኒስት ማኒፌስቶ በተሰኘው የመጀመሪያው የወዝ አደሩ ፓርቲ ፕሮግራማቸው ማርክስና ኤንግልስ ፤

«ኮሚዩኒስቶች በአንድ በኩል በተግባር እጅግ የተራመዱ የየአገሩ የሠራተኛው መደብ ክፍል የሆኑ ፤ የተቀሩትን ክፍሎች ሁሉ የሚመሩ ሲሆኑ ፤ በሌላ በኩል ደግሞ በቲዮሪ ከሰፊው ሠራተኛ የላቁ ፤ የጉዞውን አቅጣጫ ፤ ሁኔታዎችንና የሠራተኛውን እንቅስቃሴ አጠቃላይ ውጤት በግልፅ ለማየት የሚችሉ ናቸው ።»[5]

በማለት የኮሚዩኒስቶችን ተግባራዊ ተሳትፎ የቲዮሪ ንቃት ደረጃና የዓላማ ቁርጠኝነት ደህና አድርገው አብራርተዋል ።

ሠራተኛው መደብ በካፒታሊዝም ላይ የበላይነትን በመቀዳጀት አዲስ የኮሚዩኒስት ሥርዓት ለመገንባት የሚችለው የራሱና አንድ ወጥ የሆነ ነፃ ፓርቲ ሲኖረው ብቻ መሆኑንም ሲያስረዱ ፤

«ወዝ አደሩ አስፈላጊ የሆነውን ኃይል በማሰባሰብ በወሳኙ የትግል ወቅት በአሸናፊነት ሊወጣ የሚችለው ፤ የመደብ ንቃት ያለው ፤ ከሌሎች ፓርቲዎች ሁሉ የተለየና ከነሱ ጋር በተጻራሪነት የቆመ ፤ የራሱ የሆነ ፓርቲ ሲመሠርት ብቻ ነው ፤»[6] ብለዋል ።

ኋላ የመጣው ሌኒንም በማርክሳዊ መርሆዎች ላይ በመመርኮዝ ለዘመነ ኢምፔሪያሊዝም የሚበጅ የወዝ አደራዊውን አብዮት ስትራቴጂና ታክቲክ በመንደፍ ሐቀኛ ኮሚዩኒስቶችን ያቀፈ ከአድርባይነት የጸዳ ፤ በሁሉም የትግል መስክ ትክክለኛ አመራር ሊሰጥ የሚችል ፤ በአብዮታዊ ዲስፕሊን የታነጸና በሰፊው ሠርቶ አደር ሕዝብ ውስጥ ጠንካራ መሠረት የጣለ አዲሱን ዓይነት የሠራተኛ መደብ ማርክሳዊ ሌኒናዊ ፓርቲን (ቦልሼቪክ) በመመሥረት በጥቅምቱ

INFINIX HOT 8 | 13MP
AI TRIPLE CAMERA

የሩሲያ አብዮት ሶሻሊዝምን እውን ለማድረግ ችሏል ። የሠራተኛው መደብ ፓርቲ ጥንካሬ የሚመነጨው ከጠንካራ አንድነቱ ፤ ዲሞክራሲያዊነቱና ፤ ዲስፕሊኑ ነው ።

ኮሚዩኒስታዊ ድርጅታዊ አሠራር የሠራተኛው መደብ ፓርቲ የኃይል ምንጭ ነው ፤

ማርክሳዊ ሌኒናዊ ፓርቲ የኮሚዩኒስቶች የዓላማና የድርጊት አንድነት የሚገልጽበት የሠራተኛው መደብ መሪ የፖለቲካ አካል ነው ። ግንባር ቀደም ሚናውን በሚገባ ሊጫወት የሚችለው በርዕዮተዓለም አንድነት ላይ የተገነባ ጠንካራ ድርጅታዊ አሠራር ሲኖረው ብቻ ነው ። የዚህ ዓይነት ድርጅታዊ አሠራር ለፓርቲው ጥንካሬ ለአባላቱ የመፍጠር ችሎታ መዳበር ፤ ለፖሊሲው ፤ ለመመሪያዎቹና ለውሳኔዎቹ በተቀላጠፈ ሁኔታ ተግባራዊ መሆንና ችግሮችን በቆራጥነትና በጥበብ በፍጥነት መፍታት አማራጭ የማይገኝለት ነው ።

ዲሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት የማርክሳዊ ሌኒናዊ ፓርቲ ድርጅታዊ አሠራር መሠረታዊ መርህ ነው ። መርሁ ከፓርቲው ተፈጥሮ ማለትም ከቆመለት መሠረታዊ ዓላማና ተግባር የሚመነጭና እንደተጨባጭ ሁኔታው ተፈጻሚነት ያለው ነው ። ለፓርቲው ድርጅታዊ አገነባብም ሆነ ለተግባራዊ እንቅስቃሴው መሠረት ነው ። በመሆኑም ዲሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት የአባሎችን ርዕዮተዓለማዊና ድርጅታዊ አንድነት የሚያስተሳስርና በአንድ የጋራ ፖሊሲና መስመር ለመመራት የሚያስችል ሳይንሳዊ የፓርቲ ድርጅታዊ አወቃቀር ፤ አመራርና አሠራር ዘዴ ነው ። የሶሻሊስት ግንባታውም ሂደት ጠንካራ ማዕከልነቱን በተግባር ለመግለጽ እንዲችል ከሁሉም በፊት ፓርቲው የራሱን ጠንካራ ድርጅታዊ ውህደትና አንድ ወጥነት ፤ እንዲሁም አባላቱን ሁሉ ለአንድ ዓላማና ተግባር ለማሰለፍ መቻሉን ማረጋገጥ አለበት ።

የመርሁ የዲሞክራሲያዊነት ገጽታው የፓርቲ አባላት ፤ በእምነትና በፈቃደኝነት ኃይላቸውንና የመፍጠር ችሎታቸውን በመጠቀም ፤ አንድነት ባለው ድርጅታዊ አሠራር ኃይላቸውንና ዕውቀታቸውን በማስተባበር የትግል ተሳትፎ እንዲያደርጉ ሙሉ መብትና ነፃነት የሚሰጥ ነው ። የማዕከላዊነት ገጽታው ደግሞ ሥነሥርዓትን ፤ የዓላማ ጽኑነትንና ድርጅታዊ አንድነትን በማጠናከር የሠርቶ አደሩን ዓላማ ለማራመድ የሚያስፈልገውን አንድወጥ አመራር በመስጠት የተበታተኑ አብዮታዊ ኃይሎችን በአንድ የጋራ የጠራ የፖለቲካ መስመር ማሰባሰብ ማስፈለጉን የሚያሳይ ነው ። ዲሞክራሲያዊነትና ማዕከላዊነት ሁለቱም ሊነጣጠሉ የማይችሉ የዚህ ድርጅታዊ አሠራር ዘዴ ዲያሌክቲካዊ ገጽታዎች ናቸው ።

ዲሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት በፓርቲው ውስጥ ብቻ ሳይሆን ከዚያም ውጭ በተግባር የሚገለጽበት ሁኔታ አለ ። በተለይ ፓርቲው ለሥልጣን በበቃበት ሁኔታ ኮሚዩኒስቶች መርሁን የፓርቲውን አመራር በተቀበሉ መንግሥታዊ ፤ ሕዝባዊ ድርጅቶችና የሙያ ማህበሮች የዕለት ተዕለት ተግባራዊ እንቅስቃሴ ጋር በማዋሀድ በሥራ ለመተርጐም የማያቋርጥ ጥረት ያደርጋሉ ።

ፓርቲው የቆመለት ዓላማ በፓርቲው ድርጅታዊ መዋቅርና አሠራር ውስጥ ከፍተኛ የዓላማ አንድነትና የድርጊት ቅንጅትን የሚጠይቅ በመሆኑ ለዚህ ማዕከላዊነት ዋነኛው መሣሪያ ነው ። ማዕከላዊነት የፓርቲውን የፖለቲካ መስመር ፤ በፓርቲው አመራርና ድርጊት መኖር የሚገባውን አንድነት የሚመለከት በመሆኑ ለዚህ መረጋገጥ የሚከተሉት ሁኔታዎች መሟላት አስፈላጊ ነው ።

— የርዕዮተዓለም አንድነት ፤
— የፓርቲው አንድ መሪ ማዕከል ፤ አንድ ፕሮግራምና አንድ ደንብ ብቻ መኖር ፤
— የበታች አካላት ለበላይ አካላት ውሳኔና ትዕዛዝ ተገዢ መሆንና የጠነከረ ዲስፕሊን መኖር ፤
— የጥቂቶች ለብዙሀን መገዛት ፤
— የበታች አካላት ለበላይ አካላት በየጊዜው ስለ ሥራቸው ሪፖርት ማቅረብ ፤

ከዚህ ለማየት እንደሚቻለው ማዕከላዊነት በፓርቲው ውስጥ ከታች እስከ ላይ ድረስ የተዘረጉትን የፓርቲ አካላት በሥራ እንቅስቃሴ በሚገባ ለማቀናጀትና በአጠቃላይም ከፓርቲው ፖሊሲና መስመር ጋር እንዲስማማ ለማድረግ ያስችላል ። ከፓር

INFINIX HOT 8 | 13MP
AI TRIPLE CAMERA

ቲው ትክክለኛ መስመር ለመውጣት የሚደረገውንም ማንኛውንም ዓይነት ፍንገጣ ፤ ከፋፋይ አዝማሚያና አንጃኝነት ለመከላከልም ይረዳል ። ስለሆነም ለፓርቲው አንድ ወጥ ሕልውናና ትክክለኛ አመራር ማዕከላዊ አሠራር ወሳኝ ነው ።

በሌላ በኩል ደግሞ ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው በፓርቲው ድርጅታዊ አሠራር፤ ማዕከላዊነት ከዲሞክራሲያዊነት ተነጥሎ ሊታይ አይችልም ። ማርክሳዊ ሌኒናዊ ፓርቲ በዲሞክራሲያዊነትም ላይ የተገነባ በመሆኑ የፓርቲው ጉዳዮች የሚፈጸሙት በፓርቲ አባላት ፈቃድ ፤ ተሳትፎና ድምፅ ነው ። ሁሉም የፓርቲ መሪዎች ፤ ሁሉም የፓርቲ አካላት በአባላት የሚመረጡና ሊሻሩም የሚችሉ ናቸው ። በመሆኑም ማዕከላዊነት ሲባል ከቁጥጥር ውጭ የሆነ የግለሰብ ወይም የጥቂቶች አምባገነን ሥልጣን ሳይሆን ሰፊ ዲሞክራሲያዊነት ያለው አመራር ነው ። ዲሞክራሲያዊነቱም በሚከተሉት ዐበይት አሠራሮችና ልምዶች ይረጋገጣል ፤

— የፓርቲ መሪ አካሎች ሁሉ በአባላት ምርጫ የሚቋቋሙ መሆናቸው ፤
— የበታች አካላት በአካባቢ ችግሮች ላይ ውሳኔ ለመስጠትና ለመፍታት መብት ያላቸው መሆኑ ፤
— ፓርቲው በጋራ አመራር መርህ የሚሠራ መሆኑ ።
— የአባላት ሰፊ ዲሞክራሲያዊ መብት መኖር ፤
— የሂስና ግለሂስ በፓርቲው ሕይወት ውስጥ በሰፊው ሥራ ላይ መዋል

በመጨረሻም የመርሁን ሁለት ዐበይት ገጽታዎች በሥራ በመተርጐም በኩል ኮሚዩኒስቶች ከፍተኛ ጥንቃቄ ያደርጋሉ ። መርሁ አጠቃላይ ሲሆን በሥራ የሚተረጐመው ግን እንደተጨባጭ ሁኔታው መሆን ይኖርበታል ። ማዕከላዊነት መቼ መጥበቅ እንዳለበትና ዲሞክራሲያዊነት ደግሞ በምን ሁኔታ ውስጥ ሰፋ ማለት እንዳለበት መታወቅ አለበት ። አለበለዚያ የአንዱ ገፅታ ከሚጠበቀው በላይ ማመዘንና የሌላኛው አለቅጥ መደብዘዝ የተዛባ ሁኔታን በመፍጠር በድርጅታዊ ሥራና አመራር ላይ ችግር ይፈጥራል ። ስለሆነም አንድ ማርክሳዊ ሌኒናዊ ፓርቲ እንደነባራዊ ሁኔታው ማዕከላዊነትን ከዲሞክራሲያዊነት ጋር በማቀናጀት ራሱን ከአደጋ ለመከላከል የሚችል መሆን አለበት ። ይህንን በሚገባ የተረዳው ሌኒን ፤

«እኛ የቆምነው ለዲሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት ነው ። ዲሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት በአንድ በኩል ከቢሮክራሲያዊ ማዕከላዊነት ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ከሥርዐተ አልበኝነት እንደት በብዙ የተለየ እንደሆነ በግልፅ ሊታወቅ ይገባል ፤»[7]

ሲል ሁኔታውን በግልፅ አስቀምጦታል ። ያለዚህ ሳይንሳዊ የሆነ ድርጅታዊ አሠራርና ጥብቅ ዲስፕሊን ትግሉ ሊሠምር አይችልም

ኮሚዩኒስት ለመሆን የሚችለው ማነው ?

የሠራተኛው መደብ ፓርቲ የማርክሲዝም-ሌኒኒዝምን ርዕዮተዓለም ጠንቅቀው ያወቁ ፤ የመደብ ትግልንና የኅብረተሰብን የእድገት ሕግጋት በትክክል የተረዱ ፤ በትግል የተፈተኑ ፤ ታታሪ ፤ ቆራጥና ለዓለም ሠርቶ አደሮች እውነተኛ ነፃነትና እኩልነት ለመስዋት የቆሙ ታጋዮች አምነው በፈቃደኝነት በመደራጀት የሚታገሉበት በዓለምአቀፋዊነት መርህ ላይ የተዋቀረ ድርጅት መሆኑ ቀደም ሲል ተገልጿል ። ኮሚዩኒስቶችም በዚህ ዓይነቱ ፓርቲ በመታቀፍ ለኮሚዩኒዝም ግንባታ የሚታገሉና ለመታገልም ዝግጁ የሆኑ አብዮታዊ ኃይሎች ናቸው ። ተደራጅቶ መታገል የኮሚዩኒስቶች ዓይነተኛ ጠባይ ነው ። ያለአብዮታዊ ድርጅት አብዮት ሊኖር እንደማይችል ጠንቅቀው ያውቃሉ ።

የፓርቲው አባል ለመሆን የሚችለው ማንኛውም አባል ለመሆን የፈለገ ሁሉ ሳይሆን የተወሰኑ መመዘኛዎችን የሚያሟላ ብቻ ነው ። እነዚህም በተግባር የተፈተኑ ሌኒናዊ መለኪያዎች የሚከተሉት ናቸው ፤

— የፓርቲውን ፕሮግራምና ደንብ ከልብ መቀበል ፤
— ከፓርቲው አካሎች በአንዱ ውስጥ በመግባት ኮሚዩኒዝምን በመገንባት ተግባር ንቁ ተሳትፎ ማድረግ ፤
— የፓርቲውን ውሳኔዎች በተግባር መተርጐም ፤

INFINIX HOT 8 | 13MP
AI TRIPLE CAMERA

— ፓርቲውን በአባልነት መጥሮ መርዳት፤

የፓርቲ አባላት ጥራትና ብቃት በአብዛኛው የሚወሰነው በአባላቱ አመላመልና ፓርቲው ከአባላቱ በሚጠብቀውና እሱም በሚሰጣቸው መብት ነው ። ለማርክሳዊ ሌኒናዊ ፓርቲ በአባላት አመላመል ፤ ቁጥጥርና ዲስፕሊን ላይ ልል በመሆን በርዕዮተ ዓለሙና እርሱ ለቆመለት ዓላማ ፅኑ እምነት የሌላቸውን በውስጡ አቅፎ መያዝን የመሰለ አደገኛ ነገር የለም ። ፓርቲው ምን ጊዜም ቢሆን ለጊዜው ሳይሆን የሕይወታቸውን ዘመን በሙሉ ሰፊውን ሕዝብ ለማገልገል ዝግጁ የሆኑ ቆራጥ አብዮታውያንን ያቀፈ መሆን እንዳለበት ሌኒን ደጋግሞ አስገንዝቧል ።

የፓርቲ አባላት ከኅብረተሰቡ የተለየ ልዩ እንክብካቤና ጥቅም የሚሹ ሳይሆኑ ለሰፊው ሕዝብ ፍላጎትና ደህንነት ሲሉ ሁሉን ነገር ከራሳቸው አሳልፈው የሚሰጡ ፤ ከግል ጥቅም የኅብረተሰቡን ጥቅም የሚያስቀድሙና በከባድ አስቸጋሪ ሁኔታ ሁሉ ከሕዝቡ በፊት አልፈው በመቆም የችግሩና የመከራው ገፈት የመጀመሪያ ቀማሾችና ተጋፋጮች የሚሆኑ ናቸው ። በሰፊው ሕዝብና በአብዮቱ ስም በመነገድ የግል ጥቅሙን የማያሳድድ ቆራጥ ኮሚዩኒስት ታጋይ ሌኒናዊ መልኩ ይህ ነው ።

ይህ በንድፈ ሐሳብ ደረጃ ብቻ ያለ አይደለም ። ዛሬ ኮሚዩኒስት በተግባር ምን እንደሚመስል ማውሳቱ ያልታየና ይሆን ይሆናል ተብሎ የሚነገርለት አፈ ታሪክ ወይም ትንቢት ሊሆን አይችልም ። እጅግ አስቸጋሪና ውስብስብ በሆኑ ሥራዎች በግንባር ቀዳሚነት መሳተፍ የኮሚዩኒስቶች የረዥም ጊዜ ልምድ መሆኑ በአንጋፋዋ ሶሻሊስት አገር በሶቪዬት ኅብረትና በሌሎችም ሶሻሊዝምን በገነቡ አገሮች በእርግጥ ታይቷል ። በሶቪዬት ኅብረት ከ1918-21 በተካሄደው የርስ በርስ ጦርነትና የኢምፔሪያሊስት ወራሪዎች ጣልቃገብነት ወቅት በጦር ግንባሩ ጭምር የጦርነቱን ወላፈን በመጋፈጥ አመራር የሰጡት ኮሚዩኒስቶች ነበሩ ። በሶሻሊስት ግንባታውም ኢንዱስትሪዎችን በማቋቋም ፤ በገጠሩም የኅብረት እርሻዎችን በማስፋፋትና በማጠናከር የሶሻሊስት የምርት ግንኙነትን በመመሥረቱ ኮሚዩኒስቶች ዋናው አንቀሳቃሽና መሪ ኃይሎች ነበሩ ። በፀረ-ፋሽስቱም ትግል የሶቪዬት ኅብረት ኮሚዩኒስቶች ብቻ ሳይሆኑ የተለያዩ አገሮች ኮሚዩኒስት ፓርቲዎች ያደረጉት ተጋድሎና ዛሬም በዓለም አቀፍ ደረጃ በኢምፔሪያሊዝምና በአድህሮት ኃይላት ላይ የሚደረገውን ትግል በመምራት የሚጫወቱት ሚናና ኮሚዩኒዝምን ለመገንባት የሚያደርጉት ተግባራዊ ተሳትፎና ጥረት የዐይን ምስክሮች ናቸው ።

የፓርቲ አባላት የጥራት ጉዳይ እጅግ አሳሳቢ መሆን ከዚህ ፓርቲው ከቆመለት ዓላማ ታላቅነት የሚመነጭ ነው።ከኅብረተሰቡ እድገት ጋር በተለያዩ መስኮች የሕዝብ ንቃትና ማህበራዊ ተሳትፎ እየሰፋ ሲሄድ የፓርቲውም የሥራ ድርሻ እያደገና እየሰፋ ይሄዳል ። ከዚሁ ጋር የፓርቲው አባላት ቁጥርም መጨመሩ የማይቀር ቢሆንም ማርክሳዊ ሌኒናዊ ፓርቲ የሚያተኩረው አባላቱን በማብዛቱ ላይ ብቻ ሳይሆን ይበልጡንም የአንድነቱና የጥንካሬው ምንጭ በሆነው በአባላቱ ጥራት ላይ ነው ። ስለዚህ ጉዳይ ሌኒን የሶቪዬት ኅብረት ኮሚዩኒስት ፓርቲን አስመልክቶ ሲናገር ፤

«ፓርቲአችን ፤ የአብዮታዊው ሠራተኛ መደብ ፓርቲ ፤ የአባላትን ቁጥር ከማበራከት ይልቅ ጥራቱን በማሻሻል እንዲሁም ራሱን ከራስ ወዳዶች በማፅዳት ላይ የሚያተኩር በዓለም ብቸኛው መንግሥታዊ ፓርቲ ነው ፤»[8] ብሏል ።

የፓርቲ ገንቢዎች፤ የአመለካከትና የአሠራር አንድነት ያላቸው ፥ ዘወትር ራሳቸውን ለማሻሻል ጥረት የሚያደርጉ ፥ የሚያጠኑ ፥ የሚመራመሩና ስለአሏቸው ችግሮችና ስለወደፊት ሁኔታዎች በራሳቸው ትክክለኛ ውሳኔ ላይ መድረስ የሚችሉ ብቻ ናቸው ። ስለሆነም ኮሚዩኒስት ንቁ የፓርቲ ተዋጊ ፥ ቆራጥና ዓላማ ያለው የኮሚዩኒዝም ገንቢና ለሠርቶ አደሩ ሕዝብ ሟች ነው ። እዚህ ደረጃ ላይ የሚደርሰውም በትግል ሂደት በብዙ ፈተናዎች ውስጥ ተፈትናና ጠርቶ በመውጣት ብዙ ደረጃዎችን አልፎ መሆኑም መታወቅ አለበት ።

ኮሚዩኒስቶች የመላው የኅብረተሰብ አንቀሳቃሽና መሪ ናቸው ። ፓርቲው በአባል ኮሚዩኒስቶች አማካይነት ከሰፊው ሕዝብ ጋር የጠበቀ ግንኙነት አለው ። በዚህም የሕዝቡን ችግርና ብሶት በቅርብ ስለሚያውቅ ችግሮችን ለማቃለል ወቅታዊና አፋ

ጣኝ እርምጃዎችን ለመውሰድ ይችላል ። ለአንድ ኮሚዩኒስት የራሱን የሕዝቡን ልምድና የፈጠራ ችሎታ በመጠቀም እንቅፋቶችን ማስወገድ ዐቢይ ተግባሩ ነው ። ሌኒን የሰፊውን ሕዝብ ሰፊ ተግባራዊ ልምድና የፈጠራ ችሎታ ተገንዝቦ ለመጠቀም የማይችል ኮሚዩኒስት ሊባል እንደማይችል ይናገራል ። ለዚህም መሠረቱ ከሰፊው ሕዝብ ጋር መኖር የሚገባው የጠበቀ ግንኙነት መሆኑንና ይህም ግንኙነት ምን መልክ እንደሚይዝ እንደሚከተለው ያስቀምጣል ፤

«በቀጥታ በራሱ በሰፊው ሕዝብ ውስጥ መኖር ።
«ጠባዩንና ስሜቱን ማወቅ ።
«ስለሱ ያለውን ሁሉ ማወቅ ።
«ሰፊውን ሕዝብ መርዳት ።
«እርሱን ለማቅረብ መቻል ።
«ሙሉ እምነቱን ማግኘት ።
«መሪዎችን ከሰፊው ሕዝብ ፤ ግንባር ቀደሙን ከጠቅላላው ሠራዊት ስለመነጠል ።»[9]

ኮሚዩኒስቶች ሰፊውን ሕዝብ ከጐናቸው ሊያሰልፉና ሊመሩት የሚችሉት እሱን በማስተማር ብቻ ሳይሆን ራሳቸውም ከሕዝቡ በመማር ፤ በትእዛዝና በማስገደድ ሳይሆን ሳይሰለቹ በማስተማር ፤ በማሳመንና አርአያ በመሆን ብቻ ነው ። በተለይ ፓርቲው ሥልጣን በያዘበት ቦታ መንግሥታዊ አካሎች ፤ሕዝባዊ ድርጅቶች ፤ የኅብረት ሥራ ማኅበራት ፤ የሙያ ማኅበራትና ሌሎችም የሠርቶ አደሩ ድርጅቶች በፓርቲውና በሕዝቡ መካከል ያሉ ድልድዮች ናቸው ። በነዚህ ሰፊ ድርጅቶች አማካይነት ኮሚዩኒስቶች ለሰፊው ሕዝብ ርዕዮተዓለማዊ ፤ ድርጅታዊና ፖለቲካዊ አመራር በመስጠት በተለያዩ የሥራ መስኮች የፓርቲው ፖሊሲ ተጨባጭ እንዲሆን ያደርጋሉ ። ፓርቲው ሕዝባዊ ድርጅቶችን እንዴት ይመራል?

«ፓርቲው የሠርቶአደሩ ሕዝባዊ ድርጅቶች መሪና አስተማሪ ነው ። ትክክለኛውን የፖለቲካ መስመር ይቀይሳል ፤ የሁሉንም ማኅበራዊ ተቋሞች ተግባራዊ የሥራ ድርሻና አቀጣጫ ግልፅ ያደርጋል ፤ ሥራቸውን ያስተባብራል ፤ መሪ የሚሆኑትንም በመመልመል ያጠናክራቸዋል ። የሕዝባዊ ድርጅቶችንና የሥልጣን አካሎችን ሥራ ለመምራት የሚችለው የመላውን ሕዝብ ፍላጉት የሚገልፅና የጋራ ፍላጉታቸውን የሚወክል ፓርቲ ብቻ ነው ።»[10]

ኮሚዩኒስቶች በፓርቲያቸው አማካይነት በእያሉ ሕዝባዊ ድርጅቶችና የሙያ ማኅበራት ለታቀፈው ሠርቶአደር ሕዝብ የበሰለ አመራር በመስጠት በአዲሱ ኅብረተሰብ ግንባታ ተግባር ያሰልፉሉ ።ኮሚዩኒዝም የሰፊው ሠርቶ አደር ሕዝብ ንቁና ዓላማ ያለው ተሳትፎ ውጤት በመሆኑ ከዚህ ሌላ ሊመጣ የሚችልበት አማራጭ መንገድ አይኖረውም ። እውነተኛ ሰብዓዊነት የሚመጣውም በብዙሃኑ ትግልና መስዋዕትነት በዚህ አዲስ ኅብረተሰብ ኀልውና ማግኘት ብቻ ነው ።

ኮሚዩኒዝምና ሰብዓዊነት ፤

ያለንበት ዘመን ከካፒታሊዝም ወደሶሻሊዝም ሽግግር የሚደረግበት ወቅት ነው ። በዚህ ታሪካዊ ወቅት ፣ አዲስ ባይሆንም የሞኖፖል ቡርዧዎችና የመላው አድሀሮት ሃይላት ፀረ ኮሚዩኒስት ፕሮፓጋንዳና ቅስቀሳ ከመቼውም ጊዜ ይበልጥ ውስብስብና አስቸጋሪ ሆኖ መገኘቱ የሚያስደንቅን አይሆንም ። የሚያስደንቀን ነገር ቢኖር የነዚህ የፀረ-አብዮትና የአድሀሮት ሃይላት ምሽጐች «ሰብአዊነትን» ዋና ፀረ-ሶሻሊስትና ፀረ-ኮሚዩኒስት መሣሪያቸው አድርገው መነሳት ነው ። እነሱ እንደሚያቀርቡት ኮሚዩኒዝም ሰብአዊነትን የሚረግጥ ሳይሆን እንዲያውም ሰብአዊነት በትክክል የሚረጋገጥበትና እውን የሚሆንበት ስርዓት ነው ።

ሰብአዊነት ምንድነው? ፅንሰ ሀሳቡ በኀብረተሰብ እድገት ውስጥ ሰፊና ረዥም ታሪክ ያለው ቢሆንም ባመሠረቱ የሰብአዊ ክብርን ፤ ፍትህን ፤ እኩልነትን ፤ ነፃነትን ፣ የሰውን ልጅ ደህንነትና የተሟላ እድገት ጥያቄን ይዞ የሚነሳ አስተሳሰብ ነው ። ሰብአዊነት ምዝበራንና ጭቆናን በመቃወም በተደረጉት ሕዝባዊ ትግሎች ውስጥ በግብታዊነት የተከሰተ ቢሆንም ፣ በተለይም ከ14ኛው እስከ 16ኛው ምዕተ ዓመት በታየውና «የተሀድሶ ዘመን» (ሬኔሳንስ) በመባል በሚታወቀው ታሪካዊ ወቅት አንድ ራሱን የቻለ ርዕዮተዓለማዊ ንቅናቄ ሆኖ መውጣቱ አልቀረም ። ሆኖም በዚህን ጊዜ

በአብዛኛው መልኩ ፊውዳሊዝምንና የቤተ ክህነትን ተፅዕኖ ይታገል የነበረውን የቡርዧውን መደብ ርዕዮተዓለም የሚያንፀባርቅ ነበር ። የግለሰብን ነፃነት የሚያነሳ ፣ ከሞት በኋላ መንግሥተ ሰማያትን ለመውረስ በምናኔ ከኅብረተሰብ ተገልሎ መኖርን የሚቃወምና በምድራዊ ደስታ የሚያምን በመሆኑ ተራማጅነትም ነበረው ። እንደነዳንቴ ፣ ሊዮናርዶ ዳቪንቺ ፣ እራስመስ ፣ ሼክስፒር እና ፍራንሲ ስቤከን የመሳሰሉት የዚህ ዘመን ቀደምት ሰብአውያን የዚህ ዓይነቱን በጎ አስተሳሰብ ቢያስተጋቡም አስተሳሰባቸው ከሠርቶ አደሩ ሕዝብ ፍላጐትና ዓላማ የራቀ በመሆኑ ትግሉን የሚያራምድና የሚያጠናክር ሳይሆን የሚያደናቅፍ ነበር ።

የቡርዧው ስብአዊነት ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደርሶ የእድገት ጣሪያውን የነካው በ18ኛው ምዕተ ዓመት የቡርዧው መደብ «ነፃነት ፣ እኩልነት ፣ ወንድማማችነት» በማለት የሰውን ልጅ የተፈጥሮ ችሎታን ያለአንዳች እክል ማደግ በመጠየቅ በፊውዳሉ ሥርዓት ላይ ዐመፅ ባነሳበት ወቅት ነበር ። ያኔም ቢሆን የቡርዧው የስብአዊነት አስተሳሰብ ከግል ሀብት ይዞታው ፣ ከመደብ ጥቅሙና ጠባብ የግል ፍላጐት አልፎ የሠርቶ አደሩን የኑሮ ሸክም ሊያቃልል ብሶትና ዋይታውን ሊያስታግስና የተባለውን ነፃነት ሊያጐናፅፈው አልቻለም ።

ኋላ የመጡት ተምኔታዊ ሶሻሊስቶችም የካፒታሊስቱን ሥርዐት ፀረ ስብአዊ ተፈጥሮ ለማየት የቻሉና ያለርህራሄ ያወገዙ ቢሆንም ፣ ሥርዓቱን በማጥፋት በአዲስና በተሻለ ሥርዐት ለመተካት ቢነሱም የስብአዊነት አስተሳሰባቸው በኅብረተሰብ ነባራዊ የእድገት ሕግጋት ላይ የተመረኮዘ ባለመሆኑ ፍትህ ፣ ሰላምና እኩልነት የሰፈነበት ኅብረተሰብ ህልውና የሚያገኝበት ዘዴና መንገድ ሊከሰትላቸው አልቻለም ። ይህ ተሟክቶ ተግባራዊ የሆነው በሳይንሳዊ ሶሻሊዝም መመሪያ በተገነባ እውነተኛ የሶሻሊስት ሥርዓተ ማኅበር ውስጥ ብቻ ነው ።

ሶሻሊስት ወይም ኮሚዩኒስት ስብአዊነት ከዚህ ከተሳሳተው ከቡርዧው ግብዝና የይስሙላ ስብአዊነት ጋር ፍጽም የማይሄድ ነው ። የኮሚዩኒስት ስብአዊነት በማርክሳዊ ሌኒናዊ ንድፈሀሳብ በመመራት ሠራተኛው መደብ ሠርቶ አደሩን ሕዝብ አስተባብሮ በሚያካሂደው አብዮታዊ ትግል በሚገነባው የሶሻሊስት ብሎም የኮሚዩኒስት ኅብረተሰብ ውስጥ የሚገኝ ነው ። ለዚህም መሠረቱ የማምረቻ መሣሪያዎች ከግል ይዞታ ወደ ማኅበራዊ ይዞታ መሸጋገርና ከዚሁ ጋር የመደብ ጭቆና ማክተም ነው ። ይህም ስብአዊነት ተሟልቶ የሚገኘው በአንድ ጊዜ ሳይሆን ለኮሚዩኒዝም በተሟላ መልኩ መመሥረት በሚደረገው ትግል ውስጥ ያለማቋረጥ እያደገና እየዳበረ በመሄድ ነው ። የእያንዳንዱ ሰው ሙሉ ነፃነት የሚረጋገጠውና ለተሟላ ዕድገቱም ሁኔታዎች የሚፈጠሩት በዚሁ የአዲሱ ሥርዓተ ግንባታ ሂደት ውስጥ ነው ። ብዝበዛና ጭቆና በሁሉም መልኩ ሲያበቃለት ፣ በሰዎችም መካከል በእውነተኛ እኩልነት ላይ የተመሠረተ ወዳጅነት ፣ ወንድማማችነትና ጓዳዊነት ሲፈጠር እውነተኛ ስብአዊነትም ይመሠረታል ። በመሆኑም ስብአዊነት ከመደብ ጥቅም ውጭ ፍጹም ሊታይ የማይችል ነው ።

«ኮሚዩኒዝም ሁሉንም የልዩነት ቅሪቶች ጠርሶ የሚያጠፋና (ከእያንዳንዱ እንደ ችሎታው ፣ ለእያንዳንዱ እንደ ፍላጐቱ) የሚለውንና ፍትህ በከፍተኛ መልኩ የሚታይበትን መርህ ተግባራዊ በማድረግ ለግለሰቦች የተሟላ እድገት አስፈላጊዎቹን ሁኔታዎች የሚያሟላ ስለሆነ ሰብአዊነት በከፍተኛ ደረጃ የሚገለጥበት ነው ።»[11]

ከዚህ ለማየት እንደሚቻለው ኮሚዩኒዝም ግለሰብን ፣ ኅብረተሰብንና በአጠቃላይ የሰውን ልጅ ከማንኛውም የመደብ ተፅዕኖና እውር የተፈጥሮ ተገዥነት በማላቀቅ እውነተኛ ነፃነትን የሚያጐናፅፍ በመሆኑ እውነተኛ ስብአዊነት ነው ።

አስፈላጊነት ፣ ግዴታና ሰብአዊ ነፃነት

ማርክሳዊ ሌኒናዊ ፍልስፍና የቁስአካላዊውን ዓለም የለውጥና የእድገት ሕግጋት ዕውቀት ለሠርቶ አደሩ ሕዝብ በማስጨበጡ የሰው ልጅ ከማንኛውም ዓይነት ጭቆና

ራሱን የሚያላቅቅበትና አዲስ ነፃ ሕይወት የሚገነባበት ሀያል የትግል መሣሪያ አግኝቷል ።

የኮሚዩኒስት ሥርዐት የሰው ልጅ ነፃነት የሚረጋገጥበት እንደሆነ ተጠቅሶአል ። ለመሆኑ ነፃነት ምንድነው? (ተራ ትርጉሙ ነፃነት ያለአንድ የውጭ ተፅዕኖ አስገዳጅነት የፈለጉትን ማድረግ ነው ። ግን ይህ ይቻላል ወይ? በሄግል ፖለቲካዊ አስተሳሰብ ግለሰብ ራሱን ለመቆጣጠር የሚሳነው ስለሆነ በራሱ ስሜታዊ እርምጃ ተነሳስቶ ራሱን እንዳይጐዳና ለራሱ ደህንነት ሲባል በሚያደርገው ሁሉ በሌላ ኃይል ማለትም በመንግሥት መመራት አለበት በማለት የሰውን ልጅ ነፃነት በዚህ ይወስናል ። በመሠረቱ ግን ሰው በአጠቃላይ ሲታይ ስሜቱን ለመቆጣጠርና ራሱን ለመግዛት የሚችል በመሆኑ ይህ አድሀሪ አመለካከት ነው ።

በደፈናው ስለ ነፃነት መናገርም አይቻልም ። የማን ነፃነት? ነፃነት ከምን? ነፃነት ለምን? የሚሉት መሠረታዊ ጥያቄዎች መመለስ አለባቸው ። ሰዎች በተለያየ መንገድ ከተለያዩ ኃይሎች ራሳቸውን ነፃ ለማውጣት የሚታገሉት ነፃ መሆንና ነፃ አለመሆን ባለበት ማኅበራዊና ተፈጥሮአዊ ሁኔታ ውስጥ ፤ በአንድ በኩል ከአንዳንዶቹ ተፅዕኖዎች ራሳቸውን ነፃ ለማድረግ ሲችሉ፤ በሌላ በኩል ደግሞ በሌሎች ኃይሎች ተፅዕኖ ሥር ናቸው ። ተራ ምሳሌ ብንወስድ አንድ ሰው መጠለያ የማግኘት ችግሩን ቢያቃልል በሌላ በኩል በልብስ ወይም በምግብ ዕጦት ሊጠቃ ይችላል ። ከሰው ተፅዕኖ ሲላቀቅ ደግሞ የተፈጥሮ ተፅዕኖ አለበት ። ስለሆነም በዚህ ተፅዕኖ ባለበት ሁኔታ ሊኖር የሚችለው ነፃነት ከፊል እንጂ የተሟላ ነፃነት ሊሆን አይችልም ።

ቢሆንም ይህ ነፃነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየሰፋ የሚሄድ ነው ። ሰዎች ከሚፈጽሙአቸው አያሌ ተግባሮች አንፃር የሰው ልጅ ነፃነት እያደገ ይሄዳል ። በሳይንስና ቴክኖሎጂ መዳበር የሰው ልጅ በተፈጥሮ ላይ የሚኖረው ቁጥጥር ለዚህ ዋነኛው አስፈላጊ ሁኔታ ነው ። የሰው ልጅ የተፈጥሮ ሕጐችን ምስጢር የበለጠ አውቆ ለራሱ እንዲጠቅም ማድረግ መቻል የነፃነቱን አድማስ ያስፋለታል ። ሆኖም በመደብ ኅብረተሰብ በሳይንስና ቴክኖሎጂ በሚስፋው ነፃነትና በሰዎች ማኅበራዊ ግንኙነት ውስጥ ግለሰቡ ከዚህ እድገት ለመካፈል ባለው ዕድል መካከል ቅራኔ ይፈጠራል ። ገዥ መደብ የዚህን የሳይንስና የቴክኖሎጂ እድገት ውጤት የሆነውን የማምረቻና የምርምር መሣሪያዎች በግል ሀብትነት ይዞ በራሱ የመደብ ጥቅም ለመወሰን ይፈልጋል ። የዕድገቱን ፍሬ የመካፈል ዕድል የሚነፈጉት መደቦች ደግሞ ከዚህ ተፅዕኖ ለመላቀቅ ለነፃነታቸው ለመታገል ይነሳሉ ።

በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ለነፃነት መኖር የተወሰኑ ሁኔታዎች መሟላት እንዳለባቸው ማወቅ አስፈላጊ ነው ። በአንድ ወቅት ነፃነት ከሰው ቁጥጥር ውጭ በሆነ ማኅበራዊ ወይም የተፈጥሮ ኃይል ሊወሰን ይችላል ። የሰው ልጅ እነዚህን የተፈጥሮ ሕግጋት በመጣስ እሱ የፈለገውን ለማድረግ የማይችልበት ሁኔታ ይኖራል ። ይህ በሚሆንበት ጊዜ የሰው ተግባር የተፈጥሮን ሕግ መጋፋት ሳይሆን ሚስጥሩን አውቆና ተገንዝቦ ለሱ እንደሚጠቅም አድርጐ ለመጠቀም መቻል ነው ። ይህን ለማድረግ ከቻለ የነፃነቱን አድማስ ለማስፋትና የበለጠ ለመንቀሳቀስ ቻለ ማለት ነው ።

በአንድ ወቅት ይህን የማድረግ ችሎታው የተወሰነ ቢሆንም ከጊዜ በኋላ ማሟላቱ የማይቀር ነው ። ኤንግልስ እንዳለው ፤

«ነጻነት በተፈጥሮ ግደታ (ሕግ) ዕውቀት ላይ የተመሠረተ በራሳችንና በውጭው ዓለም ላይ ያለን ቁጥጥር ነው ፤ ስለሆነም የግድ የታሪካዊ እድገት ውጤት ይሆናል ። ራሳቸውን ከእንስሳት ዓለም ያወጡ የመጀመሪያዎቹ ሰዎች በአስፈላጊ ነገሮች ሁሉ እንደ እንስሳቱ ነጻ አልነበሩም ፤ ሆኖም በባህል መስክ የታየው እያንዳንዱ የወደፊት ርምጃ ወደ ነጻነት የሚያቀርብ አንድ ርምጃ ነበር ።»[12]

እንግዲህ የተፈጥሮ ሕግ መኖር በአንድ በተወሰነ ወቅት የሰውን ነፃነት የሚወስን ቢሆንም ሰው የተፈጥሮን ሕግ ምስጢር እየተረዳ መሄዱ ቀስ በቀስ ሙሉ ነፃነቱን እንዲጐናጸፍ ያስችለዋል ። ለነፃነት መስመስፋት የተፈጥሮ ሕጐች የበለጠ እየታወቁ መሄድ አስፈላጊ ይሆናል ማለት ነው ። በኅብረተሰብና በሰዎች መካከል በሚኖረው ማኅበራዊ ግንኙነትም ለነፃነት መስፋት

ማለትም ከመደባዊ ተፅዕኖ እየተላቀቁ መ
ሄድ ኅብረተሰብን የሚገዙትን ሕግጋት መና
ኖርና ምንነታቸውን መገንዘብ አስፈላጊ
ነው ። እንደ ተፈጥሮ ሕግጋት የኅብረተሰብ
የእድገት ሕግጋትም ነባራዊ ሕጐች ስለ
ሆኑ አስፈላጊ ሁኔታዎች ናቸው ። እነዚህ
አስፈላጊ ሁኔታዎች በግልፅ ሲታወቁ አስፈ
ላጊነት (ነሴሲቲ) ወደ ግዴታ (ኦብሊጌ
ሽን) ይለወጣል ። ይህም ማለት የሰው ልጅ
እነዚህን የማኅበራዊ ኑሮ ሕግጋት ጠን
ቅቆ በመረዳትና በተገኘውም ዕውቀት በሚ
ያከናውነው ድርጊት ማኅበራዊ ነፃነቱን
እያሰፋና እየሟላ ይሄዳል ። የኋላ ኋላም
በኮሚዩኒስት ሥርዐት መገንባት የሰው
ልጅ ከአስፈላጊነት ክልል ወጥቶ ወደ ተ
ሟላ ነፃነት ክልል ይሸጋገራል ። በማኅበ
ራዊ ኑሮውም ልዩ ስብዕና ፣ ልዩ ሥነ ምግ
ባር ያለው ይሆናል ።

የማርክሳዊ የስብዕና (ፐርሶናሊቴ) ፅንሰ ሀሳብ ግንዛቤ

ስለ ስብዕና ያለው አስተሳሰብም የመ
ደብ ባህሪይ ያለው ነው ። የቡርዧ ምሁ
ራን የሰውን ልጅ ተፈጥሮና የተሟላ የስብ
ዕና ዕድገት ሲተነትኑ ኢሳይንሳዊ ከሆነ
አመለካከትና የምርምር ዘዴ በመነሳት
ነው ። በዚህም አስተሳሰባቸውና አሠራራ
ቸው ሕሊናዊውን ከማኅበራዊ ሕልውናው
በማስቀደም ማርክሲስቶች የሰውን ልጅ
ተፈጥሮ ለመግለጽና ለችግሮቹም መፍትሔ
ለመሻት የሚነሱት ከኅብረተሰቡ የምርት
ግንኙነት መሆኑን ይቃወማሉ ። ከዚህ በመ
ነሳትም ሶሻሊዝም ለሰው ልጅ ደህንነት ፣
ብልጽግናና ሙሉ እድገት ጨርሶ እንዳል
ቆመ አድርገው ያቀርባሉ ። ማርክሲስቶች
ከሰው በላይ የሆነ ሶሻሊዝም በመፍጠር
ሰውን የሥራ ባሪያ የሚያደርግና መንፈሳዊ
ሕይወት የሚያሳጣ ነው በማለት ይወነጅ
ላሉ ። ሶሻሊዝም የግለሰብን ነፃነት ፣ ልዩ
ጠባይ ፣ ችሎታ ፣ ተሰጥኦና ዝንባሌ የሚያ
ጠፉና ከተፈጥሮዋቸው ውጭ በኃይል ሁ
ሉንም ሰዎች አንድ ዓይነት ለማድረግ ይፈ
ልጋል ይላሉ ። ይህ አባባል በመሠረቱ የተ
ሳሳተ አመለካከት ቢሆንም የመደብ ይዘት
ያለው ነው ። ጭቁን መደቦችን ከሶሻሊዝም
ብሩህ ዓለም ትይዩ ለማስበርገግ ሆን ተብሎ
የሚነዛ የቡርዧ ፕሮፓጋንዳ መሆኑ መታ
ወቅ አለበት ።

ስለ ማርክሳዊ የስብዕና ፅንስ ሀሳብ
ግንዛቤ ስናነሳ በቅድሚያ ግልፅ መሆን
ያለባቸው ሁለት ፅንስ ሀሳቦች አሉ ። እነ
ዚህም ግለኝነት (ኢንዲቪጁዋሊዝም) እና
ግለሰባዊነት (ኢንዲቪጁዋል ፐርሰናሊቲ)
የሚሉ ናቸው ። ግለኝነት የግለሰብ ከኅብ
ረተሰብና ከማንኛውም ማኅበራዊ ሀይል
ተፅዕኖ ውጭ መሆንና ፍጹም ነፃነትን የሚ
ሰብክ የተሳሳተ የቡርዧ አስተሳሰብ ነው ።
በዚህም ፣ ግለኝነት በሰው ተፈጥሮ ውስጥ
ያለና ሊለወጥ የማይችል ነው ይላሉ ።
በይዘቱ ከግል ሀብትና ከመደቦች ጋር ተያ
ይዞ የመጣና የግለሰብን ፍላጐት ከኅብረተ
ሰቡ ፍላጐት በላይ አድርጐ የሚመለከት
ነው ። ይህም በመጨረሻ ወደ ግለሰብ አም
ባገነንነትና ፣ የሰው ጥላቻ የሚያመራና የብ
ዙኀንን በግለሰብ መረገጥና በሰፊው ሕዝብ
ታሪክ ሠሪነት እምነት ማጣትን የሚያስከ
ትል ፀረ ስብአዊ አመለካከት ነው ።

ግለሰብአዊነት ግን የግለሰብን ልዩ
ጠባይ ችሎታ ፣ ተሰጥኦና ዝንባሌ የሚያ
ጠቃልል የግለሰብ የተፈጥሮ ባሕርያት
አጠቃላይ ድምር ነው ። ማርክሲዝም ግለ
ሰብ ካለበት ታሪካዊ ወቅትና ማኅበራዊ
ተጨባጭ ሁኔታ በመነሳት የእነዚህን የግ
ለሰብ ባህርያት መኖር ይቀበላል ። ከዚህ
ውጭ እንዲያው በደፈናው ስለ ስብዕና
መናገር እንደማይቻልና በእንቅስቃሴና በእ
ድገት ላይ የተመሰረተ መሆኑን ያምናል ።
የስብዕና ታሪካዊና ቁሳዊ ግንዛቤ መሠረቱ
ለማኅበራዊ ግንኙነቶች ሁሉ መሠረት የሆ
ነው የምርት ግንኙነት ነው ። በዚህ ውስጥ
ግለሰብ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከሌሎች
ሰዎች ጋር በአያሌ ድሮች የተሳሰረ በመሆኑ
ስብዕናውም የሚያድገውና የሚዳብረው በ
ዚሁ በተወሳሰበ ማኅበራዊ ግንኙነት ው
ስጥ ነው ። ማርክስ እንዳለው ፤

«የሰው ምንነት (ኢሴንስ) በእያንዳንዱ ግለ
ሰብ ሡስጥ ያለና ሊዳሰስ የማይችል አይ
ደለም ። በትክክል ሲታይ የማኅበራዊ ግንኙ
ቶች ጠቅላላ ድምር ነው ።»[13]

ስብዕና በማኅበራዊ ግንኙነት ዓይነት
ይወሰናል ። የአንድ የመደብ ኅብረተሰብ
አባላት ሁሉ አንድ ዓይነት ስብዕና ሊኖራ
ቸው አይችልም ። ሰው ማኅበራዊ እንስሳ
ነው ። ሆኖም ከሌሎች እንስሳት የሚለየው
በምርት ላይ ቢተመሠረቱ አያሌ ማኅበራዊ

ግንኙነቶች ነው ። እያንዳንዱ ሰው የመደብ ጀርባውንና ማንነቱን የሚያንፀባርቅ የራሱ ስብዕና አለው ። በተለያየ አካባቢ ሁኔታ የሚወለድ በመሆኑም የራሱ የተለየ ልምድና አስተዳደግ ይኖረዋል ። ከዚህም የተነሳ የራሱ ፍላጐት ፡ ዝንባሌ ፡ አስተሳሰብና ስሜት አለው ። ይህም በሥራ ምርጫው ፡ በቆመለት አላማና በአስተሳሰቡ የሚገለፅ ነው ። በመሆኑም ስብዕና ስነ-ህይወታዊ ስነ-ልቦናዊ ማህበራዊና የሌሎች አያሌ ግንኙነቶች ውጤት ነው ። በሌላ አነጋገር ስብዕና ከኅብረተሰብ ጋር ጥብቅ መተሳሰርና መስተጋብር ያለው የማኅበራዊ ግንኙነቶችና የግለሰብ ልዩ ባህሪያት ዲያሌክቲካዊ ውህደት ነው ።

ስብዕና የተወሰነ ኅብረተሰብ ውጤት መሆኑ ብቻ ሳይሆን የኅብረተሰብ ለውጥ መሣሪያም ነው ። ምክንያቱም ሰው በምርት ተግባር ተሳትፎው ፡ በሥራ ልምዱ ክምችትና በዕውቀቱ መዳበር ማኅበራዊ ግንኙነቱን በመለወጥ ኅብረተሰቡን በተሻለ ሁኔታ እንዲለወጥ ያደርጋል ። የኅብረተሰብ እድገት የስብዕናን መዳበር እንደሚያሳይ ሁሉ የእያንዳንዱም ግለሰብ ዕውቀት ፡ ንቃትና ልምድ መስፋፋት እና ጥልቀት እያገኘ መሄድ የኅብረተሰብን ዕድገት ወደ ፊት መራመድ ያመለክታል ።

ሆኖም የኮሚዩኒስት ስብዕና በሶሻሊስት ኅብረተሰብ አባሎች ላይ ሁሉ ይንፀባረቃል ማለት አይደለም ። ነገር ግን ሶሻሊዝም ለዚህ ዓይነቱ የተሟላ ስብዕና መፈጠር አመቺ ሁኔታን ስለሚፈጥር በመደብ ኅብረተሰብ በስብዕናና በኅብረተሰብ መካከል ያለው ቅራኔ በሶሻሊስት ግንባታ ሂደት ውስጥ በየጊዜው እየጠበበ በመሄድ የሁለቱን መጣጣምና አብሮ ማደግ ፡ እንዲሁም የግለሰብ ነፃነትን ከኅብረተሰቡ ነፃነት ጋር መጣጣም ያስከትላል ። የዚህ ዓይነቱም ስብዕና ኮሚዩኒስታዊ ዲስፒሊንና ሥነ ምግባር የሚንፀባረቅበት የተሟላና እጅግ የላቀ ስብእና ነው ።

ኮሚዩኒስታዊ ሥነ ምግባር በተግባር ሲገለጽ (ሞራሊቲ)

የሰው ልጅ በኅብረት መኖር ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ በአባሎቹ ላይ አንዳንድ የሥነ ምግባር ወይም የሞራል ግዴታዎችን ሲደነግግ ቆይቷል ። ሆኖም እነዚህ ድንጋጌዎች እንደ ኅብረተሰቡ የኢኮኖሚ ግንኙነቶችና እድገት ሲቀያየሩና ሲሻሻሉ ኖረዋል ። በጥንታዊ የጋርዮሽ ኅብረተሰብ የሥነ ምግባር መለኪያዎች በሁሉም የኅብረተሰቡ አባሎች ላይ ተፈጻሚነት ነበራቸው ። ቀስ በቀስም መደቦች ሲፈጠሩ የሥነ ምግባር መለኪያዎች የመደብን አቋምና ጥቅም ያንፀባርቁ ጀመር ። በመሆኑም በተፃራሪ መደቦች መካከል የመዝባሪዎች የሥነ ምግባር መለኪያዎች የበላይነቱን ያዙ ። ስለሆነም በባሪያው ኅብረተሰብ የባሪያዎቹ ጌቶች ፡ በፊውዳሉ ኅብረተሰብ የፊውዳል ገዥዎች ፡ በቡርዧው ኅብረተሰብ የቡርዧዎቹ ሥነ ምግባር መለኪያዎች ሲኖሩ በአንፃሩ ደግሞ የባሪያዎቹ ፡ የአፈር ገፊውና የወዝ አደሩ የሥነ ምግባር መለኪያዎች ነበሩ ፡ አሁንም አሉ ።

የአንድ ኅብረተሰብ የሥነ ምግባር መለኪያ ማንኛውንም የኑሮ መስክ የሚመለከት ነው ። ሰዎች ስለ ሥራም ሆነ ስለ ንብረት ባላቸው ዝንባሌ የኢኮኖሚውና የፖለቲካው አቋም ይወሰናል ።

ለምሣሌ የሶሻሊስት ሥነ ምግባር መለኪያ ሀብት የኅብረተሰብ መሆኑን ስለሚደነግግ ለሶሻሊዝም የኢኮኖሚ መሠረት ሆኖታል ። የሶሻሊስት ሥነ ምግባር መለኪያ የብዙሀኑን ጥቅም መጠበቅ ነው ። ኤንግልስ ይህንን ሁኔታ በትክክል እንዲህ ሲል ገልጾታል ፤

«ሰዎች በማወቅም ሆነ ባለማወቅ ስለ ሞራል ያላቸው አስተሳሰብ በመጨረሻ የሚመጣው የመደብ አቋማቸው ከተመሠረተበት ተግባራዊ ግንኙነቶች ማለትም የማምረትና የልውውጥ ተግባሮች ከሚያከናውኑባቸው የኢኮኖሚ ግንኙነቶች ነው ። - - - ሥነ ምግባር ምንግዜም የመደብ ሥነ ምግባር ነው ፤ ይህም ሥነ ምግባር ወይ ለገዥ መደብ የበላይነትና ፍላጐት የቆመ ወይም ጭቁኑ

መደብ ጠንክሮ ሲወጣ ጭቁኖች በዚህ የገኙ መደብ የበላይነት ላይ የሚያደርጉትን አመፅና የነሱን የወደፊት ፍላጉት የሚጠክል ነው ።»[14]

የብዙሁኑ ሞራል ጭቁኖች በትግላቸው ዘመናት ያዳበሩት ሥነ ምግባር በመሆኑ የሰው ልጅ የደረሰበት በጊዜያችን ተወዳዳሪ የሌለው የኑሮና የሥራ ሥነ ምግባር የኮሚዩኒስት ብሎም ወዝ አደራዊ ሥነ ምግባር ወይም ሞራሊቲ ነው ። የኮሚዩኒስት ሥነ ምግባር ወገናዊና አብዮታዊ በመሆኑ ማንኛውንም ዓይነት ብዝበዛና ጭቆና ለማጥፋት የሚረዳ የትግል መሣሪያ ነው ። የሰው በሰው መበዝበዝ እስካላከተመ ድረስ የሁሉም መደቦች የሆነ ሥነ ምግባር ሊኖር አይችልም ።

የኮሚዩኒስት ሥነ ምግባር በተግባር ሲገለጽ ምን ይመስላል? አንድ ኮሚዩኒስት በዓላማውና በድርጊቱ አርአያ ነው ። ሞያውን ማሻሻል ፣ የሥራ ውጤቱን ብዛትና ጥራት በየጊዜው ከፍ ማድረግ ፣ተራማጅ የሆኑ የአሠራር ዘዴዎችን ማቅረብ ፣ አዲስ ቴክኖሎጂን ማጥናትና ተራማጅ ልምዶችን መቅሰም ፣ የሶሻሊስት ንብረትን መጠበቅ መንከባከብና አጥፊዎችን በለዘብተኝነት አለማለፍ መሠረታዊ ተግባሮች ናቸው ። ኮሚዩኒስት በማንኛውም በተሠማራበት የሥራ መስክ ማለትም በምርት ፣ በንግድ ፣ በሳይንስ ፣ በሥነ ጥበብ ፣ በኢኮኖሚ ፣ በሕዝባዊ አስተዳደር ፣ በማስተማር በምርምርና በሌሎችም ዘርፎች ሁሉ በንቃትና በቆራጥነት በመሳተፍ በአሠራሩ በሥራ ውጤቱና ከሌሎች ሰዎች ጋር ባለው ግንኙነት ሁሉ ግንባር ቀደምትነቱንና አርአያነቱን በተግባር ማስመስከር አለበት ።

አንድ ኮሚዩኒስት የተጣለበት ሕዝባዊ አደራና የሥራ ሀላፊነት ክብደት ምን ያህል እንደሆነ ጠንቅቆ የተረዳ የነቃ ክፍል በመሆኑ፣ ያለሌላ የውጭ ኃይል ግፊትና አስገዳጅነት ሀላፊነቱን የሚወጣ ነው ። ኮሚዩኒስት ታጋይ ሌላ ሰው ወይም የበላይ አካል አየኝ አላየኝ ብሎ የሚሠራ አይደለም ። የማይገባ ተወዳጅነትንም ለማግኘት ሲል በሌሎች ፊት ታታሪ ሠራተኛ መስሎ የሚቀርብ አይደለም ። አብዮታዊ መፈክሮችን በማኙጉድጉድ ብቻ የአፍ ተራማጅ የተግባር ደሀ የሆነም አይደለም ። በአስቸጋሪ ሁኔታ ሌላውን በማስቀደም ከኋላ በመሆን በሌሎች መስዋዕትነት ለመኖር የሚፈልግም አይደለም ። በሁሉም ቦታ ኮሚዩኒስት ቆራጥና ከቆመለት ሕዝባዊ ዓላማ አንፃር ማድረግ የሚገባውን ሁሉ ከማድረግ ወደ ኋላ የማይል አብዮተኛ ነው ።

ኮሚዩኒስት የትግል መመሪያው የሆነውን የሳይንሳዊ ንድፈ ሀሳብ ዕውቀቱን ባለማቋረጥ የሚያዳብር ነው ። በተለያዩ ሙያዎችና መስኮች የዕውቀቱን አድማስ ለማስፋት ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይል ሌት ተቀን ይጥራል ። በሚካሄደው ፖለቲካዊ እንቅስቃሴና በመንግሥታዊ አስተዳደር ተቋሞች ውስጥ ንቁ ተሳትፎ በማድረግ በጋራ ተራድኦና ኅብረት ኮሚዩኒስታዊ ግንኙነቶችን ያጠናክራል ። የፓርቲውን መመሪያዎችና ውሳኔዎች በትክክል ሥራ ላይ ለማዋል የፓርቲውን ፖሊሲ ለሕዝብ በመግለፅና በማስረዳት በፓርቲውና በሕዝቡ መካከል ያለው ግንኙነት እንዲጠናከር ያላሰለሰ ጥረት ያደርጋል ። ለሕዝብ መቆርቆርን ፣ ችግሩን በትዕግሥት በማዳመጥ አፋጣኝ መፍትሔ መስጠትን ፣ በመከራ ጊዜ ሕዝቡ ፊት መቆምንና በደስታ ወቅት ሕዝቡን ማስቀደም ዐቢይ ዓላማው ነው ። ኮሚዩኒስት በሕዝቡ ዘንድ ተወዳጅነትን ፣ ተቀባይነትንና ክብርን የሚያገኘው በአብዮታዊ ተግባሩ ፣ ለሰፊው ሕዝብ ባለው ታማኝነቱና በአጠቃላይ በአብዮታዊ ተግባሩ ብቻ መሆኑን በሚገባ ተገንዝቦ ከዚህም አኳያ የሚታገል ነው ።

«በማንኛውም ደረጃ ያለ ሠራተኛ ኮሚዩኒስታዊ እምነት የሚታየው በሚፈጽማቸው ተግባሮች ፣ በተግባር ለጋራው ዓላማ በሚያበረክተው አስተዋጽኦ ነው ።»[15]

ኮሚዩኒስት ማርክሳዊ ሌኒናዊ ንቃቱን ከጊዜ ወደ ጊዜ እያዳበረ ለመሄድ የሚችለው መጽሐፍ በማንበብና በትምህርት ቤት በመማር ብቻ ሳይሆን በዚህ ዓይነት ቀጥተኛ የሆነ ተግባራዊ ተሳትፎ በማድረግ ነው ። ያለ አንዳች ማወላወልና ለዘብተኝነት ማንኛውንም ፀረ ሕዝብ አዝማሚያዎች ማለትም የግል ሀብት ሥነ ልቡናዊ ቅሪቶችን ፣ አድሀሪ እምነቶችን ሌሎችንም የወደቀው ሥርዓት ርዝራዥ አስተሳሰቦችንና አመለካከቶችን በመዋጋት ኮሚዩኒስታዊ ሥነ ምግባርን ያጐለምሳል ።

INFINIX HOT 8 | 13MP
AI TRIPLE CAMERA

ኮሚዩኒስቶች በሠርቶ አደሩ ሕዝብ ውስጥ የወዝ አደራዊ ዓለም አቀፋዊነትን ስሜት ለማሳደግ የሚታገሉ ናቸው ። በዚህም ጠባብ ብሔረተኛነትንና የብሔር ትምክተኝነትን በመዋጋት ለዓለም ጭቁን ሕዝቦች አንድነት ፣ ፍትህ ፣ ሰላምና ሶሻሊዝም ይታገላሉ ። የኮሚዩኒዝምን ስም የሚያጉድፉትን ሁሉ ያለርህራሄ ይዋጋሉ ። ሌሎችንም በኮሚዩኒስት መንፈስ ያንፃሉ ፣ ይመራሉ ።

በዚህ ተግባሩ ሁሉ ከአንድ ኮሚዩኒስት ከሚጠበቁት ሌኒናዊ ግዴታዎች አንዱ በማንኛውም ሁኔታ የዲሞክራሲያዊ ማዕከላዊነትን የአሠራር መርህ መከተል ነው ። ማንኛውንም ማዕከላዊ አመራርን የሚያዳክምና የሕዝቡን መብት የሚያፍን አዝማሚያ ከማጋለጥና ከመታገል ወደ ኋላ አይልም ። ኮሚዩኒስት ስሕተቶችን ለማረምና ከስሕተቶች በመማር ለመጠናከር ሁልጊዜ ዝግጁ ነው ። በሌሎች ላይ ሂስ ለማቅረብና ስሕተትን እንዲያርሙ ለማድረግ ፣ ራሱም ሂስን በመቀበል ለመታረም አይፈራም ። የጥንካሬው ምንጭ ይህ መሆኑን ያምናልና ። ኮሚዩኒስት በማንኛውም ቦታ ፣ ከባድ ፈተና ባለበት ሁኔታም ውስጥ ዓላማውን የማይስት ፣ በጥቅም የማይደለል ግንባር ቀደም የኮሚዩኒስት ሥርዓት ገንቢ ኃይል ነው ። አንድ ኮሚዩኒስት በሚሠማራበት ቦታ ሁሉ መሪና አስተማሪ ስለሆነ ሰፊው ሕዝብ ብዙ ይጠብቅበታል ። በመሆኑም በማንኛውም የአመራር ደረጃ ላይ ያለ ኮሚዩኒስት የበላይነት ስሜት ፍጹም የማያጠቃውና በሕዝቡ መካከል የወንድማማችነት ፣ የቅንነት ፣ የእኩልነት ፣ የአገልግሎት ስሜት እንዲኖር ይታገላል ። ኮሚዩኒስት በሕዝቡ መካከል በመገኘትና በየዕለት ተግባሩ አብሮ በመሳተፍ ምኞቱን ፣ ፍላጐትንና ችግሩን በቅርብ መረዳትና ማቃለል ተቀዳሚ ተግባሩ ነው ። በምንም ዓይነት ከጠባብ አስተሳሰብ በላይ መሆን ስለሚገባው የሀይማኖት ፣ የጐሣ ፣ የዘር ፣ የዝምድና ፣ የጓደኝነት መድሎም በአንድ ኮሚኒስት ዘንድ ቦታ ሊኖረው አይገባም ። ሕዝቡ በአርአያነት የሚመለከተው በመሆኑ በሥራ ወዳድነቱ በአገር ፍቅሩ ፣ በእምነቱ ፣ በግልም ሆነ በማኀበራዊ ንጹህ ኑሮው የተመሠከረለት መሆን ይጠበቅበታል ። አንድ ኮሚዩኒስት ፤

— በማርክሳዊ ሌኒናዊ ርዕዮተዓለም እምነቱ የጸና ፤
— በአገር ፍቅር የሶሻሊስት የአርበኝነት ስሜት አገሩን ከውጭም ሆነ ከውስጥ ጠላቶች ነቅቶ የሚጠብቅና ለአገሩና ለሰፊው ሕዝብ ደህንነትና እድገት ሕይወቱን መስዋዕት ለማድረግ የተዘጋጀ ፤
— በምንም ዓይነት ጥቅም የማይደለልና የአገሩንና የሰፊውን ሕዝብ ጥቅም አሳልፎ የማይሰጥ ፤
— በወዝአደራዊ ዓለምአቀፋዊነት ፅኑ እምነት ያለው ፤
— ግለኝነትን በኃይል የሚዋጋና የኀብረት አስተሳሰብንና አሠራርን የሚወድ ፤
— መሪነቱን ለበላይነት ሳያውል በቅን ልቦና ፣ በትህትና በተራ ኑሮ ከሕዝቡ ሳይለይ ትምክህተኝነትንና ትዕቢትን አስወግዶ ለሰፊው ሕዝብ አገልግሎት ሕይወቱን የሰጠ ፤
— በግል ኑሮውም ሆነ በኅብረት ኑሮው እራሱን የሚቆጣጠርና እንደስካር ፣ ዝሙት ፣ ጉቦና የሕዝብ ገንዘብ መስረቅ ከመሳሰሉት ወራዳ ድርጊቶች የራቀ ፣
— አዳዲስ ትምህርቶችንና ልምዶችን ለማግኘትም ሆነ ስሕተቶችን ለማረም ዝግጁ የሆነና ፤
— በከፍተኛ ዲስፕሊን የታነፀ መሆን ይገባዋል ።

የኮሚዩኒስቶች ዓላማ የነሱ ሥነ ምግባር በነሱ ዘንድ ብቻ ተወስኖ እንዲቀር ሳይሆን የሰፊው ሠርቶ አደር ሕዝብ ሥነ ምግባር መሠረት እንዲሆን ማድረግ ነው ። በመሆኑም የኮሚዩኒስት ሥነ ምግባር ኅብረተሰብ በሥነ ሥርዐት (ዲስፕሊን) ፣ በሥራ ክቡርነት ፣ በእኩልነት ፣ በኅብረትና በመተሳሰብ ላይ የተመሠረተ እንደመሆኑ ሶሻሊዝምን ለመገንባት ኮሚዩኒስታዊ ሥነ ምግባር መኖር አለበት ። በዚህም በኩል ሠርቶ አደሩ ሕዝብ ከፊውዳሉና ከቡርዥው የሞራል መለኪያዎች መላቀቅ ይኖርበታል ። የግለሰቡ ጥቅም የኅብረተሰቡ ጥቅም መሆን አለበት ። የኮሚዩኒስት ኅብረተሰብ ግንባታ ኮሚዩኒስታዊ ሥነ ምግባርን ይጠይቃል ። ስለሆነም ይህን የመሰለ ኅብረተሰብ ሊገነባ የተነሳ ሕዝብ በሥራው ፣ በእምነቱና በአስተሳሰቡ ሊራመዱና ሊዳብሩ የሚገባቸው የኮሚዩኒስታዊ ሥነ ምግባር መለኪያዎች አሉ ። እነዚህም ፤

— ለሶሻሊዝም የማያወላውል ድጋፍ መስጠት ፤
— በሥራ ክቡርነት በማመን ምርትን ማሳደግ ፤
— የኅብረተሰቡን ሀብት መጠበቅና መንከባከብ ፤
— የሀገር ፍቅር ስሜትን በማዳበር አብዮቱንና እናት አገሩን ከጠላት ነቅቶ መጠበቅ ፤
— የጐሣ ፣ የሃይማኖት ፣ የዘር ፣ የጾታና የመሳሰሉትን ልዩነቶች ማድረግ ለብሔራዊ አንድነትና እድገት ጐታች መሆናቸውን ተገንዝቦ እነዚህን አደገኛ አዝማሚያዎች መዋጋት ፤
— የሰውን ልጅ አንዱን ከአንዱ ሳይለዩ በማፍቀርና በመውደድ ለዓለም ሠርቶ አደሮች አንድነትና ኅብረት በጽኑ መቆምና ፤
— በግልም ሆነ በማኅበራዊ ሕይወቱ ከበሰበሱ የፊውዶ ቡርዥ የሞራል ውድቀቶች በመላቀቅ ለኮሚዩኒስታዊ የሥነ ምግባር ተሀድሶ (ትህትና ፣ ሠራተኛነት ፣ ቁርጠኛነት ፣ ዲስፕሊን......ወዘተ) መታገል ናቸው ።

ስለዚህ ከላይ የተጠቀሱት ለኮሚዩኒስታዊ ሥርዐት ግንባታ አስፈላጊ የሆኑትን የኮሚዩኒስት ሥነ ምግባር መመሪያዎች ተግባራዊ ለማድረግ የጠንካራ አቋምና ዲሲፕሊን መመሪያ በተለያየ የአመራር ደረጃ ካሉት ጀምሮ እስከ ተራው ሕዝብ ሊኖር ይገባል ። የኮሚዩኒስት ሥነ ምግባር ያለ ኮሚዩኒስት ዲስፕሊን ሊኖር አይችልም ። የኮሚዩኒስት ኅብረተሰብ ሊገነባ የሚችለው በማንኛውም የሥራ መስክ በመሪነቱም ደረጃ ሆነ በሕዝቡ መካከል ኮሚዩኒስታዊ ዲስፕሊን በማኅበራዊ ሕይወት ውስጥ እያደገ ፣ እየሰፋና ጥልቀት እያገኘ ሲሄድ ብቻ ነው ። ኮሚዩኒስታዊ ዲስፕሊን ከከፍተኛ ኮሚኒስታዊ ንቃት የሚመጣና በማንኛውም የሥራና የእውቀት መስክ በሠርቶ አደሩ ሕዝብ ሰፊ ዲሞክራሲያዊ ተሳትፎ የሚገለጽ ነው ፤

«የኮሚዩኒስት ዲስፕሊን ከፍተኛ ዲሞክራሲ፤ የንድፈሐሳብ ትጥቅና የትግል ተሳትፎ ፤ እንዲሁም ጸረ ጥቅና የጓዳዊነት መንፈስ የሚገለጽበት ነው ። የንድፈ ሐሳብ እውቀትና በሕዝባዊ ትግሎች ውስጥ የሚደረገው ተሳትፎም ይህንኑ ዲሞክራሲ የሚያጠናክር ነው ።»[16]

ይህ የኮሚዩኒስት ዲስፕሊን በመሠረቱ የፓርቲ ዲስፕሊን ነው ። አዲስ የኮሚዩኒስት ሥርዓትን መመሥረት እንደ ብረት የጠነከረ ኮሚዩኒስታዊ ዲስፕሊንን ይጠይቃል ። የኮሚዩኒስቶች የፓርቲ ዲስፕሊን ከቡርዧው በግል ሀብት ላይ የተመሠረተ ዲስፕሊን ፍጹም የተለየና የወዝ አደራዊ አብዮት ዓይነተኛ የትግል መሣሪያ ነው ። የኮሚዩኒስት የፓርቲ ዲስፕሊን የወዝአደራዊ ዲስፕሊን መሠረት ነው ። ኮሚዩኒስቶች የሠራተኛው መደብ የነቁ ክፍሎች እንደመሆናቸው ያለማቋረጥ የሠራተኛውን መደብና የመላውን ሠርቶ አደር ሕዝብ ንቃት ማጐልመስ ዓይነተኛ ተግባራቸው ነው። የዚህም ውጤት በትግሉ ሂደት ውስጥ የኮሚዩኒስት ዲስፕሊንና ሥነ ምግባር በኅብረተሰቡ ውስጥ መስፈንና በሁሉም ረገድ የተሟላ አዲስ የኮሚዩኒስት ሰው መገኘት ነው ። ለዚህ ዓይነቱ ሰው መፈጠር ደግሞ የኮሚዩኒስት ትምህርት ዓይነተኛ መሣሪያ ነው ።

ለማጠቃለል ፣ እንግዲህ ስለ ኮሚዩኒስት ዲስፕሊን ፣ ሥነ ምግባርና በአጠቃላይም ስለ ኮሚዩኒስት ስብዕና ስንናገር ይህ ከግል ሀብት ጋር ከተያያዘው የበዝባዥ መደቦች ዲስፕሊን ፣ ሥነ ምግባርና ስብዕና ፍጹም የተለየ መሆኑን መገንዘብ ይኖርብናል ። የኮሚዩኒስት ሥነ ምግባር መለኪያዎች ከ «አሥርቱ ትዕዛዝ» ፍጹም የተለየ መደባዊ ይዘት ያላቸውና ለሠራተኛው መደብና ለሠርቶ አደሩ ሕዝብ ፍትህ ፣ ነፃነትና እኩልነት የቆሙ ናቸው ። እርግጥ የኮሚዩኒስት ሥነ ምግባር የሰው ልጅ በዘመናት ያካማቸው መልካም ልምዶችን ፣ አሠራሮችንና ሥነ ምግባሮችን አጣምሮ በመያዝ ያዋሀደና ለነዚህም መደባዊ ይዘትና አቅጣጫ በመስጠት በከፍተኛ ደረጃ የሚያዳብር መሆኑ አይካድም ። በመሆኑም የኮሚዩኒስት ሥነ ምግባር እንዲሁ ከሰማይ የሚወርድ ሳይሆን የሠርቶ አደሩ ሕዝብ የረዥም ዘመን ትግልና የባሕላዊ እድገቱ ውጤት መሆኑን እንገነዘባለን ። ስለዚህ የኮሚዩኒስት ሥነ ምግባር ምዝበራና ጭቆና የሌለበትን የኮሚዩኒስት ሥርዓት ለመመሥረት በሚደረገው ትግል እንደ ትግል መሣሪያም ጭምር ሆኖ የሚያገለግል ነው ።

ከዚሁ ጋር ሌላው መጠቀስ ያለበት ጉዳይ አንድ ኮሚዩኒስት ከሁሉም በፊትና

በመጀመሪያ ደረጃ ሰው መሆኑ ነው ። ኮሚዩኒስቶች ራሳቸው የማኀበራዊ ዕድገት ውጤቶች ናቸው ። ስለሆነም ካሉበት ኅብረተሰብ ውጭ እንደ ልዩ ፍጡር ወይም እንደ መልአክ የሚታዩ አይደሉም ። ኮሚዩኒስቶች ባላቸው ሕዝባዊ ዓላማ መሠረት ከማንም ይበልጥ ከሠርቶ አደሩ ሕዝብ ጋር የተሳሰሩና አንድ የሆኑም ናቸው ። በመሆኑም በኅብረተሰብ ውስጥ የሚካሄደው ሁሉ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ፤ በጥሩም ሆነ በመጥፎ ይነካቸዋል ። በዚህም ረገድ በኅብረተሰቡ ውስጥ በተለያዩ ማኀበራዊ እንቅስቃሴዎች በሚያደርጉት ተሳትፎ አያሌ መልካም ተግባሮችን እንደሚፈጽሙ ሁሉ፤በአንድ ወቅት ስኅተት ሊፈጽሙም ይችላሉ ። በተለያዩ ምክንያቶች ጠንካራና ደካማ ጐኖች ሊኖራቸው ይችላል ። ሆኖም ኮ ሚዩኒስቶች ስህተታቸውን ለማረም ፤ ድክመታቸውን ለማስወገድና የበለጠ ጥራትና ጥንካሬ ለማግኘት ምንግዜም ዝግጁ ናቸው ። ያም ብቻ ሳይሆን ለሰው ልጅ ሕይወት አስፈላጊ የሆኑት ነገሮች ሁሉ ያስፈልጓቸዋል ። ቢሆንም ስሜታቸውንና ፍላጐታቸውን ለኅብረተሰቡ የጋራ ፍላጐትና ዓላማ የሚያስገዙና በሁሉም ረገድ ከራሳቸው ደስታ በፊት የኅብረተሰቡን ጥቅምና ደህንነት የሚያስቀድሙ ናቸው ። ኮሚዩኒስቶች ከሌሎች የኅብረተሰብ አባሎች የሚለዩት መለኮታዊነት ኖሯቸው ሳይሆን ታላቅ ኮሚዩኒስታዊ የስብአዊ ልዕልና ዓላማ ያላቸው ፤ ፍላጐታቸውን ለዚሁ ክቡር ዓላማ የሚያስገዙ በመሆናቸው ለዓላማውም ግብ መምታት በሳይንሳዊ ንድፈሀሳብ መመሪያ በሚያደርጉት ግንባር ቀደም የትግል ተሳትፎና እጅግ የላቀ ሕዝባዊ ሥነ ምግባር ያላቸው በመሆናቸው ብቻ ነው ። ስለዚህ ኮ ሚዩኒስት ሲባል ልዩ ፍጡር ሳይሆን እጅግ ከላቀ ንቃቱና ሕዝባዊ ዓላማው የተነሳ የሰውን ልጅ መልካም ባህሪዎችና ሥነ ምግባሮች ሁሉ አሟልቶ የያዘና ይህንንም ለኮሚዩኒዝም መመሥረትና ለሰው ልጅ የተሟላ ነፃነትና እኩልነት መረጋገጥ በቆራጥነት በተግባር የሚያውል ሀቀኛና አብዮታዊ ታጋይ ነው ። ከዚህም አንፃር ሲታይ ኮሚዩኒስት መባል ታላቅ ክብርና ታሪካዊ ሀላፊነት ነው ። ኮሚዩኒስት መሆን ለከባድ አብዮታዊ ተግባር በፍጹም መስዋዕትነት ራስን አሳልፎ መስጠት እንጂ ሹመት ወይም ልዩ ጥቅም የሚገኝበት ልዩ ምልክት አይደለም ።

ጓድ ሊቀ መንበር መንግሥቱ ኃይለማርያም የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግና የኢሠፓአኮ ሊቀ መንበር የአብዮታዊው ጦር ጠቅላይ አዛዥ ስለ ኢሠፓአኮ መቋቋም ታህሣሥ 7 ቀን 1972 ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ባደረጉት ንግግር ፤

«ሐቀኛ ታጋዮችን የሚመርጣቸው ፤ የሚያሰባስባቸውና የሚያደራጃቸው ማንም ሳይሆን ዓላማቸውና ተግባራቸው ነው ።»[17]

በማለት እንዳስገነዘቡት ሁሉ ኮሚዩኒስቶችን ኮሚዩኒስት የሚያደርጋቸው የማያልፍና ከሁሉም በላይ የሆነው ክቡር የሕይወት ዓላማቸው ፤ አብዮታዊ ተግባራቸውና የተቀደሰ ሥነ ምግባራቸው ነው ። ከዚህ ዓላማ ፤ ተግባርና ሥነ ምግባር ውጭ የሆነ ኮ ሚዩኒስት ሊባል ከቶ አይችልም ። ኮሚዩኒስት መባል የግል ሕይወት ማደለቢያና የወዳጅ ዘመድ መጥቀሚያ ሹመት አይደለም ፤ ከቶም ሊሆን አይችልም ። የኮሚዩኒስት ሕይወትም በግል ኑሮና በማኀበራዊ ኑሮ በሁለት የተከፈለ ሳይሆን አንድ ሕዝባዊ ዓላማ ብቻ ያለው ክቡር ሕይወት ነው ።

በስፓኝና በሶቭዬት ኅብረት የፀረ-ፋሽስቱ ጦርነት ጀግና የነበረው ኮሚዩኒስቱ የሶቭዬት ኅብረት ዜጋ ኬ. ፒ. ኦርቶቭስኪ እንዳለው ፤

«ኮሚዩኒስት መሆን ታላቅ ነገር ነው ። ማንኛውም ሰው የሚያገኘው ክብር አይደለም ። ኮሚዩኒስት አብዮታዊ ተግባሩን የሕይወቱ ዓላማ ያደረገና የራሱ የሆነ ልዩ ባህሪይ ያለው ሰው ነው ። አንድን ኮሚዩኒስት መግደል ይቻላል ፤ ለቀመለት የተቀደሰ ዓላማ ካለው እምነቱ ግን ንቅንቅ ማድረግ ፍጹም አይቻልም ።»[18]

ኮሚዩኒስት ማንም ከሜዳ ተነስቶ የሚሞካሽበትና በራሱ ፈቃድ የሚካነው ተራ ስም አይደለም ። ኮሚዩኒስት ክቡር ሥም ነው ። በመሆኑም ለዚህ ታሪካዊ ዓላማ ከልብ የቆመ እያንዳንዱ ኮሚዩኒስት ይህን በሚገባ ተገንዝቦ በሚናገረውም ሆነ በተግባር በሚፈጽመው ሁሉ እንደስሙ ሆኖ መገኘት አብዮታዊ ግዴታው ነው ።

የግርጌ ማስታወሻዎች

1. K. Marx, *Critique of the Gotha Programme*, progress publishers (Moscow: 1976), p. 26

2. Ibid, pp. 17 — 18

3. Marx - Engles & Lenin *On Scientific Communism*, progress publishers (Moscow, 1967), p. 126.

4. K. Marx, & F. Engles. *Selected works*, Vol. 2, progress publishers (Moscow: 1976), p. 19

5. K. Marx, & F. Engles *The Manifesto of the Communist party*, progress publishers (Moscow: 1975) pp. 61 — 62

6. K. Marx, & F. Engles. Quoted in *Leninist Standards of party Life*, progress publishers, p. 5.

7. V. I. Lenin, *Collected works*, Vol. 27, p. 207

8. ” ” Vol. 30, p. 63

9. V.I. Lenin, Quoted in *Leninist Standards of party Life*, progress publishers, p. 127

10. I Pronin, & M. Stepichev, *Leninist Standards of party Life*, progress publishers (Moscow: 1969), p. 129

11. M. Rosenthal, & P. Yudin. *A Dictionary of Philosophy*, progress publishers (Moscow: 1967), p. 197

12. F. Engles, *Anti Duhring*, progress publishers, (Moscow: 1975)‘ p. 133.

13. K. Marx, & F. Engles, *Collected works*, Vol. 5, p. 4

14. ከላይ የተጠቀሰው የኤንግልስ መጽሐፍ ፤ ገጽ 110 - 111

15. በተራ ቍጥር 10 የተጠቀሰው መጽሐፍ ፤ ገጽ 116

16. Harry Gould, L. *Marxist Glossary*, proletarian publishers (San Francisco: 1946), p. 42.

17. ጓድ ሊቀመንበር መንግሥቱ ኃይለማርያም የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ሊቀመንበርና የአብዮታዊው ጦር ጠቅላይ አዛዥ ስለኢትዮጵያ ሠርቶ አደሮች ፓርቲ አደራጅ ኮሚሽን መቋቋም ታኅሣሥ 7 ቀን 1972 ዓ. ም. ለመላ ኢትዮጵያ ሕዝብ ያደረጉት ንግግር ፤ ማስታወቂያና መርሐ ብሔር ሚኒስቴር ፤ አዲስ አበባ 1972 ዓ. ም ፤ ገጽ 33

18. በተራ ቍጥር 10 በተጠቀሰው መጽሐፍ ውስጥ የተጠቀሰ ።

INFINIX HOT 8 | 13MP
AI TRIPLE CAMERA

ሰው ለኑሮው የሚያስፈልገውን
ነገር ማምረቱ የህብረተሰብ
እድገት መሠረት ነው !!



INFINIX HOT 8 | 13MP
AI TRIPLE CAMERA

መስከረም



የማርክሲስት ሌኒኒስት ርዕዮተ ዓለም መጽሔት

ቅጽ 1 ቁጥር 3
መጋቢት 1973

መስከረም

ቅጽ 1 ቁጥር 3
መጋቢት 1973

የማርክሲስት ሌኒኒስት ርዕዮተ ዓለም መጽሔት

ማ ው ጫ

ገጽ

- የዝግጅት ገፅ - - - - - - - - - - - - - - - - - - 3
- ኮምኒስት ማለት ምን ማለት ነው? - - - - - - - - - - - 7
  - ገዛኸኝ ገብሬ
- ማርክሳዊ የፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ግንዛቤ - - - - - - - - - - - - 27
  - አምሃ ዳኘው
- የኢትዮጵያ ሕዝብ የነፃነት ትግልና የኢጣልያን ፋሽሽት ወረራ - - - - 37
  - በኢሠፓኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ የርዕዮተ ዓለም መምሪያ
  — የአብዮት ታሪክ ክፍል —
- የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም በቅድመ አብዮት ኢትዮጵያ - - - - - 55
  - ለገሠ ለማ
- የጊዜያችን ፀረ-ኢምፔሪያሊስት ትግል
  — የላቲን አሜሪካ ሕዝብ የብሔራዊ አርነት ንቅናቄ - - - - 70
  - ብርሃኑ ዘሪሁን
- የነጋድራስ ገ/ሕይወት ባይከዳኝ የፖለቲካዊ ኢኮኖሚ አስተሳሰብ - - - - 84
  - አየለ ዘውገ

በኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ

ርዕዮተ ዓለም መምሪያ እየተዘጋጀ በየሦስት ወር የሚወጣ ፡፡

አድራሻ

የፖስታ ሣጥን ቁጥር — 80001
የስልክ ቁጥር — 113000

INFINIX HOT 8 | 13MP
AI TRIPLE CAMERA

የማርክሳዊ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ግንዛቤ

አምሀ ዳኘው

«ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ሰፋ ባለ ግንዛቤው ፣ በኅብረተሰብ ውስጥ ሰው ለኑሮው የሚያስፈልጉትን ማቴሪያላዊ ነገሮች የሚያመርትበትና የሚለዋወጥበትን ሕግ የሚያጠና ሳይንስ ነው—በታሪክ በተወሰነ ሥርዓተ ማኅበር ውስጥ ካለው የአመራረትና የልውውጥ ዘይቤ ፣ ለዚህም መከሰት ምክንያት ከሆኑ ታሪካዊ ሁኔታዎች ጋር ያለው የምርት ክፍፍል ዘይቤ አብሮ ይወሰናል ።» [1]

የማርክሳዊ ፖለቲካዊ ኤኮኖሚ እንደ ማናቸውም ማኅበራዊ ሳይንስ (ታሪክ፣ ህግ ፣ ፍልስፍና ወዘተ. . .) ስለ ሕብረተሰብ ሕይወት የተወሰነ ገጽታ የሚያጠና ሳይንስ ነው ። የማሌ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ስለ ማቴሪያላዊ ሀብት ማኅበራዊ አመራረትና ስርጭት ማጥናቱም ከሌሎች ማኅበራዊ ሳይንሶች ይልቅ ለየት ያለ ቦታ እንዲሰጠው ያደርገዋል ። ምክንያቱም በታሪክ ውስጥ ሰው ለኑሮው የሚያስፈልገውን ነገር ማምረቱ ፣ ከሁሉም ነገር ይልቅ ተቀዳሚና ለኅብረተሰቡም እድገት መሠረት በመሆኑ ነው ። ይህንንም መሠረታዊ ሃሳብ ማርክስ እንደ ሚከተለው አቅርቦታል።

«ሰው ስለ ፖለቲካ ፣ ስለ ሳይንስ ስለ ሰነጥበብ ስለ ሃይማኖት ወዘተ— ከማሰቡ በፊት በመጀመሪያ መብላት መጠጣት መጠለያና ልብስ ማግኘት ይኖርበታል ።» [2]

የማርክሲስት ሌኒኒስት ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ስለ ኅብረተሰብ የኢኮኖሚ እድገት ፣ ማቴሪያላዊ ሀብት በማምረት ሂደት ውስጥ በሰዎች መካከል ስለሚፈጠረው የኢኮኖሚ ግንኙነት የሚያጠና ፣ የመላውን ሠርቶ አደር ሕዝብ ጥቅም ለማስከበር የሚደረገውን ትግል ፈር የሚያስይዝ ፣ ተበዝባዥ መደቦችና ጭቁን ሕዝቦች ለማኅበራዊና ለኢኮኖሚያዊ ፍትህ እንዲሁም ለሐቀኛ የፖለቲካ ነጻነት የሚያካሂዱትን የመደብ ትግል የማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ይዘት አብራርቶ የሚያቀርብ ፣ በብዝበዛ ላይ የተመሠረተው የካፒታሊስት የኢኮኖሚ ሥርዓት በውስጡ በሚነሱት የማይታረቁ ቅራኔዎች ምክንያት እንዴት እየተዳከመ ሄዶ በመጨረሻም እንደሚገረሰስ እና ቦታውን ለሶሻሊዝም እንደሚለቅ የሚያስረዳ ሳይንስ ነው ።

የማሌ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ካፒታሊዝም የግድ ቦታውን ለሶሻሊዝም እንደሚለቅ መጠቆም ብቻ ሳይሆን ለሶሻሊዝም ግንባታ ንድፈ ሃሳባዊ መርሐግብርና ተግ

INFINIX HOT 8 | 13MP
AI TRIPLE CAMERA

ባራዊ መመሪያም ይሰጣል ። በዚህም ሂደት
ውስጥ የሠራተኛውን መደብ ተልዕኮ ከማ
ብራራቱም በላይ ፣ የካፒታሊስት ሥርዓት
ጊዜው ያለፈበት እንደሆነና የሰውን ልጅ
መሠረታዊ ችግሮች ሊፈታ የማይችል
ሥርዓት እንደሆነ ፣ እንዲሁም ኢምፔሪያ
ሊዝም በባህሪው ጠብ አጫሪና ዓለምን
ወደ ጥፋት ለመግፋት የሚቃጣ መሆኑን ፣
ለዚህም የጥፋት መልክተኛ ተልዕኮው
የኢኮኖሚ መንስኤ የሆነው የሞኖፖል
ጠባዩ እንደሆነ የምንረዳበት ሳይንስ ከመ
ሆኑም በላይ በአጠቃላይ የቡርዣዋውን
ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ኢሳይንሳዊነት ግልጽ
አድርጎ ያሳያል ።

የማ.ሌ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ከማናቸ
ውም ቅድመ ሶሻሊስት የምርት ግንኙነ
ቶች ይልቅ የሶሻሊስት የምርት ግንኙነት
ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፍትህ የሰፈነበት
የምርት ግንኙነት እንደሆነ ፣ ከካፒታሊ
ዝም ወደ ሶሻሊዝም የሚደረገው ሽግግር
ህግን የተከተለ ሽግግር እንደሆነ ፣ የሚመ
ሠረተውም የሶሻሊስት መንግሥት የኢኮ
ኖሚና ማኅበራዊ ፖሊሲዎች የሚደጋገፉና
የተዋሐዱ እንደሆኑ ፣ የሀገር ብልጽግናና
የኢኮኖሚ ዕድገት የሚገኘው ሳይንስና
ቴክኒዎሎጅን በማስፋፋት የሥራ ምርታ
ማነትን በየጊዜው እንዲጨምር በማድረግ
ማኅበራዊ ምርትን በማሳደግ ብቻ እንደሆነ
የሚያስረዳን ሳይንሳዊ ንድፈ ሃሳብ ነው ።

ከዚህ በተጨማሪ በሶሻሊስት የኤኮ
ኖሚ ግንባታ ሂደት ውስጥ የሚነሱ ችግ
ሮች በሶሺያሊስት መንግሥት የማዕከላዊ
ፕላን ፣ በሳይንሳዊ የኤኮኖሚ አስተዳደርና
በሰፊው ሕዝብ የመፍጠር ችሎታ ሊቃለሉ
እንደሚችሉ ያስረዳል ።

የማሌ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ የምርት ግንኙነት ሳይንስ ነው

የማሌ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ የምርት
ግንኙነት ሳይንስ እንደመሆኑ የምርት ግን
ኙነት ከምርት ኃይልና ከላዕላይ መዋቅሩ
ጋር ያለውን ግንኙነት ፣ ግንኙነቱንም የሚ
ወስነውን ሕግ ያጠናል ። ሌኒን ፖለቲካዊ
ኢኮኖሚ የምርት ግንኙነት ሳይንስ መሆ
ኑን ሲያስረዳ «ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ታዳጊ
በሆኑ ታሪካዊ ስርዓቶች ውስጥ ስለአለው
ማህበራዊ የአመራረት ዘይቤ የሚያጠና
ሳይንስ ነው ። ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ በታ
ሪክ በተወሰኑ ስርዓተ ማህበሮች ውስጥ
ስለአሉ የምርት ግንኙነቶች አነሳስ ፣ እድ
ገትና እየተዳከሙ የመምጣታቸውን ሂደት
የሚገልጽ ትምህርት ነው ፣»[3] ብሏል ።

የምርት ግንኙነት ማለት ደግሞ በማህ
በራዊ የምርት እንቅስቃሴ ውስጥ ሰዎች
በማምረት ፣ በመለዋወጥ ፣ በመከፋፈልና
በፍጆታ ሂደት ውስጥ እርስ በርሳቸው የሚ
ፈጥሩት ግንኙነት ማለት ነው ። በምርት
ሂደት ውስጥ ሰዎች ከተፈጥሮ ጋር ብቻ
ሳይሆን በመካከላቸውም የተወሰነ ማኅበ
ራዊ ግንኙነት ይመሠርታሉ ። የሚመሠ
ረተውም ግንኙነት በመሠረቱ የምርት ግን
ኙነት ወይም የኢኮኖሚያዊ ግንኙነት ይባ
ላል ። ይህም የምርት ግንኙነት የንብረት
ግንኙነትን (Property Releationship)
ያጠቃልላል ።

ምርትን ከምርት መገልገያ ነጥሎ ለማ
የት እንደማይቻል ሁሉ ፣ በአንጻሩ ፣ የም
ርት መገልገያን ደግሞ ከምርት መገልገያ
ባለቤትነት ነጥሎ ለማቅረብ ያዳግታል ።
የተወሰነ ዓይነት የማምረቻ መሣሪያዎች
ባለቤትነት ሳይኖር ምርት ሊከናወን አይ
ችልም ።

የምርት እንቅስቃሴው ውጤት በኅብረ
ተሰቡ ውስጥ በተወሰነ መንገድ መከፋፈ
ሉን የሚወስነው በዚሁ ኅብረተሰብ ውስጥ
የምርት ማከናወኛው ባለቤትነት የተከፋ
ፈለበት ዘይቤ ነው ። ሰዎች በምርት እን
ቅስቃሴ ውስጥ ከማምረቻ መሣሪያዎች
ጋር ያላቸው ግንኙነት (ባለቤትነት ቢኖራ
ቸውም ባይኖራቸው) የንብረት ግንኙነት
ይባላል ። የንብረት ግንኙነት የሰው ኃይል
ከምርት ማከናወኛ ጋር የሚዋሐድበትን
ዘይቤ ከመጠቆሙም በላይ ፣ በኅብረተሰብ
ውስጥ ያለውን የመደብ ክፍፍልም ያመ
ለክታል ።

ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ የኢኮኖሚ ይዘት
ባለው የምርት ግንኙነት ጥናት ላይ የሚያ
ተኩር ቢሆንም ፣ በምርት ግንኙነት ውስጥ
ዋንኛውን ቦታ ይዞ የሚገኘውን የንብረት
ግንኙነት ዓይነትና የግንኙነቱንም የመደብ
ይዘት የሚወስነውን የፖለቲካ ሥልጣን
ጠባይም ይመለከታል ።

የምርት ግንኙነት አጠቃላይ ማኅበራዊ ምርት በኅብረተሰቡ የተለያዩ መደቦች መካከል የሚከፋፈልበትን ዘዴና የፍጆታውን ዘይቤ ይወስናል ። የክፍፍሉና የፍጆታው ዘይቤ ደግሞ በበኩሉ በኅብረተሰብ ውስጥ ባለው የአመራረት ዘይቤና የምርት እንቅስቃሴ ላይ ተጽዕኖውን ያሳድራል ። የተለያዩ ኅብረተሰቦች ውስጥ የምርት ግንኙነቶች የተለያዩ ቢሆኑም በመሠረቱ ግን የምርት ግንኙነት ዓይነቶችን በሁለት ለመክፈል ይችላል ።

አንደኛው የምርት ግንኙነት ዓይነት በብዝበዛ ላይ የተመሠረተ ሲሆን ሁለተኛው ዓይነት ደግሞ እርስ በርስ በመረዳዳትና በመደጋገፍ ላይ የተመሠረተ ነው ። የባሪያው አሳዳሪ ፤ የፊውዳሉና የካፒታሊስቱ ሥርዓት የምርት ግንኙነቶች በአንደኛው ውስጥ ሲመደቡ የሶሺያሊስቱ የምርት ግንኙነት ደግሞ ከሁለተኛው የምርት ግንኙነት ዓይነት ውስጥ ይወድቃል ።

ባጠቃላይ ግን በመደብ በተከፋፈለ ኅብረተሰብ የምርት ግንኙነት የሚከሰተው በመደቦች መካከል ባለው ግንኙነት አኳያ ነው ። የምርት ግንኙነት ይዘት የሚወሰነው የምርት ኃይሎች በደረሱበት የዕድገት ደረጃ ነው ። የምርትም ዕድገት የሚመነጨው ከምርት ኃይሎች ዕድገት ደረጃ ነው ። በአንድ ስልተምርት ውስጥ ከሚገኙት ሁለት ክፍሎች መካከል ማለትም ከምርት ኃይሎችና የምርት ግንኙነቶች የምርት ኃይል ፈጠን ያለ ርምጃ ስላለው የተወሰነ የምርት ኃይል ዕድገት ከቀድሞው ለየት ያለን የምርት ግንኙነት ይጠይቃል ። እንደዚህ ሲባል ግን የምርት ግንኙነት በምርት ኃይል ላይ ምንም ተጽዕኖ አያሳድርም ማለት አይደለም ። ለተወሰነ ወቅት የምርት ኃይል ዕድገትና የምርት ግንኙነት በሚጣጣሙበት ጊዜ የምርት ግንኙነት ለምርት ኃይሎች ዕድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋል ።

የሆነ ሆኖ በምርት ኃይሎች ፈጣን ዕድገት የተነሳ በምርት ግንኙነትና በምርት ኃይሎች መካከል አለመጣጣም በሚከሰትበት ጊዜ በሁለቱ መካከል ቅራኔ ይነሳና አሮጌው የምርት ግንኙነት ለአዲስ የምርት ግንኙነት ቦታውን እንዲለቅ ይገደዳል ። ይህ የምርት ግንኙነትና የምርት ኃይሎች አለመጣጣም ለማኅበራዊ አብዮት መቀስቀስ የኢኮኖሚ መሠረት ይሆናል ። የአዲስ የምርት ግንኙነት መከሰትም የአዲስ ስልተምርትን መመሥረት ያበስራል ።

ለምሳሌ ከየካቲት 66 የኢትዮጵያ አብዮት በፊት በነበረው የፊውዶ ቡርዦዋ ሥርዓት ውስጥ የነበረው አርሶአደር በፊውዳሉ አድኃሪ የምርት ግንኙነት ሳቢያ እስከ ሰባ አምስት በመቶ የሚሆነውን የጉልበቱን ፍሬ ለባለመሬቱ እንዲገብር ተገደንግጎ እንደ ነበር ይታወሳል ። የተረፈችው ከሱና ከቤተሰቦቹ ፍጆታ ውጭ ለመሆን ስለማትችልና እንዲያውም በአብዛኛው የሱና የቤተሰቡን ፍጆታ የማታረካ እንደ ነበረችም ግልጽ ነው ። ለምሳሌ አርሶአደር የሚያስቀምጠው ትርፍ ምርት ሊኖረው ቢችልም እንኳ ፤ ያገኘውን ትርፍ ምርት ገበያ አውጥቶ በመሸጥ ባገኘው ገንዘብ ለፍጆታ ከሚያስፈልገው የኢንዱስትሪ ውጤት በተጨማሪ ምርታማነቱን በማሳደግ ከፍተኛ ምርት ቢያመርት ባላባቱ የአዝመራው ወቅት ሲደርስ እማሳው ላይ በመገኘት በሚያገኘው ምርት ላይ ከቀድሞው በዛ ያለ የዓይነትም ሆነ እንደ እየአካባቢው የገንዘብ ግብር ስለሚጭንበት ፤ ግብሩን ከፍሎ የሚቀረው ምርት በቀድሞው የማምረቻ መሣሪያና የአስተራረስ ዘይቤ ሲጠቀም በነበረበት ጊዜ ከሚያገኘው እምብዛም አይለይም ነበር ። በመሆኑም አርሶአደርየምርት ኃይሎችን ለማሳደግ የሚገፋፋው ነገር አይኖርም ።

በዚህ ዓይነት ሁኔታ ከአብዮቱ በፊት በኢትዮጵያ ውስጥ የነበረው የፊውዳል የምርት ግንኙነት የምርት ኃይሎችን በማቀርቀዙ ረገድ ምን ያህል ከፍተኛ ሚና ይጫወት እንደ ነበር ለማየት ይቻላል ። ይህ የማቀርቀዝ ሂደት ለረዥም ጊዜ የተከናወነ ከመሆኑም በላይ በእርሻው ክፍለ ኢኮኖሚ የምርቱ ዕድገት እየጨመረ ከመጣው የሕዝብ ብዛት ጋር ሲነጻጸር አነስተኛ በመሆኑ ፤ ሰፊውን ሕዝብ ለረሀብ ፤ ለችግር ፤ ለበሽታና ለእርዛት ሊዳርገው በቅቷል ።

በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ይህ ከላይ የተገለጸው ፤ ሁልጊዜ ታዳጊና ወደፊት መራመድ ባለበት የምርት ኃይልና እድገቱንም ገቶ በያዘው የፊውዳል የምርት ግን

ኙነት መካከል ቅራኔ መነሳቱ የማይቀር መሆኑንም ያሳያል ። ይህ ቅራኔ ለየካቲት 66 አብዮት መነሳት ምክንያት ሲሆን ፤ የየካቲት 1967 አብዮታዊ የመሬት አዋጅ ይህን ቅራኔ በመፍታት ፤ አሮጌው የፊው ል የምርት ግንኙነት ለአዲስ ዓይነት ምርት ግንኙነት ቦታውን እንዲለቅ አድ ጓል ።* በአጠቃላይ በምርት ኃይሎችና ምርት ግንኙነት መካከል የነበረው አለ ጣጣም ፤ በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ፤ ሕዝባዊ አብዮት መቀስቀስ የኢኮኖሚ መሠረት መሆኑን መገንዘብ ይቻላል ።

የማሌ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ የኢኮኖሚ ሕጎችን ያጠናል

እዚህ ላይ ለማብራራት የሚፈለገው ዋናው ቁም ነገር የምርት ግንኙነት ይዘት የሚከሰተው በኢኮኖሚ ሕጎች አማካይነት እንደሆነና ትክክለኛ የኢኮኖሚ ሕጎች ግንዛቤ ደግሞ ለትክክለኛው የኢኮኖሚ ፖሊሲ መነደፍ መሠረት እንደሆነ ለመ ጠቆም ነው ። በርግጥ የኢኮኖሚ ሕጎች በም ርት እንቅስቃሴ ውስጥ በሰዎች አማካይነት ይገለጹ እንጂ በመሠረቱ ነባራዊነት አላ ቸው ።

ቀደም ሲል እንደተጠቆመው የምርት ግንኙነት እንደዚሁ ግብታዊ በሆነ መን ገድ የሚከሰት ሳይሆን የሚነሳው የተወሰነ የምርት ኃይል ዕድገትን መሠረት በማድ ረግ ነው ። የኢኮኖሚ ሕጎችም ከምርት ግንኙነቶች የሚመነጩ እንደ መሆናቸው መጠን ተጨባጭነታቸው የሚወሰነው በዚሁ አንጻር ነው ። የኢኮኖሚ ሕጎች ነባራዊነት አላቸው ሲባል ፤ ሰው እንደ ፈለገ የሚሠራቸውና የሚሽራቸው ሳይሆኑ እንደ ተፈጥሮ ሕጎች የራሳቸው የሆነ ባህ ርይ ያላቸው ፤ ሰው በመጀመሪያ ደረጃ ነባራዊ ህልውናቸውን ተገንዝቦ በሳይንስና በቴክኒዎሎጂ ዕድገት ላይ በመመርኮዝ ለራሱ በሚያመች መንገድ ሊገለገልባቸው እስካልቻለ ድረስ እንደዚሁ በፍላጎት ብቻ ሊያስወግዳቸው አይችልም ማለት ነው ።

እንደዚህ በሚባልበት ጊዜ አንዳንድ የኢኮኖሚ ሕጎች ከታሪክ አንጻር አላፊ መሆናቸውን በመዘንጋት አይደለም ። አብ ዛኞቹ የኢኮኖሚ ሕጎች በጊዜው ካለው የምርት ግንኙነት የሚመነጩ እንደ መሆ ናቸው መጠን ያ በታሪክ የተወሰነ የምርት ግንኙነት ቦታውን ለሌላ አዲስ የምርት ግንኙነት ሲለቅ ፤ ከቀድሞው የምርት ግን ኙነት የመነጩ የኢኮኖሚ ሕጎች በአዲሱ የምርት ግንኙነት ውስጥ ለሚነሱ የኢኮ ኖሚ ሕጎች ቦታቸውን ይለቃሉ ። እስከ ዚያው ድረስ ግን ቋሚነት ስለአላቸው ሰው እንደፈለገ ሊቀያይራቸው አይችልም ለማለት ነው ።

የኢኮኖሚ ሕጎችን ነባራዊነት ማጥናት የኢኮኖሚ ሳይንስ ዋንኛውና ተቀዳሚው ተግባር ነው ። የኢኮኖሚ ሕጎችን ነባራዊ ነት አለመገንዘብ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴን ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ለመመርመር አለ መፈለግን የሚያመለክት ከመሆኑም በላይ ሳይንሳዊ የሆነ የኢኮኖሚክ ፖሊሲ እንዳይ ነደፍ በማድረግ የሚተለመው የፖለቲካ መስመር በጀብደኝነት የተበከለ እንዲሆን ያደርጋል ። በተለይ ከሶሺያሊስት ኢኮኖሚ ግንባታ አንጻር ለኢኮኖሚ ዕድገት ትክክ ለኛ ፖሊሲ ለመቀየስ በኢኮኖሚው ፤ በፖ ለቲካው ፤ በማኅበራዊ ኑሮውና በባህሉም አንጻር መኖር የሚገባውን የተያያዘና ውስ ብስብ የሆነ ሂደት መገምገም ያስፈልጋል ። ሌኒን ፖለቲካ ተጨምቆ የወጣ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ውጤት ነው በሚልበት ጊዜ በሳይንሳዊ የማ.ሌ ፖለቲካ ኢኮኖሚ ግም ገማ ላይ ያልተገነባ የኢኮኖሚ ፖሊሲ ነጸብራቁ የሆነውን የፖለቲካ መስመር የተዛባ እንደሚያደርገው ለመጠቆም ነው።

ስለ ኢኮኖሚ ሕጎች ከተነሳ አይቀር በመጠኑም ቢሆን ዘርዘር ባለ ሁኔታ ማቅ ረቡ ተገቢ ነው ። የኢኮኖሚ ሕጎች በሶስት የተለያዩ ክፍሎች ሊመደቡ ይችላሉ ። እነሱም ፤

ሀ) አንድ የተወሰነን ሥርዓተ ማኅበር ብቻ የሚያገለግሉ የኢኮኖሚ ሕጎች

---

* ስር ነቀል የሆነው የየካቲት 1967 የመሬት አዋጅ በኢትዮጵያ አብዛኞቹ ቦታዎች የፊውዳሉን የምርት ግንኙነት ያንኮታኮተው ሲሆን ፤ በምትኩ በገጠር የሶሺያሊስት የምርት ግንኙነት እንዲከሰት አላደረገም ። ፀረ ፊውዳልና ዲሞክራሲያዊ ለውጥ እንደመሆኑም ሊያደርግ አይችልም ። ስለዚህ ጉዳይ በዚሁ መጽሔት የወደፊት እትም ላይ እንመለስበታለን ።

ለ) ከአንድ በላይ የሆኑ ሥርዓተ ማኅ
በሮችን የሚያገለግሉ የኢኮኖሚ
ሕጎች

ሐ) ሁሉንም ሥርዓተ ማኅበሮች የሚ
ያገለግሉ የኢኮኖሚ ሕጎች ናቸው።

በ(ሀ) ተራ ቍጥር ላይ ለተጠቀሰው
የኢኮኖሚ ሕግ እንደ ምሳሌ ሊወሰድ የሚ
ችለው የትርፍ እሴት ሕግ (The Law
of Surplus Value)* ነው ። የትርፍ
እሴት ሕግ የካፒታሊስት ኢኮኖሚ የሚ
መራበት ዋንኛው የኢኮኖሚ ሕግ እንደ
መሆኑ መጠን የካፒታሊስቱ ኢኮኖሚ ቦታ
ውን ለሶሺያሊስቱ ኢኮኖሚ በሚለቅበት
ጊዜ ሕልውናው የሚያከትም ሕግ ነው ።
እስከዚያው ድረስ ማናቸውም ካፒታሊስት
የትርፍ እሴትን ሕግ በመጻረር እሠራለሁ
ቢል ካፒታሊስት ሆኖ ለመቆየት አይች
ልም ። በሌላ በኩል ይህ የትርፍ እሴት ሕግ
በካፒታሊስቱ ሥርዓት ውስጥ በሚካሄደው
የመደብ ትግል ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ ያደ
ርጋል ። የወዝአደሩ መደብ የማ.ሌ ፓር
ቲው ይህ ለወዝአደሩ መደብ ብዝበዛ ምክ
ንያት የሆነው የኢኮኖሚ ሕግ መንስኤው
የካፒታሊስት የምርት ግንኙነት መሆኑን
ስለሚገነዘብ መላውን ሠርቶአደር ሕዝብ
በማስተባበርና በመምራት የሶሺያሊስት
አብዮቱን በማካሄድ ብዝበዛ የሌለበት የም
ርት ግንኙነት እንዲመሠረት ይታገላል ።

በዚሁ በሀ/ ተራ ቁጥር ውስጥ የሶሻ
ያሊስቱን ኢኮኖሚ ብቻ በማገልገል እንደ
ምሳሌነት የሚጠቀሱ የኢኮኖሚ ሕጐች
አሉ ። ከእነሱም መካከል በሶሺያሊስት
ሥርዓት ውስጥ በየጊዜው እያደገ የሚሄ
ደውን የሰፊውን ሠራተኛ ሕዝብ ፍላጐት
የማሟላት ሕግ ፣ የብሔራዊ ኢኮኖሚ ሚዛ
ናዊና የተመጣጠነ የእድገት ሕግ ፣ ከእያን
ዳንዱ እንደ ችሎታው ለእያንዳንዱ እንደ
ሥራው የመክፈል ሕግና የሶሺያሊስት
ክምችት ሕግ ይገኙበታል ። እነዚህን የሶ
ሺያሊስት የኢኮኖሚ ሕግጋት በትክክል
መረዳት እና በተግባር መተርጐም የሶሺ
ያሊስት የኢኮኖሚ ፕላን ቅድመ ሁኔታ
ነው ።

በ(ለ) ተራ ቍጥር ለተጠቀሰው የኢ
ኮኖሚ ሕግ ዓይነት በምሳሌነት ሊጠቀስ
የሚችለው የእሴት ሕግ ነው ። (The Law
of Value)* ነው ። የእሴት ሕግ
የሸቀጥ ምርት ባለበት ማናቸውም የኢ
ኮኖሚ ሥርዓት ውስጥ ባለው የምርት
እንቅስቃሴ ላይ ተጽእኖ የሚያደርግ የኢ
ኮኖሚ ሕግ ነው ። በሶሺያሊስቱም ኢኮ
ኖሚ ውስጥ ቢሆን የሸቀጥ ምርት ስለ
አለ ኢኮኖሚውን በእቅድ ለመምራት የፕ
ላን ነዳፊ ክፍሎች በፕላኑ ውስጥ የእሴት
ሕግን ተጽእኖ ማገናዘብ ይኖርባቸዋል ።
የሸቀጥ ምርት በሚጠፋበት በከፍተኛው
የኮሚኒስት የእድገት ደረጃ የእሴት ሕግም
አብሮ ይጠፋል ። እስከዚያው ድረስ ግን
የሸቀጥ ምርት በመጀመሪያ ከተስፋፋበት
ከባሪያው አሳዳሪ ሥርዓት ጀምሮ እስከ
ሶሺያሊስቱ የኢኮኖሚ ሥርዓት ድረስ የእ
ሴት ሕግ በማናቸውም የኢኮኖሚ እንቅ
ስቃሴ ውስጥ ተጽእኖውን ያሳድራል ።
ተጽእኖውም የሚከሰተው በሸቀጦች የዋጋ
ሥርዓት (Price System) አማካይነት
ነው ።

በ(ሐ) ተራ ቍጥር ላይ ለሰፈረው የኢ
ኮኖሚ ሕግ እንደ ምሳሌ ሊጠቀስ የሚችል
የኢኮኖሚ ሕግ የሥራ ምርታማነትን በየ
ጊዜው የማሳደግ ሕግ ነው ። ይህ የኢኮ
ኖሚ ሕግ በማናቸውም ሥርዓተ ማኅበር ው
ስጥ (የኮሚኒስቱንም ሥርዓት ጨምሮ) ከፍ
ተኛ ተጽእኖ የሚያደርግና ተግባራዊ መሆን
ም ያለበት ነው ። ይህ ሕግ ተግባራዊ በማ
ይሆንበት ጊዜ የምርት ኃይሎች ዕድገት
እየተገታ መምጣቱን ፤ የምርት ውጤት
ማቀልቀሉን የሚጠቁም ስለሆነ ተጻራሪ
መደቦች እስካሉበት ጊዜ ድረስ ለማኅበ
ራዊ አብዮት መቀስቀስ ምክንያት ሲሆን
ተጻራሪ መደቦች ከጠፉ በኋላ ሰው ከተፈ
ጥሮ ጋር የሚያደርገው ትግል በማያቋርጥ
ሁኔታ መቀጠል እንደሚኖርበት ይጠቁ
ማል ።

---

* የትርፍ እሴት ሕግ (The Law of Surplus
Value) በእሴት የጉልበት ንድፈ ሐሳብ ላይ
የተመሠረተ ሕግ ሲሆን ፤ በካፒታልና በጉ
ልበት መካከል ያለው ግንኙነት ፤ ከላይ
ሲታይ ፤ ካፒታል ለጉልበት ተገቢ የሆነ
ክፍያ (on the basis of equivalant
exchange) ካደረገ በኋላ፣ ከተገቢ ክፍያ በስ
ተጀርባ ካፒታል ጉልበትን እንደሚበዘብዝ
የሚያስረዳ የኢኮኖሚ ሕግ ነው ።

* የእሴት ሕግ (The Law of Value) የሸቀጥ
ምርት የኢኮኖሚ ሕግ ሲሆን ፤ ተመርተው
የሚሸጡ ሸቀጦች እነሱን ለመሥራት በፈ
ሰሰው ማኅበራዊ ተቀባይነት ባለው የሥራ
ኃይል መጠን መለዋወጣቸውን የሚቆጣጠር
ሕግ ነው ።

INFINIX HOT 8 | 13MP
AI TRIPLE CAMERA

የማ.ሌ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ የኢኮኖሚ ሕጎችን የሚያጠና ከመሆኑም በላይ ተግባራዊ ሊሆኑ የሚችሉት በሳይንሳዊ የፕላንና የኢኮኖሚ የአስተዳደር ዘይቤ ሲደገፉ እንደሆነ ያስረዳል ። የፓርቲና የመንግሥት የኢኮኖሚያዊ ፖሊሲዎች በነባራዊ የኢኮኖሚ ሕጎች ዕውቀት ላይ መገንባት እንደሚኖርባቸው ይጠቁማል ። ለመንግሥት የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ አመራር የሚሰጠው የፓርቲው የኢኮኖሚያዊ ፖሊሲ ከሳይንሳዊ የኢኮኖሚ ንድፈ ሐሳብ የሚመነጭ በመሆኑ የማ.ሌ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ለሶሻሊስት የፕላን ሳይንስ ተጨባጭ የሆነ ንድፈሃሳብ መሠረት ይሆናል፤ መሆንም ይኖርበታል ። ሶሻሊስት የፕላን ሳይንስ በፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ንድፈ ሐሳብ ከታጠቀ የኢኮኖሚ ሕግጋትን በተግባር ለመተርጎም ትክክለኛ የአሠራር ዘዴ ይነድፋል ፤ የኢኮኖሚው የዕድገት እቅድ ተግባራዊ የሚሆንበትን መንገድ ይጠቁማል ።

የሽግግር ወቅት የኢኮኖሚ ሕግ

የሶሻሊስት ሥርዓት ኢኮኖሚ ሙሉ በሙሉ ባልተገነባበት የሶሻሊስቱ የምርት ግንኙነት ባልሰፈነበት በሽግግር ወቅት ያለውን ወይም መኖር የሚገባውን ዋንኛውን የኢኮኖሚውን አንቀሳቃሽ ኃይል ወይም ሕግ መገንዘብ በጣም አስፈላጊ ነው ። እንደ የአገሮቹ የዕድገት ደረጃ ሊያጥርም ሊረዝምም በሚችል የሽግግር ወቅት ጊዜ ስለሚኖረውና ትኩረት ስለሚያስፈልገው የኢኮኖሚ ሕግ ምንነት ከማውሳት በፊት ፤ ይህ ሕግ ለመኖር የሚችልበትን የሶሽዮ ኢኮኖሚክ ሁኔታ ማብራራቱ ተገቢ ነው ።

በመሠረቱ የሽግግር ወቅት ምን ማለት ነው? ዓላማውስ ምንድን ነው? የሽግግር ወቅት በተለይም በመጀመሪያው ጊዜ ተንሰራፍቶ በሚገኘውና ተደላድሎ የያዘውን ቦታ ላለመልቀቅ በሚታገለው ቅድመ ሶሺያሊስት የምርት ግንኙነትና ዋና ዋና የምርት ማከናወኛዎች የመንግሥት ንብረት መሆን በሚጀምሩበት ጊዜ በእንጭጭነት በሚከሰተው የሶሺያሊስት የምርት ግንኙነት መካከል ከፍተኛ ትግል የሚካሄድበት ወቅት ነው ። ትግሉም በሽግግሩ ወቅት ከሶሺያሊስቱ የኢኮኖሚ ይዞታ ይልቅ ተስፋፍቶ የሚገኘውን የሶሺያሊስት ያልሆነ ይዞታ (ማለትም የካፒታሊስት ፤ የአነስተኛ ሸቀጥ አምራቾችና ቅድመ ፊውዳል የኢኮኖሚ ይዞታ) ደረጃ በደረጃ በሶሺያሊስት የኢኮኖሚ ይዞታ ለመተካት የሚደረግ ትግል ነው ። ዓላማውም ባጭሩ ለዳበረ ሶሺያሊዝም መሠረት በመጣል የሶሺያሊስት ኢኮኖሚን መገንባት ነው ። የሶሺያሊስት ኢኮኖሚ መገንባት ማለት ደግሞ የሶሺያሊስቱን የምርት ግንኙነት ማዳበርና የተለያዩትን ክፍላተ ኢኮኖሚዎች በዘመናዊ የማሽን የአመራረት ተቋም እንዲታጠቁ ማድረግ ማለት ነው ።

ይህን ለማድረግ ከፍተኛ የመዋእለ ነዋይ መጠን ማስፈለጉ ግልጽ ነው ። ይሁንና የተገኘውንም ያህል ቢሆን የሶሺያሊስት ኢኮኖሚ መሠረት በመጣሉ አንጻር በትክክል ጥቅም ላይ መዋሉንና አለመባከኑን ማረጋገጥ ከዚህ ነጥብ ጋር የተያያዘ ነው በመሆኑም ከዚህ ከተነሳን በሽግግሩ ወቅት ያለውና መኖርም ያለበት ዋንኛው የኢኮኖሚ ሕግ የቅድመ ሶሺያሊስት የጥሪት ክምችት ሕግ (Primary Socialist Accumilation) መሆኑ ግልጽ ይሆናል ። የቅድመ ሶሺያሊስት የጥሪት ክምችት ሕግ የተባለው ከሶሺያሊስት የጥሪት ክምችት ሕግ የተለየ መሆኑን ለማመልከት ነው ። የሶሺያሊስት የጥሪት ክምችት የሚገኘው ከሶሺያሊስት የኢኮኖሚ ይዞታ ውስጥ ሲሆን የሚውለውም ለሶሺያሊስት የተስፋፋ እርባታ ነው። የቅድመ ሶሺያሊስት የጥሪት ክምችት በሽግግሩ ወቅት ለማደግ ከሚታገለው የሶሺያሊስት የኢኮኖሚ ይዞታ ባብዛኛው ሊገኝ አይችልም ። ምክንያቱም በሽግግሩ ወቅት የሶሺያሊስት የኢኮኖሚ ይዞታ የሚያተኩረው መሠረተ ልማት በመዘርጋቱ ላይ ስለሆነና ይኸም ሁኔታ በአጭር ጊዜ ውስጥ አስፈላጊ የሆነውን የጥሪት ክምችት ሊያስገኝ ባለመቻሉ ነው ። በመሆኑም በሽግግሩ ወቅት ከመሠረተ ልማት በተጨማሪ ለኃይል ማመንጫና ለኢንዱስትሪ ግንባታ የሚያስፈልገው ፤ ከሀገር ውስጥ መገኘት ካለበት የጥሪት ክምችት አብዛኛው መመንጨት ያለበት በዚሁ በሽግግር ወቅት ካልጠፋውና ተንሰራፍቶ ከሚገኘው ቅድመ ሶሻሊስት ከሆነው የካፒታሊስትና የጥቃቅን ሸቀጥ አምራቾች ይዞታ፤ በተለይም እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ኢኮኖሚያቸው በእርሻ ላይ በተገነባ አገሮች ከእርሻው ክፍለ ኢኮኖሚ ነው ። የእርሻው ክፍለ ኢኮኖሚ ይህን ለማድረግ እንዲችል በቅድሚያ በአ

ራቾች የኅብረት ሥራ ማኅበራት መደራጀት ይኖርበታል ።

ለሶሻሊስት የኢኮኖሚ ግንባታ አስፈላጊ የሆነው የጥሬት ክምችት ሊገኝ የሚችለው ግንባታውን የሚያከናውነው መንግሥት በሚከተለው የኢኮኖሚ ፖሊሲ አማካይነት ነው ። የመንግሥት የኢኮኖሚ ፖሊሲ ደግሞ የገቢና የወጭ (Fiscal) ፖሊሲን ፤ የዋጋ ፖሊሲን ፤ የውጭና የሀገር ውስጥ ንግድ ፖሊሲን ፤ የብድርና ባጠቃላይ የፋይናንስ ፖሊሲን እንዲሁም የሰው ኃይል ስርጭት ፖሊሲን የሚያጠቃልል መሆን ይኖርበታል ። እነዚህ በመንግሥታዊ የኢኮኖሚ ፖሊሲ ውስጥ የታቀፉ ንኡሳን ፖሊሲዎች ተግባራዊ በሚሆኑበት ጊዜ በሽግግሩ ወቅት ካለው ዋንኛ የኢኮኖሚ ሕግ ማለትም ከቅድመ ሶሻሊስት የጥሬት ክምችት ሕግ ጋር የተገናዘቡና እሱን የሚያጠናክሩ መሆናቸው ሊረጋገጥ የሚችለው ፓርቲው ለመንግሥታዊው የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ በሚሰጠው አመራር አማካይነት ነው ።

የማሌ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ የመደብ ይዘት አለው

በጽሑፉ መግቢያ ላይ እንደተጠቀሰው የማሌ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ማኅበራዊ የሆነውን የአመራረት ሥርዓት በማጥናት ያለውን የፖለቲካ ሥልጣን ይዘት የምንረዳበት ሳይንስ ነው ። ምክንያቱም ማናቸውም ሥርዓተ ማኅበር የምርት ኃይል ፤ የምርት ግንኙነትና የላዕላይ መዋቅሩ አንድ ክፍል የሆነው የፖለቲካ ሥልጣን በአንድ ላይ ተዋህደው የሚገኙበት በመሆኑ ነው ። በተለይም ደግሞ የምርት ግንኙነት በቅድሚያ የሚያተኩረው በተለያዩ ሥርዓተ ማኅበሮች ውስጥ በሚገኙ ማኅበራዊ መደቦችና የመደብ ግንኙነቶች ላይ እንደመሆኑ መጠን ፤ የፖለቲካ ኢኮኖሚ በኅብረተሰቡ ውስጥ ያለውን የኢኮኖሚ ግንኙነት በማጥናት በተለያዩ መደቦች መሠረታዊ ጥቅም ላይ ያተኩራል ። ለዚህም ነው የማሌ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ የመደብ ይዘት አለው የሚባለው ። ሁሉንም መደቦች የሚያቅፍ አንድ የፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ሊኖር አይችልም ።

በአሁኑ ጊዜ የቡርዧ ኢኮኖሚስቶች የቡርዧ ርዕዮተ ዓለማቸውንና የቡርዥዋውን መንግሥት ከመደባቸው ጥቅም ጋር ያልተሳሰሩና ከመደቦች በላይ እንደሆኑ አርገው እንደሚያቀርቡ ሁሉ የቡርዥዋውንም የኢኮኖሚ አመለካከት ሁለንተናዊ ፤ ከመደቦችና ከፓርቲዎች በላይ እንደሆነ አርገው ለማቅረብ ይሞክራሉ ።

የቡርዥዋው ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ እንደ አሁኑ ከቡርዥዋው ማኅበራዊ ሳይንስ ውስጥ ስሙ ከነጭራሹ ጠፍቶ የተለያዩ የኢኮኖሚ ክፍሎችን በሚያጠኑ ቴክኒካዊ የጥናት ዘርፎች ከመዋጡ በፊት የተለያዩ የዕድገት ደረጃዎችን አልፏል ። የቡርዥዋው መደብ የፊውዳሉን መደብ በመጻረር ለካፒታሊስት የምርት ግንኙነት የበላይነትና መደቡንም የፖለቲካ ስልጣን ለማስጨበጥ በሚታገሉበት ጊዜ የቡርዥዋ የፖለቲካ ኢኮኖሚስቶች ከዊልያም ፒቲ ጀምሮ እስከ ዴቪድ ሪካርዶ ድረስ ያሉት ለፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ጥናት ሳይንሳዊ መሠረት ጥለዋል ። በዚህም ወቅት በዋና ዋና የቡርዧ የፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ጠበብቶች አሁን የማርክሲስት ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ የጀርባ አጥንት የሆነው የእሴት የሥራ ንድፈ ሐሳብ (The Labour Theory of value) ተነደፈ ። ለቡርዥዋ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ጥናት ከፍተኛና የመጨረሻ ዕድገት ያስገኘው ዴቪድ ሪካርዶ የሀብት ሁሉ ምንጭ የሰው ጉልበት መሆኑን አበሰረ ። በዚህ ወቅት ከካፒታሊዝም ዕድገት አለመደርጀት የተነሳ ወዝአደሩ በቡርዣዋው አብዮት ውስጥ በመሳተፍ በካፒታሊስቱ እየተመራ ጸረ ፊውዳል ትግል ያካሂድ ነበር ።

የካፒታሊስት ሥርዓት ተስፋፍቶ የቡርዥዋው መደብ በፖለቲካውም በኢኮኖሚውም መስክ በፊውዳሉ መደብ ላይ የበላይነቱን ከተቀዳጀ በኋላ በኅብረተሰብ የዕድገት ሂደት ታሪክ ውስጥ ቀደም ሲል የነበረው ተራማጅነት እያከተመ የካፒታሊዝም ዕድገት ከፈጠረው የወዝአደሩ መደብ ጋር ግጭት ይፈጥራል ። ቀደም ሲል የቡርዥዋው የፖለቲካ ኢኮኖሚም አመለካከት በመጠነኛ ደረጃ የነበረውን ሳይንሳዊ ይዘት ሳያጣ ሲያራምድ የነበረው የእሴት የጉልበት ንድፈ ሐሳብ ፤ ቡርዥዋው በኅብረተሰብ የዕድገት ሂደት እየተገፋ ከተራማጅነት ወደ አድኅሪነት በተሸጋገረበት ወቅት በራሱ ላይ የተነጣጠረ መሣሪያ ሆነበት ። ቡርዥዋው ከጥፋት ለማምለጥ ሲል

የመሣሪያውን አፈሙዝ አቅጣጫውን መቀየር ነበረበት ። ይህ የፖለቲካ ኢኮኖሚን ጽንሰ ሐሳብ አቅጣጫ የማድበስበስ ፤ ብሎም የመቀየር ሂደት ጊዜ የወሰደና ብዙ የቡርዥዋ የኢኮኖሚ ጠበብቶች የተካፈሉበት ሲሆን ፤ በዚህ ሂደት ውስጥ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ በመጀመሪያ ደረጃ በተራ (Vulgar) ኢኮኖሚ ፤ በኋላም በማርጅናሊስቶች (Marginalist) አመለካከት እንዲተካ ተደርጎ ነበር ። ተራ (Vulgar) የሆነው የቡርዥዋ ኢኮኖሚ አመለካከት የክላሲካል የቡርዥዋ ፖለቲካ ኢኮኖሚስቶችን በመቃወም ከተለያዩ የንብረት ይዞታዎች በሚመነጩ ገቢዎች መካከል ማለትም በመሬት ፤ በካፒታልና በሥራ ኃይል በአንድ በኩል በወለድ በትርፍና በምንዳ በሌላ በኩል ምንም ዓይነት ግንኙነት እንደሌለና በመካከላቸውም ምንም ዓይነት ቅራኔ እንደማይነሳ አርገው ያቀርቡታል ። አንዳንዶቹ የካፒታሊስቱን ትርፍ በሙሉ ወይም በከፊል እራሱ ካፒታሊስቱ ባፈሰሰው የሥራ ኃይል ሳቢያ እንደተገኘ አርገው ይወስዱታል ። ምንዳ ፤ ትርፍና ወለድ በምርት ሂደት ውስጥ በአንድነት ሥራ ላይ የሚውሉት በመካከላቸው ጥሩ ስምምነት ስለአለ ነው ይላሉ ።

‘ማርጅናሊዝም’ በአሁኑ ጊዜ ተስፋፍቶ የሚገኝ የቡርዥዋ የኢኮኖሚ አመለካከት ነው ። የሚያተኩረውም ግለሰቦች ለሸቀጦች ካላቸው ውስጣዊ ፍላጎትና ጠቀሜታ (Utility) ፤ ይህም ውስጣዊ ጠቀሜታ በሚተመንበት ዘዴ ላይ ነው ። ‘ማርጅናሊስቶች’ የሚመረት ነገር ሳይኖር የሸቀጥ ልውውጥ ሊኖር እንደማይችል በመገንዘብ የኋላ ኋላ በሸቀጦች የአመራረት ዘይቤ ላይ አንዳንድ አስተሳሰቦችን ለመሰንዘር ተገደዋል ።

በመሠረቱ የአመራረቱ ዘይቤ በማምረቻ መሣሪያዎች ባለቤትነትና ይህም ባለቤትነት በክፍፍሉ መስክ የሚያሳድረው ተጽእኖ ያለ መሆኑ ግልጽ ሆኖ ሳለ ፤ ማርጅናሊስቶች ግን ያለውን የሀብት አከፋፈል (Resource Allocation) እንዳለ በመቀበል ፤ የሚያተኩሩት በግለሰቦች ስሜታዊ ምርጫዎችና ምኞቶች ላይ ነው ። ከግለሰቦች ስሜታዊ ምርጫዎችም በመነሳት በስሜታዊ መሠረት ላይ ጠቅላላ የኢኮኖሚ ‘ሥርዓት’ ለመፍጠር ይሞክራሉ ።

የታወቀው የቡልጋሪያ የፖለቲካ ኢኮኖሚ ሊቅ ፕሮፌሰር ኬሪል ግሪጎሮቭ የኢኮኖሚ አስተሳሰቦች ታሪክ በተባለው መጽሐፉ ውስጥ ስለ ማርጅናሊስቶች የኢኮኖሚ አመለካከት [illegible] ሳይኮሎጂና ህሊና ውስጥ የተፈጠሩ [illegible] የምርት ክፍፍል ሕጎች ላይ እንደሚያተኩሩ አብራርቷል ። በተጨማሪም ማርጅናሊስቶች ጥናታቸውን የሚጀምሩት ኢኮኖሚውንና የኢኮኖሚ ዕድገትን ነባራዊ የታሪክ ሂደት አድርገው ሳይሆን ፤ ሜታፊዚካዊ በሆነ መንገድ ግለሰቡን የጥናታቸው ማእከል በማድረግ እንደሆነ ይጠቁማል ።

ይህ ብቻ ሳይሆን ማርጅናሊስቶች ፤ ዋጋን ፤ ገንዘብን ፤ ካፒታልን ፤ መዋእለንዋይን ፤ ወለድን ፤ ወዘተ. . . በሚገልጹበት ጊዜ ከስሜታዊ ፍላጎትና ጠቀሜታ አንጻር እንደሚነሱ ፤ ከዚህም በመነሳት የካፒታሊስቱ ኢኮኖሚ መሠረታዊ ባህርዮች በሁሉም የኢኮኖሚ ሥርዓቶች ውስጥ እንደሚኖሩና ካፒታሊዝምም በተለያዩ መጠኖች በሁሉም ሥርዓተ ማኅበሮች ውስጥ እንዳለ አድርገው እንደሚያቀርቡት ፕሮፌሰር ኬሪል ግሪጎሮቭ ከላይ በተጠቀሰው መጽሐፉ ውስጥ በሚገባ አብራርቶታል ።

የካፒታሊስቱ ሥርዓት በዓለም አቀፍ ደረጃ ከፍተኛ የኢኮኖሚ ቀውስ ውስጥ እስከ ወደቀበት እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር ከ1929-1933 ድረስ ፤ በአጠቃላይ እስከ 1930ዎቹ መጨረሻ ድረስ የነበሩት የተለያዩ የቡርዥዋ ኢኮኖሚ አመለካከቶች የኢኮኖሚ ጥናት ሲባል በማምረትና ምርትንም በመለዋወጥና በመከፋፈል ሂደት ውስጥ ሰዎች እርስ በርሳቸው የሚፈጥሩት ግንኙነት ሳይሆን ፤ በሰዎች በአንድ በኩል በተፈጥሮ ወይም በበቂ መጠን ባልተመረቱ ነገሮች መካከል በሌላ በኩል ያለውን ግንኙነት እንደሚያጠና አድርገው ያቀርቡታል ። ኤንግልስ የቡርዥዋ የኢኮኖሚ ጠበብቶች አመለካከት ትክክል እንዳልሆነ ሲያስረዳ ፤

የቡርዥዋ የኢኮኖሚ ጥናት ጠበብቶች አእምሮ በትክክል ያልተረዳው ነገር ፤ የኢኮኖሚ ጥናት በሰዎች መካከል ብሎም በመደቦች መካከል ያለውን ግንኙነት እንጅ በነገሮች መካከል ያለውን ግንኙነት እንደማይመለከት ነው፤»[4] ብሎ ነበር ።

ከታላቁ የኢኮኖሚ ዝቅጠት (The Great Depression) ወዲህ በእንግሊዙ የኢኮኖሚ ሊቅ በጆን ሚራንድ ኪይንስና በተከታዮቹም አማካይነት ፤ የቡርዥዋ የኢ

ኮኖሚ ጥናት የካፒታሊስት መንግሥታት የካፒታሊስቱን ኢኮኖሚ ቀስፎ በያዘው የኢኮኖሚ ቀውስ (ማለትም የሥራ አጥነት እየበዛ መሄድ ፣ በአንድ በኩል የዋጋ መናር ከሚያስከትለው የኑሮ ውድነት በሌላ በኩል) ጥያቄ ላይ በማተኮር ፤ የካፒታሊዝምን ሥርዓት ህልውና ለማራዘም አንዳንድ ዘዴዎችን ቀይሰዋል ። ኪይንስ በካፒታሊስቱ ኢኮኖሚ ውስጥ ስለአሉ ቋሚ የሚዛናዊነት መፋለሶችና እነዚህም መፋለሶች በመንግሥት ጣልቃገብነት አንጻራዊ በሆነ መንገድ ሊወገዱ የሚችሉበትን ዘዴ በማቲማቲክስና በጂኦሜትሪ ፎርሙላዎች አቅርቧቸዋል ። ዞሮ ዞሮ ግን የኬይንስ የኢኮኖሚ አመለካከት የቡርዥዋውን የመደብ ጥቅም ለማስከበር ሥርዓቱን ከውድቀት ለማዳን የተደረገ ሙከራ መሆኑ ግልጽ ነው ።

እንዲያውም በአሁኑ ጊዜም ሆነ ፣ ቀደም ሲል ከሀያኛው ክፍለ ዘመን መባቻ ጀምሮ ፣ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ የሚባለውን ቃል በቡርዋዥው ዓለም ከማኅበራዊ የሳይንስ ዘርፎች ውስጥ ደብዛውን በማጥፋት «ኢኮኖሚክስ» በሚል የተለያዩ ዘርፎችን ባዘለ ሌላ ማኅበራዊ ሳይንስ ዘርፍ እንዲዋጥ አድርገውታል ። በአሁኑ ጊዜ በካፒታሊስት አገሮች እንደሚታየው የቡርዥዋ ኢኮኖሚክስ የሚያጠናው ከኅብረተሰብ ግንኙነት ስለተነጠለ «የቴክኒዎሎጂካል የአመራረት ዘይቤ» ሆኗል። የቡርዥዋ ኢኮኖሚስቶች እንደሚያቀርቡት ኢኮኖሚክስ ለምርት የሚያገለግሉ (Factors of Prodction) ማለትም የሰው ጉልበት ፤ ካፒታልና መሬት ወጭን ሊቀንሱና ትርፍን ሊያበዙ በሚችሉበት መንገድ ሥራ ላይ ሊውሉ የሚችሉበትን ዘዴ የሚያጠና ‘ሳይንስ’ ሆኗል ።

የታወቀው እንግሊዛዊው ማርክሳዊ የኢኮኖሚ ሊቅ ሞሪስ ዶብ በፖለቲካዊ ኢኮኖሚና በኢኮኖሚክስ መካከል ስለአለው ልዩነት An Introduction to Economics በተባለው ጽሑፉ ውስጥ ሲያብራራ «‘ኢኮኖሚክስና’ ‘ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ’ ለአንድ ነገር የተሰጡ የተለያዩ ስሞች አይደሉም ። ኢኮኖሚክስና ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ የተለያዩ ነገሮችን የሚመረምሩ ፤ በይዘትም ሆነ በዓላማ የተለያዩ ናቸው ፤»[5] በማለት አስፍሮታል ።

በመሆኑም በአሁኑ ጊዜ በካፒታሊስቱ ክፍለ ዓለም የፖለቲካ ኢኮኖሚ ጥናት ፤ ምንም እንኳን በዚህ ስሙ ባይታወቅም ፤ በአጠቃላይ ያለው የቡርዥዋው የኢኮኖሚ አመለካከት ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው በገሀድ የቡርዥዋውን የመደብ ጥቅም በማራመድ ላይ በመሆኑ ፤ ሁለንተናዊና ከተወሰነ (ከቡርዥዋው) የመደብ ጥቅም በላይ እንደሆነ ተደርጎ ሊወሰድ አይቻልም ።

በተቃራኒ የማ.ሌ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ በአጠቃላይ የሠራተኛው መደብና የፓርቲው የትግል መሣሪያ መሆኑን በግልጽ ያስታውቃል ። ምክንያቱም የሠራተኛው መደብ ጥቅም ተጨባጭ ከሆነው የኅብረተሰብ የዕድገት ሂደት ጋር የሚጣጣምና እራሳቸውንም ከማናቸውም ዓይነት ብዝበዛ ነጻ ለማውጣት ከሚታገሉ ሕዝቦች ጥቅም ጋር የተሳሰረ በመሆኑ ነው ።

የማ.ሌ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ የወዝአደሩ መደብ ከብዝበዛ ለመላቀቅ በሚያደርገው ትግል ዋንኛው የርዕዮተዓለም መሣሪያው ከመሆኑም በላይ ፤ ማኅበራዊ ምርት ከዝቅተኛ ደረጃው እስከ ከፍተኛ የዕድገት ደረጃው ድረስ ያለፈበትን መንገድ በመቃኘት የታሪክ ግሥጋሴ የግዴታ ወደ ሶሻሊስት የኢኮኖሚ ሥርዓት ብሎም ወደ ኮምኒስት ሥርዓተ ማኅበር እንደሚያመራ ያሳያል ። የማ.ሌ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ መላ ሠርቶአደር ሕዝቦች የኅብረተሰብ ዕድገትን በሚወስኑ የኢኮኖሚ ሕጎች ዕውቀት እንዲታጠቁ ከማድረጉም በላይ ለሠርቶአደሩ ሕዝብ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ጥያቄ መርሐ ግብር ሳይንሳዊ መሠረት ይሆናል ። የሶሻሊስት የዕድገት ፈለግ የሚከተሉ አገሮችንም ለብሔራዊ ብልጽግናቸው መሠረት የሆነውን የኢኮኖሚ ነጻነትና ዕድገት የሚጎናጸፉበትን መንገድ ከማሳየቱም በላይ ፤ ሥር ነቀል የሆነ የሶሺዮ ኢኮኖሚክ ለውጥ ለማድረግ መንደፍ ያለባቸውን የኢኮኖሚያዊ ፖሊሲ ይጠቁማቸዋል ።

---

1. F. Engles; *Anti-Duhiring*; p. 163-164
2. Marx-Fngles; selected Works; Vol. 3;p. 162
3. Lenin; *Marx-Engles Marxism*; p. 15
4. Karl Marx; *A contiribution to the critique of polotical Economy*; Translected by Maurice Dobb; p. 218
5. Maurice Dobb; *An Itroduction to Economics*; quoted in John Strachey; *The Nature of Capitalist Crisis*; p. 117

መስከረም



የማርክሲስት ሌኒኒስት ርዕዮተ ዓለም መጽሔት

ቅጽ 1 ቁጥር 3
መጋቢት 1973

INFINIX HOT 8 | 13MP
AI TRIPLE CAMERA

መስከረም

ቅጽ 1 ቁጥር 3
መጋቢት 1973

የማርክሲስት ሌኒኒስት ርዕዮተ ዓለም መጽሔት

ማ ው ጫ

ገጽ

- የዝግጅት ገፅ - - - - - - - - - - - - - - - - - 3
- ኮምኒስት ማለት ምን ማለት ነው? - - - - - - - - - - - 7
  - ገዛኸኝ ገብሬ
- ማርክሳዊ የፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ግንዛቤ - - - - - - - - - - - - 27
  - አምሃ ዳኘው
- የኢትዮጵያ ሕዝብ የነፃነት ትግልና የኢጣልያን ፋሽሽት ወረራ - - - - 37
  - በኢሠፓኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ የርዕዮተ ዓለም መምሪያ
  — የአብዮት ታሪክ ክፍል —
- የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም በቅድመ አብዮት ኢትዮጵያ - - - - - 55
  - ለገሠ ለማ
- የጊዜያችን ፀረ-ኢምፔሪያሊስት ትግል
  — የላቲን አሜሪካ ሕዝብ የብሔራዊ አርነት ንቅናቄ - - - - 70
  - ብርሃኑ ዘሪሁን
- የነጋድራስ ገ/ሕይወት ባይከዳኝ የፖለቲካዊ ኢኮኖሚ አስተሳሰብ - - - - 84
  - አየለ ዘውገ

በኢሠፓኦ ማዕከላዊ ኮሚቴ

ርዕዮተ ዓለም መምሪያ እየተዘጋጀ በየሦስት ወር የሚወጣ።

አድራሻ

የፖስታ ሣጥን ቍጥር — 80001
የስልክ ቍጥር — 113000

የኢትዮጵያ ሕዝብ የነፃነት ትግልና የኢጣልያን ፋሽሽት ወረራ

በኢሠፓአኮ የርእዮተዓለም መምሪያ
የአብዮት ታሪክ ክፍል

የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ነጻነቱንና ብሔራዊ አንድነቱን ለመጠበቅ ከተለያዩ የውጭ ወራሪዎች ጋር አያሌ ፍልሚያዎች አካሂዷል ። ከነዚህ ፍልሚያዎች ውስጥ ፋሽስት ኢጣልያን የቃጣችባትን የቅኝ ገዥነት እብሪት ለማሸነፍ ያደረገው ትግል አንዱ ነው ። በኢትዮጵያ ረጅም የታሪክ እድሜ ውስጥ በተለይም ከ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ወዲህ የተለያዩ የውጭ ወራሪዎች አገሪቱን በቁጥጥራቸው ሥር ለማድረግ ተከታታይ የሆኑ ሙከራዎች አድርገዋል ።

እያንዳንዱ ወራሪ ኃይል በየወቅቱ ይዞት የተነሳው ልዩ ዓላማና ባህርይም ነበረው ። ቱርኮችና ግብጾች በአካባቢው የበላይነትን በመያዝ ንግድን ለመቆጣጠርና ግዛቶችን ለማስፋፋት በነበራቸው እቅድ መሠረት የተነሱ ሲሆን ፣ ፖርቱጋሎች ፣ ፈረንሳዮች፣እንግሊዞችና ኢጣልያኖች ደግሞ በምእራብ አውሮፓ ውስጥ የነበረውን የካፒታሊዝም እድገት መነሻ በማድረግ በየደረጃው ከዚህ እድገት ጋር የመነጩትን የቅኝ ግዛትና የብዝበዛ ፍላጐቶች ለማሟላት በኢትዮጵያ ነጻነት ላይ ተሰልፈዋል ።

በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጨረሻ ላይ ታላቁ የአድዋ ድል የኢትዮጵያን ነጻነት እስካረጋገጠ ድረስ የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ያካሄደው ያላቋረጠ ትግል ሁሉ ከዚህ ጋር የተያያዘ ነው ።

በ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የመጀመሪያ አጋማሽ ውስጥ ፋሽስት ኢጣልያ ኢትዮጵያን ለመያዝ የተነሳችበት ዓላማ ይህንኑ እድገት ተከትሎ የመጣ ሲሆን ፣ በመሀከሉም የነበሩትን ለውጦችና የወቅቱን ዓለም አቀፋዊ ሁኔታ የሚያንፀባርቅ የራሱ ባህርይ ነበረው ።

ካፒታሊዝም ወደመጨረሻ የዕድገት ደረጃው ወደኢምፔሪያሊዝም ከተሸጋገረ በኋላ ከታላቁ የጥቅምቱ ሶሻሊስት አብዮት ጋር የተወለደውን አዲስ የዕድገት ኃይል ለመቋቋም እጅግ የከረረ የትግል ምዕራፍ ተከፍቷል ። የቡርዧው መደብ ጥቅሙን ለመጠበቅ በዚህ ደረጃ ይዞት የተነሣው ማህበራዊ ኃይል ፋሺዝም ነበር ። ኢጣሊያ በኢትዮጵያ ላይ የከፈተችው ወረራ ከዚህ ኃይል የመነጨ በመሆኑና የኢትዮጵያ አርበኞች ያካሄዱትም ተጋድሎ የዓለም አቀፍ ፀረ ፋሺስት እንቅስቃሴ አካል ስለነበር የዚህን ክስተት ባህርይ ባጭሩ መመልከት ለአርእስታችን ተገቢ መግቢያ ይሆናል ።

ወቅቱ ከመጀመሪያው የዓለም ጦርነት ፍጻሜ በኋላ ነው ። በዚህ ጦርነት ውስጥ ዋና ተፋላሚ የነበሩት ኢምፔሪያሊስት አገሮች በጦርነቱ የተዳከሙ ቢሆንም በአፍሪካና በእስያ ሕዝቦች ላይ የነበራቸው የቅኝ ግዛት ፍጹም የበላይነት ገና እንዳለና እንደተጠበቀ ነበር ።እንዲያውም ለጦርነቱ ዋና የመነሻ ምክንያት የነበረው እነዚህ ኢምፔሪያሊስት አገሮች የአፍሪካንና የእስያን ሕዝቦች በባርነት ለመግዛትና ኃብታቸውን ለመዝረፍ ሲሉ እርስ በርስ ያነሱት ሽሚያና ፉክክር መሆኑም አይዘነጋም ።

ከዚህ ጦርነት ውስጥ የእንግሊዝና የፈረንሣይ ቡርዧ መደቦች በአሜሪካ ድጋፍ በአሸናፊነት የወጡ ሲሆን ፣ ተሸናፊ የሆኑትና የቅኝ ግዛት ዓላማቸው ያልረካው የጀርመንና የኢጣሊያን ቡርዧዎች ደግሞ ከፍተኛ ውድቀት ደርሶባቸዋል ። በአፍሪካ ውስጥ ቀድሞ የጀርመን ቅኝ የነበሩ ግዛቶች ለእንግሊዝና ለፈረንሣይ ፣ ወይም የነርሱ ደጋፊ ለነበሩ መንግሥታት ተሰጡ ። ኢጣሊያም በጦርነቱ ውስጥ በተጫወተችው ያልተቋረጠ ሚናና በነበራት ደካማነት የተነሣ የቅኝ ይዞታዋን ለማስፋፋት ያቀረበችው ጥያቄ በድል አድራጊዎቹ ዘንድ ተቀባይነት አላገኘም ። በዚህ ምክንያት አሸናፊና ተሸናፊ በሆኑት የኢምፔሪያሊስት አገሮች የቡርዧ መደቦች መካከል ከፍተኛ ቅራኔ ተፈጠረ ።

ነገር ግን በተለያዩ የቡርዧው መደቦች መካከል እርስ በርስ ከተፈጠረው ከዚህ የከረረ ቅራኔ ሌላ ሁሉንም የኢምፔሪያሊስት አገሮችን የቡርዧ መደቦች ከፍተኛ ሥጋት ላይ የጣለ ሁኔታ ከጦርነቱ ፍጻሜ ጋር አብሮ ተከስቷል ። ይህ ክስተት ሦስት የተያያዙ መልኮች ነበሩት ። እነዚህም ፦

1/ በታላቁ የጥቅምቱ ሶሻሊስት አብዮት አማካኝነት ለሶሻሊዝም የቆመ ጠንካራ የወዝአደር መንግሥት የዓለም አንድ ስድስተኛ ክፍል በሆነችው ሶቭዬት ኅብረት ውስጥ መመሥረቱ ፤

2/ በኢምፔሪያሊስት አገሮች ውስጥ የሚካሄደው የወዝአደሩ ትግል በጥቅምቱ አብዮት ድል ጥንካሬና አርአያነት እያገኘ ከፍተኛ ኃይል መሆኑና ፤

3/ የእስያና የአፍሪካ ሕዝቦች የአርነት ንቅናቄ በታላቁ የጥቅምቱ ሶሻሊስት አብዮት ሙሉ ድጋፍና በኢምፔሪያሊስት አገሮች መዳከም እየተበረታታ ወደ ከፍተኛ የትግል ደረጃ መሸጋገሩ ናቸው ።

ፋሺዝም በታሪክ መድረክ ላይ የከረረና የከፋ መልኩን ይዞ በምዕራብ አውሮፓ ኢምፔሪያሊስት አገሮች ውስጥ የተከሰተው በዚህ ሁኔታ ነው ።

በመሠረቱ ፋሺዝም የሚፈጠረው ቡርዧው መግቢያና መውጫ ሲያጣና መደባዊ ጥቅሙን በሚያናጉ ኃይሎች ተወጥሮ ሕልውናውን ለማስጠበቅ የከፋ ትግል ሲያካሂድ ነው ። ይህም በመሆኑ ፋሺዝም በአጠቃላይ በኢምፔሪያሊስት አገሮች ውስጥ ሁሉ በተጠቀሰው የታሪክ ወቅት ታይቷል ። ይሁን እንጂ በእያንዳንዱ አገር ውስጥ ኃይልና ሥልጣን ለመያዝ የነበረው ችሎታ እንደየአገሩ ሁኔታ የተለያየ ነበር ። ለምሳሌ ዓለምአቀፍ ቡርዧው ባጠቃላይ የወደቀበትን ውጥረት በመገንዘብ በእንግሊዝና በፈረንሣይ ውስጥ ሰፊ የፋሺስት እንቅስቃሴ ተፈጥሮ ነበር ። ነገር ግን የነዚህ አገሮች ገዥ መደቦች የተደላደሉና በቅኝ ግዛት ይዞታቸውም እጅግ የረኩ ስለነበር ፋሺዝም ሙሉ ኃይል ሊያገኝና የመንግሥት ለውጥ ሊያስከትል አልበቃም ። ይልቁንም በጀርመንና በኢጣሊያ የነገሰው ፋሺዝም በእንግሊዝና በፈረንሳይ ገዥ መደቦች ላይ የተለያዩ የግዛትና የቅኝ ግዛት ጥያቄዎች ይዞ ስለተነሣ ፤ ይህን አደጋ ለመከላከል ሲሉ ሁለቱ አገሮች እንዲያውም ፀረ ፋሺስት አቋም እየያዙ ለመምጣት ችለዋል ።

ከዚህ በላይ እንደተጠቀሰው ፋሺዝም መደባዊ መሠረት ይዞ ሙሉ ኃይልና የመንግሥት ሥልጣን ለማግኘት የበቃው በሙሶሊኒና በሂትለር መሪነት በኢጣልያና በጀርመን ነበር ። በዚህ ጥርት ባለ መልኩ ፋሺዝም ሦስት መሠረታዊ ዕቅዶችን ይዞ ተነስቷል ።

1/ ለቡርዧው ሕልውና ከፍተኛ ጠንቅ የሆነውን ሶሻሊዝምን ለማጥፋት የመጀመሪያዋና በዚያን ጊዜ ብቸኛ የወዝ አደር መንግሥት የተቋቋመባትን ሶሻሊስት ሶቭዬት ኅብረትን መደምሰስ ፤

2/ ከዚሁ ጋር አያይዞ በካፒታሊስት አገሮች ውስጥ የነበረውን የኮምዩኒስትና የሠራተኞች እንቅስቃሴ መምታትና ወዝደአሩን በብሔርተኝነት ርዕዮተዓለም መርዞ ለፋሺዝም ዓላማ ማሰለፍ እና ፤

3/ በቅኝ ግዛት እጦት ምክንያት በጀርመንና በኢጣሊያ ውስጥ የታፈነውን ካፒታሊስታዊ ዕድገት ለማፍታታት ሁለቱ አገሮች በአውሮፓ ፤ በአፍሪካና በእስያ ግዛታቸው እንዲስፋፉ የጦርነት ዝግጅት ማድረግ ነበረ ።

ከነዚህ ሦስት እቅዶች ውስጥ በመጀመሪያዎቹ በሁለቱ ላይ መላው የኢምፔሪያሊስት አገር ቡርዧ መደቦች የዓላማ አንድነት ነበራቸው ። በየአገሮቻቸው የነበረውን የኮሚዩኒስትና የሠራተኞች እንቅስቃሴ ለማፈን ሁሉም ተመሳሳይ የሆነ ስትራቴጂና ፀረ አብዮት ፖሊሲ አካሂደዋል ። ሶቭዬት ኅብረትን መምታት በሚለው አቋም ላይም እንደዚሁ አንድነት ነበራቸው ። ሒትለር በፈረንሳይና በእንግሊዝ ላይ ጦርነት ከከፈተ በኋላ እንኳንስ ፤ «የጋራ ጠላታችን በሆነችው ሶቭዬት ኅብረት ላይ ተባብረን በመዝመት ፈንታ ለምን እርስ በርስ እንዋጋለን» የሚል የምስጢር ድርድር ሲያደርጉ መቆየታቸው ለቡርዧ መደቦች የጋራ ፀረ ሶሻሊስት አቋም እውን ምስክር ነው ። በዚያን ጊዜ የሒትለር ምክትል የነበረውና ዛሬም በእስር ላይ የሚገኘው ሩዶልፍ ሒስ የተባለው ከፍተኛ የናዚ የጦር አለቃ በጦርነቱ መካከል ወደ እንግሊዝ አገር የበረረውም ለዚህ ተልዕኮ እንደነበር የተረጋገጠ ሐቅ ሆኗል ።

INFINIX HOT 8 | 13MP
AI TRIPLE CAMERA

ይሁን እንጂ ሦስተኛው የሒትለር የሙሶሊኒ ዕቅድ በተለያዩ የቡርዧው መደቦች መካከል የማይታረቅ ቅራኔ ስለፈጠረ የቡርዧ ዓለምአቀፋዊ ፀረ ኮሚዩኒስት አቋም ሊፀና አልቻለም ። በመጨረሻም በእስያ ክፍለ ዓለም ውስጥ ከፍተኛ የመስፋፋት ዕቅድ ይዞ የተነሳው የጃፓን ሚሊታሪስት መንግሥት ከጀርመን ናዚዝምና ከኢጣሊያ ፋሺዝም ጋር በነበረው የዓላማ አንድነት «በርሊን-ሮም-ቶኪዮ’ (Axis) የተባለው የጦር ኅብረት ተመሥርቶ ዓለም ለሁለተኛው የዓለም ጦርነት እልቂት ተዘጋጀች ።

ፋሺስት ኢጣሊያ በ1935 በኢትዮጵያ ላይ የከፈተችው ወረራ በዚህ ዓለም አቀፋዊ ሂደት ውስጥ የተፈጠረ ስህተት ነው ። በአንጻሩም የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብና የኢትዮጵያ አርበኞች ያካሄዱት መራራ የነጻነት ትግል ፣ በዓለምአቀፍ ደረጃ ይካሄድ የነበረው የፀረ ፋሺስት ትግል አካልና የሁለተኛው የዓለም ጦርነት አንድ ታሪካዊ ገጽታ ነው ።

ይህን ትግል በቀጥታ ከመመልከታችን በፊት ግን የኢትዮጵያን ሰፊ ሕዝብ ረዥምና አኩሪ የነጻነት ተጋድሎ ታሪክ ብቅድሚያ በአጭሩ እንመረምራለን ።

ከቱርኮች ሙከራ እስከ አድዋ

ኢትዮጵያን የቅኝ ግዛት አድርጎ ለመያዝ ብዙ አገሮች ሙከራ አድርገው ሳይሳካላቸው እንደቀረ የአለፈው ፀረ ኮሎኒያሊስት ትግላችን ይመሰክራል ። የኦቶማን ቱርክና የግብጽ ተስፋፊዎች ፣ የፖርቱጋል ቅኝ ገዥዎች ፣ የመሐዲስት ወራሪዎች ፣ የኢጣሊያ ፣ የእንግሊዝና የፈረንሳይ ኢምፔሪያሊስት ኃይሎችና እንዲሁም የኢጣሊያ ፋሺስቶች በማከታተል ያደረጓቸውን ስውርና ግልጽ ሙከራዎች ነጻነት ወዳዱ የኢትዮጵያ ሕዝብ በተባበረ ክንዱ ሊያከሽፋቸው ችሏል ። እነዚህ ግዛትን ለመድፈር የሞከሩ ኃይሎች ኢትዮጵያን ለመያዝ ካደረጓቸው ሙከራዎች አብዛኞቹ በስውር የተደረጉ ነበሩ ። ይህም ሚሲዮናውያንና ቆንስላዎችን አስቀድመው በመላክ ቦታውን ካስጠኑ በኋላ ወታደሮችን በመላክ የሚያደርጉት የወረራ ሙከራ ነው ። ይህን አስመልክተው አጼ ቴዎድሮስ ሊዠን ለተባለው ፈረንሳዊ ሚሲዮናውያን ለምን ወደ ኢትዮጵያ እንዲገቡ እንደማይፈቅዱ ሲናገሩ ፡—

አውሮፓ መንግሥታት የምሥራቅ ግዛቶ ችን ለመያዝ ሲሹ የሚጠቀሙበትን ታክ ቲክ አውቀዋለሁ ። መጀመሪያ ሚሲዮና ውያንን ይልካሉ ። እነሱን እንዲረዱ በማለት ቆንስላዎችን ይልካሉ ፤ በማከታተልም ቆን ስላዎችን እንዲረዱ በማለት ወታደሮች ይል ካሉ - - - እኔ እንደ ሒንዱስታን ገዥ (ራጃ) እንዲህ የሚቀለድብኝ አልምሰ ልህ - - ይህን ከማደርግ ከጦሩ ጋር ግንባር ለግንባር መግጠሙን እመርጣለሁ » - - -»[1] ብለዋል ።

ተስፋፊዎችና ቅኝ ገዥዎች ስውር የሆነ ፖለቲካ አላማቸውን ከግብ ለማድረስ የሚጠቀሙበትን ዘዴ አጼ ቴዎድሮስ በግ ልጽ የተረዱት ይመስላል ። ነገር ግን አፄ ቴዎድሮስም ሆኑ ተከታዮቻቸው በየጊዜው በሚነሱት የፊውዳል የሥልጣን ተቀናቃ ኞች ምክንያት ፣ የውጭ ወታደሮች ሰርገው ከመግባታቸውና ግዛትን ከመድፈራቸው በፊት ለመመከት ያደረጓቸው ሙከራዎች አጥጋቢ ሊሆኑ አልቻሉም ነበር ።

እነዚህ የቅኝ ግዛት ጥመኞች በሚሲዮ ናውያን ፊታውራሪነት ፣ በቆንስላዎች ጋሻ ጃግሬነትና ግልጽ በሆነ ወረራ ኢትዮጵያን ለመያዝ ከ1557 ጀምሮ ከፍተኛ ጥረት አድ ርገዋል ። የቀደምትነቱን ቦታ በመያዝ የወረራው በር ከፋች የሆኑት የኦቶማን ቱርኮች ነበሩ ። የመስፋፋት አላማውን በዓለም ላይ ለመዘርጋት አስቦ የነበረው የኦቶማን ቱርክ ፓሻ (መሪ) ኡትማን በቀይ ባህር አካባቢ ያሉትን አገሮች በቁጥጥሩ ሥር ሲያደርግ የኢትዮጵያን የባህር በር ከ1557 ጀምሮ እስከ አሥራ ዘጠነኛው ምእተ ዓመት አጋማሽ ከፊላዊ ሥልጣን (nominal authority) በመያዝ ሲቆጣጠር ቆይቷል ።

የኦቶማን መንግሥት ኃይል ሲዳከም አካባቢውን በተተኪው ለመያዝ የሞከረው በመሐመድ አሊ የተገነባው የግብጽ መን ግሥት ነበር ። የግብፅ ተስፋፊዎች እንደ ኦቶማን ቱርኮች በምጽዋ ወደብ ብቻ ሳይ ወሰኑ ወደ መሐል አገር ዘልቀው በመግባት ግዛት ለማስፋፋት ቆርጠው ተነሱ ። በዚህ ጊዜ አጼ ቴዎድሮስ ጀምረውት የነበረው ማእከላዊ መንግሥትን የማጠናከሩ ተግ ባር እየጎለበተ በመምጣቱ ወራሪው ኃይል እንዳሰበው ግዛቱን ለማስፋፋት ሳይችል ቀረ ። በዚህ መሠረት በ1875 እና በ1876 ጉንዳትና ጉራዕ ላይ በአጼ ዮሐንስ በሚመራው ጦር ተከታታይ ድል በመመ ታታቸው የወረራ እቅዳቸው ሊከሽፍ ችሏል ።

በ1880ዎቹ ዓመታት የኢጣሊያ ቅኝ ገዥዎች በሰሜን አፍሪካ ቅኝ ግዛት ለመ ያዝ ይጥሩ ጀመር ። ሆኖም ይህ የአፍሪካ ክፍል በጊዜው ተስማሚ ሆኖ ስላላገኙት አንድ የግል ኩባንያ ከአንድ የፊውዳል ገዥ አሰብ አካባቢ በገዛው መሬት ላይ ዓይናቸውን ማሳረፍ ግድ ሆነባቸው ።

ከዚህ በመነሳት በሱዳን የመሐዲ ንቅ ናቄ ካሰጋቸው እንግሊዞች ጋር የውስጥ ስምምነት በማድረግ በ1885 አካባቢ የም ጽዋን ወደብ ያዙ ። ይህ ድርጊት በኢትዮ ጵያውያን ዘንድ ከፍተኛ ተቃውሞ አስከ ትሎ ሁለቱም ወገኖች ጦርነት እስከማወጅ ደረጃ ተዳርሰው በ1887 ዶጋሊ ላይ በተደ ረገው ጦርነት ኢትዮጵያውያን ኢጣልያ ኖችን አሳፍረው መለሷቸው ።

አጼ ዮሐንስ በ1889 ከሞቱ በኋላ ዘው ዱን ለመያዝ በተደረገው ሽሚያ ከተለያዩ የፊውዳል ተቀናቃኞች መካከል ምኒልክ በአሸናፊነት ወጡ ። ከዘመነ መሳፍንት በኋላ ኢትዮጵያን በአንድ ጠንካራ ማእከላዊ የፊውዳል መንግሥት ሥር ለማስተዳደር በመቻሉ የውጭ ጠላቶችን ለመከላከል ቀድሞ ከነበረው ይበልጥ አመቺ ሁኔታ ሊፈጠር ቻለ ። ምኒልክም በአንድ በኩል ለአስተዳደራቸው ጠንካራ መሠረት ለመ ጣል ሲጥሩ ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ከጠላት ጋር ላለመጋጨት ሰላማዊ የሆነ የዲፕሎ ማቲክ ዘመቻ ማካሄድ ጀመሩ ። በመካከ ሉም በ1889 በኢጣሊያና በኢትዮጵያ መካ ከል የውጫሌ ውል ተፈረመ ። ይህ ውል በተለይም አንቀጽ 17 በኢጣልያንኛ ቋንቋ ትርጉም በተዘዋዋሪ መንገድ ኢትዮጵያን የኢጣልያ ቅኝ ግዛት የሚያደርግ ነበር ። የአንቀጹን አሻሚነትና የጠላትን መሠሪ ነት የተረዱት አጼ ምኒልክ በ1893 ውሉን መሠረዛቸውን ለኢጣልያ መንግሥት በግ ልጽ አስታወቁ ።

---

* በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ያለው የዘመን አቆጣጠር (እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር ተብሎ እስከአል ተጠቀሰ ድረስ) በአውሮፓውያን አቆጣጠር ነው ።

በሸፍጥ ኢትዮጵያን ለመያዝ ያልተሳካላቸው የኢጣልያ ቅኝ ገዥዎች በኃይል ከመጠቀም ሌላ አማራጭ በማጣታቸው ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ከፍተኛ የጦር ዝግጅት ማድረግ ቀጠሉ ። በማን አለብኝነት ግዛት ክልላቸውን በማስፋፋት የአሥመራና የሀማሴንን ሜዳማ ክፍል እስከ መረብ ወንዝ ድረስ ያለውን ግዛት ከመያዛቸውም በላይ ወደ መሐል አገር ዘልቀው ለመግባት በአክሱም አካባቢ ያንዣብቡ ጀመር ። የኢጣልያ ያልታሰበ አገርን የመውረስ ሙከራ ያሰጋቸው አፄ ምኒልክም የሁኔታውን አሳሳቢነት በመገንዘብ የበኩላቸውን ዝግጅት ማድረግ ቀጠሉ ።

የሁለቱ ተቃራኒ ወገኖች ቁርሾ እየተባባሰ ሄዶ የቋያው እሳት በመጋቢት 1, 1896 አድዋ ላይ ነደደ ። በዚህ ጊዜ መቶ ሺህ[2] ይሆናል ተብሎ በውጭ ታሪክ ፀሐፊዎች የተገመተው የኢትዮጵያ ጦር የኢጣልያንና የከሀዲ ተባባሪዎቻችን ጦር አይቀጡ ቅጣት በመቅጣት በጥቁር ዓለም ታይቶ የማይታወቀውን ድል ተጎናጸፈ ።



አድዋ ላይ የኢጣልያ ቅኝ ገዥነት ቅስም መሰበር በኢምፔሪያሊስት አገሮች አካባቢ ብዙ የፖለቲካ ውጣ ውረዶችን ከማስከተሉም በላይ ፣ ኃያላን የሚባሉ ሁሉ ኃይላቸው የቱን ያህል እንደሆነ ዞር ብለው እንዲያጤኑ አስገድዷቸዋል ። ከአድዋ ድል በኋላ ማንኛውም የኢጣልያ ተወላጅ አገሩ የተከናነበችውን ሀፍረትና ሽንፈት መበቀል እንዳለበት እየተነገረው ያድግ ጀመር ። የፋሺዝም ቀንደኛ መሪዎች የሆኑት እነ ሙሶሊኒም የዚህ ትውልድ ውጤቶችናቸው ።

የሙሶሊኒ የግዛት ግንባታ ፕሮግራም

የኢንዱስትሪ ካፒታሊዝም በመጀመሪያ በታላቋ ብሪታንያ በኋላም በሌሎች የአውሮፓ አገሮች በ19ኛው ምእተ ዓመት አጋማሽ ላይ ከፍተኛ እድገት በማሳየቱ የዚህን እድገት ግስጋሴ ለመጠበቅ የቅኝ ግዛት አስፈላጊነት በካፒታሊስት አገሮች ዘንድ እያደገ መጣ ። ለዚህ ስርአት ንግድ መናኸሪያ የሚሆኑ የንግድ ቦታዎችን በቅኝ ግዛቶች ውስጥ ማቋቋሙን የአውሮፓ ቅኝ ገዥዎች ተያያዙት ። በዚህ መሠረት የተጽእኖ ክልል (Sphere of Influence) ለመመሥረት በጊዜው ኃያላን ይባሉ የነበሩት እንግሊዝ ፣ ፈረንሳይና ጀርመን መሪነቱን ያዙ ። ፋሽስት ኢጣልያና ሚሊታሪስት ጃፓንም የነሱን ኮቴ በመከተል ወደ ውድድሩ ዓለም ብቅ አሉ ። በተለይም ፋሽስት ኢጣልያ በጊዜው የተጽእኖ ክልሏ አድርጋ ይዛቸው የነበሩት ሊቢያ ፣ አልባንያና ገሚስ የሱማሌ ግዛት ሲሆኑ ፣ እነዚህ «ግዛቶች ፣» በረሀማ በመሆናቸውና የተፈለገውን የኢንዱስትሪ ጥሬ ዕቃ ስለ ማያመርቱ ፋሽስት ኢጣልያ ፊቷን ወደ ሌላ ማዞር ግድ ሆነባት ።

ፋሺስት ኢጣልያ ኢትዮጵያን ቅኝ ግዛት አድርጋ ለመያዝ ከ1869 ጀምራ ያልተቆጠበ ጥረት አድርጋለች ። የመስፋፋት ምኞቷን ከግቡ ለማድረስ እንደ ሌሎች የአውሮፓ ቅኝ ገዥዎች ቀላል ሆኖ አላገኘችውም ። ለዚህም ምስክሩ በ1887 እና በ1896 ዶጋሊና አድዋ ላይ የደረሱባት ከፍተኛ ጥቃቶች ናቸው ። የኢጣልያ ፋሽስቶች የተከናነቡት የውርደት ሸማ ትምህርት ሊሆናቸው ስላልቻለ ፣ ከ1906 ጀምሮ ከፍተኛ የዲፕሎማቲክ ጥረትና የጦር ዝግጅት በማድረግ ኢትዮጵያን ለመውረር ቆርጠው ተነሱ ። ፋሽስት ኢጣሊያ ለምን ኢትዮጵያን ፈለገች?

የፋሺስት መሪዎች አላማቸው ተሳክቶ ኢትዮጵያን ቢይዙ ከማንም የቅኝ ገዥ

INFINIX HOT 8 | 13MP
AI TRIPLE CAMERA

ኃይል ጋር ስለማያጋጫቸውና ኢትዮጵያ ውስጥ አለ ተብሎ የተገመተው የተፈጥሮ ሀብት ስለአጓጓቸው ነበር ።

ይህን አላማቸውን ከግቡ ለማድረስ የፊታውራሪነቱን ቦታ የያዘው ቤኒቶ ሙሶሎኒ ነበር ።

ቤኒቶ ሙሶሊኒ በፋሽስት ርእዮተዓለም የተጠቀመና ፋሽዝምን በዓለም ለማራመድ ታጥቆ የተነሳ እምባገነን መሪ ነበር ። በ1920ዎቹ መጀመሪያ ዓመታት ላይ የፋሺስት መንግሥትን ከፍተኛ ሥልጣን የያዘው ሙሶሊኒ የፋሽስትን የመስፋፋት ፖሊሲ በአውሮፓና በቀረው ዓለም ለማሠራጨት ቆርጦ ተነሳ ። ሆኖም በወቅቱ በነበረው የአውሮፓ የኃይል 'ሚዛን አሰላለፍ ምክንያት በአውሮፓ ሊያደርግ ያቀደው ዓላማ ስላልተሳካለት የበቀል ፈላጊው ትውልድ የበኩር ልጅ የሆነው ሙሶሊኒ «የግዛት ግንባታውን» ወደ አፍሪካ ቀንድ በማዞር ከ1923 ጀምሮ ኢትዮጵያን ለመያዝ ከፍተኛ ዝግጅት ማድረጉን ቀጠለ ። ለወረራው መጀመር አብይ ምክንያት የሆነው ታህሣሥ 5 ቀን 1934 በኢጣልያ ጦርና ከእንግሊዞች ጋር የግጦሽ ቦታ ለመከለል ለሄደው የኢትዮጵያ ልዑካን አጃቢ ሆኖ በሄደው በጥቂት የኢትዮጵያ ጦር መካከል ወልወል ላይ የተደረገው ግጭት ነበር ።

እስከ 1925[3] የታተሙት ካርታዎች (ማፖች) እንደሚያመለክቱት ወልወል በግምት አንድ መቶ ኪሎ ሜትር ከኢጣልያ ሶማሌ (መጀርቲ) ጠረፍ ወደ ኢትዮጵያ ገባ ብሎ የሚገኝና 359 ያህል የውሀ ጉድጓዶች የሚገኙበት ቦታ ነው ። ነገር ግን ከ1929 ጀምሮ ግጭቱ እስከተፈጸመበት ድረስ ቁጥራቸው በውል የማይታወቅ የፋሽስት ወታደሮች ይዘዋወሩበት ነበር ።[4]

ሙሶሊኒ የግዛት ማስፋፋት ምኞቱን ከግቡ ለማድረስ መጀመሪያ ጎንደር ላይ በኢጣልን ቆንስላ ውስጥ ተመድበው ይሰሩ በነበሩ የኢጣልያ ሰላዮች ላይ ኢትዮጵያውያን አድርሰውት በነበረው ጉዳትና ኋላም ወልወል ላይ በተደረገው ግጭት በማሳበብ የጥፋት መልእክተኞቹን ወደ ኢትዮጵያ መላክ ጀመረ ።

የምዕራብ አገሮች ክህደትና የወረራው መከፈት

ኢትዮጵያን በተናጠል ሳይሆን በጋራ ለመቃረጥ የአሰቡት የፈረንሳይ ፣ የእንግሊዝና የኢጣልያ ኢምፔሪያሊስቶች በ1906 አንድ ውል ተፈራረሙ ። ይህም ኢትዮጵያ ውስጥ እንዲኖራቸው ያሰቡትን ጥቅም በጋራ ለማስከበር የሚያስችል ውል በመሆኑ በአድዋ ጦርነት ጊዜ ውርደትና ሽንፈት ለደረሰበት የኢጣልያ ፋሺዝም እንደ ታላቅ የዲፕሎማቲክ ድል የሚቆጠር ነበር። የእንግሊዝና የፈረንሣይ ኢምፔሪያሊስቶች ኢትዮጵያን እንደ ገፀ በረከት በመስጠት ለመጀመሪያ ጊዜ ኢትዮጵያ የኢጣልያን ቅኝ ግዛት እንድትሆን በመስማማታቸው ለወረራው ድጋፍ ሰጪ መሆናቸውን በገሃድ አስመስክረዋል ።

ኢትዮጵያን ሳያማክሩ ሶስቱ ኢምፔሪያሊስት አገሮች ያደረጉት ስምምነት የኢትዮጵያን ነጻነት በግልጽ እንደደፈሩ የሚያስቆጥራቸው ነው ። እስከ 1929 ኢትዮጵያን በተጽእኖ ክልል መቃረጥ አለብን የሚለው ሃሳባቸው ሳይለወጥ በመቆየቱ ፣ በተለይም የእንግሊዝና የፈረንሣይ ቡርዧዎች የናዚ ጀርመን የጦር ስጋት ስለነበረባቸው ለኢጣልያ ያደረጉት ድጋፍ ፋሺስት ኢጣልያ በ1935 ላደረገችው ወረራ የተለየ የማበረታቻ መንገድ ሊከፍትላት ችሏል ።

በዚህ የልብ ልብ ያገኘው ፋሺዝም የዓለምን አስተያየትና ኢትዮጵያ ያቀረበችውን የሰላም ጥሪ ከምንም ሳይቆጥር የእብሪት ወረራን በኢትዮጵያ ላይ ከፈተ ።

የኢጣልያ ፋሽስቶች ለጦርነቱ መጀመር የበኩላቸውን መሠረተቢስ የሆነ ሰበብ ቢደረድሩም ለወረራው መንስኤ የሆኑት አበይት ምክንያቶች ፣......

1. ፋሽስት ኢጣልያ በምዕራብ አውሮፓ በ1929 ገደማ ደርሶ ከነበረው ከፍተኛ የኢኮኖሚ ውድቀት ለማገገም ባለመቻሏ ከውድቀቷ ለመነሳት ተፈላጊ የሆኑትን የኢንዱስትሪ ጥሬ እቃዎችን በተቻለ ፍጥነት ከኢትዮጵያ ለመዝረፍ ፣

2. በኢኮኖሚው ውድቀት ሳቢያ የደረሰውን ከፍተኛ የሥራ አጥ ችግር ለማቃለል ዜጎቿን በወታደርነት ፣ በልማት ሥራና በሌሎች የሥራ መስኮች በኢትዮጵያ ለማሠማራት

3. ከሁሉም በላይ ኢትዮጵያን ቅኝ ግዛት አድርጋ በመያዝ ዜጐቿን ለዘለቄታው በኢትዮጵያ ለማስፈር ፣

4. ከአርባ ዓመት በፊት የኢጣልያ ተስፋፊዎች የደረሰባቸውን ሽንፈት ለመበቀልና ፣

5. ሙሶሊኒና ፋሺስት ተከታዮቹ የቀድሞ ሮማውያንን ዓለም አቀፋዊ «ታላቅነትና» የግዛት ስፋት መልሰን እናቋቁማለን በሚል የተነሱበት ቅዠት ነበር ።

አጼ ምኒልክ ካረፉ ከ1913 በኋላ የሥልጣን ተቀናቃኝ ፊውዳሎች ሰፊውን ሕዝብ በሃይማኖት ፣ በዘርና በጎሣ በመከፋፈልና በሕዝቡ መካከል የሃይማኖት መናናቅና ጥላቻ እንዲሰፍን በማድረጋቸው ለጠላት የመግቢያ ቀዳዳ ከፍተውለታል ።

በኢትዮጵያ የተከሰተውን የመከፋፈል አዝማሚያ በቅርብ ሆነው ይመለከቱ የነበሩት የኢጣልያ ፋሽስቶች የአሰቡት ዓላማ እንዲሰምር አርባ ቆንስላዎችን ስትራተጂ በሆነ የኢትዮጵያ ክፍሎች በማቋቋም ፊውዳሎችን ይበልጥ የመከፋፈሉን ዘመቻ ተያያዙት ። በተለይም በጎንደር ፣ በዶንጎሎ ፣ በወሎ ፣ በጎጃምና በአዜቡ ኦሮሞ[6] በቆንስላዎቻቸው አማካኝነት የሚካሄደውን ስለላና ሕዝቡን የመከፋፈሉን ተግባር ይበልጥ በማጠናከራቸው የጠላትን ጦር ቀድሞ ይመክታል ተብሎ የተገመተው ብዛት ያለው የዚህ ክፍል ጦር ተባብሮና ተጠናክሮ ወደ ጠላትን እንዳይመክት አደረጉ ። ይህን አስመልክቶ የሙሶሊኒ የጦር አበጋዝ የነበረው ማርሻል ኤሚሎ ዲ. ቦኖ ሲናገር ፣ «......መረዳት ያለብን ዋናው ቁም ነገር ይህ ነው...... ከወረራው ዋዜማ ጀምሮ በሃሳብ የመከፋፈል ምልክቶች (በኢትዮጵያውያን) ተከስተዋል ። ይህም ጠላታችንን 200,000 ያህል ጦር እንዳሳጣው እሙን ነው......።[7] ይህ አባባል ዓላማቸው የቱን ያህል እንደተሳካላቸው ሊያስገነዝበን ይችላል ።

ለአገር አንድነትና ነጻነት ደንቃራ የሆኑት አንዳንድ የፊውዳል አለቆች በፋሺስት ኢጣልያ ሰላዮች ቁጥጥር ሥር በመዋል በየአውራጃዎችና ወረዳዎች ለሚገኙ ተከታዮቻቸው ፀረ አንድነት ፕሮፓጋንዳ በመንዛት ፣ ከጌቶቻቸው የተመጸወቱትን የጦር መሣሪያ በማከፋፈልና ጉቦ በመስጠት የሕዝቡን ኃይል እንዲከፋፈል አድርገዋል ። የተጠናከረ ፀረ ፋሺስት ኃይል እንዳይመሠረት ለጠላት ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርገዋል ።

በዘመናዊ የጦር መሣሪያ የተጠናከረውን የጠላት ጦር ይመክታል የተባለው የኢትዮጵያ ጦር የተውጣጣው ከንጉሱ የቅርብ ረዳት ፊውዳሎች ፣ ከማእከላዊው መንግሥት ጦርና ከንጉሱ ቋሚ ጦር ብቻ ስለሆነ ይህ ጦር ቁጥሩ አነስተኛ ከመሆኑም በላይ በተፈጥሮ ካገኘው ልምድ በቀር ዘመናዊ የጦር ስልት ያልቀሰመ ነበር ። በትጥቅም ረገድ ኢትዮጵያ ቀደም ብላ ከአውሮፓ አገሮች ለመግዛት ጠይቃው የነበረውን የጦር መሣሪያ በተቀነባበረ የኢምፔሪያሊስቶች ሴራ ምክንያት ልታገኝ አልቻለችም ነበር ።[8]

ስለሆነም ባለው ኃይልና መሣሪያ ጠላትን ለመቋቋም የነበረው ዝግጅት የሚያመረቃ አልነበረም ። በጦር አዝማቾች መካከል የሀሳብ ግጭት ይታይ ስለነበር ከፊሎቹ ለምን የጠላት ጦር ሥር እስኪሰድ እንጠብቀዋለን አሁኑኑ ባለን ኃይል እንዋጋ ሲሉ የቀሩት ደግሞ በተለይም ወጣት አርበኞች አቅማችን የተወሰነ ስለሆነ በግንባር መግጠሙ የማያዋጣ በመሆኑ የሽምቅ ውጊያ ማካሄድ ይኖርብናል ይሉ ነበር ። በዚህ መካከል ደግሞ ንጉሡ ሁለቱንም አስተያየቶች ባለመቀበል ሁኔታውን ለዓለም ማኅበር ማሳወቅ አለብን በማለት የማፈግፈግ ዝንባሌ ያሳይ ነበር ። ይልቁንም ሁኔታውን ለጠላት አመቺ በማድረግ ከጠላት ጋር የተፋጠጠውን የኢትዮጵያ ጦር ሰላሳ ኪሎ ሜትር እንዲያፈገፍግና የዓለም ማኅበርን ውሳኔ እንዲጠባበቅ አደረገ ። ይህም ጠላት በወታደራዊ ዝግጅቱ እንዲገፋና አመቺ ቦታዎችን ቀድሞ እንዲይዝ አጋጣሚ ሁኔታን ፈጠረለት ።

ምንም እንኳን በጊዜው ኃያላን የሚባሉት አገሮችና አብዛኛው የዓለም መንግ

INFINIX HOT 8 | 13MP
AI TRIPLE CAMERA

ሥታት ማህበር አባላት ኢጣልያ ላደረገችው ወረራ አፋዊ ተቃውሞ ቢያሰሙም ተግባራዊ የሆነ ድርጊት አልፈፀሙም ። ኢጣልያ ላደረገችው ወረራ የንግድ ማዕቀብ እንዲያደረግባት ቢደነገግም ለወረራው አስፈላጊ የሆነው የነዳጅ ዘይት ከተዘረዘሩት የንግድ እቃዎች ውስጥ ባለመግባቱ ፋሽስት ኢጣልያን ከወረራዋ ሊገታት አልቻለም ። በሌላ በኩል ደግሞ የእንግሊዝና የፈረንሣይ ገዥ መደብ አባላት ኢጣልያ ከናዚ ጀርመን ጋር ኃይሏን ታስተባብራለች የሚል ስጋት ስላደረባቸው በኢጣልያ ላይ ሁለቱ አገሮች ይሰነዝሩት የነበረው ተቃውሞ የይስሙላ ያህል ነበር ። እነዚህን ሁኔታዎች በሚገባ ያላጤነው ንጉሥ ወረራውን በአለው ኃይል እንደመቋቋም ፈንታ እጃችንን አጣጥፈን ተቀምጠን የዓለም ማሕበርን ውሳኔ መጠበቅ አለብን ማለቱ የአገር መሪነት ኃላፊነትን ምንነት ያልተገነዘበ መሆኑን ያሳያናል ።

ወታደራዊ ፍልሚያ

የመጀመሪያው የፋሽስት ጦር በመስከረም ወር 1927 (እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር) በጄኔራል ዴ ቦኖ እየተመራ ከኤርትራ ተነስቶ ወደ አድዋ ገሠገሠ ። በምሥራቅም በኩል በጄኔራል ግራዚያኒ የሚመራው ጦር በ፣ ሌ በኩል በምሥራቃዊ ደቡብ ኢትዮጵያዊ ጦር ከፈተ ።

የሀገሩን ነጻነትና አንድነት ለመጠበቅ በተለያዩ ወቅቶችና ጊዜያት ጠላቶቹን ድል እየነሳ የቆየው የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ኃይሉን የሚያስተባብርና ትጥቁን እንዲያዘጋጅ የሚያደርገው አመራር ባያገኝም ባለፈው ታሪኩ የነበረውን ጀግንነት ወኔና የነጻነት ፍቅር ይዞ ወደ ጦር ግንባር አመራ ።

ቢሆንም የፋሺስት ጦር በብዙ ጊዜ ዝግጅት የዳበረ ነበር ። ቀደም ሲል በሰሜን ኢትዮጵያ በኤርትራ ክፍለ ሀገር ውስጥ የቅኝ ግዛት አስተዳዳሪ የነበረውና በመጀመሪያው ወታደራዊ ፍልሚያ ወቅት የሰሜኑን የፋሺስቶችን ጦር የመራው ጄኔራል ዲ ቦኖ ሦስት ዲቪዝዮን ጦር ወደ ኤርትራ እንደላከለት ቢጠይቅ ሙሶሊኒ በብዛት ትችገር እንደሆነ እንጂ ለሶስቱስ ዲቪዝዮን አትጨነቅ ፤ አምስት ዲቪዝዮን ከመደበኛው ጦርናአምስት ዲቪዝዮን ከባለጥቁር ሸሚዝ ለባሹ ልዩ የፋሺስት ጦር ይላክልሀል ባለው መሠረት በሚያዝያ ወር 1935 የመጀመሪያው ባታሊዮን ጦር ምፅዋ ደረሰ ። በሚቀጥሉት ተከታታይ ወሮች አንድ ዲቪዝዮን ጦርና መጠነኛ ባለጥቁር ሸሚዝ ለባሽ ባታሊዮኖች ለሱማሌ የቅኝ ግዛት አስተዳዳሪ ለነበረው ለጄኔራል ግራዚያኒ ሲላኩ በሰሜን ጦር ግንባር የፋሺስቶች ጦር ብዛት (በሁለት መቶ ሺህ) ሰው ኃይል የተገነባ ፤ በሰባት ሺህ መኮንኖች የሚመራ ፤ (ስድስት ሺህ) መትረየስ ፤ (ሰባት መቶ) የተለያዩ መድፎች ፤ (አንድ መቶ ሃምሳ) ታንኮችና ተዋጊ የጦር አይሮፕላኖች የተጠናከረ ነበር ።[9] በአንድ ወቅት አንድ የሙሶሊኒ የጦር ፀሐፊ ባቀረበው ዘገባ ከአንድ ክፍለ ሀገር ከኔፓልስ ብቻ ኢጣሊያን ለወረራ ከላከችው ጦር (አንድ መቶ ሺህ) ወታደሮች ፤ (አንድሚሊዮን) ልዩ ልዩ የጦር ዕቃዎችና ቁጥር ስፍር የሌለው ጥይት ፤ (ሁለት መቶ) መድፎች ፤ (ስድስት ሺህ) በቅሎዎችና (ሁለት ሺህ ሦስት መቶ) የጦርና የስንቅ የጭነት መኪናዎች ወደ ጦር ግንባር በመርከብ እንደተላኩ አስታውቋል ።[10] ይህ ባለብዙ ብረት ለበስ ጦር በዓይነትም ሆነ በጥራት እንደዚህ ሊጐለብትና ሊዳብር የቻለው ያለ ምክንያት አልነበረም።ኢጣሊያን በጊዜው በነበራት የኢንዱስትሪ ፤ የቴክኖሎጂና የሳይንስ ዕድገት ውጤትና አብዛኛው የኢጣሊያን ኢንዱስትሪዎች ለዚሁ ለጦር መሣሪያ ምርት መላው ኃይላቸውን በማስተባበር አዳዲስና ልዩ ልዩ መሣሪያዎችን ከማውጣቸውም ሌላ በየጊዜው ለምርቱ ጥራትና ብዛት ድጋፍ በመስጠታቸው ነበር ። ከዚህም ባሻገር የፋሺስት የጦር አውሮፕላኖች በሕግ በተከለከለ የጋዝ መርዝ ጪስ የተደገፉ መሆናቸው ሌላው የጦር ዝግጅት ገጽታቸው ነበር ። በዚህ ዓይነት የዕድገት ደረጃ የደረሰ ኅብረተሰብ በሌላው መልኩ ከጦር መሣሪያ ብዛትና ጥራት ባሻገር የሠራዊቱ የአሠለጣጠንና የአደረጃጀት ሁኔታዎች ከኅብረተሰቡ የዕድገት ደረጃ ጋር አብሮ የተያያዘና መስተጋብርም ያለው ነው ። በዚህ ረገድ የፋሺስት ጦር ሀገርን ለመከላከል ብቻ የሚሰለጥን ሳይሆን ለማጥቃት ወደ ባህር ማዶ የሚላክና ለወረራ የተዘጋጀ ነበር ። ስለዚህም ፋሽስቶች ለአሥራ ሦስት ዓመታት ያህል የኢጣሊያንን ሕዝብ አዲስ ዓለም ለማውረስ ፤ ከችግሩ ለማላቀቅና የብሔረተኛ ስሜቱን ለማርካት ባደረጉት ፕሮፓጋንዳና ቅስቀሳ ባገኙትም ተቀባይነት በወታደራዊ አሰለጣጠናቸው

የጥፋት መልዕክተኞች እንዲሆኑ አድርጓ
ቸዋል ።

በአንጻሩ የወገን ጦር ከጀግንነቱና ከወ
ኔው በስተቀር ከዚህ ዓይነቱ ዘመናዊ ፣ ኃያ
ልና የዳበረ ጦር ጋር ለመፋለም በአመራር
ያልታደለ በመሆኑ ያልተዘጋጀም ያልዳበ
ረም ነበር ። ለውነታውና ለአባባሉ ብዙ
ምክንያቶችን ማቅረብ ቢያስፈልግም ፣ መ
ሠረታዊ ገጽታው ግን ሀገሪቱ ከነበረችበት
ኋላቀር ፊውዳላዊ የኢኮኖሚ ስልተምርት
ዕድገት የተንፀባረቀ ይፋዊ ገጽታው ነው ።
ይህ ዓይነቱ ሥርዓት እንኳንስ የጦሩን ኃይል
ማዳበሩና ማዘጋጀቱ ቀርቶ የሚታዩትን
የኅብረተሰቡን ማኅበራዊ ችግሮች የማይ
ፈታና በተለያዩ ጦር አበጋዞች የተከፋፈለና
በውስጣቸውም የሥልጣን ሽኩቻ የሚበ
ዛበት ማዕከላዊነት የሌለው ደካማ ፊው
ዳላዊ መንግሥት ነበር ። የጦሩም አቋም
ቢሆን ቋሚነት የሌለው በአደጋ ጊዜ ብቻ
በክተትና በመልእክት ጥሪ የሚሰለፍ ፣ ስን
ቅና ትጥቅ ያላሟላ ኃይል ነበር ። የአሰለጣ
ጠኑም ፣ የዲስፕሊኑም ጉዳይ ከዚሁ የዕድ
ገት ደረጃው ጋር የተያያዘ በመሆኑ ፣ ከተ
ደራጀና ካኅለበተ ጦር ጋር በሚደረጉ ፊል
ሚያዎች ተጠቂ መሆኑ ግልጽ ነው ። በዚህ
ረገድ ፋሽስቶች ለወረራ ማንኛውንም ዝግ
ጅት አድርገው ባጠናቀቁበት ወቅት የኢት
ዮጵያ የገበሬ ሠራዊት በእጁ ከነበረው
ኋራዴና ጋሻ ሌላ መጠነኛ ጊዜው ያለፈባ
ቸው የጦር መሣሪያዎች በመያዝ ጠላቱን
ለመቋቋም ተነሳ ።

ከዚህ ኃይል ውስጥ በድርጅትና በት
ጥቅ የዳበረው የንጉሡ ትንሽ የክብር ዘብ
ወታደሮችና በሆለታ ጦር አካዳሚ የሠለ
ጠኑ የጦር መኮንኖች ካልሆኑ በስተቀር ሌ
ላው ጦር ስንቅ አልባና ለመደራጀትም ሆነ
ለመንቀሳቀስ ብዙ ጊዜንና ድርጅትን የሚ
ጠይቅ ነበር ። በተለይም ከዚህ ጋር ተያይዞ
መታየት የሚገባው በየክፍለ ሀገራቱ ያሉ
ትን የፊውዳል ገዥዎች በአንድ ላይ ቀስ
ቅሶና አስተባብሮ ጦራቸውን ወደ ጦር ግን
ባር እንዲልኩ ማድረጉ ገና ጦርነቱ ከመጀ
መሩ በፊት ጀምሮ ያጋጠመ ችግር ነው ።
አንዳንድ ቀንደኛ የፊውዳል መሪዎች ከማዕ
ከላዊው የፊውዳል መንግሥት አስተዳደር
ጋር ባላቸው የሥልጣን ቅራኔ ፣ የርስ በርስ
የሥልጣን ግጭቶችና ፋሽስቶች ባደረጉላ
ቸው ፀረ ማዕከላዊ የፊውዳል አስተዳደር
ፕሮፓጋንዳና ቅስቀሳ በአንዳንድ ቦታዎች
ሰፊው የገበሬ ጦር በጠላቱ ላይ እንዳይዘ
ምት ማድረጋቸውና ራሳቸውም በተለያዩ
መንገዶች ለጠላት አገልጋይ በመሆናቸው
የጦሩን ዝግጅት ድክመት ከሰጡት ምክን
ያቶች አንዱ ነበር ። በተጨማሪም በጊዜው
የዓለምን የዲፕሎማሲ ግንኙነት ያራምዱ
የነበሩ ኃይሎች በተለይም የእንግሊዝና የፈ
ረንሳይ መንግሥት በኢትዮጵያ ውስጥ የራሳ
ቸውን ጥቅም ለማስጠበቅ የሚያስችልና
በዓለም አቀፍ ደረጃም በጊዜው በጀርመን
የሂትለርን ናዚዝም ከሚቃወሙት ኃይሎች
ከፈረንሣይና ከእንግሊዝ ጎን ሞሶሎኒ እንደ
ደሚሰለፍ ባገኙት ቃል መሠረት የጦር መ
ሣሪያዎች ለኢትዮጵያ እንዳይሸጥላት ማድ
ረጋቸው ይታወሳል ። በመሆኑም የእንግ
ሊዝ መንግሥት ኢትዮጵያ በግዥም ሆነ
በስጦታ የጦር መሣሪያ እንዳታገኝ ደነገገ ።

ፈረንሣይም ቀደም ሲል ከኢትዮጵያ
ጋር በተዋዋለችው መሠረት በሸያጭ የተ
ገኙትን መሣሪያዎች ከጂቡቲ ወደብ እንዳ
ይንቀሳቀሱ አደረገች ። በዚህም ኢትዮጵያ
ያለአንዳች ረዳትና ትብብር ብቻዋን ለግፍ
ወረራ ተጋለጠች ።

በሰሜን ፤ እንደዚሁም በምሥራቅና በደ
ቡብ ጦር ግንባር በተከፈተውና ለሰባት
ተከታታይ ወሮች ያህል የቆየው የፋሽስት
ጦር የመጀመሪያውን የጦር ፍልሚያ ያደረ
ገው በሰሜኑ ግንባር በተንቤን ነበር ።
በዚህ ጦርነት ጠላት ባለ 36 ባታሊዮን
ያለው ሁለት ክፍለ ጦር ሲያሰልፍ ወገን
ከ20 እስከ 40 ሺህ ጦር እንዳሰለፈ ይነገ
ራል ።[11] ምንም እንኳ የፋሽስት ጦር በትጥቅ
የዳበረ ሆኖ የበላይነት ቢኖረውም የወገን
ጦር ከመጀመሪያው ውጊያ ከተነሳበት ሰዓት
ጀምሮ በቆራጥነት ፤ በጀግንነትና በጨበጣ
ውጊያ በጠላቱ ላይ ታይቶ ያልታወቀ የጦር
ትርኢት እንዳካሄደ የፋሽስቶቹ ጦር አዝ
ማች የነበረው ፔትሮ ባዶሊዮ ባቀረበው
ዘገባ ያረጋገጠው ነው ። አዛማቹ እንደገለ
ጸው ከ60 በላይ የጦር መኰንኖች ፣ 605 የኢ
የኢጣሊያን ወታደሮችና 417 የቅጥር ወታ
ደሮች እንዳለቁባቸው ገልጿል ።[12]

ከተንቤን ጦርነት በኋላ የወገን ጦር
በሦስት አቅጣጫዎች ማለትም በእንደርታ
በኩል ሰማኒያ ሺህ ጦር ፣ በተንቤን ሰላሳ
ሺህ ፤ በሽሬ አርባ ሺህ ጦር አሰለፈ ። የፋሽ

INFINIX HOT 8 | 13MP
AI TRIPLE CAMERA

ስት ጦርም የመጀመሪያውን አራት ዲቪዚ
ዮን ባለአርባ ባታሊዮን ጦር ወደ ደቡብ
መቀሌ ፥ ሁለተኛውን ባለ 44 ባታሊዮን
ጦር በአድዋና በአክሱም አካባቢ በሚገኙ
ቦታዎች ፥ ሦስተኛው ክፍል ባለ 29 ባታ
ሊዮን ተከላካይ ጦር በተንቤን አቅጣጫ
በኩል አሰማራ ።

ከዚህ በኋላ የፋሽስት ጦርና የወገን ጦር
ወሣኝ የሆኑ ጦርነቶችን በእንደርታ ፥ በሽሬ
በአሸንጌና በማይጨው አካሂዷል ። በሽሬ
ጦርነት የወገን ጦር በጠላት እንደተነገረው
63 የጦር መኰንኖችንና 894 የኢጣሊያን
ወታደሮችን ደምስሷል።[13] በውጊያው ወቅት
ከ80 ሺህ ቶንስ በላይ ፈንጅዎች ከአየር በወ
ገን ላይ ስለተጣለበት ብዙ ጉዳት ደርሷል ።
በአሸንጌም ጦርነት ወቅት ጠላት 68 የጦ
ር መኰንኖች 332 ወታደሮችና 873
ቅጥር ወታደሮች እንዳለቁበት አረጋ
ግጧል ።[14] በተጨማሪም የዚህን የአሸን
ጌን ጦርነት የተከታተለ አንድ ኢጣሊያዊ
እንደጻፈው ፋሽስቶች 73 ቶንስ ፈንጅዎ
ችን በአየር በወገን ጦር ላይ ከማዝነባቸ
ውም ሌላ የፋሽስት የጦር አይሮፕላኖች
የመርዝ ጪስ በመበተን ሕፃናትን፥ሽማግሌ
ዎችንና እንስሳትን አቃጥለው ፈጅተዋ
ቸዋል ።[15] ቢሆንም ሰፊው የኢትዮጵያ
ሕዝብ በዚህ ወረራ እስከአፍንጫው ድረስ
የታጠቀውን የፋሽስት ጦር በማይበገረው
ጀግንነቱና ድፍረቱ ተቋቁሞታል ።

ነገር ግን ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት የፊ
ውዳል ፖለቲካ ካስከተላቸው ኋላቀር የሆነ
ሶሽዮኢኮኖሚ ስርዓት ከወለዳቸው ድክ
መቶች ሌላ የንጉሡ የታክቲክና የስትራቴጂ
ስህተቶች ጦሩን ለጥቃት አጋልጠውታል ።

ይህ እውነታ በኢትዮጵያውያን አንደ
በት በየጊዜው የተገለጸ ቢሆንም በጠላቶቻ
ችንም የተነገረ ምስክርነት ያለው ሐቅ
ነው ። «እንደሀበሻ ጦር ብዛትና እንደስ
ርጭቱ፤እንደ ጀግንነቱና እንደወኔው ግፊት
በተፈለገው ጊዜ ለማጥቃትም ሆነ ለመከ
ላከል የሚያንቀሳቅሰው ጥሩ መሪዎች ቢኖ
ሩት የማይበገር ጦር ነው ፤»[16] ሲሉ ቃላ
ቸውን ሰጥተዋል ። ነገር ግን ባዶሊዮ እንዳ
ስተዋለው የአቢሲኒያ ጦር መሪ አልባ ነበር።
የአብሲኒያ የጦር አዛዦችና የፊውዳል አበጋ
ዞች ፊት ለፊት ካለው ጠላት ይልቅ ከጎና
ቸው ወይም ከኋላቸው ያለውን ጓደኞቻ
ቸውን ከመፍራት የተነሳ መላውን ጦራቸ
ውን በትግል ሜዳው ከማሰለፍ የተቆጠቡና
የራሳቸውን ጥቅምና ክልል ጠባቂዎችና
አጠናካሪዎች ነበሩ ።[17] ሲል አረጋግጧል ።

ይህ ግንዛቤ የሚያመለክተን የፊውዳል
የጦር አበጋዞች ምን ያህል አለመተማመን
በመሀከላቸው እንዳለና የቱን ያህል የስል
ጣንና የግዛት ሽኩቻ እንደሚያካሂዱ ፤
ይኸውም ገጽታቸው በጦር ሜዳም ጭምር
መንጸባረቁን ከማሳየቱም ሌላ ኃይልን አስ
ተባብሮ ጠላትን ለመምታት ባላቸው የስ
ልት አቀነባበርና አስተዋጽኦ ምን ያህል
ኋላቀር እንደነበሩ ያስገነዝበናል ። ለዚህ
ጥሩ ምሣሌ የሚሆነው የራስ ካሣ ጦር በፋሽ
ስቶች ጦር ሲጠቃና ማፈግፈግና መበተን
ሲጀምር ራስ ካሣ የራስ ሙሉጌታን የኃይል
ርዳታ በጠየቁበት ጊዜ ራስ ሙሉጌታ ስም
ተው እንዳልሰሙ ፥የዝሆን ጆሮ ይስጠኝ
በማለት የራስ ካሣንም ጥያቄ ሆነ የንጉሱ
ንም ትእዛዝ ያልተቀበሉበት ወቅት እንደ
ነበረ ታሪክ ያስታውሳል ።

የፊውዳል ገዥዎች ከአመራር ድክመ
ታቸው ፥ ከሥልጣን ጭቅጭቅና ከራስ ወዳ
ድነታቸው በተጨማሪ ሰፊውን ሕዝብ በማ
ወናበድና ከትግል ሜዳ በመክዳት ለፋሽስ
ቶች በአገልጋይነት እጃቸውን የሰጡም ያጎ
በደዱም አያሌዎች ናቸው ። የጎጃሙ ራስ
ኃይሉና እነራስ ጌታቸው ፥ ደጃች መንገሻ
ውቤና እነራስ ኃይለሥላሴ ጉግሣ...... ወዘተ
ከከሀዲዎች መካከል ነበሩ ።

ከሁሉም በላይ ደግሞ የፊውዳሎቹ የበ
ላይ አዛዥ የነበሩት ንጉሡ ገና ከአዲስ አበባ
ደሴ ከዚያም ወደኮረም ሳይንቃንቁ ጦሩ
ስንቁ ሳያልቅበትና የትግል ወኔው ሳይበር
ድበት ጦርነቱን በአጥቂነት እንዲጀመር
በተለያዩ የጦር ግንባሮች ፈቃድ እንዲ
ሰጠው ቢጠይቅ ንጉሡ ከደሴው ቤተ
መንግሥታቸው በመሆን ጦሩ በያለበት
ሆኖ እንዲከላከልና እንዲጠባበቅ እንጂ
በምንም ዓይነት ጦርነት እንዳይጀምር ትእ
ዛዝ ማስተላለፋቸውን[18] የፋሽስቶች የጦር
መሪ የነበረው ባዶሊዮ ገልጿል ።

ለዚህም ነበር አብዛኛው ጦር ለረሀብና
ለችግር የተጋለጠው ። በጦርነቶች ታሪኮች
ስልት ረገድም ቢሆን ይህ ዓይነቱ ስህተት
ሽንፈትን እንጂ ድልን አስከትሎ አያው

ቅም ። ምክንያቱም የዘመተ ጦር ስንቁ ካለቀ
በት ፤ ወኔው ከበረደና ለጠላቱ መዘጋጀትና
መደራጀት ጊዜና ፋታን ከሰጠ ውሎ አድሮ
መዳከሙ አይቀርም ። በመሆኑም አስቀድሞ
በረሀብና በችግር ቀጥሎም በጠላት አጥቂ
ነት በአውላላ ሜዳና በየፈፋው ላይ የተንጠ
ለጠለው የኢትዮጵያ ሠራዊት የቦንብ መ
ርዝ ጢስ ወረደበት ።

ስለዚህም በመጀመሪያ በአመራር ድክ
መትና በእቅድ አወጣጥ በኋላም በስንቅ
ማነስ በረሀብና በቸነፈር፤በመጨረሻም በፋ
ሽስቶች የተደጋገመ ከአየር በወረደ የጋዝ
መርዝ ጢስ የተዳከመው ሠራዊት ምንም
እንኳን በየግንባሩ ጀግንነቱን ለጠላቱ ቢያ
ስመሰክርም ወደኋላ ማፈግፈግና በየአቅ
ጣጫው መበተን ግዴታ ሆነበት ። ከመበ
ተንና ከሞት የተረፈው ጥቂት ጦር ከንጉሱ
ጋር አብሮ ከዘመተውና በቆቦና በማይጨው
መካከል ከሠፈረው ጦር ጋር በመደባለቅ
የመጨረሻውን የሰሜን ውጊያውን በማይ
ጨው አደረገ ። በዚህ ወጣ ገባና ለጦርነት
ስልት አመቺ ባልሆነ ቦታ ወገን ከ30 እስከ
50 ሺህ ጦር ባለስድስት ባታሊዮን እግረኛ
ጦርና ፣ አንድ ባታሊዮን መድፈኛ ጦር በማ
ሰለፍ በከፍተኛ ሞራልና በጀግንነት በጠላቱ
ላይ ከፍተኛ ጉዳትን ካደረሰ በኋላ ሊቋቋ
መው ባልቻለው የአየር ቦንብ ውጊያና የጋዝ
መርዝ ጢስ ግንባሩን እንዲለቅ ተገደደ ።

ለኃይለሥላሴና በአካባቢው ለተሰለፉ
የቤተ መንግሥት ባለሟሎችና ተከታዮች እ
ነዚህ ወሣኝ የነበሩት የተንቤን፣ የአሸንጌና
የማይጨው ጦርነቶች ለኢትዮጵያ ነፃነትና
አንድነት የመጨረሻ ቀን ሆኖ ታያቸው ።
ስለዚህ እራስን ማዳን ተቀዳሚ ተግባራቸው
አድርገው በመያዝ አስፈላጊውን የሽሽት
ዝግጅት ሁሉ ጀመሩ ። የማይጨው ጦርነት
በተካሄደ በወሩ ጠላት አዲስ አበባን ከመ
ያዙ በፊት አዲስ አበባ ገስግሰው ገቡ ።
አዲስ አበባ በገቡ በማግሥቱ ሚያዝያ 23
ቀን 1928 (እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር)
ከሌሊቱ በአምስት ሰዓት የቤተ መንግሥት
ሀብታቸውን ፤ልጆቻቸውንና የልጅ ልጆቻ
ቸውን እንዲሁም የቅርብ ባለሟሎቻቸ
ውን በባቡር አሳፍረው በጅቡቲ በኩል
ወደ እንግሊዝ ሀገር ሸሹ ።

ነገር ግን የጠላት ወደ መሀል ሀገር
መግባትና የንጉሱ መሸሽ ለኢትዮጵያ
አርበኞች ለወጣቱ ለሽማግሌውና ለሴቱ
የመደናገጥን፣ ፣ የመሸሽ ወይም የመሰደድን
ሁኔታ አላስከተለም ። እንዲያውም አንዱ
የትግል ምዕራፍ ተዘግቶ ሌላው መራራና
ረጅም የትግል ምዕራፍ የተከፈተበት የታ
ሪክ ወቅት ነበር ። ይህ ዓይነቱ ትግል እንደ
ቀድሞው ጠላትን ፊት ለፊት በመግጠም
ሳይሆን በልዩ ብልሀትና ዘዴ ፣ በተለያየ የት
ግል ስልት ማለትም በሽምቅ ውጊያ ለሕዝ
ባዊ አመጽና ጦርነት የሚያዘጋጅ ጊዜ
ነበር ።

የአምስቱ ዓመታት የአርበኞች ትግል ገጽታ

ፋሽስቶች የኢትዮጵያ ሕዝብ ሰጥ ለጥ
ብሎ ይገዛል ብለው ያሰቡት የተለዩ ሆኖ
አገኙት ። የኢጣሊያን የቅኝ አገዛዝ ፖሊሲ
በተለይም የፋሽስቶች አስተዳደር የሌላውን
ባሕል በመናቅ ፣ በዘረኝነትና በማን አለብኝ
ነት እብሪት የተመሠረተ ነበር ። በዚህም
ምክንያት መኖሪያ ቤቶችን ማቃጠል ፣ ከብ
ቶችን መዝረፍ ፣ ምርትን ማቃጠልና የተለ
ያዩ የንብረት ዝርፊያዎችን ማካሄድ የፋሽ
ስቶች የዕለት ተዕለት ሥራቸው ሆነ።የዚሁ
የግፍ ጭፍጨፋ፣የጭቆናና የግድያ ውጤት
የሕዝቡን አመጽ ይበልጥ አጠናከረው ። በ
መሆኑም የኢትዮጵያን ሕዝብ የታጋይነ
ትና የነፃነት ወዳድነትን የተገነዘበው የፋ
ሽስቶች መንግሥት መሪ ቤንቶ ሙሶሊኒ ፣
የቅኝ ግዛት አማካሪዎቹና እንዲሁም የኢጣ
ሊያን ኅብረተሰብ ኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን
የነፃነት ንቅናቄ ለማጥፋት ቀላል ጉዳይ
እንደማይሆን በግልጽ ተረድተዋል ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዛኛው ገበሬ
በመሆኑ የምርቱን ሥራ በአንድ በኩል የነ
ፃነቱን ትግል በሌላ በኩል አካሂዷል ። ስለ
ሆነም አጠቃላይ የትግሉን ስፋት ፣ ስርጭ
ትና እንቅስቃሴ ከነተጨባጭ ማስረጃዎቹ
ለማቅረብ ብዙ ጽሑፎችንና ጥናቶችን
የሚጠይቅ ቢሆንም ዋና ዋናዎቹን ግን
ባጭሩ እንመለከታለን ።

ዛሬ አንዳንድ የኢትዮጵያን አርበ
ኞች የትግል ታሪክ የገመገሙ የታሪክ ፀሐ
ፊዎች እንዳመለከቱት አንዳንድ አርበኞች
የሚዋጉት በአጠቃላይ የሀገሪቱን ነፃነት

በሚመለከት ሳይሆን አካባቢያቸውን ለመከ
ላከል ብቻ ሲታገሉ ሌሎቹ ከንጉሱ ጋር
የቅርብ ግንኙነት የነበራቸው ንጉሱን ለማ
ስመለስ ሲዋጉ ፣ የወጣት ክፍል አርበኞች
በተለይም የሆለታ የጦር አካዳሚ ወታደ
ሮችን ያቀፈው ንቅናቄ ትግሉ ሀገር አቀፍ
እንዲሆን ብዙ ጥረት አድርጓል ። ምንም
እንኳን እነዚህ የአመለካከት ልዩነቶች ፣
የሀሣብ መከፋፈልና የአካባቢ የፊውዳል
ገዥዎች የሥልጣን ሽኩቻዎች አልፈው አል
ፈው በየጊዜው ቢከሰቱም ሰፊው የኢትዮ
ጵያ ሕዝብ ነፃነቱንና አንድነቱን ለማስ
መለስ ለአምስት ዓመታት ያህል ያልተቋ
ረጠ ትግል አካሂዷል ።

የፋሽስት ጦር ኢትዮጵያ ውስጥ ይደረግ
የነበረውን የአርነት እንቅስቃሴ በኃይልና
በጭፍጨፋ ለማፈን ያላደረገው ጥረት አል
ነበረም ። ግራዚያኒ በምዕራባዊ ኢትዮጵያ
ውስጥ ይንቀሳቀስ የነበረውን በጥቁር አን
በሳ ወጣት አርበኞች የተገነባውን ኃይል
ለማውደም ቆርጦ ተነሳ ። ይህ የአርበኞች
ኃይል በሆለታ ጦር አካዳሚ መኰንኖች መ
ሪነት ማለትም በሌተና ኰሎኔል ክፍሌ
ነሲቡ በሌ/ኰሎኔል በላይ ሀይለአብና በሌ
ተና ኰሎኔል ከተማ በሻህ የሚመራ 300
ወታደሮችና ዘመናዊ ትጥቅ የያዘው ኃይል
ነበር ። ግራዚያኒ ሰኔ 26 ቀን 1936 ሦ
ስት የጦር አውሮፕላኖች ከ13 የጦር መኰ
ንኖችና ከሦስት ሺህ የማሪያትሬዛ የ
መዳሊያና አዲስ ወታደሮችን በአካ
ባቢው ለማስልጠን የሚረዳ ብር ወደ ነቀ
ምት ላከ ። በዚሁ ምሽት የተላኩት አውሮ
ፕላኖች በወጣት አርበኞች ቦናያ ከሚባለው
ቦታ በእሳት ጋዩ ። ከተላከውም ጦር አሥራ
ሁለቱ በጥይት ተደብድበው ሞቱ[19] ። ፋሽ
ስቶች ምዕራብ ኢትዮጵያን ለመያዝ የነበ
ራቸው ተስፋ ከመክሸፋም በላይ ኢትዮ
ጵያን በቁጥጥሬ አድርጌያለሁ በማለት ለ
ዓለም ኅብረተሰብ የሚያናፍሱትን የፕሮፓ
ጋንዳ ጦርነት አከሸፈባቸው ። በዚህም
በወጣት አርበኞች የሚመራው አርበኛ ምዕ
ራባዊ ኢትዮጵያን በተለይም የወለጋን አካ
ባቢ ፣ የጨንለቆን ፣ የጎዳዩ ፣ የጉደርንና የአ
ምቦን ወዘተ...... ቦታዎች በቁጥጥሩ ሥር
በማድረግና የትግል ዕድገቱን እየጨመረ ፤

ኧረ በለው አትለውም ወይ
ጥቁር አንበሳ አይደለህም ወይ
ያድዋ ጀግኖች ቅርስ አይደለህም ወይ
ጥንታዊ ጀግና አይደለህም ወይ
ለዚህ ላታላይ ትሰጋለህ ወይ ፤

በማለት መላው ሕዝብ በፋሽስቶች ላይ እን
ዲያምጽና እንዲዘምት ቅስቀሳውን ቀጠለ ።
በኋላም በራስ እምሩ ከሚመራው ከ600
በላይ የሰው ኃይልና በትጥቁም ሆነ በሞ
ራሉ ተወዳዳሪ ከማይገኝለት አርበኞች ጋር
ጎሬ ላይ በመደባለቅ በአጋሮና በጅማ አካ
ባቢዎች ከፍተኛ ውጊያዎችን አካሂዷል ።
በተለይም ጌራ በተባለው ቦታ በተካሄደ
ው ጦርነት የሁለት መቶ የፋሽስቶች
ወታደሮችንና ብዙ መሣሪያዎችን ማርከ
ዋል ።

ሁለተኛው የአርበኞች ከፍተኛ እንቅ
ስቃሴ የታየባቸው የአዲስ አበባና የአካባ
ቢው ቦታዎች ነበሩ ። የዚህ እንቅስቃሴ
ዓላማ ፋሽስቶች ጦራቸውን ከአዲስ አበባ በ
ማስነሳት ወደ ደቡባዊ ምሥራቅ ኢትዮጵያ
የሚያደርጉትን እንቅስቃሴ ለመግታትና ለ
ማፈን ነበር ። እንቅስቃሴውን ለመግታትና
ለማፈን በአዲስ አበባ ውስጥ በመሸገው
የጠላት ጦር ላይ እርምጃ መውሰድ አስፈላጊ
በመሆኑ በከተማው በሚገኘውና ሁለት ሺህ
ሰላሳ መኰንኖች ፣ አሥራ ዘጠኝ ሽህ ሰባት
መቶ ሦስት የፋሽስት ወታደሮችና አራትሺህ
አራትመቶየቅጥር ወታደሮችን ባቀፈው ጦር
ላይ ከከተማውምዕራባዊ ሰሜንና ምሥራቃዊ
ደቡብ በኩል በተለያዩ ጊዜያት አርበኞች
ተደጋጋሚ ጥቃት አድርሰውበታል ። አንዳ
ንድ የአይን ምስክሮች እንዳስተዋሉት ፋሽ
ስቶች ከመርበድበዳቸው የተነሣ የአዲስ
አበባን ዳርቻ በጠንካራ የሽቦ አጥርና
በ38 የሲሚንቶ ምሽጎች ከበዋት እንደነበር
አረጋግጠዋል ።

በሌላ በኩል አርበኞች እንቅስቃሴአ
ቸውን ያጠናከሩት በፋሽስቶች የመገናኛ
አውታሮች ሲሆን በተለይም ዋናው የመገ
ናኛ መስመር በሆነው አዲስ አበባንና
ጅቡቲን ከሚያገናኘው የባቡር ሐዲድ ላይ
ነበር ። ጠላት አብዛኛውን የባሕር ማዶ
የጦር መሣሪያ ፣ ስንቅና መላው ትጥቁና
የመሳሰሉትን ቁሣዊ ነገሮች ሁሉ ወደ ኢት
ዮጵያ የሚያስገባው በዚህ መስመር በመ
ሆኑ አርበኞቹም ይህኑ መስመር ኢላማቸው
ያደረጉት ይህን ለጠላት የሚደርሰውን ትጥ
ቅና ድርጅት ለማቋረጥ ነበር ። በእንቅስቃ
ሴው ተሰማርቶ የነበረውና በአውቶማቲክ
ትጥቅ የዳበረው በነጋድራስ ቦጋለና በደ
ጃች ፍቀረማርያም የሚመራው ሁለትሺህ
በላይ የሚሆኑ አርበኞች ነበሩት ። ምንም

እንኳ ፋሽስቶች በርካታ ታንኮችን ፣ ከ100 የማያንሱ የጦር አውሮፕላኖችንና በየ50 ኪሎ ሜትር ርቀት ተዘዋዋሪ የጦር ዘቦችን ያቆሙ ቢሆንም አርበኞች የባቡር ሐዲዶችን በማወላለቅ ፤ ድልድዮችን በማፈራረስ ፣ የስልክ መስመሮችን በመበጣጠስና ባቡሮችን በማጋየት ከጥቅም ውጭ በማድረግ ከፍተኛ ትግል አካሂደዋል ።

አርበኞች በተለያዩ ጊዜያት ፣ ወቅትና አቅጣጫዎች ባደረጉት ተጋድሎ በተለይም የአዲስ አበባው ከበባና የባቡር መስመሩ በየጊዜው ከአገልግሎት ውጭ መሆን ፤ ፋሽስቶችን ይበልጥ ስለአሰጋቸውና ስለ አስፈራቸው ጭፍን የሆነ አረመኔያዊ ጭፍጨፋቸውንና ግድያቸውን ተያያዙት ። የፋሽስትን አገዛዝ ይቃወማሉ ፣ ከአርበኞች ጋር በመላላክ መሣሪያ ያቀብላሉ ፣ ለአርበኞች የሞራልና የማቴሪያል ድጋፍ ይሰጣሉ እየተባሉ የሚጠረጠሩትን በግፍ በመግደል በአደባባዮች እንዲሰቀሉ አደረጉ ። የዚህን የግፍ ጽዋ በመጀመሪያ የቀመሱት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ጳጳስ የነበሩት አቡነ ጴጥሮስ በሕዝብ ፊት በአደባባይ እንዲሰቀሉ ተደረጉ ። ሌሎችም የሞትና የስቅላት ፍርድ የደረሰባቸው አያሌ ተጋድሎ ያደረጉ ጀግኖች ነበሩ ። ፋሽስቶች የንቅናቄውን መሪዎችና ጀግኖች በመግደል ትግሉ የማይቀጥልና የሚቀዘቅዝ መስሎአቸው በሰላማዊ ሕዝብ ላይ ከፍተኛ የግፍ ጭፍጨፋ ፈጽመዋል ። ነገር ግን የብዙ ሰማዕታት መስዋእትነት የአርበኞችንና የሰፊውን ሕዝብ ሞራልና የትግል ጥንካሬ ይበልጡኑ እንዲጠናከር አደረገው እንጂ ፋሽስቶች እንደሚገምቱት ከቶውንም ሊያኮላሸው አልቻለም ።

በጠላት ላይ ከተቃጡት ከፍተኛ ሙከራዎች አዲስ አበባ ውስጥ የካቲት 12 ቀን 1928 እንደኢትዮጵያ አቆጣጠር በሁለት አገር ወዳድ ወጣት አርበኞች ማለትም አብርሃም ደቦጭና ሞገስ አስገዶም ግራዚያኒን ለመግደል ያደረጉት ሙከራ አንዱ ነው ። ግራዚያኒ የተቃጣበትን የግድያ ሙከራ ለመበቀል ከአራት ሺህ ያላነሱ መኖሪያ ቤቶችን ፣ ሰላሳ ሺህ ሰላማዊ ሽማግሌዎችንና ሕፃናትን ካቃጠለና ከገደለ በኋላ ለዚህ ሙከራ ተባባሪ ናቸው በመባል በደብረ ሊባኖስ ገዳም ውስጥ ኗሪ የነበሩትን 499 መነኮሳት ገድሏል ። ይህ ግድያና ዕልቂት የፋሽስቶችን አረመኔነት እያጎላው መጣ ። በመሆኑም ይህ አረመኔያዊ ጭፍጨፋ የአርነቱን ትግል ስፋትና ጥልቀትን እያገኘ የአርበኞች እንቅስቃሴ በይበልጥ ተስፋፋ ።

በሸዋ ክፍለ ሀገር በመንዝ ፣ በመረሐቤቴ ፣ በተጉለትና ቡልጋ አካባቢዎች የተሰማራው አርበኛ ትግሉን በይበልጥ አስፋፋው ። በአጠቃላይ በጎንደርና በጎጃም ክፍላተ ሀገራት የነበረው አርበኛ የማጥቃት እርምጃውን አፋፋመው ።

በምሥራቅ ኢትዮጵያ ክፍልም የትግሉ እንቅስቃሴ ከሌሎች ቦታዎች በማያንስ ጠላትን መንቀሳቀሻ አሳጥቶታል። በዚህ የነበረው አርበኛ የጠላትን ትጥቅና ድርጅት ከማቃጠልና ከማውደም ሌላ በሱማሊያና በኢትዮጵያ በኩል የጠላት መተላለፊያ መገናኛዎችን ከጥቅም ውጭ አድርጓል ።

በጐንደር ክፍለ ሀገር ውስጥ የነበረው ከሁለት ሺህ በላይ የሚገመተውና በሙሉ በጠመንጃ የታጠቀው አርበኛ በአርማጭሆ ፣ በጠገዴ ፣ በጠለምት ፣ በወገራ ፣ በጭልጋ ፣ በደንቢያና በበለሳ ፣ በጨውጫዊትና በወልቃይት ሜካዎች ከመሰማራቱ ሌላ አሥመራንና ጎንደርን የሚያገናኘውን ጐዳና በመዝጋት ጠላቱን አስጨንቋል [20] በሌላው በኩል በጎንደር የተለያዩ አውራጃዎች አርበኞች ወደ ሌሎች ክፍላተ ሀገራት እየተራመዱ ጠላትን ወግተዋል ። የስማዳ አርበኞች ሳይንትና ቦረና ላይ ፣ የጋይንት ፤ የጥናፋና የነገላ አርበኞች በሸሎን ተሻግረው ዳውንት ላይ ፣ ዥጣን ተሻግሮ ደላንታና ወገልጤና ላይ ፣ ጨጨሆን አልፈው ላስታና መቄት ላይ ከፍተኛ መስዋእትነት ሲከፍሉ ፣ የጠገዴና የወልቃይት አርበኛም በትግራይ በኩል የተከዜን ሸለቆ በመከተል እየደጋገመ ለመሻገር የሞከረውን የፋሽስትን ጦር አሳፍሮ መልሶታል [21] ። በጐጃም በሜጫና ዴንሳ የተሰባሰበው ሦስት ሺህ የታጠቀና በበላይ ዘለቀ ሥር የነበረው የአርበኛ ኃይል ጠላት አባይን እንዳይሻገር ብርቱ ጥረት ፣ ትግልና መስዋእትነት ከፍሏል ።

በትግራይም ውስጥ የነበረው አርበኛ በተንቤን አውራጃና በሌሎችም አካባቢዎች እየተዘዋወረ ፋሽስትን መግቢያና መውጫ

አሳጥቶታል ። በሌላ በኩል ምንም እንኳ
በጠላት ኃይል ቢታፈኑም ብዙ የኤርትራ
ክፍለ ሀገር ተወላጆች ከፋሽስት ጦር እያመ
ለጡ ከመሰል ወንድሞቻቸው ጋር በመቀ
ላቀል ለውድ እናት ሀገራቸው በየጋራውና
በየሸንተረሩ ደማቸውን ያፈሰሱ አያሌ ና
ቸው ። በአክሱምና በአድዋ በኩል በመዝ
ለቅ በተከዜ ወንዝ አካባቢ ብዙ የአርበኝነት
ሥራን ሠርተዋል ። በመረብ ፥ በተሰነይና
በከሰላ ጠረፎች ይዘዋወር የነበረውና በነ
ቀኝአዝማች አምዶም ተስፋና በፊታው
ውራሪ መስፍራ ረዳ የሚመራው አርበኛ
በከሰላ እያቋረጠ እስከ ጎንደር አርማጭሆ
ድረስ ይዘልቅ ነበር ። እነዚሁ አርበኞች በአ
ቆርዳትና ከረን መካከል ባለው መንገድ
በመሰማራት አንድ የኢጣሊያን መሐንዲስ
ሲገሉ 3 መጋዘኖች አቃጥለዋል ። በተሰነ
ይና በኡማሀጀር መካከልም ጋሉይ ከተ
ባለው ቦታ አንድ የኢጣልያን ኮሚሳር ገ
ለው ብዙ የጦር መኪናዎችን በእሳት አጋ
ይተዋል ። በሁመራ አካባቢ ብዙ መኪናዎ
ችን ሲያቃጥሉ በኡማሀጀር ሁለት ፋሽስቶ
ችን ገለው ብዙ መሣሪያዎችን ማርከዋል[22]
ምንም እንኳ አያሌ የኤርትራ ተወላጆች
አርበኞች ደማቸውን ያፈሰሱ ቢሆንም በተ
ለይ የዘርዓይ ደረስ ፥ የቀኝአዝማች ተስፋዬ ፥
የአብርሀም ደቦጭና ሞገስ አስገዶም መስ
ዋዕትነት ወዘተ..... በኢትዮጵያ ሕዝብ የነ
ፃነት ታሪክ ውስጥ ሕያው ሥፍራ ይዟል ።

በደቡባዊ ኢትዮጵያ በአርሲና በባሌ የነ
በሩት አርበኞች ያደረጉት የትግል እንቅስ
ቃሴ ቀላል ነው ባይባልም ፥ በተለይ በሲዳሞ
አካባቢ ከአንድ ሺህ በላይ የሚሆን አ
ርበኛ በደቡብ ክፍላተ ሀገራት በተለይም
ጨቦና ጉራጌና አውራጃ ውስጥ በመንቀሳቀስ
ጠላት ከአዲስ አበባ ወደ ጅማ እንዳይሻ
ገር አድርጓል ። በምእራብ አዲስ አበባም
በኩል የነበረው አርበኛ የአዲስ አበባንና
የነቀምቴን አውራ መንገድ በቁጥጥር ሥር
አድርጓል [23]።

በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ሕዝቦች ፀረ
ፋሽስት እንቅስቃሴና የአርበኞች ትግል
በፋሽስቶች ግፍና ግድያ ቢደርስባቸውም
መኖሪያ ቤታቸውና ሰብላቸው ቢቃጠልም ፥
ታዋቂና ስመጥር መሪዎቻቸውንም ቢያ
ጡም ፥ ንብረትና ሀብታቸውን ቢዘረፉም
አንዳንድ ከሀዲ የፊውዳል ገዥዎች ለጠ
ላት በማጐብደድ እጃቸውን ቢሰጡም ስፊ
ውን ሕዝብና አርበኞችን ከትግል ሊያቆግ
ማቸው የሚችል ኃይል አልተገኘም ።

ነፃነትን ለማስመለስ ማንኛውንም ከንብ
ረት እስከ ሕይወት ያለውን መስዋእትነት
ከፍለዋል ። በተለይም የወጣት አርበኞችና
የሆለታ ወታደራዊ የጦር አካዳሚ መኰን
ኖች በነበራቸው የትምህርት ደረጃና የን
ቃተ ሕሊና እድገት የቅኝ አገዛዝን
አሲቃቂነትን በመግለጽና በመቀስቀስ ትግ
ሉን ስልትና ቅንጅት እንዲኖረው ያደረጉት
አስተዋጽኦ በንቅናቄው ታሪክ ውስጥ ሲያ
ንፀባርቅ ይኖራል ።

ፋሽስቶች መላዋ ኢትዮጵያን በቁጥ
ጥራቸው ሥር አድርገናል በማለት የመላ
ውን ዓለም ሕዝብ ለማሳሳት ከፍተኛ ሙ
ከራ አድርገዋል። በተለይም የጥቁር አንበሳን
የአርበኞች ኃይልን ካዳከሙ ፥ የአርበኞቹን
መሪ እራስ እምሩን ካገኙና ጋምቤላንና አንዳ
ንድ የምዕራብ ኢትዮጵያ ክፍላተ ሀገራት
ከተሞችን በጊዜያዊነት ከያዙ በኋላ ኢትዮ
ጵያን በሙሉ ከአጥናፍ እስከ አጥናፍ እንደያ
ዙ አድርገው የሃፍረት መግለጫ አወጡ። ይህ
ዓይነቱ ቅጥፈት የፋሽስቶች የፕሮፓጋንዳ
ጦርነት መሆኑ ቢታወቅም እውነትን መካድ
ግን በታሪክ ይገለጣል ። እውነቱ ግን ምንም
ጊዜም ቢሆን ፋሽስቶች አርበኞች እንደ
አሸን የሚፈሉባትን ገጠሪቱን ኢትዮጵያን
እንዳልያዙ ታሪክ ያውቀዋል ። በከተሞ
ቹም ቢሆን ፋሽስቶች በየጊዜው ተጠቅ
ተዋል ።

ከዚህ በተረፈ ፋሽስቶች በየቦታውና
በየጊዜው አረመኔያዊ ጭፍጨፋን ቢያካሂ
ዱም ይህ መላውን ሕዝብ ከዳር እስከዳር
ያንቀሳቀሰው የነፃነት ስሜት የኢጣሊያንን
ኃይል በአድዋ ፍልሚያ ጊዜ ቅስሙን እንደ
ሰበረውና ድራሹን እንዳጠፋው ሁሉ በሁለ
ለተኛው ዙር የነፃነት እንቅስቃሴው ወቅ
ትም የፋሽስትን የእብሪተኝነት ስሜት ሰባ
ብሮታል ። የሙሶሊኒ መንግሥት በሀገሩ
ውስጥ የገጠመውን ፖለቲካዊ ፥ ኢኮኖ
ሚያዊና ማኅበራዊ ችግሮች ኢትዮጵያን
የቅኝ ግዛቱ በማድረግ ሊወጣው ያሰበውን
የተስፋና የመስፋፋት ድርጊቶች ሊያስቀሩ
ችለዋል ። ስለሆነም ፋሽስቶች ኢትዮጵያን
ለመግዛት ከኃይልና ከግድያ በስተቀር ሌላ
አማራጭ የለም በሚለው አረመኔያዊ ፖሊ
ሲያቸው የተነሳ በየቦታውና በየጊዜው ባካ

ሄዱት ውጊያ በየትግል ሜዳው የደረሰባ
ቸው የማቴሪያል ጉዳት በብዙ ቢሊዮን እን
ደሚቆጠር ይገመታል ። አንድ የኢጣልያን
የታሪክ ዶኩሜንት (መዝገብ) እንደሚያ
መለክተው የሙሶሊኒ መንግሥት ከ1937
እስከ 1940 ባለው ጊዜ ብቻ በየዓመቱ ለ
ወታደራዊ በጀት መድቦት የነበረው የ
ገንዘብ መጠን ሦስት ትሪሊዮን ዘጠ
ኝ መቶ ሰማኒያ ዘጠኝ ቢሊዮን የኢ
ጣሊያን ሌሬ ነበር ። [24] ከዚህ በትሪሊዮን
ከተገመተው የወታደራዊ ባጀት አብዛኛው
የቅኝ ግዛቶችን ለማስፋፋት የዋለ ሲሆን
በይበልጡ ግን የኢትዮጵያን ሕዝባዊ የአር
በኞች እንቅስቃሴ ላይ ለተቃጣው ዘመቻ
የዋለ ነው ።

አርበኞች በጠላት ላይ ካደረሱበት የሞ
ራልውድቀት ሌላ በማቴሪያልና በሰውኃይል
በኩልም ያደረሱት ጥፋትና ዕልቂት ከፍተኛ
ነበር ። አንዳንድ በትክክል ያልተጠናቀቁ
አማካይ ግምገማዎች እንደሚያመለክቱት
ፋሽስቶች በአምስቱ ዓመታት ከአርበኞች
ጋር ባደረጉት ተጋድሎ ለ426 የጦር
መኰንኖች አምስት ሺህ የኢጣሊያን
ወታደሮችና አሥር ሺህ ቅጥር ወታደ
ሮች እንዳለቁባቸው ሲገመት ፣ ቁጥሩ
ቀድሞ ኢትዮጵያን ለመያዝ በሰሜንና በም
ሥራቅ ግንባር ከተደረገው የወረራ ጦርነታ
ቸው ከደረሰባቸው ጉዳት ጋር ሲነፃፀር በሦ
ስት እጅ በልጦ ይገኛል [25]። ይህ ቁጥር
በጦር ሜዳ የቆሰሉባቸውን 703 መኰንኖች
አሥራ ስድስት ሺህ የኢጣሊያን ወታ
ደሮች ፣ ስድስት ሺህ ሁለትመቶ አ
ርባ አራት የቅጥር ወታደሮችና የተማረኩ
ባቸውን ሳይጨምር ነው ። በተጨማሪም
አርበኞች የጠላትን ወታደሮች ከመማረካ
ቸው ፣ ከማቁሰላቸውና ከመግደላቸው
በላይ በነፃነት ዋዜማ ማግሥት ሦስት
ሺህ ሦስት መቶ አሥራ ሦስት ከባድ የጦር
መሣሪያዎችን 5,313 መትረየሶችን ስ
ድስት መቶ ሰባስምንት ሺህ የተለ
ያዩ ቀላልና ከባድ ጠብመንጃዎችን ፣ 24
ባለ ኤም ታንኮችን ፣ 35 ባለ ኤል ታንኮችን፣
126 ብረት ለበስ መኪናዎችን ፣ በርከት ያ
ሉ የጦር አይሮፕላኖችን 994 መድፎችን
ና ሞርታሮች ፣ ስድስት ሺህ ሁለት መቶ
ሰማኒያ ስድስት የጦርና የትጥቅ መመላ
ለሻ ተሽከርካሪ መኪናዎችን ማርከዋል [26] ።

ማጠቃለያ

በመግቢያው ላይ እንደተመለከትነው
የፋሽስት ኢጣሊያ ኢትዮጵያን መውረር
ከወቅቱ ዓለም አቀፋዊ ፍልሚያ ጋር ተያይ
ዞ የመጣ እንደነበር ሁሉ፤የኢትዮጵያ ሕዝብ
የነጻነት ትግልና በመጨረሻም በፋሺዝም
ላይ የተቀዳጀቻቸው ድል እንደዚሁ ጉልህ
የሆነ ዓለም አቀፋዊ ገጽታ አላቸው ።
የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ የከፈለው ከፍተኛ
የቅድሚያ መስዋእትነት በዛን ጊዜ የሰውን
ልጅ ከፋሽዝም አረመኔነት ለማዳን በመ
ላው ዓለም ውስጥ ይካሄድ ለነበረው ተጋ
ድሎ ታሪካዊ መግቢያ የነበረና የመጀመሪ
ያውን የድል ጮራ የፈነጠቀ ነው ።

ፋሽስት ኢጣሊያ ኢትዮጵያን ከወረ
ረች በኋላ ሁለተኛውን የዓለም ጦርነት
የሚያቃርቡ ድርጊቶች በዓለም አቀፉ ግንኙ
ነት ውስጥ መኾጐድጐድ ጀመሩ ። ኢት
ዮጵያን አሳልፎ በመስጠት ከፋሽዝም ጋር
ዕርቅ የወረደ የመሰላቸው የእንግሊዝና የፈ
ረንሣይ ገዢ መደቦች የሥህተታቸውን ግዙ
ፍነት ለመገንዘብ ብዙ ጊዜ አልወሰደ
ባቸውም ።

ይልቁንም የነርሱን ፍርሀትና በዓለም
መንግሥታት ሊግ ውስጥ የገቡትን ቃል
ኪዳን እንኳን ለማክበር አለመቻላቸውን
የተረዳው ፋሺዝም የልብ ልብ አግኝቶ የወ
ረራ ዕቅዱንም በግልጽ ማካሄድ ጀመረ ።
በተለይ የሶቭዬት ኅብረትን ሶሻሊስት መን
ግሥት ለመደምሰስና የሶቭዬትን ግዛቶች
በስፊው ለመያዝ ቆርጦ የተነሣው ሒትለር
ወረራውን ለማመቻቸት ሲል በአካባቢው
የነበሩትን ሀገሮች በወታደራዊ ኃይል አከ
ታትሎ ያዘ ። አውስትሪያ (ነምሳ) ፤ ቼኮ
ዝሎቫኪያ ፤ፖላንድና ሌሎችም የምሥራቅ
አውሮፓ ክፍሎች በናዚዎች ጫማ የተረገ
ጡት በዚህን ጊዜ ነው ።

ውሎ ሳያድር የሒትለር የዕብሪት ጦር
ነት ፊቱን ወደ ምዕራብ በማዞር ፈረንሣይ
ንና እንግሊዝንም አጥለቀለቃቸው ። ዓላ
ማው ቀላል መስሎ የታዬውን የምዕራብ
አውሮፓን ክፍል በቁጥጥሩ ሥር ካደረገ
በኋላ ፣ ኃይሉን በሙሉ አደራጅቶ በሶቭዬት
ኅብረት ላይ ለመዝመትና የዘለቄታ ዓላማ
ውን ዕውን ለማድረግ ነበር ።

በመጨረሻም ፣ የሙሶሊኒና የሒትለር የ ጥፋት ተባባሪ የነበሩት የጃፓን ሚሊታሪስ ቶች በእስያ አህጉርና በፓስፊክ ውቅያኖስ ላይ የበላይነትን ለመያዝ ሲሉ በእንግሊዝና በፈረንሣይ ቅኝ ግዛቶችና እንዲሁም በአሜ ሪካን ላይ ጦርነት በመክፈታቸው የሁለ ተኛው የዓለም ጦርነት የኃይል አሰላለፍ የመጨረሻ መልኩን ሊይዝ በቅቷል ።

ለአምስት ዓመታት ሙሉ ያለምንም ዓለም አቀፋዊ ድጋፍ ለፋሺዝም ጭፍጨፋ ተጋልጦ የቆየው የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ይፋ አዋጅ በኋላ ለትግሉ መሣካት አመቺ ሁኔታ ሊያገኝ ችሏል ። ፋሺዝምን መግራትና ማባበል የሚ ቻል መስሎአቸው ሲወላውሉ የነበሩ መንግ ሥታት ራሳቸውም በጦርነቱ ወላፈን በመገ ረፋቸው የፀረ-ፋሺስት ኃይሎች ትግል ይበ ልጥ እየሰፋና ዓለም አቀፋዊ ቅንብርም እያ ገኘ ሄደ ። በኢትዮጵያ አርበኞች ተወጥሮ የቆየው የኢጣሊያ ፋሺዝም ለግብአተ-መሬት የበቃውም በዚህ ሁኔታ ውስጥ ነው ።

ቀድሞ ኢትዮጵያን ለፋሺዝም አሳል ፈው ሲሰጡ ምንም ቁም ነገር ያልመሰላቸ ውም የምዕራብ አውሮፓ መንግሥታት ሁለ ተኛው የዓለም ጦርነት ከተጀመረ በኋላ ለአ ርበኞች የመሣሪያና ሌላም ድጋፍ ማድረግ የጀመሩት በድንገት ለሕዝቡና ለሀገሪቱ ነፃ ነት ተቆርቋሪነት ይዟቸው እንዳልሆነ ግልጽ ነው ። ይልቁንም የኃይለሥላሴ አስተና ጋጅ የነበረችው ታላቋ ብሪታኒያ ፤ በምሥ ራቅ አፍሪካ ውስጥ የነበሯትን ቅኝ ግዛቶ ቿን ለመከላከል ስትል የኢትዮጵያን አርበ ኞች ድጋፍ የግድ ማግኘት ነበረባት ።

ለእንግሊዝ መንግሥት ታላቅ ሥጋት የሆነባት ኢትዮጵያ ውስጥ ሰፍሮ የነበረው 220,000 የኢጣሊያን ጦር በአካባቢው የእ ንግሊዝ ቅኝ ግዛቶች የነበሩትን ሱዳንን ፣ ኬንያንና የእንግሊዝ ሱማሌን እንዳይወ ርና ፣ የቀይ ባሕርን ስትራቴጂክ መሥመር እንዳይዘጋባት ነበር ።

ይህን ጦር ሊቋቋም የሚችል ሠራዊት ለማደራጀትና ለማጓጓዝ በወቅቱ ችሎታው ስላልነበራት ፣ እንግሊዝ ለዓላማዋ መሳካት ያለምንም አማራጭ መፍትሔ ሆኖ ያገኘ ችው በፀረ-ፋሺስት ተጋድሎውና ጀግን ነቱ ዝና ካተረፈው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ጊዜያዊ ትብብር ማድረግ ነበር ። በእርግ ጥም በዚህ ትብብር ቀድሞውኑ በአርበ ኞች ትግል ተዳክሞ የነበረው የኢጣሊያ ጦር ጨርሶ በመሸነፉ የፋሺዝም ቀንበር ከኢ ትዮጵያ ምድር ተወግዷል ። እንግሊዝም በአካባቢው ከነበረባት ከፍተኛ ስትራቴጂክ ሥጋት በኢትዮጵያ ሕዝብ ተጋድሎ ልት ድን ችላለች ።

ሀቁ ይህ ሆኖ ሳለ እንግሊዝ ኢትዮጵያን ነፃ አወጣች ፤ እንግሊዝ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ደህንነትና ነፃነት ተጋድላለች እየተባለ ሲ ወራ የኖረው ሁሉ ታሪክ ሀሰት መሆኑ ግልጽ ነው ። የእንግሊዝ መንግሥት ለኢት ዮጵያ ሕዝብ ደህንነት ምንም ቁም ነገር እንዳልነበረው የሚመሰክረው የራሱን ጥ ቅም ያደላደለ መስሎት የገባውን ቃል ኪዳን በመሻር አገሪቱን ለፋሺዝም አሳልፎ መስጠቱ ነው ። በኋላም በኤርትራ ክፍለ ሀገር ውስጥ ተክሎት ባለፈው የታሪክ መ ርዝ ፣ «ታላቋ ሶማሊያ» የሚለውን ቅዠት በመጠንሰስ ለኢትዮጵያ ሕልውና የማይ ተኛ ኃይል አደራጅቶ በማለፉና ፣ እንዲሁም የኢትዮጵያን ሕዝቦች በብሔረሰብና በሀ ይማኖት ለመከፋፈል ያደረገው ሙከራ ሁሉ ለኢትዮጵያ ነፃነትም ሆነ አንድነት ምንም ፋይዳ እንዳልሰጠው ይመሠክራል ። በመጨረሻም የኢትዮጵያ ሕዝብ ፀረ-ፋሺ ስት ተጋድሎ የእንግሊዝን መንግሥት ከፍተኛ ስትራቴጂክ ውድቀት አዳነ እንጂ እንግሊዝ ኢትዮጵያን ነፃ አላወጣም ።

በእርግጥ የእንግሊዝ መንግሥት ለአድ ሀሪው የፊውዳል ሥርዓትና የዚሁ ሥርዓት ቁንጮ ለነበረው ንጉሥ ውለታ ጥሎ አል ፏል ። ይህ ውለታ ግን የኢትዮጵያን ሕዝብ ለተጨማሪ 33 ዓመታት ለፊውዳል ብዝበ ዛና ጭቆና ዳረገው እንጂ ነፃ አላወጣውም ።

ከጦርነቱ ሜዳ ላይ ሸሽቶ ከሄደ በኋላ አምሥት ዓመት ሙሉ በተንደላቀቀ እንግ ድነት የኖረው ንጉሥ እንደገና በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የጭቆና ሥርዓቱን ለመዘርጋት የቻለው በንግሊዞች ድጋፍ ነው ። ይህም ያለምክንያት አልነበረም ። አስቀድሞ ከእን ግሊዝና በኋላም ከአሜሪካን ኢምፔሪያሊ ዝም ጋር በነበረው ጥብቅ ግንኙነት ንጉሱ ለኢምፔሪያሊስቶች ዓለም-አቀፍ የብዝበዛ ፖሊሲ ታማኝ አገልጋይነቱን አረጋግጧል።

ይህን በቅድሚያ ያወቁት ኢምፔሪያሊስ ቶችም በኃይለ ሥላሴ ላይ ተንስተው የነበሩ የተቃውሞ እንቅስቃሴዎችን ለመደምሰስ ሙሉ ድጋፍ ያደርጉለት የነበረውም ለዚሁ ነው ።

ፋሺስቶችን በመዋጋት ከፍተኛ መስዋ ዕትነት ሲከፍሉ የቆዩት የኢትዮጵያ አርበ ኞች ግን ታሪካቸውን ከመቀማታቸውም ሌላ ፤ በተለያዩ ዘዴ እንዲታሰሩ ፤ እንዲገ ደሉና እንዲገለሉ ተደርገዋል ። በ1969 ሕዝባዊ አብዮት የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ የታ ሪኩ ባለቤት ለመሆን እስከበቃበት ጊዜ ድረስ ታሪካዊው ፀረ-ፋሺስት ተጋድሎ አችን በትክክለኛ ገጽታው እንዳይታወቅ የሆነበትም ምክንያት ይኸው ነው ።

የግርጌ ማስታወሻዎች

1. ኢሚል በርንስ ፤ አቢሲንያና ጣሊያን ፤ 1935 ዓ. ም. ገጽ 68
2. ጆርጅ በዩር ፤ የጣሊያንና የኢትዮጵያ ጦርነት አመጣጥ ፤ 1967 ገጽ 4
3. ኢሚል በርንስ ፤ አቢሲንያና ጣሊያን ፤ 1935 ገጽ 15
4. ኢሚል በርንስ ፤ ገጽ 15
5. ክርስቲን ሳንፎርድ ፤ ኢትዮጵያ በኃይለ ሥላሴ አገዛዝ ሥር ፤ 1946 ፤ ገጽ 93-94
6. ሪቻርድ ግሪንፊልድ ፤ ኢትዮጵያ ፤ አዲሱ የፖለቲካ ታሪክ ፤ 1965 ፤ ገጽ 193
7. ዴል ቦካ ፤ የኢትዮጵያውያን ጦርነት ፤ 1969 ፤ ገጽ 13
8. ሪቻርድ ግሪንፊልድ ፤ገጽ 192
9. አንጀሎ ዴል ቦካ፤ የኢትዮጵያውያን ጦር ነት (ከ1935-1941) እ.ኤ.አ. 1969፤ገጽ 21
10. አንጀሎ ዴል ቦካ፤ የኢትዮጵያውያን ጦር ነት (ከ1935-1941) እ.ኤ.አ. 1969፤ገጽ 21
11. ፔትሮ ባዶሊዎ ፤ የአብሲኒያ ጦርነት እ.ኤ.አ. 1937፤ገጽ 50
12. ፔትሮ ባዶሊዎ ፤ የአብሲኒያ ጦርነት እ.ኤ.አ. 1937፤ገጽ 53
13. ፔትሮ ባዶሊዎ ፤ የአብሲኒያ ጦርነት እ.ኤ.አ. 1937፤ገጽ 118
14. ፔትሮ ባዶሊዎ ፤ የአብሲኒያ ጦርነት እ.ኤ.አ. 1937፤ገጽ 118
15. አንጀሎ ዴል ቦካ ፤ የኢትዮጵያውያን ጦር ነት (ከ1935-1941) እ.ኤ.አ. 1969፤ገጽ 177
16. ፔትሮ ባዶሊዎ ፤ የአብሲኒያ ጦርነት እ.ኤ. አ. 1969 ፤ ገጽ 177
17. ፔትሮ ባዶሊዎ፤ የአብሲኒያ ጦርነት እ.ኤ. አ. 1937 ፤ ገጽ 66-68
18. ፔትሮ ባዶሊዎ ፤ የአብሲኒያ ጦርነት እ.ኤ.አ. 1937 ፤ ገጽ 64
19. አልቤርቶ ሳቦቺ ፤ የኢትዮጵያ አመጽ በጣ ሊያን አገዛዝ ላይ (1936-40) ፤ ገጽ 585
20. አልቤርቶ ሳቦቺ ፤ የኢትዮጵያ አመጽ በኢ ጣሊያን አገዛዝ ላይ (1936-40)፤ገጽ 591
21. ገሪማ ታፈረ ፤ ጎንደሬ በጋሻው ፤ ገጽ 189-190
22. ገሪማ ታፈረ ፤ ጎንደሬ በጋሻው ፤ገጽ 59
23. አልቤርቶ ሳቦቺ ፤ የኢትዮጵያ አመጽ በኢ ጣሊያን አገዛዝ ላይ (1936-40)፤ ገጽ 592
24. አልቤርቶ ሳቦቺ ፤ የኢትዮጵያ አመጽ በኢ ጣሊያን አገዛዝ ላይ (1936-40)፤ገጽ 584
25. አንጀሎ ዴል ቦካ ፤ የኢትዮጵያውያን ጦርነት (ከ1935-41) ፤ ገጽ 201
26. አንጀሎ ዴል ቦካ ፤ የኢትዮጵያውያን ጦርነት (ከ1935-1941) ፤ ገጽ 256

INFINIX HOT 8 | 13MP
AI TRIPLE CAMERA

መስከረም



የማርክሲስት ሌኒኒስት ርዕዮተ ዓለም መጽሔት

ቅጽ 1 ቁጥር 3
መጋቢት 1973

መስከረም

ቅጽ 1 ቁጥር 3
መጋቢት 1973

የማርክሲስት ሌኒኒስት ርዕዮተ ዓለም መጽሔት

ማ ው ጫ

ገጽ

- የዝግጅት ገፅ - - - - - - - - - - - - - - - - - - 3
- ኮምኒስት ማለት ምን ማለት ነው? - - - - - - - - - - 7
  - ገዛኸኝ ገብሬ
- ማርክሳዊ የፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ግንዛቤ - - - - - - - - - - - - - 27
  - አምሃ ዳኘው
- የኢትዮጵያ ሕዝብ የነፃነት ትግልና የኢጣልያን ፋሽሽት ወረራ - - - - 37
  - በኢሠፓኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ የርዕዮተ ዓለም መምሪያ
  — የአብዮት ታሪክ ክፍል —
- የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም በቀድመ አብዮት ኢትዮጵያ - - - - - 55
  - ለገሠ ለማ
- የጊዜያችን ፀረ-ኢምፔሪያሊስት ትግል
  — የላቲን አሜሪካ ሕዝብ የብሔራዊ አርነት ንቅናቄ - - - - 70
  - ብርሃኑ ዘሪሁን
- የነጋድራስ ገ/ሕይወት ባይከዳኝ የፖለቲካዊ ኢኮኖሚ አስተሳሰብ - - - - 84
  - አየለ ዘውገ

በኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ

ርዕዮተ ዓለም መምሪያ እየተዘጋጀ በየሦስት ወር የሚወጣ ።

አድራሻ

የፖስታ ሣጥን ቍጥር — 80001
የስልክ ቍጥር — 113000

INFINIX HOT 8 | 13MP
AI TRIPLE CAMERA

INFINIX HOT 8 | 13MP
AI TRIPLE CAMERA

የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም በቅድመ አብዮት ኢትዮጵያ

ክፍል 1፡- እ.አ.አ. ከ1900 ገደማ እስከ 1950ዎቹ የመጀመሪያ ዓመታት

ለገሠ ለማ

የ1966 አብዮት ማእበል ኢትዮጵያን ሲያጥለቀልቃት የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም ጥገኛውን ንጉሣዊ አገዛዝ ለማዳን ፈጥኖ ወደ ኢትዮጵያ ወታደራዊ ኃይል አልላከም ። የኢትዮጵያ አብዮት ሂደት የተለየ ባሕርይ ስልትና ታክቲክ በመጀመሪያ ላይ ኢምፔሪያሊዝምን ይሄንን ያህልም አላስደነገጠውም ነበር ። እንቅስቃሴው በመንግሥታዊ ለውጥ የሚቆም እንጂ ሥር ነቀል ወደሆነና የሶሻሊስቱን የእድገት ፈለግ ወደሚከተል አብዮት ይሸጋገራል ብለው አልገመቱም ነበር ።

በሌላ በኩል ደግሞ ከአብዮታችን ፍንዳታ አንድ ዓመት ቀደም ሲል የአሜሪካን ሠራዊት ቬየትናም ውስጥ ተመትቶና ተደቁሶ የሽንፈት ጽዋውን ጨልጦ ነበር ። ከዚህ አሳፋሪ ውርደት በኋላ ኢምፔሪያሊዝም በቀጥታ ወታደሮቹን አሰልፎ ከመዋጋት ይልቅ በእጅ አዙር ሕዝቦችን እርስ በርሳቸው ለማፋጀት የሚያስችለው የውክልና ጦርነት ስልት ቀየሰ ።

ለአርነትና ለሶሻሊዝም የሚካሄዱ ፀረ ኢምፔሪያሊስት ትግሎችን ለመቋቋምና ለማፈን የአሻንጉሊቶቹን ሠራዊት ማስታጠቅና ማሰልጠን ጀመረ ። የተቃጠለች ጣት እሳት ትፈራለች ፤ እንደተባለው ኢትዮጵያ ውስጥ ጣልቃ መግባት «አዲስ ቬየትናም» መፍጠር ይሆናል በማለትና በመፍራት ወደኋላ እንዳለም ለመገመት አያዳግትም ። የብዝበዛ መረቡን ለማቆየት ያስችለኛል በማለት የቀየሰውን አዲሱን ስልት በማስፋፋትና መልክ በማስያዝ የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም ያገር ውስጥ አድሀሪ ኃይሎችን ከማሰልጠንና ከማስታጠቅ አልፎ በዓለም ልዩ ልዩ ክፍሎችና ቀጠናዎች አንዳንድ አባ ወራዎችን የጥቅም ጠባቂ ዘበኞች በማድረግ ማጠናከር ያዘ ። ለምሳሌ ያህል በመካከለኛው ምሥራቅና በአፍሪካ ቀንድ የሻሁን ኢራን ፤ ፊውዳሉንና አድሀሪውን የሳውዲ መንግሥት ፤ ጽዮናዊት እስራኤልን፤

የሳዳትን ግብጽ ፤ ወዘተ...... በጦር ኃይል ማጉልበት ጀመረ ።

የኢትዮጵያ አብዮት የበለጠ ሕዝባዊና ሥርነቀል በመሆን በሶሻሊዝም አቅጣጫ የሚሄድ መሆኑን በይፋ መግለጽና ተግባራዊ ማድረግ ሲጀምር ፤ ኢምፔሪያሊዝም ምኞቱና ፍላጐቱ እየከሸፈበት መሄዱን በመገንዘብ የውስጥና የውጭ አድሀሪያንን በማሰባሰብና በማስታጠቅ አብዮታችንን መፈታተን ጀመረ ። ከውስጥ የአድሀሪውን ሥርዓት ርዝራዦች ፤ ጠባቦችንና ትምክህተኞችን ፤ ተገንጣዮችንና አናርኪስቶችን በማሰባሰብና በማስተባበር፤ ከውጭ በአድሀሪውና ተስፋፊው የሶማሌ ገዥ መደብ በስተጀርባ ቀንደኞቹን አሻንጉሊቶች የኢራንን ፤ የግብጽን ፤ የፓኪስታንን ፤ የሳውዲን ፤ ወዘተ...... አድሀሪ የገዥ መደቦች በማሰለፍና ከቻይና አድሀሪ አመራር ጋር በመተባበር አብዮታችንንና ብሔራዊ ሕልውናችንን ከከፍተኛ አደጋ ላይ ጣለ ። በሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብና በወዝአደራዊ ዓለም አቀፋዊነት ከባድ ተጋድሎ የኢምፔሪያሊዝምና የአድህሮት ቀንድ ተመታ ። አብዮታችን ተጠናከረ ፤ ሕልውናችንም ተረጋገጠ ። ይሁንና አሁንም ቢሆን ኢምፔሪያሊዝምና አድህሮት እጃቸውን ከላያችን ላይ አላነሱም ፤ ፊታቸውንም አላዞሩም ።

የቬየትናምን ትምህርት በመርሳትና ያቀነባበረብንን የውስጥ ቡርቦራና የውጭ ወረራ ክሽፈት በመዘንጋት በአሁኑ ጊዜ የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም በአካባቢያችን የጠብ አጫሪነትና የወረራ እንቅስቃሴውን በተጠናከረ አኳኋን እያካሄደ ነው ። በህንድ ውቅያኖስ ፤ በፋርስ ባሕረ ሰላጤና በቀይ ባሕር አካባቢ «የፈጣን ጣልቃ ገብ» ጦር ሰፈሮች እያደራጀ መሆን የኢምፔሪያሊዝምን ለሌላ አደገኛ ወረራና ጦርነት መዘጋጀት በግልጽ ያሳያል ። በእነዚህ አካባቢዎች ባሁኑ ወቅት የኢምፔሪያሊስት የጦር ሰፈሮች መስፋፋትና የወታደራዊ ኃይሎች እንቅስቃሴ ፤ በተለይም የቀንደኛው የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም ከአድሀሪውና ተስፋፊው የሱማሌ ገዥ መደብ ጋር ግንኙነቱንና ሽርክናውን ማጠናከር ፤ በኢትዮጵያ አብዮትና ብሔራዊ ሕልውና ላይ የተቃጣ አደገኛ ሴራ መሆኑ ለማንም ግልጽ ነው ። ይህንን በማስመልከት አሜሪካ በኢትዮጵያ ላይ ስለጣለችው ትኩረት ታሪክን መለስ ብሎ መመልከት አስፈላጊ ይሆናል ። የዚህ ጽሑፍና ወደፊት በዚሁ መጽሔት ላይ የሚወጣው ተከታይ ክፍል ዓላማም ከምእተ-ዓመቱ መጀመሪያ አንስቶ እስከአብዮታችን ፍንዳታ ድረስ በኢትዮጵያ የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝምን እንቅስቃሴ መቃኘት ነው ።

በኢትዮጵያ የአሜሪካ ኢምፔሪያሊስት ተግባር አጀማመር

(እ.ኤ.አ. ከ1900 ገደማ እስከ1935)

እ.ኤ.አ. በ1903 በኢትዮጵያና በአሜሪካ መካከል የዲፕሎማቲክ ግንኙነት ተጀመረ ። ግንኙነቱ የተመሠረተበት ዋና ምክንያትም የአውሮፓ ኃያላን እንደቅርጫ ሥጋ በተከፋፈሏትና የውጭ ንግዷንም ከሞላ ጐደል በቁጥጥራቸው ሥር በአደረጉት በአፍሪካ አህጉር ውስጥ የፖለቲካ ነፃነቷን ጠብቃ ከኖረችው ከኢትዮጵያ ጋር የኢኮኖሚ ፤ በተለይም የንግድ ግንኙነቱን ለማጠናከር አሜሪካ የነበረው ጉጉት ነው ። ሶስቱ የአውሮፓ ኢምፔሪያሊስት አገሮች ፤ ማለትም እንግሊዝ ፤ ፈረንሳይና ኢጣልያ በኢትዮጵያ ላይ የነበራቸው ከፍተኛ ተጽእኖ ስጋት ላይ ስለጣለው ፤ አሜሪካንንም በዚሁ በኢምፔሪያሊስቶች መካከል በነበረው ሽኩቻ ውስጥ በማስገባት የሶስቱን የአውሮፓ ኢምፔሪያሊስት አገሮች ተጽእኖ ለማዳከም የኢትዮጵያ የገዥ መደብ የነበረው ፍላጐትም ለግንኙነቱ መመሥረት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳደረገ ይገመታል ። ይሁንና በመጀመሪያ ጊዜ አሜሪካ በኢትዮጵያ ውስጥ ያካሄደችው የፖለቲካ ተግባራት ገደብ ነበራቸው ። ይህም የሆነበት አንድ ዋና ምክንያት የአውሮፓ ሀገሮች ወደአሜሪካ አህጉራት እስካልደረሱ ድረስ በሚያካሂዱት የኢምፔሪያሊስት ተግባር ውስጥ ጣልቃ አለመግባት በሚሉት የ«አይሶሌሽኒዝም»እና የ«ሞንሮ ዶክትሪን »መርሆች ላይ የፖለቲካ ተግባሯ ከሞላ ጐደል የተመሠረተ ስለነበር ነው ።

በ19ኛው ምእተ ዓመት ማብቂያ ላይ ከኢትዮጵያ ጋር የቅርብ ግንኙነት እንዲመሠረት አንዳንድ የአሜሪካ ባለሥልጣኖች ፤ በተለይም ሮበርት ስኪነር ፤ ኃሳብ አቀረበ ። ስኪነር ፤ ማርሴይ በተባለችው የፈረንሣይ የወደብ ከተማ ውስጥ የአሜሪካ ቆንሲል ጄኔራል ሆኖ ያገለግል ነበር ። አሜ

ሪካ ሴጦና ቡና ከኢትዮጵያ እንደምትገዛም በሚገባ ያውቅ ነበር ። ኢትዮጵያ ወደፊት ከፍተኛ ንግድ ይኖራታል የሚል እምነት ስለነበረውም አሜሪካ በቀጥታ ወደኢትዮጵያ እንድትገባ ፈለገ ። እ.ኤ.አ. በ1900 አንድ የአሜሪካ ቡድን ወደኢትዮጵያ እንዲላክ ፕሬዚዳንት ማኬንሊን ጠየቀ ። ምንም ነገር አለመደረጉን ሲያይም ቡድኑ እንዲላክ ደጋግሞ ጎተጎተ ። በ1902 እንዲህ በማለት አስገነዘበ ።

መብት አገኙ ፤ ለራሳቸውና በሀገሪቱ ውስጥ ለሚገኘው ንብረታቸው ዋስትና ፤ እንደሌሎች ሀገሮች ዜጎች ሁሉ በኢትዮጵያ ውስጥ ባሉ በቴሌግራፍ ፤ በፖስታና በሌሎች የመገናኛ ዘዴዎች እንዲጠቀሙ መብት ተሰጣቸው ። የውጭ ንግድን ፤ በተለይም የውጭ ንግድ ቀረጥን እና ሕጋዊ መብትን በሚመለከት ረገድ ለማንኛውም ሌላ አገር የምታደርገውን ሁሉ ለአሜሪካም ለማድረግ ኢትዮጵያ ቃል ገባች ።[2]



በሮበርት ስኪነር የተመራው የአሜሪካ መልእክተኛ ቡድን የመጀመሪያ ካምፕ በድሬዳዋ—1896

«ስለ ትሪፖሊ የተናገርኩት አቢሲኒያን በሚመለከት ረገድ ይበልጥ እውን እንደሚሆን አምናለሁ… አንድ ቀን ፤ ምናልባትም ያኔ መስኩ በሌሎች ተይዞ በምናገኝበት ጊዜ ፤ ንግዳቸውን መሻታችን ስለማይቀረው አገሮች ሁኔታ እራሳችንን እንደምንበድል ከዛሬ ሁለት ዓመታት በፊት ይልቅ ዛሬ በሚገባ ተረድቻለሁ ።[1]

በዚህ ጊዜ ቆንስሉ ያሰበው ተሳካለት ። እ.ኤ.አ. በ1903 አንድ የአሜሪካ ቡድን በመምራት ወደ አዲስ አበባ መጥቶ ከምኒልክ ጋር ስምምነት ተፈራረመ ። በዚህ የንግድ ስምምነትም የአሜሪካ ዜጎች በኢትዮጵያ ለመዘዋወርና የንግድ ሥራ ለማካሄድ

ቡድኑ ስምምነቱን ከመፈራረሙ ሌላ ካከናወናቸው ተግባራት መካከል «ስለ ንግድ ብዙ መረጃዎችን» ፤ ዋና ዋና የሆኑትን የኢትዮጵያ የእህል ዘሮች እና በተለይም ለከፋ ቡና የተለየ ትኩረት በመስጠት የአገሪቷን የእርሻ ሁኔታ የሚያሳዩ አሐዞችን መሰብሰብና በአገሪቱ ውስጥ ይገኙ የነበሩትን ነጋዴዎች ከአሜሪካ የኢንዱስትሪ ውጤት የሆኑ ሸቀጣ ሸቀጦችን እንዲያስመጡ «ማነቃቃት» ይገኙባቸዋል ። ከሶስት ዓመታት በኋላም ፤ ማለት በ1906 ፤ የአሜሪካ ቆንስል ጄኔራል ጽሕፈት ቤት አዲስ አበባ ውስጥ ተቋቁሞ አልፎ አልፎ እየሠራም እ.ኤ.አ. እስከ 1914 ድረስ ቆየ ።[3]

INFINIX HOT 8 | 13MP
AI TRIPLE CAMERA

በኋላም ኃይለሥላሴ አሜሪካ ይበልጥ በኢትዮጵያ ጉዳይ ውስጥ እንድትገባ መገፋፋቱን ያዘ ። እ.ኤ.አ. በ1923 ለፕሬዚዳንት ሀርዲንግና እሱንም ለሚተካው ለኩሊጅ የአሜሪካ ሌጋሲዮን መልሶ አዲስ አበባ ውስጥ እንዲከፈት በመማጸን ጻፈ ። ኃይለሥላሴ ለፕሬዚዳንት ሀርዲንግ በላከው መልእክት ፤ «ከአሜሪካ ሕዝብ ጋር የወዳጅነት ግንኙነት ለመመሥረት ማንኛውንም ሙከራ እያደረግሁ ነው ። ይሁን እንጂ በየጊዜው በሐሳቤ የማውጠነጥነውን እቅድ ላዋየው የምችለው በኢትዮጵያ የመንግሥታችሁ ተወካይ ወይም ኃላፊነት ያለው ኩባንያ ባለመኖሩ በጣም አዝኛለሁ» ብሏል ።

በተጨማሪም ደብዳቤው ራስ ተፈሪ በአሜሪካ ውስጥ በሚገኝ ባንክ ለማስቀመጥ የሚሻው የገንዘብ ክምችት እንዳለው እንደሚከተለው አስረድቷል ፡—

«በአሁኑ ወቅት እንኳ ፤ አባቴ ከነበረበት ጊዜ ጀምሮ በአውሮፓ ባንኮች ውስጥ የተቀመጠውን ገንዘቤን የማስቀምጥበት የታወቀ የአሜሪካ ባንክ ወይም ኩባንያ ጋር የሚያገናኘኝ አንድም ሰው ከአገርዎ ማግኘት አልቻልኩም ።

ስለዚህ ገንዘቤን የማስቀምጥበት ባንክ ወይም እምነት የሚጣልበት ኩባንያ ለማግኘት ይረዱኝ ዘንድ እርሰዎን ለማስቸገር ተገድጃለሁ... የገንዘቡ መጠንም 100,000 ፓውንድ እስተርሊንግ ነው።» [4]

ራስ ተፈሪ አዲስ ለተመረጠው ፕሬዚዳንት ፤ ለፕሬዚዳንት ኩሊጅ ፤ የላከው መልእክት ደግሞ በሁለቱ አገሮች መካከል የነበረው ግንኙነት ይበልጥ እንዲስፋፋ የሚጠይቅ ነበር ።

በአያሌ አጋጣሚዎች ከእርስዎ በፊት ለነበሩት ፕሬዚዳንት የመጻጻፍ እድል እንደገጠመኝ ሁሉ በአሜሪካና በኢትዮጵያ መካከል የወዳጅነትና የንግድ ግንኙነቶችን ስለመመሥረቱ ጉዳይ ልዩ ትኩረት የምሰጠው መሆኔን በዚህ አዲስ አጋጣሚ ለሚስተር ፕሬዚዳንት ለማስታወስ እወዳለሁ ። ስለዚህ ነው ለሁለቱ አገሮቻችን የጋራ ጥቅም ሲባል በመካከላቸው ፀንቶ የቆየውን ወዳጅነት ለማጠናከር ብቻ ሳይሆን በጽኑ መሠረት ላይ ይበልጥ ለማዳበርም የበኩሌን አስተዋጽኦ ለማድረግ እጅግ በጣም የምደሰተው ።» [5]

ከአሜሪካ ኢምፔሪያሊስቶች ጋር የጠነከረ ግንኙነት ለመመሥረት ራስ ተፈሪ ያደረገው ጥረት ውጤት አልባ አልነበረም ። ተፈሪ ገና በልጅነቱ ፤ ማለትም እ.ኤ.አ. በ1910 ፤ የወደፊት ጠቃሚ ግብረአበራቸው እንደሚሆን በአሜሪካ ኢምፔሪያሊስቶች ታጭቶ የነበረ መሆኑ በዚህ አንጻር ሊረዳው ችሏል ። በዚያን ዓመት ፤ ማለትም እ.ኤ.አ. በ1910 አዲስ አበባ የነበረው የአሜሪካ ሌጋሲዮን የላከው ዘገባ እንዲህ ይላል ፡—

«ተፈሪ ለአውሮፓውያንና ለአውሮፓ ስልጣኔ ከፍተኛ ፍቅር ያለው ይመስላል ። ጥንካሬ ፈጽሞ የጐደለው ጠባይ ይታይበታል ፤ ነገር ግን ፤ ከፍተኛ ሥልጣን ከተሰጠው ማለትም የአባቱ ግዛት የነበረውን ሐረርን ቢሰጠው እና በውጭም በኩል አይዞህ ከተባለ ምናልባት የኋላ ኋላ በኢትዮጵያ የውጭ ኃይሎችን ጥቅም ለማስፋፋት ጥሩ መሣሪያ ሊሆን ይችል ይሆናል ።

ከእንግሊዝ ሱማሌ ጋር ለምትዋሰነዋ ለም ለሆነችው ለሐረር ክፍለ ሀገር ከፍተኛ ግምት የሚሰጡት እንግሊዞች ለተፈሪ ከፍተኛ ድጋፍ የሚሰጡት መሆናቸውንም ተረድቻለሁ ።» [6]

ተፈሪ ፤ አልጋ ወራሽ እና የመንግሥቱ ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ከሆነ በኋላ ፤ ኤደን የነበረው የአሜሪካ ቆንሲል ዘገባውን ወደአሜሪካ ሲያስተላልፍ፡ «የውጭን ተጽእኖ (በኢትዮጵያ) ውስጥ ለማስገባት ተስፋ ያለው በተፈሪ በኩል ብቻ ነው ፤ እርሱ ከሥልጣን ቢወርድ ግን መንግሥቱና ሕዝቡ ከውጭ ተጽእኖ ከምንጊዜም የበለጠ ሊርቁ ይችላሉ» [7] ብሏል ።

እንደ አውሮፓ አቆጣጠር በ1923 ፤ የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የቅርብ ምሥራቁ ክፍል ፤ በኢትዮጵያ የአሜሪካን ሌጋሲዮን እንደገና መቋቋም እንዳለበት በሚከተለው አኳኋን በጥብቅ ደግፏል ፡—

የጥጥ ንግዳችን ምንጊዜም ከፍተኛውን ሥፍራ እንደያዘ ነው ። አቢሲኒያ ቆዳ ፤ የበግና የፍየል ሌጦ ፤ ቡና እንዲሁም አነስ ባለ ደረጃ እንደማር ፤ ሰም ፤ የዝሆን ጥርስ ፤ ዝባድ... የመሳሰሉትን ለውጭ ገበያ ማቅረብ ትችላለች ። ከርሰ ምድሯም በወርቅ ፤ በብር ፤ በመዳብ ፤ በብረት ፤ በድንጋይ ከሰል ፤ በድኝ ፤ በነዳጅና በፖታሽ የተሞላ

ነው ። በአገሪቷ ውስጥ የነዳጅ መኖር የተረጋገጠ ሲመስል ፤ ከኢጣልያ ጋር በምትዋሰንባቸው አቀራቢያዎች የፖታሽ ክምችት በብዛት አለ ። የቨርጂኒያና የካሮላይና የኬሚካል ኩባንያዎች የአንግሎ አሜሪካ የነዳጅ ኩባንያ በአቢሲኒያ ውስጥ ጥቅም ፈላጊ ናቸው ። የአውሮፓ ኃያላን እኛን በማገለል ተደላድለው በኢትዮሎያ ላይ እስከሚቀመጡ ድረስ ከመጠበቅ ይልቅ እነዚህ ምንም ያልተነካላቸው የተፈጥሮ ሀብቶች ሲለሙ እዚያው መገኘት ጠቃሚ ይሆናል ። ጥንቃቄ ለማድረግና መረጃዎችንም ለመሰብሰብ እንዲረዳ በሊጋሲዮን ደረጃ ዲፕሎማቲክ ግንኙነት መመሥረት እጅግ አስፈላጊ ነው ።[8]

ይሁንና የአሜሪካ ቆንሲል ጄኔራል ጽሕፈት ቤት እስከ 1928 ድረስ አዲስ አበባ ውስጥ እንደገና አልተከፈተም ነበር ። ከአንድ ዓመት ቀደም ብሎ የአሜሪካ መንግሥት «ለትርፍ ማጋበስ ተስማሚ ወደሆነችዋ አቢሲኒያ የአሜሪካ ካፒታል ማምራት አለበት» በማለት ሲወተውት[9] የኢትዮጵያ መንግሥት የጣናን ሐይቅ ግድብ ለማሠራት ከኒውዮርክ ኋይት ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን ጋር ግንኙነት መሥርቶ ስለነበር ጽ/ቤቱ በ1928 እንደገና ሊከፈት ቻለ ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እ.ኤ.አ. እስከ ሚያዝያ 1937 የአሜሪካ ሌጋሲዮን በአዲስ አበባ ክፍት ሆኖ ሊቆይ ችሎ ነበር ።[10] በሌላ አነጋገር የኢጣልያ ፋሺስት ጦር አዲስ አበባን ይዞ አንድ ዓመት እስከሞላው ድረስ የአሜሪካ ሌጋሲዮን በኢትዮጵያ ዋና ከተማ ክፍት ሆኖ ቆይቷል ።

ከሁለቱ አገሮች የዲፕሎማቲክ ግንኙነት ምሥረታ በፊት በመካከላቸው የማይናቅ የኤኮኖሚ ግንኙነት ተመሥርቶ ነበር ። በያዝነው ምእተ ዓመት መግቢያ አካባቢ በኢትዮጵያ የውጭ ንግድ ላይ አሜሪካ የበላይነት ነበራት ። እ.ኤ.አ. በ1903 ለምሳሌ ፤ 2.3 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ካስገኘው ጠቅላላ የኢትዮጵያ የውጭ ንግድ (ወጪና ገቢ ንግድ) ውስጥ የአሜሪካ ድርሻ 59 በመቶ (ሀምሳ ዘጠኝ በመቶ) ያህሉ ነበር ።[11] ኋላ ግን አሜሪካ ከሌሎች ኢምፔሪያሊስት አገሮች ከፍተኛ ውድድር ገጥሟት ነበር ። ለምሳሌ እ.ኤ.አ. በ1927 በኤደን የአሜሪካ ቆንሲል ጽሕፈት ቤት «ቀደም ሲል (ኢትዮጵያ ውስጥ) የበላይነት የነበረው የአሜሪካ ናፍጣ የዛሬ አራት ዓመት ገደማ የእንግሊዝ ናፍጣ በአነስተኛ ዋጋ በኢትዮጵያ ገበያ ላይ በቀረበበት ጊዜ ተፈላጊነቱ አሽቆልቁሏል»[12] ብሏል ። የኢትዮጵያን የውጭ ንግድ በሚመለከት ረገድ አሜሪካን ትወዳደር የነበረችው ሌላዋ ሀገር ጃፓን ናት ። ከሌሎች አገሮች ጋር ስትወዳደር ጃፓን ዋጋው እርካሽ የሆነ የጥጥ ልብስ ለኢትዮጵያ ገበያ በማቅረቧ ለምሳሌ ፤ «በጂቡቲ በኩል ለኢትዮጵያ ገበያ ይቀርቡ ከነበሩት ሸቀጣ ሸቀጦች ጠቅላላ ዋጋ የአሜሪካ ፋንታ እ.ኤ.አ. በ1917 ሰማንያ እጅ ከመቶ የነበረው በዓመቱ በ1918 ወደ አሥር እጅ ከመቶ ዝቅ እንዲል ተገደደ ።» እ.ኤ.አ. በ1931 በጃፓንና በቻይና ውስጥ ይገኙ በነበሩ የጃፓን ፋብሪካዎች ተሠርቶ ወደኢትዮጵያ የገባው ብትን ካኪ ጨርቅ በአጠቃላይ ወደኢትዮጵያ በዚያን ዓመት ከገባው ዘጠና አምስት ከመቶ ያህል ነበር። እ.ኤ.አ በ1934 አሜሪካ ለኢትዮጵያ ገበያ ያቀረበችው ከኢትዮጵያ ጠቅላላ ገቢ ንግድ 3.9 እጅ ከመቶ ብቻ ቢሆንም ኢትዮጵያ ወደውጭ ከላከቻቸው ሸቀጣ ሸቀጦች 24 እጅ ከመቶ ያህሉን ገዝታ ነበር ። በዚያን ጊዜ አሜሪካ ወደ ኢትዮጵያ ትልክ ከነበረው ሸቀጣ ሸቀጦች መካከል አውቶሞቢሎችና ከአውቶሞቢል ጋር የተዛመዱ ሸቀጣ ሸቀጦች ዋና ዋናዎቹ ነበሩ ። በመሆኑም የአሜሪካ አውቶሞቢል ንግድ ወኪል እ.ኤ.አ. በ1929 አዲስ አበባን ጎብኝቶ ነበር ። ፋሺስት ኢጣልያ አገራችንን በወ’ረችበት ዓመት በኢትዮጵያ ውስጥ የንግድ ወኪሎች ከነበሯቸው የአሜሪካ ኩባንያዎች መካከል ፎርድ ፤ ክራይስለርና ፔልሙት በመባል የሚታወቁት የመኪና አምራች ኩባንያዎች ይገኛሉ ።[13]

የአሜሪካ ካፒታሊስቶች በኢትዮጵያ ውስጥ የኢኮኖሚ ኮንሴሽን በመሻት ረገድም እርምጃዎችን ወስደው እንደነበር የሚታወስ ነው ። ለምሳሌም ያህል የአንግሎ አሜሪካ የነዳጅ ኩባንያ ፤ ለኢትዮጵያ ባለሥልጣኖች የሚቀርብ 2 ሺህ ፓውንድ ስተርሊንግ ዋጋ ያለው ገጸ በረከት የያዘ አንድ የልዑካን ቡድን የነዳጅ ፍለጋ ስምምነት እንዲያደርግ እ.ኤ.አ. በ1920 ወደ ኢትዮጵያ ተልኮ ነበር ።[14]

ይሁንና ይህ ኩባንያ ጥቂት ዓመታት የነዳጅ ፍለጋ ካካሄደ በኋላ ስምምነቱን

የራስ መኰንን በሐረር የአሜሪካን መልእክተኛ ቡድን ካምፕ ጉብኝት 1896

«ኢትዮጵያ ለንግድ ምን ያህል ምቹ እንደሆነች አጥንቶ ሪፖርት ለማድረግ ፣ አሁን በኢትዮጵያ ያለንን ጥቅም ለማስከበር የሚያስችል የንግድ ውል ለመፈራረም — እነዚህ ነበሩ የመልእክተኛ ቡድኑን ለመላክ ያስፈለገበት ምክንያቶች ። ስለ ፖሊሲያችን በዚህ ላይ የምንጨምርበት ወይንም የምንደብቀው ምንም አልነበረም ።»...... ሮበርት ስኪነር ፣ 1899

አፍርሶ ተግባሩን አቋርጧል ። ሌላ በአሜሪካ ካፒታል ሊካሄድ ታቅዶ የነበረ ታላቅ ፕሮጀክት የጣና ግድብ ነበር ። እ.ኤ.አ. በ1927 ተወጥኖ በነበረው በዚህ እቅድ የኒውዮርኩ ጄ.ጂ. ኋይት ኤንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን አምስት ሚሊዮን ፓውንድ ስተርሊንግ የሚፈጅ ግድብ እንዲሠራ ታስቦ ነበር ። የሚጠራቀመውም ውሀ ከፊሉ ለመስኖ ልማት ለሱዳን እንዲሸጥ ፤ ከፊሉ ደግሞ በኢትዮጵያ ውስጥ ለመስኖ እርሻ ልማት እንዲውል ፤ የኢትዮጵያ መንግሥትም ከውሀው ሽያጭ ገቢ ክፍያ እንዲያገኝ ታስቦ ነበር ።[15] እ.ኤ.አ. ከ1934 ጀምሮም ኮርፖሬሽኑ ጥናት ማካሄድ ጀመረ ። ይሁንና የፋሽስት ኢጣልያ ወረራ እየተቃረበ በመጣበት ጊዜ ኮርፖሬሽኑ በኢትዮጵያ ውስጥ ያካሂድ የነበረውን ተግባር አቋረጠ ።[16]

እ.ኤ.አ. በግንቦት 1935 የስኮኒቫኪዩም እና የስታንዳርድ ኦይል የጋራ ንብረት ለነበረውና በስታንዳርድ ቫኪዩም ኦይል ኩባንያ ቁጥጥር ሥር ለነበረው ለአፍሪካ የማእድን ፍለጋና ልማት (አፍሪካን ኤክስፕሎሬሽን ኤንድ ዲቨሎፕመንት) ኮርፖሬሽን በአገሪቷ አጋማሽና ምሥራቃዊ ክፍል ውስጥ የነዳጅ ዘይት ፍለጋ ፈቃድ ተሰጠው። በዚያን ጊዜ የኢጣልያ ቅኝ ገዢዎች በኢትዮጵያ ላይ የነበራቸው ፍላጎት ግልጽ እየሆነ በመምጣቱ ከአሜሪካ መንግሥት የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በተደረገ ግፊት መሠረት በተፈራረሙ በአንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ ኩባንያው ስምምነቱን ሰረዘ ።[17]

በኒውዮርክ ታይምስ መሠረት ሉይ ዋይ. ቻርቶክ የተባለ የኒውዮርክ ደላላ እ.ኤ.አ. በነሐሴ 1935 በለንደን የኃይለ ሥላሴ መልእክተኛ በነበረው በዶክተር ወርቅነህ ማርቲን አማካኝነት አንድ ሚሊዮን ዶላር በመክፈል በወለጋ ክፍለ ሀገር ውስጥ የማእድን ፍለጋ ፈቃድ ተሰጥቶት ነበር ። ኢጣልያ ኢትዮጵያን ከያዘች በኋላ ፤ ቻርቶክ በዚያን ጊዜ በግዞት የነበረውን ንጉሥ ፍርድ ቤት በመክሰስ ገንዘቡን ለማስመለስ ሞክሮ ነበር ።[18]

እዚህ ላይ ኢጣልያ ኢትዮጵያን ስለመውረርዋና ስለመያዝዋ አሜሪካ የነበራትን አቋም መግለጽ ጠቃሚ ሊሆን ይችላል ።

እ.ኤ.አ. በጥቅምት 1935 ኢጣልያ የኢትዮ
ጵያን ወሰን ጥሳ ስትገባ አንድ የቀድሞው
የዓለም መንግሥታት ማህበር ኮሚቴ ኢጣ
ልያ በኢትዮጵያ ላይ ወረራ ፈጽማለች ሲል
ወሰነ ። ይህም ማለት የጦር መሣሪያ ፤ ጥይ
ትና ሌሎች ለጦርነት አስፈላጊ የሆኑ መሣ
ሪያዎችና ቁሳቁሶች ለወራሪዋ አገር እንዳይላ
ክ የሚያግድ ውሳኔ ነበር ። ኮሚቴው ይህንን
ውሳኔ ባስተላለፈበት ቀን አሜሪካ «የገለልተ
ኝነት ደንብ» የተባለ ደንቧን በመጥቀስ
ወራሪውን ከተጠቂው ባለመለየት ጦርነት
ለገጠሙት ለሁለቱም አገሮች የጦር መሣ
ሪያዎች ፤ ጥይቶችና ሌሎች ለጦርነት የሚ
ያስፈልጉ መሣሪያዎችና ቁሳ ቁሶችን የሚ
የግድ አዋጅ አወጣች ። ይህም የአሜሪካ
ካፒታሊስቶችን ከጦርነቱ ከፍተኛ ትርፍ
ለማካበት አላገዳቸውም ፤ እንዲያግዳቸውም
የታቀደ አልነበረም ። እንዲያውም በኢጣ
ልያና በአሜሪካ መካከል የነበረው ንግድ ፤
ነዳጅን በመሳሰሉ ለጦርነት አስፈላጊ በሆኑ
ሸቀጦች ጭምርም ፤ በከፍተኛ ደረጃ ሊጨ
ምር ቻለ ። ለምሳሌ እ. ኤ. አ. በ1934
የኢጣልያ ከአሜሪካ ላይ ወርሐዊ አማካይ
የነዳጅ ዘይት ግዢ 505,000 የአሜሪካን
ዶላር የነበረው በሚቀጥለው ዓመት በህዳር
ወር ወደ 1,253,000 እና በታህሣሥ ወር
ውስጥ ደግሞ ወደ 2,296,000 ከፍ ሊል
ችሎ ነበር ። እንዲሁም በዓለም መንግሥ
ታት ማህበር የእገዳ መዝገብ ውስጥ የተዘ
ረዘሩት እንደጎማና ብረታ ብረት የመሳሰ
ሉት ጭምር በአሜሪካ በኩል ወደ ኢጣልያ
መላካቸው የታወቀ ነው ።[19] የአሜሪካ
መንግሥት በፋሺስት ወረራ ወቅት የኢትዮ
ጵያን ነጻነት የሚጻረር ድርጊት መፈጸሟ
ብቻ ሳይሆን እ.ኤ.አ. በ1941 ኢትዮጵያ
ከፋሺስት ነፃ እንድትወጣ ጉልህ የሆነ
ድርሻ ከማድረግም ተቆጥባለች ። ይሁንና
ከነፃነት በኋላ የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝ
ምና የኃይለሥላሴ መንግሥት የኢትዮጵያን
ሕዝብ ጥቅምና ደህንነት በሚጻረር መንገድ
ጠንካራ ወዳጅነት መስርተው ነበር ።

የአሜሪካ ኢምፔሪያሊስቶች በኢትዮ
ጵያ ውስጥ ከወሰዷቸው ኢኮኖሚያዊ እር
ምጃዎች መካከል ለኢትዮጵያ ገዢዎች ገጸ
በረከት የማቅረብንም ቅርጽ የያዙ ነበሩ ።
ለምሳሌ ያህል ፤ ኃይለሥላሴ እ.ኤ.አ.በ1930
ንጉሠ ነገሥት ተብሎ ዘውድ በጫነበት
ጊዜ ቁጥራቸው በርከት ያለ ኢምፔሪያሊ
ስት አገሮች ገጸ በረከት አቅርበውለት ነበር።
ከእነዚህ ኢምፔሪያሊስት አገሮችም መካ
ከል አንዷ አሜሪካ ነበረች ። አሜሪካ ካቀረ
በቻቸው ገጸ በረከቶች መካከል ተንቀሳቃሽ
ፊልሞች ፤ ሬዲዮ ፤ ማቀዝቀዣና የአሜሪካ
ሙዚቃ የተቀረጸባቸው አንድ መቶ ሸክላ
ዎች ይገኙባቸዋል ።[20] የተንቀሳቃሽ ፊል
ሞቹን ስጦታ በሚመለከት ረገድ ፤ በኢት
ዮጵያ የአሜሪካ ቆንሲል የነበረው ሳው
ዛርድ ፤ «ኢትዮጵያውያን ስለአሜሪካ እድ
ገትና ኃያልነት እንዲገነዘቡ ለማድረግ»
የአሜሪካ የፊልም ኩባንያዎች ለንጉሥ
ተፈሪ ተንቀሳቃሽ ፊልሞችን በገጸ በረከት
መልክ እንዲልኩ ሐሳብ ያቀረበው ከዘውዱ
በዓል አንድ ዓመት ቀደም ብሎ እንደነበር
ይታወሳል ። በመሆኑም ተንቀሳቃሽ ፊል
ሞች በገጸ በረከትነት ከቀረቡበት ምክን
ያቶች አንደኛው ፤ በመፈጠር ላይ በነበረው
ሽርክና ውስጥ ያላቸውን ቦታ የኢትዮጵያ
መሳፍንት ተረድተው ፤ በአሜሪካ ኢምፔ
ሪያሊዝም ቁጥጥር ሥር እንዲውሉ ለማ
ድረግ እንደነበር ግልጽ ነው ። ሳውዛርድ
ባቀረበው ዘገባ መሠረት ከዚህ ገጸ በረከት
ሌሎች ዓላማዎች መካከል «አሜሪካ ወዳጁ
መሆኗን አውቆ ንጉሡ እንዲደሰት ማድ
ረግ »፤ የኢትዮጵያ ገበያ ወደፊት ቀስ በቀስ፤
ግን ያለጥርጥር የሚዳብር በመሆኑ የአሜ
ሪካ ተንቀሳቃሽ ፊልሞችን በኢትዮጵያ
ውስጥ ለመሸጥ በር ለመክፈት እና አንዳ
ንድ የአውሮፓ አገሮች ለንጉሡ ተንቀሳ
ቃሽ ፊልሞችን የሚሰጡ በመሆናቸው
ከነሱ ጋር ተወዳድሮ በኢትዮጵያ ውስጥ
የአሜሪካን ጥቅም ማስጠበቅና ማዳበር
ይገኙባቸዋል ።[21]

ራስ ተፈሪም በበኩሉ ከአሜሪካ ኢም
ፔሪያሊስቶች ጋር ያለውን ወዳጅነት ለማ
ጠናከር ከፍተኛ ጉጉት ያደረበት እንደ
መሆኑ አንድ አይሮፕላን ፤ ሁለት ታንኮች፤
ለመግዛትና ወታደራዊ አሠልጣኞችና የሲ
ቪል አማካሪዎች ለማስመጣት የአሜሪካን
መንግሥት በ1928 ጠየቀ ። ይሁንና «የአ
ሜሪካ አማካሪዎች ከኢትዮጵያ መንግሥት
ጋር መቀራኘት ለጊዜው ጠቃሚ ሊሆን
አይችልም» በማለት የአሜሪካ የውጭ
ጉዳይ ሚኒስቴር አዲስ አበባ ለሚገኘው
ለአሜሪካ ቆንስላ በምስጢር በመግለጹ
የራስ ተፈሪ ልመና ተቀባይነት አጣ ።[22]
ይህ የአሜሪካ መንግሥት ውሳኔም በዚህ
ጉዳይ ላይ ሳውዛርድ ቀደም ሲል እንደ
ሚከተለው ካቀረበው ዘገባ ጋር የሚስማማ
ነው ።

በእኔ አስተያየት አሜሪካኖች የመንግሥት አማካሪዎች በመሆን የተሳካ ሥራ እንዲያካሂዱ ኢትዮጵያ ገና ምቹ አልሆነችላቸውም ። አንድ ኢትዮጵያዊ ባለሥልጣን በትእቢት በመወጠር አንድን የውጭ አማካሪ የሚቆጥረው እንደ አንድ ተራ የጽሑፍ ሠራተኛ ነው ። የውጭ አገር አማካሪዎች ሊሰጣቸው ስለሚገባ ክብርና ሊኖራቸው ስለሚገባ ቦታ የኢትዮጵያን ገዥዎች የማስተማሩ ተግባር ገና ብዙ ይቀረዋል ። አሁን ያሉ ጥቂት የአውሮፓ አማካሪዎች በሚያደርጓቸው ጥረቶችና በሚደርሱባቸው ውጣ ውረዶች መንገዶች ከተጠረጉ በኋላ የአሜሪካ አማካሪዎች የተሳካ ሥራ ለመሥራታቸው ትንሽ ተስፋ ሊኖር ይችላል ።[23]

እርግጥ በትምህርት ፤ በገንዘብና በውጭ ጉዳይ መስክ ለማማከር ፍራንክ ኧርነስት ወርክ ፤ ኤቨረት ኤ.ኮልሰንና ጆን ኤች ስፔንሰር የተሰኙ ሶስት አሜሪካውያን እ.ኤ.አ. ከ1930 ጀምሮ ወደ አዲስ አበባ መጥተው ነበር ።[24] በኃይለሥሌሴ መንግሥትና በአሜሪካ ኢምፔሪያሊስቶች መካከል ጠንካራ ወዳጅነት የመመሥረቱ ጉዳይ ግን ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ ያሉትን ጊዜያት መጠበቅ ነበረበት ።

ይሁንና በዚያን ጊዜ የነበረው የኢትዮጵያና የዩናይትድ ስቴትስ ትምህርታዊ ግንኙነት ወደ ኃይለሥላሴ ዙፋን ፕሮፌሰር ወርክን ከመላክም ያለፈ ነበር ። ለምሳሌ ፤ ኢጣልያ ኢትዮጵያን ከመውረሯ በፊት ትምህርትን በኢትዮጵያ ከአካሄዱ ሚሲዮናውያን መካከል የሰባተኛው ቀን አድቬንቲስቶችንና የአሜሪካ የተባበረው ፕሬስቢቴሪያን ቤተክርስቲያን ነበሩበት ። እ.ኤ.አ. ከ1918-35 ባሉት ዓመታት ውስጥ ለትምህርት ወደ ውጭ ከተላኩት 200 ያህል ኢትዮጵያውያን ወጣቶች መካከል ስምንቱ የተላኩት ወደ ዩናይትድ ስቴትስ ነበር ።[25] የሰሜን አሜሪካ የተባበረው የፕሬስቢቴሪያን ቤተክርስቲያን አባል የነበረው ዶክተር ቶማስ ላምቢ በኢትዮጵያ ያካሄዳቸው ሥራዎች ፤ የውጭ ቤተክርስቲያን መልእክተኞች ሚና ኋላቀር በሆኑ አገሮች ውስጥ ለትውልድ አገራቸው ኢምፔሪያሊስታዊ ተግባር ሁኔታዎችን ማመቻቸት መሆኑን ያስታውሰናል ፡ ላምቢ ወደ ኢትዮጵያ የገባው እ.ኤ.አ. በ1918 በሱዳን በኩል አድርጎ አንድ የወሰን ከተማ ውስጥ ሥራውን በመጀመር ነበር ። በማከታተልም ትምህርት ቤቶችና ሆስፒታሎችን በክፍለ ሀገር ከተሞችና በአዲስ አበባም ከፈተ ። በተፈሪም ዘንድ ተሰሚነትን ያገኘ ሰው ሆነ ። የአሜሪካ ኢምፔሪያሊስት ጥቅም በኢትዮጵያ ውስጥ እንዲዳብር ለማድረግ ካካሄዳቸውም ጥረቶች መካከል በኢትዮጵያ ውስጥ ቀደም ሲል ተከፍቶ የነበረው የአሜሪካ ሌጋሲዮን ዝግ ሆኖ በቆየባቸው ዓመታት ውስጥ ኤደን ይገኝ ለነበረው የአሜሪካ ሌጋሲዮን መረጃ ማቀበሉ ይገኛል ። ላምቢ አራት ኢትዮጵያውያን ወጣቶችንም አሐዮ ወደሚገኘው ሙስኪንጋም ኮሌጅ ልኳል ። ይህ ኮሌጅ ኋላም ከፕሮፌሰሮቹ አንዱ የነበረውን ፍራንክ ኧርነስት ወርክን ለኢትዮጵያ መንግሥት የትምህርት አማካሪ እንዲሆን የላከ ነው ።[26] ፕሮፌሰር ወርክ በኃይለሥላሴ አገዛዝ ዘመን በኢትዮጵያ ውስጥ እንዲሠሩ ለተደረጉት በሺህ ለሚቆጠሩ አሜሪካውያን ኤክስፐርቶችና መምህራን ፈር ቀዳጅ ሆነ ። ላምቢ ወደ አሜሪካ ለትምህርት የላካቸውም አራቱ ኢትዮጵያውያን ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት በኋላ ከማንኛውም አገር በበለጠ የኢትዮጵያን ተማሪዎች ተቀባይ ለመሆን ወደቻለችው ወደ አሜሪካ በብዛት ለተጓዙት ኢትዮጵያውያን ወጣቶች እንደዚሁ ፈር ቀዳጅ ሊሆኑ ችለዋል ።

ሆኖም ኢጣልያ ኢትዮጵያን ከመውረሯ በፊትም ቢሆን የአሜሪካ ኢምፔሪያሊስቶች ከኢትዮጵያ ጋር የትምህርት ግንኙነት መመሥረት ጥቅም ሊያስገኝላቸው እንደሚችል ያምኑ ነበር ። ለምሳሌ እ.ኤ.አ. በ1923 የዩናይትድ ስቴትስ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ከኢትዮጵያ ጋር ለምን እንደገና የዲፕሎማሲ ግንኙነት መመሥረት እንዳለበት ከሰጣቸው ምክንያቶች መካከል የሚከተለው ይገኛል ። «ባሁኑ ወቅት (ተፈሪ) የላካቸው ቍጥራቸው በርከት ያለ የአበሻ ተማሪዎች በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ በመማር ላይ ይገኛሉ ። ይህም በእርግጥ ኢትዮጵያውያን ስለ አሜሪካ ተቋሞችና ስለ አሜሪካ ንግድ መልካም አስተያየት እንዲኖራቸው ይረዳል» ። ይሁንና ባሳውዛርድ እ.ኤ.አ. በ1929 ከአዲስ አበባ ባስተላለፈው ሪፖርት ፤ ወደ ውጭ ሄደው ለመማር የሚፈልጉ ኢትዮጵያውያን ተማሪዎች የሚማርካቸው የዩናይትድ ስቴትስ ሳይሆን የፈረንሣይ ትምህርት እንደ ነበር

INFINIX HOT 8 | 13MP
AI TRIPLE CAMERA

INFINIX HOT 8 | 13MP
AI TRIPLE CAMERA

ጠቅሶ ለዚህም ያቀረበው ምክንያት በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ዘረኝነት ስፍና መገኘቱን ነበር ። [27]

በአሜሪካ ውስጥ ተንሰራፍቶ የነበረውን ዘረኝነትን በዚያው አገር የነበሩ ኢትዮጵያውያ ወጣቶች ምን ያህል አስቃቂ ሆኖ እንዳገኙትና ምንስ ያህል ይቃወሙት እንደ ነበር ጥቆማ ለማግኘት ዘውዴ በየነ የተባለ ተማሪ ወደ አገሩ ልኮት በብርሀንና ሰላም ጋዜጣ ላይ ወጥቶ የነበረውን ጽሑፍ መጥቀስ ጠቃሚ ነው ። እ.ኤ.አ. ሰኔ 16 ቀን 1927 ታትሞ በወጣው በዚህ ጋዜጣ ላይ ሰፍሮ የነበረው ይህ ጽሑፍ በኤደን የአሜሪካ ሌጋሲዮን በእንግሊዝኛ በመተርጎም ወደ ዋሽንግተን ያስተላለፈው እንደሚከተለው የሚል ነበር ፡—

«ጥቁሮች (በዩናይትድ ስቴትስ) ከፍተኛ ጭቆና ከነጮች ይደርስባቸዋል ። የጥቁሮች ኑሮ... እንደድመትና ውሻ ነው ።... ጥቁሮች የዕረፍት ጊዜያቸውን በትላልቅ ቲያትር ቤቶችና ሆቴሎች ውስጥ ለማሳለፍ ቢፈልጉ ለመግባት አይፈቀድላቸውም ።... የጥቁሮች ደም እንደውሻ ደም በከንቱ ይፈሳል ።... የነጮቹ ልጆች ኀበዝ ይሁኑ ደደብ ጥሩ ጥሩ ሥራ ሲሰጣቸው ፤ ከባዱና ዝቅተኛው ደግሞ ለጥቁሮች ይተዋል ። ሥራ የማግኘት ዕድል ሲጠብ ጥቁሮች ምንም ኀበዝ ቢሆኑ ፈጽሞ ሥራ አያገኙም ፤ እንዲያውም በአንዳንድ ቦታዎች ጥቁሮቹ ለብዙ ዓመታት ከሠሩበት ይባረሩና ሥራቸው ለነጮች ይሰጣል ። [28]

ዘውዴ በየነ በዚያን ጊዜ ቁልጭ አድርጎ ያሳየው ይህ የገዥው መደብ አባላት ጥቅማቸውን ለማዳበሪያና የብዝበዛውን ሥርዓት ዕድሜ ለማራዘሚያ የሚገለገሉበት የአሜሪካ አስከፊ ገጽታ አሁንም የሚታይ ነው ።

እ.ኤ.አ. በ1928 የአሜሪካ ሌጋሲዮን በአዲስ አበባ እንደገና ከተከፈተም በኋላ የዘር መድልዎ ጉዳይ ለሌጋሲዮኑ አስቸጋሪ መስክ ሆኖበት ነበር ። ለምሳሌም ያህል ሳውዛርድ እ.ኤ.አ. በታኅሣሥ 5 ቀን 1929 ባቀረበው ዘገባ ላይ ፤ በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ሌሎች የውጭ ዜጎች በኢትዮጵያውያን ዘንድ ከፍተኛ ተቀባይነትን ለማግኘት በአሜሪካ ውስጥ ያለውን የዘር መድልዎ ጉዳይ በማንሳት የኢትዮጵያውያኖችን ስሜት እንደሚያነሳሱ ከጠቆመ በኋላ ፤ «ይህንን ለመቋቋም ጥረት ማድረግ ከሌጋሲዮኑ ውስብስብ ተግባራት ውስጥ አንዱ ነው» ብሏል ። [29]

ከኢጣልያ ወረራ በኋላ የዩናይትድ ስቴትስ መንግሥት ከኢትዮጵያ ጋር የትምህርት ግንኙነት ማድረግ የጀመረው እ.ኤ.አ. በ1944-45 ነበር ። ከ1940ዎቹ መጨረሻ ዓመታት ጀምሮም በአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የዓለም አቀፍ የትምህርት ልውውጥ ፕሮግራም አማካይነት ብዙ ኢትዮጵያውያን ወደ አሜሪካ ሊሄዱ ቻሉ ። ሆኖም የፕሮግራሙ የዚያን ጊዜ ትኩረት መደበኛ በሆነው የዩኒቨርስቲ ትምህርት ላይ አልነበረም።ለምሳሌ እ.ኤ.አ. በ1949-60 በተሰጠው በዚህ ፕሮግራም ላይ ከተሳተፉት 28 ኢትዮጵያውያኖች መካከል አሥራ አንዱ «መሪ» ፤ አሥራ አምስቱ «ባለሙያ» ፤ እንዲሁም ሁለቱ «ተማሪ» በመባል ተከፍለዋል ። ከተሳታፊዎቹ መካከል የፓርላማ አባል የነበረው ኃይሌ ቢራ ፤ የጋዜጣ አዘጋጅ የነበረው አሐዱ ሳቡሬ ፤ በቤተመንግሥት የዜና ተወካይና የሬዲዮ አንባቢ የነበረው ወርቅየ ክፍሌና የሐረር ጳጳስና ኋላም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን መሪ የነበሩት አቡነ ቴዎፍሎስን የመሳሰሉና በገዥው መደብ ዘንድ ተሰሚነት የነበራቸው ሰዎች ይገኙባቸዋል። [30] በኢትዮጵያና በአሜሪካ መካከል በትምህርት መስክ ለጠንካራ ግንኙነት መንገድ የጠረገው የፖይንት ፎር ፕሮግራም በአሜሪካ መንግሥት እስከተቋቋመበት እ.ኤ.አ. 1950 ድረስ የትምህርት ልውውጡ ይህን ያህል ሥር የሰደደ አልነበረም ። ይህንንም ሁኔታ በዚህ መጽሔት ወደፊት በሚወጣው ክፍል ሁለት ውስጥ እንመለከተዋለን ።

በኢትዮጵያ ውስጥ ቀንደኛ ኢምፔሪያሊስትነቱን አሜሪካ ከእንግሊዝ መረከቡ

(እ.ኤ.አ. ከ1940ዎቹ መጀመሪያ ዓመታት እስከ 1950ዎቹ መጀመሪያ ዓመታት)

ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ የካፒታሊስቱን ዓለም በግንባር ቀደምትነት

የሚመራው አሜሪካ በኢትዮጵያ ውስጥ የበላይነቱን የያዘ የኢምፔሪያሊስት አገር ሆና በእንግሊዝ እግር የተተካው በ1950 ዎቹ መጀመሪያ ላይ ነበር ። ይሁንና ይህን አንዱ በሌላው እግር የመተካቱን ሂደት ከመመልከታችን በፊት ፤ ቀደም ባለው ጊዜ ውስጥ በእንግሊዝ ኢምፔሪያሊዝምና በኢትዮጵያ መካከል ስለነበረው ግንኙነት አንዳንድ ጉዳዮችን ባጭሩ ማጤን ተገቢ ነው ።

በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ፋሺስት ኢጣልያ ከጀርመን ጎን ተሰልፋ እ.ኤ.አ. በሰኔ 1940 በእንግሊዝና በፈረንሣይ ላይ ጦርነት ማወጇ[31] ፤ ኢጣልያ በኢትዮጵያ ላይ ስለአካሄደችው ወረራ እንግሊዝ ቀደም ሲል ወስዳ የነበረውን አቋም ለወጠው ። የእንግሊዝ መንግሥት የኢትዮጵያን በፋሺስት ኢጣልያ መያዝ አውቆ የተቀበለ መሆኑን እ.ኤ.አ. በታኅሣሥ 1938 በይፋ ማስታወቁ የሚታወስ ነው ።[32] ሙሶሊኒ ጦርነት ባወጀበት ጊዜ ግን ከእግር ጥፍሩ እስከ ራስ ጸጉሩ ድረስ የታጠቀውንና በደንብ የተደራጀውን ቊጥሩ ከ200,000 በላይ የሚገመት የፋሺስት ኢጣልያን ጦር ከኢትዮጵያ ጋር ተባብራ መውጋት ጠቃሚ መሆኑን እንግሊዝ ተረዳች ። በተለይም ብዙም ሳይቆይ ይህ የፋሺስት ኢጣልያ ጦር የእንግሊዝ ሶማሌ ግዛት በመባል ይታወቅ የነበረውን የእንግሊዝ ቅኝ ግዛት መውረሩና በእንግሊዝና በግብጽ ቊጥጥር ሥር የነበረችውን ሱዳንንና የእንግሊዝና የፈረንሣይ ንብረት የነበረውን የስዊዝን ቦይ ደህንነት አደጋ ላይ መጣሉ በአካባቢው ከሚገኙ የሙሶሊኒ ጠላት ከሆኑ ኃይሎች ጋር በአፋጣኝ ትብብር መፍጠር ጠቃሚ መሆኑን እንግሊዝ ተገነዘበች ።

ይሁንና የእንግሊዝ ኢምፔሪያሊስቶች የኢጣልያን ጦር ለመውጋት ከኢትዮጵያ ጋር ለመተባበር በወሰዱት ርምጃ በመጀመሪያ ደረጃ ትብብሩን ለመፍጠር የፈለጉት በአገሪቷ ውስጥ ይዋጉ ከነበሩት ኢትዮጵያውያን የነጻነት አርበኞች ጋር ሳይሆን በእነርሱ አገር ተሸሽጎ ይኖርና ከወረራውም በፊት በኢትዮጵያ ውስጥ የኢምፔሪያሊዝምን ጥቅም አስከባሪ ከነበረው ከንጉሥ ኃይለሥላሴ ጋር ነበር ። ስለሆነም እ.ኤ.አ. በጥር ወር 1941 የእንግሊዝ ወታደሮች ኃይለሥላሴን በሱዳን በኩል ወደ ኢትዮጵያ በማስገባት በዚያው ዓመት በግንቦት ወር በንጉሡ የሚመራ አሻንጉሊት መንግሥት አዲስ አበባ ውስጥ አቋቋመ ።

እንግሊዝ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በአገሪቱ ውስጥ ያካሄደችውን ዝርዝር የኢምፔሪያሊስት ደባ መተንተን የዚህ ጽሑፍ ዓላማ አይደለም ። ሆኖም ፤ በ1950ዎቹ መጀመሪያ ላይ አሜሪካ በኢትዮጵያ ውስጥ እንግሊዝ የነበራትን ሚና እስከተረከበችበት ጊዜ ድረስ እንግሊዝ በአገሪቱ ውስጥ ከፍተኛ ሚና ስትጫወት መቆየቷ የሚታወስ ነው ።

የአሜሪካ በኢትዮጵያ ውስጥ በእንግሊዝ እግር መተካት በአንድ ቀን የተከናወነ አልነበረም ። የአሜሪካ መንግሥትና የኢትዮጵያ ዘውዳዊ አገዛዝ ሆን ብለው እ.ኤ.አ. ከ1940ዎቹ የመጀመሪያ ዓመታት ጀምሮ የወሰዷቸው ርምጃዎችና በመጨረሻም ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ አሜሪካ በካፒታሊስቱ ዓለም ተወዳዳሪ የሌላት ኃያል መሆኗን እንግሊዝ የማመኗ ውጤት ነበር ።

ኃይለሥላሴ ከኢጣልያ ወረራ በፊት ጀምሮ ያልተለየውን ከአሜሪካ ኢምፔሪያሊስቶች ጋር የተጠናከረ ግንኙነት የመመሥረት ፍላጎቱን ለማርካት እንግሊዞች ወደ አዲስ አበባ እንደመለሱት ርምጃዎችን መውሰድ ጀመረ ። በዚያን ጊዜ እንግሊዞች የፖለቲካ ሥልጣን ይቀሙኛል የሚል ሥጋት አድሮበት የነበረው ንጉሥ ተቀዳሚ ዓላማም በሥልጣን ላይ ለመቆየት የአሜሪካን ድጋፍ መሻት ነበር ። በዚህ መሠረት አዲስ አበባ በገባ በሶስተኛው ቀን በጊዜው የአሜሪካን ፕሬዚዳንት ለነበረው ለሩዝቬልት መልእክት ላከ ። በዚህ መልእክት ፤ በሌሎች አገሮች ይካሄድ በነበረው በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ለመሳተፍ ይችሉ ዘንድ በኢትዮጵያ ይገኙ የነበሩ የእንግሊዝ ወታደሮችን ኢትዮጵያን ከኢጣልያ ወረራ ሙሉ በሙሉ ከማላቀቁ ተግባር ነጻ ለማድረግ ማቀዱን መጥቀሱ[33] የእንግሊዞች ተጽእኖ ያስጋው መሆኑን ለዋሽንግተን መጠቆሙን ያሳያል ።

ይህ የኃይለሥላሴ ጠንካራ ግንኙነት ከአሜሪካ መንግሥት ጋር የመመሥረት ፍላጎት ከዋሽንግተን ፍላጎትም ጋር የሚ

INFINIX HOT 8 | 13MP
AI TRIPLE CAMERA

ጸረር አልነበረም ። በዚያን ጊዜ በተለይ በኤርትራ ላይ አሜሪካ ዓይኗን ጥላ ነበር ። ንጉሡ ወደ አዲስ አበባ ከመግባቱ ጥቂት ወራት ቀደም ሲል የአሜሪካ የባሕር ኃይል ምጽዋ ወደብ የኢጣልያ ወታደሮች አበላሽተውት የነበረውን የመርከብ ማራገፊያ አሳደሰ ። በሚቀጥለውም ዓመት አሜሪካ ምጽዋ ውስጥ የባሕር ኃይል ሠፈር መሠረተ ፤ በአሥመራም አጠገብ የአይሮፕላን መጠገኛ ሠፈር አቋቋመ ።[34] የዚህ የአሜሪካ ጦር ሠፈር በኤርትራ አጀማመር ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ዝግጅት ጋር የተያያዘ ቢሆንም ጦር ሠፈሩን አሜሪካ እንዴት እንዳስፋፋውና ለዓለም አቀፍ ኢምፔሪያሊስት ተግባሩ እንዴት እንዳዋለው ወደፊት በጽሑፉ ሁለተኛ ክፍል የሚገለጽ ይሆናል ።

እ. ኤ. አ. በ1942 በአሜሪካ ፕሬዚዳንት ሩዝቬልትና በኃይለሥላሴ መካከል በተደረገ የመልእክት ልውውጥ መሠረት ቀደም ሲል በዚያው ዓመት በተለይ ለሁለተኛው ዓለም ጦርነት ሲባል ተፈርሞ የነበረ የተባበሩት መንግሥታት ስምምነት አባል ለመሆን ኢትዮጵያ መቻሏ ፤ በአሜሪካ መንግሥትና በኃይለሥላሴ መንግሥት መካከል ለተፈጠረው ግንኙነት መዳበርና በአንጻሩም የኃይለሥላሴ መንግሥት የፖለቲካ ሥልጣንን ከእንግሊዝ እጅ ቀስ በቀስ እያላቀቀ ለመሄዱ አመቺ ሁኔታን ፈጠረ ። ኢትዮጵያ የተባበሩት መንግሥታት ስምምነት አባል በመሆኗ የአሜሪካ መንግሥት በዚያው ዓመት መጨረሻ ከኢትዮጵያ ጋር የብድር ስምምነት በቀጥታ ለመደራደር መወሰኑን ገለጸ ። ይህ መግለጫ ከመውጣቱ ከአንድ ሣምንት በፊት ኢትዮጵያ በጀርመን ፤ በኢጣሊያና በጃፓን ላይ ጦርነት አውጃ እንደ ነበርም የሚታወስ ነው ።[35] በዚሁ መሠረት በሚቀጥለው ዓመት በአሜሪካና በኢትዮጵያ መካከል አንድ ለስሙ ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት ጋር ተያይዞ የነበረ የብድር ስምምነት ተፈረመ ።[36]

ምንም እንኳ በዚያን ወቅት በሰሜን ምሥራቅ አፍሪካ በጣሊያን ላይ ይካሄድ የነበረው ጦርነት ያበቃና የኢትዮጵያ ሠራዊት ከአገሩ ውጭ በሁለተኛው ዓለም ጦርነት ያልተሳተፈ ቢሆንም ስምምነቱ በሕዝብ አመጽ ፤ በተለይም በጎጃምና በትግራይ ክፍላተ ሀገሮች ተወጥሮ ለነበረውና የመንግሥቱን መዋቅር እንደገና በመዘርጋት ላይ ይገኝ ለነበረው ለኃይለሥላሴ መንግሥት ርዳታ ለመስጠት ለአሜሪካ መንግሥት አመቺ ሁኔታን ፈጠረለት ።

እ.ኤ.አ. 1945 የኢትዮጵያና የአሜሪካ ግንኙነቶች የተጠናከሩበት ዓመት ነበር ። በዚያን ዓመት አሜሪካ ኢትዮጵያን በተለይ ከመካከለኛው ምሥራቅ ፖሊሲው ጋር የማቀራረኘት ፍላጎት ያለው መሆኑ በግልጽ ታወቀ ። ይህን አርዕስት በዚህ ጽሑፍ ክፍል ሁለት ወደፊት እንመለስበታለን ።እዚህ ላይ ትኩረት የምናደርገው በሩዝቬልትና በኃይለሥላሴ መካከል እ.ኤ.አ. የካቲት 20 ቀን 1945 በተደረገው ስብሰባና በ1940ዎቹ መጨረሻ ዓመታት በተከናወኑ አንዳንድ ጉዳዮች ብቻ ይሆናል ። ስብሰባው የተከናወነው የአሜሪካ ፕሬዚዳንትና የእንግሊዝ ጠቅላይ ሚኒስትር ቸርችል የግብጽ ከተማ በሆነችው በአሌክሳንደርያ ከተገናኙ በኋላ በስዊዝ ቦይ አካባቢ በሩዝቬልት መርከብ ውስጥ ሲሆን ፤ ታይምስ የተሰኘው የለንደን ጋዜጣም ፤ በዚያን ጊዜ በሩዝቬልትና በቸርችል መካከል ተካሂዶ የነበረውን ውይይት «የመካከለኛውን ምሥራቅ የወደፊት ሁኔታ በሚመለከት ረገድ ከዚህ በፊት ከተደረጉት ውይይቶች ሁሉ እጅግ የላቀ» በማለት ገልጾታል ።[37] ከኃይለሥላሴ በተጨማሪም ፕሬዚዳንት ሩዝቬልት በጦር መርከቡ ውስጥ ከሌሎች ሁለት የመካከለኛው ምሥራቅ መሪዎች ማለትም ከግብጹ ንጉሥ ፋሩቅና ከሳውዲ ዓረቢያው ከንጉሥ ኢብን ሳውድ ጋር ስብሰባ አካሂዷል ። ኒው ዮርክ ታይምስ የተሰኘው ጋዜጣ ስለስብሰባዎቹ ዓላማ በርዕስ አንቀጹ እንደሚከተለው አስፍሮ ነበር ፡—

«ፕሬዚዳንት ሩዝቬልት የኢትዮጵያን ፤ የሳውዲ ዓረቢያንና የግብፅን ነገሥታት ተቀብሎ ያነጋገራቸው እንዲያው ለስሙና ለድምቀቱ አልነበረም … እንደገና ሥልጣን የያዘው የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት የግዛት መጠን ፤ የመንግሥቱ ባሕርይና ጥንካሬ ፤ የመላው ዓረብ እንቅስቃሴ አጠቃላይ ውጤት ፤ ተባባሪዎቻችን የሆኑት የእንግሊዝ እና የፈረንሣይ አቋም ፤ የፍልስጥኤም ችግር መፍትሔ የማግኘቱ ጉዳይ … እነዚህ ሁሉ ከሦስት ዓመት በፊት ትኩረት ያላደረግንባቸው ዛሬ ግን ዋጋ የምንሰጣቸው ናቸው።[38]

ፕሬዚዳንት ሩዝቬልት ከኃይለሥላሴ ጋር ባደረገው ስብሰባ ላይ አጠንክሮ የተናገረው «ሁለቱ አገሮች እርስ በርሳቸው በደንብ እንዲተዋወቁ» ይቻል ዘንድ በሁለቱ አገሮች መካከል ያለውን ግንኙነት የማሻሻሉን አስፈላጊነት ነበር ። በዚሁ መሠረት በሶስት ወራት ውስጥ ሩዝቬልትን የተካው ፕሬዚዳንት ትሩማን በአሜሪካና በኢትዮጵያ መካከል የተዘረጋውን ቀጥታ የሬዲዮና የቴሌግራም አገልግሎት መርቆ ከፈተ ።[39] በተከታዩ ዓመትም ትራንስ ወርልድ የሚባለው የአሜሪካ የአየር ማመላለሻ ኩባንያ ከአሜሪካ መንግሥት ጋር በተደረገ ስምምነት መሠረት የኢትዮጵያን አየር መንገድ ማቋቋም ጀመረ ።[40]

የአሜሪካ መንግሥት ስለመካከለኛው ምሥራቅ ያለው ፖሊሲ በ1940ዎቹ መጨረሻ ላይ ይበልጥ ግልጽ እየሆነ ሲመጣ ኢትዮጵያንም ለዚሁ ፖሊሲው ሊጠቀምባት ፈለገ ። ኢትዮጵያንና በዚያን ጊዜ ገና ከኢትዮጵያ ጋር ያልተቀላቀለችውን ኤርትራንም በሰሜን አትላንቲክ የጦር ቃልኪዳን ድርጅት ውስጥ ለማስገባት የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ አውጭዎች አቅደው ነበር ። እቅዱ ተግባራዊ አልሆነም ። ይሁንና የአሜሪካ መንግሥት ባለሥልጣኖች አሜሪካ አሥመራ ይገኝ በነበረው የጦር ሠፈር ለረዥም ጊዜ መገልገል መቻል አለመቻሉን የሚወስነው ስለ ኤርትራ የወደፊት ዕድል የሚደረስበት ውሣኔ ነው በማለት ፍላጎታቸውንና እቅዳቸውን በይፋ ገልጸዋል ።[41] ኋላም ዋሽንግተን የኤርትራን ከኢትዮጵያ ጋር መቀላቀል የደገፈው ይህንኑ ጥቅሙን ለማስከበር አስቦ እንጂ ለኢትዮጵያና ለኤርትራ ሕዝቦች አንድነትና ብልጽግና አስቦ እንዳልነበር ግልጽ ነው ።

ብሪታኒያ በኢትዮጵያ ላይ የነበራት የበላይነት ወደ አሜሪካ መሸጋገሩ በሙሉ ፈቃደኝነት ነው ባይባልም ሥርዓት ባለው ሁኔታ የተከናወነ ነበር ። የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ምክትል ሚኒስትር የነበረው አክሊሉ ሀብተወልድ እ. ኤ. አ. በ1945 ወደ ዩናይትድ ስቴትስ በሜሄድ እንግሊዝ በጊዜያዊነት ይዛው የነበረውን ኦጋዴንን ጨምሮ በመላው የኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ የነዳጅ ዘይት ፍለጋ እንዲያካሄድ ሲንክሌር ከተባለ የአሜሪካ የነዳጅ አውጭ ድርጅት ጋር የሀምሣ ዓመት ውል ተፈራረመ ። «ለአያሌ ዓመታት ነዳጅ አውጭ ድርጅቶች ከተደራደሯቸው ውሎች ሁሉ እጅግ የላቀ» በማለት ኒው ዮርክ ታይምስ የተባለው ጋዜጣ የገለጸው ይህ ውል ፤ የአሜሪካ ኢምፔሪያሊስቶችና የኃይለሥላሴ መንግሥት ግንኙነታቸውን ምን ያህል ለማጠናከር እንዳሰቡ ለእንግሊዝ ኢምፔሪያሊስቶች ግልጽ የሆነ መልዕክት ያዘለ እንደነበር መገመት አያዳግትም ። እርግጥ በመጀመሪያ ሲንክሌር በጥድፊያ ሰዎቹን ወደ ኦጋዴን ልኮ ጥበቃ እንዲደረግላቸው የእንግሊዝ መንግሥትን ሲጠየቅ ሰዎቹ ኦጋዴን ውስጥ የገቡት ያለፈቃዱ ስለሆነ ጥበቃ የማድረግ ኃላፊነት የለብኝም በማለት ለመተባበር ሳይፈቅድ ቀርቶ ነበር ። ይሁንና እ.ኤ.አ. በ1948 በእንግሊዝና በኢትዮጵያ መካከል በተደረገ የፕሮቶኮል ስምምነት መሠረት ኦጋዴን በከፊል ለኢትዮጵያ በመመለሱ በኢትዮጵያ ውስጥ አሜሪካ እንግሊዝን የመተካቱ ተግባር አዲስ ምዕራፍ ላይ ደረሰ ። ለምሳሌ ይህ የኦጋዴን በከፊልም ቢሆን በኢትዮጵያ መንግሥት አስተዳደር ሥር እንደገና መዋል ኒውዮርክ ታይምስን «አሁን ኦጋዴን ለኢትዮጵያ በመመለሱ ፤. . . የዩናይትድ ስቴትስ ነዳጅ አውጭ ድርጅቶች ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር በቀጥታ ለመደራደር ይችላሉ»[42] በማለት እንዲጽፍ ገፋፍቶት ነበር ።

የአሜሪካና የእንግሊዝ ተጠሪዎች ፤ በተለይም እ.ኤ.አ. በ1947 እና በ1949 ያካሄዷቸው «የፔንታጎን ውይይቶች» በኢትዮጵያ ውስጥ የበላይነቱን እንግሊዝ በሥርዓት ለአሜሪካ ማሸጋገሯን ይጠቁማሉ ። በ1947ቱ ውይይት ላይ ኢትዮጵያን የሚመለከቱ አራት ነጥቦች ተነስተው ነበር ። አንደኛ ፤ የሲንክሌርን የነዳጅ ዘይት ውል በሚመለከት ፤ ሁለቱም አገሮች «በኦጋዴን ሕግና ሥርዓት የሚከበርበትን» ሁኔታ ለመፍጠር መተባበራቸውን ፤ በኦጋዴን የነዳጅ ዘይት በሚገኝበት ጊዜ በእንግሊዝ የሶማሌ ግዛት ውስጥ የነዳጅ ዘይት ቧንቧዎች ስለመዘርጋት መብት ጉዳይና በመካከለኛው ምሥራቅ ውስጥ ችግር ቢፈጠር ኢትዮጵያ ሌላዋ የዘይት ማግኛ አማራጭ ለመሆን ስለምትችልበት ጉዳይ ተወያይተዋል ። ሁለተኛ ፤ ቀደም ሲል በኢጣልያ የቅኝ አገዛዝ ሥር የነበሩ አገሮችን ፤ ኤርትራንም

INFINIX HOT 8 | 13MP
AI TRIPLE CAMERA

ጨምሮ ፤ በሚመለከት ረገድ ፤ ዋናው ቁም
ነገር የአሜሪካንና የእንግሊዝን ጥቅም በሚ
ያዳብር አኳኋን የወደፊት ዕድላቸውን መወ
ሰን መሆኑን ሁለቱም ወገኖች ተስማምተ
ውበታል ። ሶስተኛ ፤ የአሜሪካንም ሆነ
የእንግሊዝን ጥቅም በኢትዮጵያ ውስጥ
ለማስከበር የሚቻለው የኢትዮጵያ መንግ
ሥት የሀገሩን ውስጣዊ ሥርዓትና ሕግ ለማ
ስከበር ሲችል በመሆኑ አስፈላጊው ጥንካሬ
ሊኖረው እንደሚገባ ተስማምተው ፤ ንጉሡ
ሀገሪቱን ከአንድ ማዕከል ለማስተዳደርና
የዘውዱን ሥልጣንና ክብር ለማሳደግ ለሚ
ያደርጋቸው ጥረቶች ማንኛውንም ድጋፍና
ርዳታ መስጠት እንዳለባቸው ተስማምተ
ዋል ። አራተኛ ፤ ቀደም ሲል ኢትዮጵያ
ከዩናይትድ ስቴትስ የጦር መሣሪያዎች
ለመግዛት በጠየቀችው መሠረት ከዋሽን
ግተን ተፈቅዶላት ሳለ ሶቭዬት ኅብረት
ለኢትዮጵያ የጦር መሣሪያዎችን በነጻ ለመ
ስጠት መፍቀዷ ተጠቅሶ ፤ ዩናይትድ ስቴ
ትስ ማንኛውንም የጦር መሣሪያ ሊሸጥላት
የሚችለው ከሶቭዬት ኅብረት የቀረበላትን
የጦር መሣሪያ ስጦታ ያልተቀበለች እንደ
ሆነ መሆኑን ለኢትዮጵያ መንግሥት ማስ
ገንዘብ ስለማስፈለጉ ጉዳይ ላይ ውይይት
ተደርጓል ።[43] ስለሆነም የ1947ቱ «የፔን
ታጎን ውይይቶች» በኢትዮጵያ ውስጥ የዓ
ለም አቀፍ ኢምፔሪያሊዝምን ኢኮኖሚ
ያዊና ስትራተጂያዊ ጥቅሞች ማስጠበቅና
ማዳበርን ፤ አሻንጉሊቱን የኃይለሥላሴን
መንግሥት ማጠናከርና የሶሺያሊስቱ ዓለም
ከኢትዮጵያ ጋር ግንኙነት እንዳይኖረው
ማድረግን የሚያጠቃልል ነበር ።

ኢትዮጵያን በሚመለከት ረገድ ፤ በአ
ሜሪካ እና በእንግሊዝ መካከል የተካሄዱት
የ1949ኙ «የፔንታጎን ውይይቶች» በአገ
ሪቱ ውስጥ «የኮምዩኒስት ሥጋት» ለተባለ
ጉዳይ ትኩረት ሰጥተው ነበር ። ኢትዮጵያ
አንድ አነስተኛ የጥይት ፋብሪካ ከቼኮዝሎ
ቫኪያ መግዛቷን የእንግሊዝ ተወካይ ከጠ
ቀሰ በኋላ «በተለይ በዚህ አደገኛ በሆነ
ወታደራዊ ርዳታ አማካይነት ቼኮዝሎቫ
ኪያ ፤ ከዚህ ጋር በመያያዝ ኮምዩኒዝም
ወደ ኢትዮጵያ ሠርጎ እንዲገባ የሚያስችል
ሁኔታ መፈጠሩ» ያሰጋው መሆኑን ገል
ጿል ። የአሜሪካውም ተወካይ በበኩሉ
«ጉዳዩ መንግሥቱን እንደዚሁ ያሳሰበው»
መሆኑንና ለኢትዮጵያ «እስከ አሁን ከተደ
ረገላት የሚበልጥ ርዳታ ለመስጠት» የሚ
ያስችል መንገድ መሻት አስፈላጊ መሆኑን
ጠቀሰ ።[44]

ቀደም ሲል ማለትም እ.ኤ.አ. ጥር 29
ቀን 1948 ፤ ፕሬዚዳንት ትሩማን ካደረገው
ንግግር የአሜሪካ መንግሥት የዚህ ዓይነ
ቱን ርዳታ ለማሳደግ መወሰኑን ለመረዳት
ተችሎ ነበር ። በዚህ ንግግር የአሜሪካ መን
ግሥት የውጭ ፖሊሲውን በተግባር ለመ
ተርጎም ለሌሎች አገሮች የሚሰጠውን የኢ
ኮኖሚና የሚሊተሪ ርዳታ ለማሳደግ መወ
ሰኑ ተገለጸ ። ይህም እ.ኤ.አ. በ1950 ለተ
ጀመረው «ፖይንት ፎር» ተብሎ ለተጠ
ራው የርዳታ ፕሮግራም መሠረት ሊሆን
ችሏል ።[45]

እንደታሰበውም ፤ በ«ፖይንት ፎር»
ፕሮግራም አማካይነት የአሜሪካን ርዳታ
ለመጀመሪያ ጊዜ ካገኙት አገሮች ኢትዮ
ጵያ አንዷ ሆነች ። ይህ ከመሆኑ በፊት
ግን ፤ ኢትዮጵያ ለአሜሪካን ኢምፔሪያሊ
ዝም «በሯን ክፍት» የማድረግ ፖሊሲ
እንድትከተል የሚያስገድዳትን «የወዳጅ
ነትና የኢኮኖሚያዊ ግንኙነት ውል» የን
ጉሡ መንግሥት ከበላይ ኢጋሩ ጋር መፈ
ራረም ነበረበት ። ይህ ውል እ.ኤ.አ. መስ
ከረም 7 ቀን 1951 ተፈርሞ ፤ ወዲያው ፤
በሁለቱ አገሮች መካከል ስለሚኖረው የኢ
ኮኖሚያዊና የወታደራዊ ግንኙነቶች ዝር
ዝር ስምምነቶች ተፈረሙ ። «የቴክኒካዊ
ርዳታ አጠቃላይ ስምምነት» መፈረም ፤
በዚሁ ዓመት በኢትዮጵያ ውስጥ «የፖይ
ንት ፎር» ፕሮግራም እንዲጀምር አደረገ ።
በኋላም ፤ እ.ኤ.አ. ግንቦት 22 ቀን 1953
ወታደራዊ ግንኙነትን የሚመለከቱ ሁለት
ስምምነቶች ተፈረሙ ። አንደኛው ፤ ኢት
ዮጵያውያን የጦር መኮንኖችን በአሜሪካ
ውስጥ ማሠልጠንን ጨምሮ ወታደራዊ
ርዳታን የሚመለከት «የጋራ መከላከያ
ርዳታ ስምምነት» የተሰኘ ሲሆን ፤ ሌላው
ደግሞ የአሜሪካ «የጦር ሠፈሮችን በኢት
ዮጵያ ውስጥ ማቋቋም» የተሰኘው ነው ።
ይህም እ.ኤ.አ. ከ1942 ጀምሮ አሜሪካ
በኤርትራ ክፍለ ሀገር ታካሂደው የነበረውን
የጦር ጣቢያ በተከታታይ እንድታስፋፋና
እስከ 1978 እንድታካሂድ የፈቀደላት ስም
ምነት ነበር ። ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር
በፌዴሬሽን የተቀላቀለችው እ. ኤ. አ.
በ1952 እንደ ነበር ይታወሳል ። ይህ የመ
ጨረሻው ስምምነት በኢትዮጵያ ውስጥ

ወደሚገኙ የአሜሪካ ጦር ሠፈሮች የሚመጡትንም ሆነ ከጦር ሠፈሮቹ የሚሄዱትን መርከቦች የመቆጣጠሩን መብት ፤ ኃይልና ሥልጣን ለአሜሪካ ከመስጠቱም በላይ በአገሪቱ ውስጥ በሚገኙ የአይሮፕላን ማረፊያዎች ባስፈለገ ጊዜ የመጠቀም መብትም ሰጥቶታል ።[46]

እ.ኤ.አ. በ1950ዎቹ የመጀመሪያ ዓመታት የአሜሪካና የኢትዮጵያን ግንኙነት በሚመለከት ረገድ ከተከናወኑ ጉዳዮች መካከል በዚህ ጽሑፍ ሁለተኛው ክፍል ወደፊት የምንመለስበት በአሜሪካ አነሳሽነትና መሪነት በሰሜን ኮርያ ላይ በተደረገው የተባበሩት መንግሥታት ዘመቻ የኢትዮጵያ ወታደሮች መሳተፍና የኃይለ ሥላሴ እ.ኤ.አ. በ1954 ለመጀመሪያ ጊዜ በአሜሪካ ጉብኝት ማድረግ ይገኛሉ ። በጉብኝቱ ወቅት ንጉሡ ባደረገው ንግግር ኢትዮጵያ ለአሜሪካ የኢኮኖሚና የስትራተጂ ጠቃሚነት ያላት መሆኗን ገልጿል ። በተለይም ኢትዮጵያ በቀይ ባሕር ዳርቻና በአፍሪካ ቀንድ ላይ የምትገኝ በመሆኗ ከመካከለኛው ምሥራቅና ከአፍሪካ ጋር የጠበቀ ታሪካዊ ግንኙነት ያላት መሆኗን አስገንዝበ ።[47] ይህን የመጨረሻውን የንጉሡን አባባል ዓይነተኛ የሚያደርገው ወደፊት እንደሚናየው በሚቀጥሉት ዓመታት የአሜሪካ ኢምፔሪያሊስቶች ኢትዮጵያንና እራሱን ንጉሡን በልዩ ልዩ ወቅቶች ለመካከለኛው ምሥራቅና ለአፍሪካ ፖሊሲዎቻቸው ሊገለገሉባቸው መቻላቸው ነው ■

የኢጣልያ ወታደሮች ከኢትዮጵያ ከተባረሩ በኋላ በአገሪቷ የበላይነትን ለማግኘት በእንግሊዝና በአሜሪካ መካከል ይህን የመሰለ ውድድር ተካሂዶ እ.ኤ.አ. በ1950ዎቹ መግቢያ አካባቢ የአሜሪካን በኢትዮጵያ ውስጥ ቀንደኛ ኢምፔሪያሊስትነት አስከተለ ። በዚያን ጊዜ በኢትዮጵያ ውስጥ ይገኝ የነበረው የእንግሊዝ የሚሊተሪ ልዑካን በአሜሪካን የሚሊተሪ ልዑካን ከመተካቱም በላይ አካባቢው በአሜሪካ ነዳጅ አውጭ ኩባንያዎች እጅ የገባ መሆኑን በመገንዘብ እንግሊዝ ጓዟን ጠቅልላ ከኦጋዴን ለመውጣት ተገደደች ። እንዲሁም ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር ስትቀላቀል አሜሪካ በእንግሊዝ እግር ወደ ኤርትራ በመግባት የጦር ሠፈሩን አስፋፋ ። እ.ኤ.አ. ከ1950ዎቹ መጀመሪያ አንስቶ እስከ አብዮቱ ዋዜማ ድረስ አሜሪካ በኢትዮጵያ ያከናወነውን የኢምፔሪያሊስት ተግባር ወደፊት በዚህ መጽሔት ውስጥ በሚወጣው በዚሁ ጽሑፍ ሁለተኛው ክፍል እንመለከታለን ■

የ ግ ር ጌ ማ ስ ታ ወ ሻ

1. U.S. Department of state, Memorandum on Official Relations between the United States of America and Abyssinia, may 4,1923.
2. "Treaty to Regulate Commercial Relations betwen the United States of America and Ethiopia," December 27,1903.
3. Memorandum on Official Relations between the United States of America and Ethiopia.
4. Tafari Makonnen to president Warren Harding, February 1923.
5. Tafari Makonnen to president Calvin Coolidge, November 16, 1923.
6. American Legation, Addis Ababa, to to U.S. Secretary of State, January 17, 1910.
7. American consulate, Aden, to U.S. Secretary of State, October 1, 1919.
8. Memorandum on Officail Relations between the United States of America and Ethiopia.
9. *Times* (London), may 25, 1927.
10. *New york Times*, April 9, 1937.
11. David Shinn, "a Survey of American — Ethiopian Relations prior to the Italian Occupation of Ethiopia," *Ethiopia Observer* 14 (1971) : 298.
12. American Consulate, Aden, to U.S. Secretary of State, June 14, 1919.
13. "A survey of American — Ethiopian Relations Prior to the Italian occupation of Ethiopia," pp. 298-299
14. *Times* (London); October 1, 1935.
15. *Westminister Gazette*, November 4, 1927, *Morning Post* (London), November 5, 1927.

INFINIX HOT 8 | 13MP
AI TRIPLE CAMERA

16. "Survey of American — Ethiopian Relations prior to Italian occupation of Ethiopia," p. 300.

17. *Keesing's Contemparory Archives*, I (1931-34), p. 1005, II (1934 — 37), p. 1783.

18. *New York Times*, August 29, 1937.

19. Carnegie Endowment for International Peace. *Internation Conciliation: Documents for the Year* 1937, New York, [1937], pp. 558-59.

20. *New York Times*, October 26, 1930.

21. Southard to U.S. Secretary of State, July 25, 1929.

22. U.S. Secretary of State to Southard, December 3, 1929.

23. Southard to U.S. Secretary of State, 1928.

24. *New York Times, September* 13 1930, November 17, 1930, *Times* (London) May 11, 1936.

25. Richard Pankhurst; *Economic History of Ethiopia*: 1800 — 1935, pp. 46, 681. Richard Pankhurst; "Ethiopia," in David Scanlon, ed., *Church, State and Education in Africa*, 1966, p. 51, *New York Times*, October 9, 1935.

26. See, for example, J.Loder park to U.S. Secretary of State, December 7, 1925; Southard to U.S. Secretary of State; July 29, 1929, *New York Times*, September 13, 1930, "Survey of American—Ethiopian Relations prior to Italian occupation of Ethiopia," p. 301.

27. Memorandum on the Official Relations between the United States of America and Abyssinia,
May 4, 1923, Southard to U.S. Secretary of State, December 5, 1929.

28. James Loder Park to U.S. Secretary of State, July 26, 1927.

29. Southard to U.S. Secretary of State, December 5, 1929.

30. U.S. Department of State, *International Educational, Cultural and Related Activities for African Countries South of the Sahara*, 1961, pp. 3, 269 — 70.

31. *Times* (London), June 11. 1940.

32. *Keesing's Contemporary Archives*, III (1937-40), p. 23.

33. *New York Times*, *May* 13, 1941.

34. *Facts on File*, II (1942), pp. 74, 242, 249.

35. *Ibid.*, PP. 324; 397; *Keesing's Contemporary Achives*, v (1943-45), p. 5847.

36. "Lend-Lease Agreement" between the United States of America and Ethiopia, August 9, 1943.

37. *Times* (London), February 21, 1945.

38. *New York Times*, February 22, 1945.

39. *Ibid.*, February 21, 1945; May 18, 1945.

40. *International Educational, Cultural and Related Activities for African Contries South of the Sahara*, p. 96.

41. U.S. Department of State, *Foreign Relations of the United States* 1949, Vol. VI: *Near East, South Asia and Africa*, pp. 31-32.

42. *New York Times*, September 7, 1945, October 16, 1948.

43. U.S. Department of State, *Foreign Relations of the United States* 1947, Vol V: *Near East and Africa*, PP. 527-555.

44. *Foreign Relations of the United States* 1949, Vol. VI: *Near East, South Asia and Africa*, p. 87.

45. U.S. Congress, House, *Inaugural Addresses of the presidents of the United States from George Washington* 1789 *to Harry* S.*Truman* 1949, 1952, pp. 241-242.

46. "Treaty of Amity and Economic Relations between the United States of America and Ethiopia," September 7, 1951; "Mutural Defense Assistance Agreement between the Government of the United States and the Imperial Ethiopian Government," May 22, 1953, "Utilization of Defense Installations within Empire of Ethiopia," May 22, 1953.

47. U.S. Congress, *Congressional Record* 100: 7356-58.

መስከረም

INFINIX HOT 8 | 13MP
AI TRIPLE CAMERA



የማርክሲስት ሌኒኒስት ርዕዮተ ዓለም መጽሔት

ቅጽ 1 ቁጥር 3
መጋቢት 1973

መስከረም

ቅጽ 1 ቁጥር 3
መጋቢት 1973

የማርክሲስት ሌኒኒስት ርዕዮተ ዓለም መጽሔት

ማ ው ጫ

ገጽ

- የዝግጅት ገፅ - - - - - - - - - - - - - - - - - - 3
- ኮምኒስት ማለት ምን ማለት ነው? - - - - - - - - - - - - - 7
  - ገዛኸኝ ገብሬ
- ማርክሳዊ የፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ግንዛቤ - - - - - - - - - - - - 27
  - አምሃ ዳኘው
- የኢትዮጵያ ሕዝብ የነፃነት ትግልና የኢጣልያን ፋሽሽት ወረራ - - - - 37
  - በኢሠፓኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ የርዕዮተ ዓለም መምሪያ
  — የአብዮት ታሪክ ክፍል —
- የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም በቅድመ አብዮት ኢትዮጵያ - - - - - 55
  - ለገሠ ለማ
- የጊዜያችን ፀረ-ኢምፔሪያሊስት ትግል
  — የላቲን አሜሪካ ሕዝብ የብሔራዊ አርነት ንቅናቄ - - - - 70
  - ብርሃኑ ዘሪሁን
- የነጋድራስ ገ/ሕይወት ባይከዳኝ የፖለቲካዊ ኢኮኖሚ አስተሳሰብ - - - - 84
  - አየለ ዘውገ

በኢሠፓኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ

ርዕዮተ ዓለም መምሪያ እየተዘጋጀ በየሦስት ወር የሚወጣ ።

አድራሻ

የፖስታ ሣጥን ቍጥር — 80001
የስልክ ቍጥር — 113000

INFINIX HOT 8 | 13MP
AI TRIPLE CAMERA

Proudly brought to you by
www.binyamhk.wordpress.com

የነጋድራስ ገ/ሕይወት ባይከዳኝ የፖለቲካዊ ኢኮኖሚ አስተሳሰብ

«መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር» ስለተሰኘው መጽሐፋቸው የቀረበ ሂሳዊ ግምገማ

አየለ ዘውገ

ኢትዮጵያ አገራችን ቀደም ባሉት ጊዜያትም ቢሆን ሊያሳድጓት ፤ ሊያበለጽጓትና ጠንካራ እንድትሆን ይጥሩላት የነበሩ ቀናዒ እድገት የሆኑ አስተዋይ ልጆች ነበሯት ። አሁንም በሺ የሚቆጠሩ አሏት ። ወደፊትም ይኖሩዋታል።የነዚህ ታታሪ ልጆቿ ጥረትና ዓላማ ግን እንደነበሩበት ታሪካዊ ወቅት የተለያየና ይህን ዓላማቸውንም ከግብ ለማድረስ የሚጠቀሙባቸው መንገዶች በዚያው ልክ ይበልጡኑ በወቅቱ አጠቃላይ ሁኔታዎች የተገዙ ናቸው ። በመሆኑም ለአገራቸው እድገት ከፍተኛ የመቆርቆር ስሜት ስለነበራቸው የተለያዩ ግለሰቦች በተለያዩ ጊዜያት ያከናወኑትን ተግባራት ስንመረምር ተገቢውን የታሪክ ሥፍራቸውን ለማጎናጸፍ መልዕክቶቻቸውን ከነበሩበት ተጨባጭ ታሪካዊ የአገር ውስጥና የውጪ ሁኔታዎች ጋር በማዛመድ መመልከት ተገቢ ይሆናል ። እኔም ይህቺን የምታህል አጭር መልዕክት በቅድሚያ መሰንዘሬ ከላይ የተጠቀሱትን ግለሰብ የፖለቲካዊ ኤኮኖሚ አስተሳሰብ በመመርመር የያንዳንዱን ነጥብ ጉልህነት ለመረዳት ይቻለን ዘንድ በመጠኑም ቢሆን አንባቢያንን በቅድሚያ ማስታወስ ይረዳ እንደሆን ብዬ ነው ። ደግሞም የዚህ ዓይነቱን ግለሰብ ሥራዎች ማጤን መሠረታዊ ዓላማን እንዲያው በጥቅሉ ለማስቀመጥ ብንሞክር አብዮታውያንን ካለፈው ትውልድ እንዳንድ አባላት ጠቃሚ ሥራ ጋር በማስተዋወቅ የትግል ስሜታቸውን የበለጠ ለመቀስቀስና የአሁኑ ትውልድ ለተተኪው ትውልድ ምን ማውረስ ይገባዋል? የሚል ጤናማ ጥያቄ በአእምሮአችን እንዲጉላላ በማድረግ እያንዳንዳችን ራሳችንን ላንድ አፍታ እንድንጠይቅ ለማድረግ ነው ። በተጨማሪም ይህ ጽሑፍ በፊውዳሏ ኢትዮጵያ ውስጥ ለአገራቸው እድገት ተቆርቋሪ የሆኑ ግለሰቦች ዕጣ ምን እንደነበር በማሳየት ያለፈውን ሥርዓት አስጸያፊ ባህሪ ያሳያል የሚል እምነት አለኝ ።

INFINIX HOT 8 | 13MP
AI TRIPLE CAMERA

እንግዲህ ወደተባለው የነጋድራስ መጽሐፍ ግምገማ ከማምራታችን በፊት በቅድሚያ የሕይወት ታሪካቸውን ባጭሩ መመልከቱ ለግምገማው ግንዛቤ ስለሚረዳ እንደሚከተለው ሊቀርብ ይችላል ።

ነጋድራስ ገ/ሕይወት ባይከዳኝ ከአባታቸው ከሻቃ ባይከዳኝ ገብረእዝጊና ከእናታቸው ከወ/ሮ ኃለፉ ወልደ ስላሴ ሐምሌ 24 ቀን 1878 በትግራይ ክፍለ ሀገር በአድዋ አውራጃ በተለይም ዘንጉይ ወይም ማይምሽም በተባለው ቀበሌ ተወለዱ ።[1] በተወለዱበት አካባቢም በተለያዩ ምክንያቶች በደረሰው ችግር የተነሳ ገ/ሕይወት ገና የሰባት ዓመት ልጅ እያሉ ከእናታቸው ጋር ወደ ሐማሴን ለመሰደድ ተገደዱ ። በዚሁ ጊዜ ገ/ሕይወት ከመሰል ጓደኞቻቸው ጋር ሆነው ባሕረምጽዋን ለማየት ሄደው ከባሕሩ ቆማ የነበረች መርከብ ውስጥ ገብተው ሲቃኙ የጓደኞቻቸውን መውረድ ሳያስተውሉ መርከቧ በመነሳቷ ጉዞዋቸውን ወደ «ነምሳ» (አውስትሪያ) ቀጠሉ ። ገ/ሕይወት ለመሄድ ፈልገው ይደበቁ ወይም ዘንግተው ከፍላጎታቸው ውጪ ይሂዱ በውል የታወቀ ነገር የለም ። ለማንኛውም ነምሳ እንደደረሱ የመርከቧ ካፒቴን ገ/ሕይወትን ሶርኒ ለተባሉ ነምሳዊት ሴት በእናትነት እንዲያሳድጉት ይሰጣል ። ገ/ሕይወትም ትምህርታቸውን በነምሳ ለተወሰነ ጊዜ ከተከታተሉ በኋላ ለከፍተኛ ትምህርት ጎረቤት ወደሆነችው ጀርመን ተልከው በርሊን ዩኒቨርሲቲ ገቡ ። እንደልጃቸው ባላምባራስ አሸብር ገብረሕይወት አባባልም በ18 ዓመታቸው በሕክምና በዲግሪ ተመረቁ ። ከተመረቁም በኋላ በጥቁርነታቸው የተነሳ ሥራ አጥተው ሲጉላሉ ሳሉ አጼ ምኒልክ ታመው ኑሮ ለጀርመን መንግሥት ሐኪም እንዲላክላቸው በጠየቁት መሠረት እነኝሁኑ ሐኪሞች ለመምረጥ በተሰጠው ፈተና ተካፍለው ስላለፉ ከዶ/ር ሲንቲግራፍና ካርልስ ጋር ወደ ኢትዮጵያ መጡ ። ወደኢትዮጵያ ከመጡም በኋላ እቴጌ ጣይቱ (ምናልባትም በኢትዮጵያዊነታቸው ንቀዋቸው ይሆናል) ሁለቱ ፈረንጆች አጼ ምኒልክን እንዲያክሙ ሲስማሙ ገ/ሕይወትን ግን አሻፈረኝ አሉዋቸው ። ገ/ሕይወትም የአጼ ምኒልክ ልዩ ጸሐፊና አስተርጓሚ እንዲሆኑ ተደረገ ። በዚህ ጊዜም ነጋድራስ አጼ ምኒልክ ስለልጅ እያሱ አልጋወራሽነት ለማስታወቅና አደራ ለማለት ለተላኩት መልእክተኞች አስተርጓሚ በመሆን ወደጀርመን፣ቱርክና ፈረንሳይ አገሮች ሄደው ነበር ። እቴጌይቱ ድንገት አጼ ምኒልክ ሲሞቱ ከቤተመንግሥቱ ቀርተው ላስተዳድር ብለው ችግር እንዳይፈጥሩ ነጋድራስ ባቀረቡት ሐሳብ ከንግሥት ዘውዲቱ ጋር እንጦጦ እንዲቀመጡ ተደረገ ። ይህንን የእቴጌይቱን በእንጦጦ መወሰን ሌሎች ያወቁብኝ እንደሆን ብለው በመፍራት ወደሱዳን ተሰደዱ ። እዚያም እያሉ «አጤ ምኒልክና ኢትዮጵያ» የተባለውን ጽሑፋቸውን ጻፉ ። በኋላም የእቴጌይቱን ከቤተመንግሥት ሥራ መወገድና የልጅ ኢያሱን ሥልጣን ላይ መውጣት አውቀው እንደገና ወደአዲስ አበባ ተመለሱ ። በዚህ ጊዜም በመጀመሪያ በግምጃ ቤት ሹምነት በኋላም በ1909 በፍራንኮ ኢትዮጵያ ምድር ባቡር ተቆጣጣሪነት እንዲሠሩ ተደረገ ። ከአንድ ዓመት በኋላም የድሬዳዋ ነጋድራስ ተባሉ ። ገ/ሕይወት ባይከዳኝ ነጋድራስ የተባሉት ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ነው ። በዚህ ጊዜ ነበር «መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር» የተሰኘውን መጽሐፋቸውን ከዛሬ 60 ዓመት ገደማ በፊት የጻፉት ። ነጋድራስ ከተፈሪ ጋር በመሆን ልጅ ኢያሱን ከሥልጣን በማውረዱ ሴራ ውስጥ ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል።ስለዚሁ ጉዳይ ሪቻርድ ግሪንፊልድ የተባለው አሜሪካዊ ፤ ነጋድራስ ልጅ ኢያሱን ለመጣል ለምን ከተፈሪ ጋር እንደተባበሩ የሰጡትን ምክንያት ጠቅሶ

«ከወደፊቱ የረዥም ጊዜ አደገኛ ጠላት ጋር በመተባበር የዛሬውን የአጭር ጊዜ ጠላት መታገል ነው ፤»[2]

ማለታቸውን ጽፏል ። የዚህ አባባላቸውን ትክክለኛነት ጽሑፎቻቸውና ካወረሱን ቋሚ ቅርሶቻቸው በግልጽ ማየት ይቻላል ። ነጋድራስ ይሰነዝሯቸው የነበሩ ሐሳቦች የፊውዳሉን የገዥ መደብ አባላት ጥቅም በቀጥታ የሚፃረር በመሆኑ ባፈሩዋቸው ጠላቶች የተነሳ በመጀመሪያ አቶ ጎሹ እዝነህ የተባሉ የአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት ሹም ሕይወታቸውን እንዲያጠፉ ተመርጠው እኙሁ ግለሰብ ይህንኑ ተልዕኮ ለመፈጸም ፈቃደኛ ሁነው ባለመገኘታቸው በምሽት ከበራፋቸው ላይ በጥይት ሲደበደቡ፣ለዚህ ተመሳሳይ ተልዕኮ ዶ/ር ኒኮላይ ዜርቦስ የተባለ ግሪካዊ ተመርጦ ሕይወታቸውን በ1911 ሰኔ ወር ላይ በ33 ዓመታቸው አጠፋ ። ግሪካዊውም ግለሰብ ቆይቶ ሲሞት እስከሪኑ የቢትወደድነት ማዕረግ ተሰጥቶታል ።



ነጋድራስ ገብረሀይወት ባይከዳኝ
(1878 - 1911)

ነጋድራስ በነዚህ ተባዮች የተነጠቁት ሕይወታቸውን ብቻ ሳይሆን ምርጥ አባባሎቻቸውንም ጭምር ነው ። ለምሳሌ ኃይለሥላሴ ተናገራቸው ተብለው ለብዙ ጊዜ ሲጠቀሱ ከነበሩት አባባሎች መካከል ፤

«ሰው ከትልቅ ወይንም ከትንሽ ቢወለድ ራሱን ለትልቅ ሥራ መውለድ አለበት ።»

«ሃይማኖት የግል አገር የጋራ ነው»

የሚሉት የነጋድራስ አባባሎች የነበሩ መሆናቸው ቋሚ ምስክሮች ናቸው ። ይህንኑ በማያወላዳ አኳኋን ለማረጋገጥ በመላው የነጋድራስ ጽሑፎች ውስጥ የሚገኙ መሆናቸው ነጋድራስ«አጤምኒልክና ኢትዮጵያ» በተሰኘው ጽሑፋቸው ውስጥ ለፈጣን የሥልጣኔ እርምጃ «በቶሎ ቢፈጸሙ ማለፊያ ነበር» ብለው በነደፉት ባለአሥር ነጥብ መርሐ ግብራቸው በአሥረኛ ተራ ቁጥር ላይ ያሰፈሩትን በከፊል መጥቀሱ ብቻ በቂ ይሆናል ።

«አሥረኛ ፤ የሃይማኖት አርነት ይታወጅ የሃይማኖት አርነት ጥቅም መሆኑን የማያውቀ ብዙ ሰው ይኖራል ስለዚህ የሚከተለውን ብናስተውል ደግ ነው ። ያገራችን ሰው የተዋህዶ ሃይማኖት ከሁሉ ሃይማኖት ይበልጣል ብሎ ያምናል ። በልጠ ግን ምን ረባን ፤ ማንስ አወቀው - - - የሃይማኖት አርነት ቢታወጅ ሃይማኖት ይታወቃል እንጂ አይጠፋም- - - ሃይማኖት የልብ ነገር ነው ፤»[3]

ሲሉ ግልፅ አርገው አስቀምጠውታል ።

እንግዲህ ጠቅለል ባለ መንገድ የነጋድራስ ገ/ሕይወት የሕይወት ታሪክ ይህን ሲመስል ገና በቅጡ መመለስ የሚገባቸውን ጥያቄዎች ያዘለ ታሪክ መሆኑ ግልጽ ነው ። ለምሳሌ አንዱን ብንጠቅስ ፤ ነጋድራስ በርግጥ በሕክምና ሙያ ለመመረቃቸው ምን ማስረጃ አለ? ደግሞስ በዚህ ሙያ መስክ የሰለጠኑ ከሆነ ባወረሱን ጽሁፎቻቸው ውስጥ በተዘዋዋሪ መንገድም እንኳን ቢሆን ለምን አልተንጸባረቀም? ይህንን እንዲያንጸባርቁ በማያስችሏቸው ርዕሶች ላይ እንዴት ጻፉ? ወይስ የሕክምናውን ጉዳይ እርግፍ አድርገው በመተው ዝንባሌያቸው ወደሌላ አመራ? እነኝህና እነኝህን የመሳሰሉ ሊመለሱ የሚገባቸው በርካታ ጥያቄዎች አሉ ። እነኝህን መሰል ጥያቄዎች ተብራርተው የሚመለሱበት ጊዜ ሩቅ እንደማይሆን በመተማመን በዚህ ጽሑፍ ግን «መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር» የሚል መጽሐፋቸውን በመገምገም ለመወሰን እገደዳለሁ ።

«መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር»

የካቲት 1 ቀን 1916

ነጋድራስ በመጽሐፋቸው መቅድም ላይ

«ማናቸውም ሕዝብ ቢለማም ቢጠፋም በገዛ እጁ ነው ። ሕዝብ የሚጠፋበት አንዳንድ ጊዜ ቢገኝ ያውም ምክንያት ባንዳንድ ሰው ቢመካኝ ነገሩ ትክክል አይሆንም ። የልማትን መንገድ ለማግኘት የሚጥር ሕዝብ ባንዳንድ ክፉ ሰው ምክንያት ሊጠፋ አይችልም ። እንዲሁም ደግሞ የልማትን መንገድ ለማግኘት የማይጣጣር ሕዝብ ባንዳንድ ደህና ሰው ኃይል ለማት ሊያገኝ አይችልም ። ደግሞም ማናቸውም ሕዝብ የሚለማበት መንገድ አንድ መንገድ ብቻ ነው ፤»[4]

ሲሉ ያሰፈሩት ቃል መጽሐፉ የተጻፈበትን ዐቢይ ዓላማ ይገልጻል ። የመጽሐፋቸው ዓላማ ይህን አንድ ብቸኛ መንገድ ለማሳየት ነው ። ግን እንደ ነጋድራስ አስተሳሰብ ይህ ብቸኛ መንገድ ምንድነው? በመ

INFINIX HOT 8 | 13MP
AI TRIPLE CAMERA

ጽሐፋቸው ውስጥ የተስተጋቡት መልዕክ
ቶች በሙሉ ይህንኑ ብቸኛ መንገድ ብለው
የሚያምኑትን በማሳየት ላይ ያተኮረ በመ
ሆኑ እኛም ለዚሁ ጥያቄ መልስ ራሳቸው ፤

«እስከመጨረሻው ለማንበብ ፈቃድህ ካል
ሆነ ግን ነገሩ ምንም እንደሆነ አትረዳውምና
ጊዜህ በከንቱ ይባክንብሃል ፤ ስለዚህ ባትጀ
ምረው ይሻልሃል ፡፡»[5]

ብለው ባስጠነቀቁት መሠረት ፣ከመጽሐፉ
ቆንጽለን ከማውጣት በመቆጠብ ይህንኑ
አባባላቸውን ከተወሰኑ አንጻሮች ብቻ ለመ
ገምገም እንሞክራለን ። በመቅድማቸው
ውስጥ ነጋድራስ ማስተላለፍ የፈለጉት መል
ክት አጭርና ግልጽ ነው ። የአንድ ሕዝብ
ዕድገት ወይም ውድቀት በአንዳንድ ደህና
ወይም መጥፎ ሰዎች እንደማይወሰን ፤ ልማ
ትንም ሆነ ጥፋትንም የሚወስነው ሕዝቡ
እራሱ እንደሆነ ለማሳየት መፈለጋቸው
ግልፅ ነው ። ነጋድራስ በዚህ ብቻም አልተ
ገቱም ። ሕዝቦችን ሁሉ የሚፈጥር አንድ
አምላክ ነው ካሉ በኋላ «ይህም አምላክ
የምንለው የሕዝቦች ፈጣሪ» ይላሉ ፤ ለሕዝ
ቦች የሚያስፈልጋቸውን ነገር ሁሉ ከሙሉ
ፈቃድና ሥልጣን ጋር በጃቸው ሰጥቷቸዋ
ልና አንድ ሕዝብ ቢለማም ቢጠፋም በገዛ
እጁ ስለሆነ እንደህብስተ መና ከሰማይ የሚ
ወርድ የለምና ወደላይ ከማንጋጠጥ ወደታች
መለስ ብለን መፍትሔ መሻት እንዳለብን
ገልጸዋል ። ነጋድራስ የሕዝቦች ፈጣሪ
ያሉት አምላክ ሕዝቦችን እንዴት እንደ
ፈጠረ ብዙ ለመስበክም አልቃጣቸውም ።
ይልቁንም ፤

«ሰው ለምን እንዲፈጠር ፤ ለምንስ እንዲሞት
እንዲህ ነው ለማለት ግን ሥራችን አይደለም ።
ሰው ሁሉ ለራሱ የሃይማኖት ካህናት አሉ
ትና ከነዚያ ይጠይቅ ፡፡»[6]

ብለው ፥ ይህንን ነጥባቸውን ከገቱ በኋላ እርሳ
ቸው ለማውሳት የፈለጉት ምንስ ሕዝቦች
ዘራቸው ፤ ቋንቋቸውና ሀይማኖታቸው የተ
ለያየ ቢሆን ፤

«አስማምቶ የሚያስኪደው ሥርዓት ግን
መሠረቱ አንድ ነው ። ሕዝቦች ሁሉ የሚ
ፈጠሩ በዚህች ምድር ላይ ነው ሁሉም
ምድር የምትሰጠውን ሲሳይ ለማግኘት ይጥ
ራሉ ፡፡»[7]

በማለት የአንድ ኅብረተሰብ እድገት መሠ
ረት የማምረት ተግባር መሆኑን ያስቀም
ጣሉ ። በዚህ ረገድ ምንም እንኳን ነጋድ
ራስ የማምረትን ተግባር በማኅበራዊ አን
ጻሩ ከመመልከት ይልቅ ኤኮኖሚያዊ ንድፈ
ሐሳቦቻቸውን ከግለሰብ በመነሳት ለማሳ
የት የሚሞክሩ መሆናቸውን ወደፊት የም
ናይ ቢሆንም ፥ የኅብረተሰብ እድገት በልዩ
መለኮታዊ ኃይል ፈቃድና በጥሩ ወይም
መጥፎ ግለሰቦች ባህርይ ላይ የማይመረኮዝ
መሆኑን ለማስተማር መሞከራቸው አንዱ
ጉልህ አስተዋጽኦአቸው ነው ። ከላይ ከጠ
ቀስነው አባባልም ሆነ ወደፊት ከምንጠ
ቅሳቸው ሌሎች አባባሎቻቸው በግልጽ
መረዳት የምንችለው ነጋድራስ በመጽሐፋ
ቸው ውስጥ ያስተላለፉዋቸው መልእክቶ
ችን በወቅቱ ከነበረው ሁኔታ ጋር በማዛመድ
ምናልባት ችግር ሊያስከትሉ ይችላሉ ብለው
የሚገምቱዋቸውን ነጥቦች ማስወገዳቸውን
ነው ። ለዚህም ከላይ ባየነው ጥቅስ«ሕዝቦች
ለምንስ እንዲፈጠሩ ፤ ለምንስ እንዲሞቱ
ሆነ» የሚለውን ጥያቄ መልስ እራሳቸው
ከመስንዘር ይልቅ የተለያዩ ሀይማኖቶች
ካህናት የሥራ ድርሻ አድርገው ራሳቸውን
ከጥያቄው ለማግለል መጣራቸው በቂ ምስ
ክር ነው ። በዚህ ዓይነት ተመሳሳይ ስልታዊ
አቀራረባቸው ሰው በምድር ላይ ለምን
ያህል ጊዜ እንደኖረ የአውሮፓን ሊቃውንት
ጥናት ውጤት መሠረት በማድረግ በማስ
ረጃ እየደገፉ ከ135ሺ ዓመት በላይ የሆን
መሆኑን ከጠቀሱ በኋላ ይህ መጽሐፍ
ቅዱስ ውስጥ ከተጠቀሰው ጋር የሚፈጥረ
ውን ግጭት አንስተው እንደ አውሮፓ ሊቃ
ውንት አባባል በእግዚአብሔር ዘንድ አንድ
ቀን በሰው ዘንድ ሺ ዓመት ነው በማለት
ትንሽ ካፌዙ በኋላ ፈጥነው ራሳቸውን ከዚህ
ዓይነቱ አባባል ለማግለል ፤

«ከዚህ በላይ የተጻፈውን ነገር ሁሉ እውነት
ይሁን አይሁን ለመከራከር ግን ለኛ አያስ
ፈልግም ። እኛ ይህንን አጭር ቃል መጻፋ
ችን የሕዝብ አስተዳደር መሠረት ምን እንደ
ሆነ ለማሳየት ነውና እንዲህ ዓይነት ክርክር
በሐሳባችን አይገባም ፡፡»[8]

ሲሉ ይዘጉታል ። እኛም የዚህን መጽሐፍ
ግምገማ ስናደርግ ከላይ በተጠቀሰው ረገድ
በተወሰኑ ጥያቄዎች ላይ የራሳቸውን አቋም
የማድበስበሱን ጉዳይ ማንሳታችን ባጠቃ
ላይ በመጽሐፋቸው ውስጥ ያስተላለፉዋ

INFINIX HOT 8 | 13MP
AI TRIPLE CAMERA

ቸውን መልእክቶች ለመረዳት ስልታዊ የሆነ አቀራረባቸውን መገንዘብ አስፈላጊ መሆኑን ለመጠቆም ነው ። ወደሌላ ነጥባቸው ከማለፋችን በፊት እዚህ ላይ መነሳት ያለበት ሌላው ጉዳይ ከላይ የጠቀስነውን መልእክት ካስተላለፉ በኋላ በመጽሐፋቸው ውስጥ በሚያነሷቸው ነጥቦች ለመጽሐፋቸው ከሰጡት ርዕስ ማለትም የሕዝብ አስተዳደር ጋር እንዲያያዝላቸው ፤

«የሕዝብ አስተዳደር ትምህርት ሲባል ሕዝቦች የሚለሙበትንና የሚጠፉበትን መንገድ የሚያሳይ ትምህርት ነው ፤»[9]

ሲሉ ማስቀመጣቸውን ነው ። የነጋድራስ መጽሐፍ የኢኮኖሚ ንድፈ ሃሳቦችን በማብራራት ላይ ያተኮረና በመሠረቱ የፖለቲካዊ ኢኮኖሚ መጽሐፍ ሆኖ ሳለ ራሱን የቻለ የጥናት መስክ ወይንም ዲስፕሊን ከሆነው አስተዳደር ተውሰው «መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር» የሚል ስያሜ መስጠታቸው በወቅቱ በቂ ምክንያት ያለው ይመስለኛል ። ይኸውም በመጽሐፋቸው ውስጥ ያስተላለፉዋቸውን መልዕክቶች ሥራ ላይ እንዲያውሉላቸው ይፈልጉ የነበሩት ሻል ይላሉ ብለው የሚገምቱዋቸው የፊውዳሉን የገዥ መደብ አባላት ስለነበር ፣ ምናልባት ለመጽሐፋቸው ቀጥታ የሆነውን ተገቢ ስያሜ ቢሰጡት ከሚያስከትለው ውጤት ይልቅ «መግዛት» «ማስተዳደር» «መምራት» በሚሉት ከሕጻንነታቸው ጀምሮ እንዲሠረጽባቸው በሚደረግ ፣ የገዥነት ስሜትን በሚያንጸባርቁ አባባሎች አኳያ መቅረቡ ምናልባት ወደመጽሐፉ እንዲጠጉ ሳያደርጋቸው አይቀርም በሚል ምክንያት ይመስላል ። ደግሞም የመጽሐፉ ይዘት በውጫዊ መልኩ ከወሰደው ርዕስ ጋር ያለውን ያለመጣጣም ስንመለከት ይህንኑ እንድናምን ያስገድደናል ። ነጋድራስ ቀጥለውም አንድ ሕዝብ እንዴት እንደሚበለጽግ ለማሳየት ፤

«አንድ ሰው ከነሚስቱ ለብቻው ተለይቶ ለብቻው ሌላ አጋዥ ሳይኖረው መሣሪያም አልባ ሆኖ ወዳንድ የባህር ደሴት መሰደዱን እናስብ ፤»[10]

ብለው ከጋበዙን በኋላ ቀስ በቀስ እንዴት የሰው ቁጥር እየጨመረ እንደሄደ ፣ መሣሪያዎች እየተሻሻሉና የሥራ ክፍያም እየተደረገና ምርትም እያደገ እንደመጣ ሊያሳዩን ይሞክራሉ ። በማያያዝም የዚህ ዓይነቱ ጤናማ የዕድገት ጉዞ በተለያዩ ምክንያቶች በመናጋቱ አንድ ሕዝብ እንደሚደኸይ ያወሳሉ ። የእድገት እንቅፋቶች ናቸው ብለው ነጋድራስ ወደሚያነሱአቸው ነጥቦች ከመራመዳችን በፊት ቀደም ሲል ወደጠቀስነው የነጋድራስ አቀራረብ ብንመለስ አንድ ጉልህ ነጥብ እናገኛለን ። ይኸውም ነጋድራስ እንድናሰላስል ስለሚጋብዙን አጋዥ የሌለው ሰው ሁኔታ ከ18ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ጀምሮ በተለያዩ ዲስፕሊኖች ማለትም በፍልስፍና፣በፖለቲካዊ ኢኮኖሚና በሌሎች ልዩ ልዩ የጥናት መስኮች ሁሉ ላይ የተንጸባረቀው ቁልጭ ያለ ሮቢንሰናይድ አቀራረብ ነው ። የዚህ ዓይነቱ ከግለሰብ የመነሳት አቀራረብ ከላይ የጠቀስነው ሮቢንስናይድ የሚል ስም ያገኘው ዳንኤል ዴፎይ የተባለ ደራሲ «ሮቢንስን ኩሩስ» በሚል ስያሜ ከጻፈው ልብ ወለድ ታሪክ ነው ። ይህ መጽሐፍ አንድ ግለሰብ እንዴት ኑሮውን በአንድ ደሴት ውስጥ ለብቻው ማሸነፍ እንደቻለ የሚተርክ ነው ። ታዲያ ይህ ልብወለድ ታሪክ በፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ግምገማ ረገድ ያስከተለውን አመለካከት ብናጤን ፣ የኢኮኖሚ ሕጎችን ነባራዊ በሆኑ ማኅበራዊ ግንኙነቶች ክልል ውስጥ ለማጥናት ከመሞከር ይልቅ የማምረትን ተግባር ማኅበራዊነት በመካድ ግለሰቦች በተናጠል እንደሚያካሂዱትና፣ግለሰቦች ከተፈጥሮ ጋር ባላቸው ግንኙነት አንጻር ብቻ መታየት እንደአለበት ለማሳመን መሞከሩ ነው ። የዚህ ዓይነቱ አቀራረብ መሠረታዊ ስህተት ከላይ እንደተጠቀሰው የኢኮኖሚ ሕጎችን ምንጊዜም ማኅበራዊ ከሆነውና በተለያዩ የኅብረተሰብ የእድገት ደረጃዎች ውስጥ ከሚገኙ ተጨባጭ ታሪካዊ ሁኔታዎች ጋር በተያያዘ መንገድ ለማጥናት ከመሞከር ይልቅ በግምት ላይ የተመረኮዘ ሞዴል ፈጥሮ ወደ ሃሳባዊነት መዘፈቅን ማስከተሉ ነው ። ለዚህም ነው ካርል ማርክስ የዚህ ዓይነቱ አስተሳሰብ «ከኅብረተሰብ ተገልሎ አንድ ግለሰብ ቋንቋ ያውቃል የማለትን ያህል አስቂኝ ነው» ሲል የተቸው ። ነጋድራስም በጊዜው ጎልቶ ይስተጋባ ከነበረው ከዚህ ዓይነቱ ስህተተኛ አቀራረብ ተፅእኖ ውጪ ሊሆኑ ባለመቻላቸው በመጽሐፋቸው ውስጥ ያሰፈሩዋቸውን ኢኮኖሚያዊ ንድፈሃሳቦች ለማብራራት በተደጋጋሚ ሲያወሱት ይታያሉ ። ይህ ሙከራ

INFINIX HOT 8 | 13MP
AI TRIPLE CAMERA

ቸው በመጽሐፋቸው ውስጥ ከሚታዩ ጉልህ ስህተቶች አንዱ ሲሆን ፤ በሌላ በኩል ግን ይህ ስህተታቸው ደግሞ ነጋድራስ በፖለቲካዊ ኢኮኖሚ አስተሳሰባቸው ምንም አንዳንድ የራሳቸው የሚመስሉ ሃሳቦችም አልፎ አልፎ የሰነዘሩ ቢሆንም ፤ ባጠቃላይ ግን በክላሲካል ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ክልል ውስጥ የሚመደቡ ወይንም ባብዛኛው የክላሲካል ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ደቀመዝሙር መሆናቸውን በገሃድ ያሳያል ። እንግዲህ በአቀራረብ ወይንም በአጠናን ዘዴ ረገድ ያለውን ስህተትና ምንጩን ካየን ዘንድ ቀደም ሲል ነጋድራስ ለተባለው እድገት እንቅፋት ናቸው ብለው ወደተናገሩአቸው ነጥቦች ስንመለስ ፤

«ካየርና ከመሬት ክፉት የሚበልጥ በምድር ላይ ለሕዝቦችም ኑሮ እንቅፋት የሚሆን ሊላ ነገር አለ ። ርሱም ሽፍታና ጦርነት ነው ።»[11]

«ጦርነትን የሚያነሱ ነገሥታቱን አለቆች ሁሉ ልባቸው ሃብት እንደ ፈለገ አይገልፁም፤ ዳሩ ግን ስም ለመፈለግና ለማግኘት ወይም ሃይማኖትን ለማስፋፋት ወይም የተጠቃውን ለመርዳት አስመስለው ይነሳሉ ። የጦርነቱ ሁሉ ርጳሚና ምኞት ግን መዝረርና ማስገበር ነው ፤»[12]

ሲሉ አስቀምጠውታል ። ይህም የሚያስከትለውን ሲጠቁሙ ፤

«ያንዱን ትንሽ አገር ንጉሥ ሌላው እየጠቀለለው ይሄዳል ። በውስጣቸውም በግዳይና በዘረፋ የባሰውን እያዩ፤ራስ ፤ ደጃዝማች እያሉ ይሾማሉ ፤ የነገሡበትንም አገር ለነርሱ ያካፍላሉ ፤ የቀረው ሁሉ የነዚህን ማዕረግ እያየ ስምና ሹመት አገኛለሁ እያለ በሕዝቡ ውስጥ ያለው እያንዳንዱ ሰው በግዳይና በዘረፋ እንዲመሰገን ይጥራል ። ጦርነቱም ከዱሮ የባሰ ይሆናል ፤»[13]

በማለት በጊዜው ገዳይና ዘራፊ ተንሰራፍቶባት በነበረችው ኢትዮጵያ ውስጥ ሆነው በከፍተኛ ጀግንነት አብራርተዋል ። እንዲያውስ ፤

«ሰውን ፈርቶ እውነቱን የሚሸሽግ ሰው እንደ ወንድ ይቆጠራልን?»[14] ብለው የለ።

ነጋድራስ ቀጠል አድርገው ፊውዳሎች ለራሳቸው ጥቅም ሲሉ ነውና የሚያጫርሱህ መሣሪያ አትሁን በማለት አስተምረዋል ።

«ገባሮቻቸውን እያተራረዱ ቀሮዎቹ ርስበርሳቸው በፍቅር ለመላላክ አይመለሱም»[15]

በመሠረቱ ነጋድራስ አንድ አለ የሚሉትን ብቸኛ የእድገት ጎዳና የሚያጨናግፉ ሌሎች ምክንያቶችና መፍትሔ ይሆናሉ ብለው የሚያስቡትን በመጽሐፋቸው ውስጥ የሰነዘሩ ቢሆንም ፤ ጦርነትን ግን እንደዋንኛ የዕድገት እንቅፋት በተለየ ትኩረትና ግልፅነት ማስቀመጣቸው በተለይ ከ18ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ በመሳፍንት መካከል ለበላይነት ይደረግ የነበረ መናቆር በኢትዮጵያ ያደረሰው ውድቀት ግንዛቤ ያስከተለው አቋም ይመስላል ። ነጋድራስ ኢትዮጵያ በእንደዚህ ዓይነት ጦርነቶች የተነሳ በአክሱም የሥልጣኔ ዘመን ከደረሰችበት ዕድገት እንዴት እያቆለቆለች እንደመጣችና አንዳንድ ነገሥታት ግን ሁኔታውን ለመለወጥ ጥረት ቢያደርጉም ይበልጡኑ ተጠያቂ የሚሆኑበትን ድርጊቶቻቸውን ታሪክ ጸሐፊዎች ነን ባዮች በትክክል ከማሳየትና ካለው ስህተት ትምህርት የሚገኝበትን መንገድ ከመጠቆም ይልቅ ለሆዳቸው ያደሩ ጭፍን አወዳሾች እንደሆኑ ፤

«አጤ ምኒልክና ኢትዮጵያ» በተሰኘው መጽሐፋቸው ውስጥ በከፍተኛ ብሔራዊ ቁጭት ሲያወሱ ፤

«- - - ከድካሙም በኋላ አክሱማውያን ተብለው የደረሱበትን የክብረት ከፍታ ቀጥለውም በሃይማኖት ልባቸው ተለያይቶ መጀመሪያ አርመናችና ፈላሾች ሁለተኛም ፈላሾችና ክርስቲያኖች ቀይተውም ክርስቲያኖችና እስላሞች እየተባባሉ እርስ በርሳቸው ተፋጅተው ዝቅ ብሎ ጠፍቶ የነበረው መንግሥታችን ባባ ታጠቀ ቴዎድሮስ ሲታደስ በወሬሳው ካሣም ሲዋሃድ እንዴት እንደ ነበረ ባባ ዳኘው ምኒልክም እንዴት አርጎ ሰፍቶ እንደረጋ ገልጾ የሚያዋጋን የታሪክ ጸሐፊ ከቶ መቼ ይወጣ ይሆን ?»[16] ብለዋል ።

ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው ድክመትንና ጥንካሬን በማነጻጸር በትክክል ከማስ

ቀመጥ ይልቅ ያልሆነውን ሆነ ብለው ፍሬ ከርስኪውን ሁሉ መተረኩ የተለመደ መሆኑን ፤

«እንደአገራችን ሰው ትምህርት የሌለው ሕዝብ እውነቱን ሊሰማ አይወድም ፤ ቢሰማም አይገባውም አንድ ንጉሥ እንዲህ አድርጎ ጥሮ ነገሠ ፥ ከነገሠም በኋላም በእንዲህ ያለ ነገር ወደቀ ወይም ለማ ከሚሏቸው ይልቅ እገሌ ከሰማይ ወይም ከጠንቋይ እንደዚህ ያለ ትንቢት መጥቶለት ለመንግሥት የተወለደ ሰው መሆኑን አውቆ ታውቆ እገሌና እገሌ ታጠቁለት ። እገሌና እገሌም ሰይጣን አስተዋቸው ተዋግተውት አሸነፉቸው ። ነገሠም ፤ ከነገሠም በኋላ እገሌ ቅዱስ ወይም ናዝራዊ መክሮት ይህንን አደረገ ፤ ከሰይጣንም በፍቅር እንዲህ ያለ ጉዳት ወረደበት ፤ በፍካሬ የሱስ የተነባውም ጊዜያቱ ተፈፅሞ ሞተ ብለው ቢዋሹላቸው ይወዳሉ ፤»[17] በማለት ገልጸዋል ።

እዚህ ላይ ዛሬም በአብዮታችን ሂደት ውስጥ በየጊዜው የሚወሰዱ እርምጃዎች ካገራችን ተጨባጭ ታሪካዊ ሁኔታ የመነጩና የማይቀሩ የታሪክ ግዴታዎች መሆናቸውን መዋጥ እያቃታቸው ሺ ጊዜ ፍካሬ የሱስን እየጠቀሱ ለሚያላዝኑ ደናቆርት በነጋድራስ ምህረት ዬለሽ ቃል ቡራኬ ፍትሀታቸውን ያገኙ ዘንድ ልቦና ይሰጣቸው እያልን ወደ ነጋድራስ አባባል እንመለሳለን ።

እነዚህ የታሪክ ጸሐፊ ነን ባዮች ነገሥታትን ያወደሱ እየመሰላቸው የጻፉዋቸውን ግስንግስ ገድሎች እንደጻፉት አርገን ከተመለከትነው ግን በዓለም ላይ ከነገሡት ነገሥታት መካከል እንደ ኢትዮጵያ ነገሥታት ደካሞች የሉም የማለት ያህል መሆኑን ብልህነት በተሞላበት መንገድ ሲተረጉሙት ፤

«ጉልበተ የሌለው ብዙ ንጉሥ ኑሮዋል ። ይኖርም ይሆናል ። ነገር ግን የታሪካችን ቃል እውነት ከሆነ ዘንድ እንዲሁ በብዙ የቅዱሳንና የአጋንንትን ርዳታ እንደ ኢትዮጵያችን ነገሥታትና ገዢዎች የሚያስፈልገው ሰው በዓለም ታሪክ ከቶ አልተሰማም ፤»[18] በማለት ይተቻሉ ።

እንግዲህ ከላይ እንዳስቀመጥኩት ነጋድራስ ከኖሩበት ዘመን ጥቂት መቶ ዓመታት ጀምሮ በኢትዮጵያ ውስጥ በነገሥታት መካከል በየጊዜው ይደረጉ የነበሩ ጦርነቶች ብዛትና በሕዝቡ ላይ ያስከተለውን ችግር መገንዘብ ነጋድራስ ጦርነትን እንደዋነኛ ፀረ እድገት መሰናክል አድርገው እንዲያቀርቡት አድርጓቸዋል የሚል እምነት አለኝ ። እዚህ ላይ አንድ መጤን ያለበት ነገር አለ ። ይኸውም በግርድፉ ሲታይ የሚቃረኑ የሚመስሉ አባባሎች ስለመኖራቸው ጉዳይ ነው ።

እነዚህም ከላይ ቀደም ሲል ነጋድራስ ስለ ማንኛውም ጦርነት ዓላማ ሲገልጹ ምንም እንኳን ውጫዊ መልኩ የተለያየ ቢሆንም ዓላማው ዘረፋ መሆኑንና በዚህ ረገድ የትኛውም ንጉሥ ከየትኛውም እንደማይለይ ሲያስቀምጡ በሌላው በኩል ግን ለእነ አጼ ቴዎድሮስ ያላቸው የተለየ አስተያየት ከዚህ ጥቅል አባባል ጋር የሚጋጭ መምሰሉ ነው ። ታዲያ ይህንን ነጥብ በሚገባ ለመረዳት ፥ ነጋድራስ በመጽሐፋቸው ውስጥ ያነሱዋቸውን ሌሎች ነጥቦችና የነዚሁ ነጥቦች ምንጭ በማየት ለማብራራት መሞከሩ ከላይ የተጠቀሱትን የአባባሎች ተቃርኖ ለመፍታት ብቻ ሳይሆን ፤ በአጠቃላይ ነጋድራስ ምንን በማን ለማሠራት እንደፈለጉ የሚያሳይ ስለሚሆን ዘርዘር ባለ መንገድ ለማየት እንሞክራለን ።

ከላይ አልፎ አልፎ እንዳየነውና ወደፊት በሚገባ ለማየት የሚቻለው ነጋድራስ ቁልጭ ያለ ፀረ ፊውዳል አቋም ያላቸው ግለሰብ መሆናቸውን ነው ። የቆሙለትን አቢይ ዓላማም ስናጤን ብሔራዊ ካፒታሊዝም በኢትዮጵያ ሊያድግ የሚችልበትን መንገድ መሻት ነው ። በወቅቱ ለዚህ ዓላማ መቆም ማለት የፊውዳሉን የፖለቲካና የኢኮኖሚ የበላይነት ለማስወገድ መቆም ማለት ነው ። ነጋድራስ ግን በኢኮኖሚው መስክ ወደፊት እንደምናየው መሬት ለሕዝቡ እንዲከፋፈል በመሟገት የፊውዳሉን ሥርዓት ኢኮኖሚያዊ መሠረት ለመናድ ሲሹ ፥ ይህንን ለማድረግ የፖለቲካ ሥልጣኑ ግን በፊውዳሎች እጅ እንዳለ ሊከናወን የሚችል አድርገው ይገምታሉ ። እዚህ ላይ ምናልባት ሊጠቀስ የሚገባው ነጋድራስ በወቅቱ በኢትዮጵያ ተመስርቶ የነበረው ባንክ ኦፍ አቢሲኒያ በሞኖፖሊ መቋቋሙ የሚያስከትለውን ጉዳት አስታከው ፤

«ለሰው አውራ ቀስቃሽ ግን ባላንጣ ነው ፤»[19] ሲሉ ያስፈሩት

ቃል ፀረ ፍጹማዊ ዘውድ አገዛዝ አቋም ያላቸው ለመሆኑ በቂ ፍንጭ ሲሆን፣ ጽሁፋቸውን ባጠቃላይ ስንመለከት ግን ይህን አቋማቸውን ለሪፐብሊክ መመስረት በቀጥታ ከመቆም ይልቅ ነገሥታቱን ራሳቸውን በመጠቀም ለካፒታሊዝም ማደግ መቆሙ የተሻለ ነው ብለው የሚያምኑ ይመስላሉ ። ይህንን ግምት የበለጠ እንድናጠናክር የሚያደርገን ይበልጡኑ ዝንባሌያቸው የየትኛውን አገር ፈለግ መከተል እንዳለብን ደጋግመው የሚጠቅሱትን ስናጤን ነው ።

ይህንኑ በሚገባ ለማየት ነጋድራስ ስለ መንግሥት ያላቸው አመለካከት ምን እንደ ሆነ በቅድሚያ መመልከት ጠቃሚ ይሆናል። እንደነጋድራስ አባባል ፤

«አስተካክለን ካሰብን ዘንድ መንግሥት መቆሙ ለሕዝቡ ሁሉ ጥቅም ነው ። መንግሥት ሕዝቡን ሁሉ በትክክል ለመጥቀም ካላሰበ መንግሥት በዙፋኑ ሊቆም አይችልም ። ላንዱ ነገድ ወይም ለጥቂት ሰዎች ብቻ ማድላት ለመንግሥት የሚገባ ሥራ አይደለም ።»[20]

እዚህ ላይ እንደምንመለከተው መንግሥት በኅብረተሰቡ የተለያዩ የእድገት ደረጃዎች የኢኮኖሚና የፖለቲካ የበላይነት ያላቸው መደቦች ተቀናቃኝ መደቦችን ለመጨቆን እንደሚጠቀሙበት መሣሪያ ሳይሆን በኅብረተሰቡ ውስጥ ካሉ መደቦች ውጪ ያለና ለሁሉም መደቦች እኩል የሚያገለግል አድርገው የሚመለከቱት መሆናቸውን ነው ። ከዚህ አመለካከታቸው በመነሳት ነው ፊውዳሎች የፖለቲካ ሥልጣኑን በያዙበት ሁኔታ ስር ካፒታሊዝም ሊያድግ የሚችልበት ሁኔታ እንዲፈጠር የጣሩት ። ለዚሁም አስተሳሰባቸው በጃፓን እ. አ. አ. በ1868 ገደማ የነበረው ሁኔታ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳደረገ በመጽሐፎቻቸው ውስጥ በግልጽ ይታያል ።

እ. አ. አ. በ1868 በጃፓን ሾጌኔት በመባል በሚታወቅ የአካባቢ ፊውዳሎች እጅ ተበታትኖ የነበረው የፖለቲካ ሥልጣን ወጣት መሳፍንት የሜጂ ተሀድሶ (Meiji-Restoration) ተብሎ በሚታወቀው እንቅስቃሴያቸው ለማሰባሰብ መቻላቸውና ፤

1ኛ/ የአካባቢ ፊውዳሎችን የግዛት ድንበር በማፍረስ አዲስ የማዕከላዊ አስተዳደር ድንበሮች መመሥረታቸው ፤

2ኛ/ ከአውሮጳ አገሮች ጋር ያለውን የንግድ ግንኙነት በማቋረጥ ብሔራዊ የካፒታሊስት የምርት ተቋሞች የሚመሠረቱበትን አመቺ ሁኔታ መፍጠራቸውና ፤

3ኛ/ በመሬት ላይ ያለውን የጕሳ ባለቤትነት በማስወገድ መሬት በግል ተይዞ መሸጥ መለወጥ እንዲቻልና የመሳሰሉትን ለካፒታሊዝም እድገት አመቺ ሁኔታ የሚፈጥሩ እርምጃዎችን በመውሰድ በጃፓን ካፒታሊዝም እንዲያድግ ማድረጋቸው በነጋድራስ አስተሳሰብ ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ ያለው ይመስላል ። ይህንንም ከጽሁፋቸው ጋር በማዛመድ ለመመልከት ያህል ፣ አጤ ምኒልክና ኢትዮጵያ በተሰኘው መጽሐፋቸው ውስጥ ፤

«የዚህ ዓለም ንግሥት በድሮ ዘመን ድንቁርና ነበረች ። ዛሬ ግን የማትቻል ብርቱ ጠላት ተነሳችባት ፤ እርስዋም የኤሮፓ አእምሮ ትባላለች ። ለርስዋም ቤቱን የሚከፍት ክብረት ይጨምራል ፤ ቤቱን የሚዘጋባት ግን ይደመሰሳል ። ኢትዮጵያችን የኤሮፓን አእምሮ የተቀበለች እንደሆነ የሚደፍራት ጠላት የለም ። ያልተቀበለች እንደሆን ግን ትፈርሳለች ወደ ባርነትም ትገባለች ። በዚህ ምክንያት ክቡር ወልዑል ያጤ ምኒልክ ወራሽ የጃፓን መንግሥት እንደት እንዳደረገ አስመርምረው መንገዱን እንዲከተሉት ተስፋ እናድርግ ፤»[21]

ሲሉ የጠቀሱትንና «መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር» በተሰኘው መጽሐፋቸው ውስጥ ስለአውሮፓ አገሮች ኃያልነት ካወሱ በኋላ ፤

«መላው ዓለም ለነሱ ሰግዷል ። ከጃፓንና ከቱርክ ከሺናም (ቻይና) ከሲያም ከኢትዮጵያ ነገሥታት በቀር ዛሬ ዓለም ሁሉ በመላው ቅኛቸው ሆኗል ። ከነዚህም እስከ ዛሬ አርነታቸው ከቀየላቸው ነገሥታት አለ ጃፓን የቀሩት ነገሥታት አርነት አላቸው ቢባል ለስም ብቻ ነው ፤»[22]

INFINIX HOT 8 | 13MP
AI TRIPLE CAMERA

ሲሉ ያስፈሩትን መጥቀሱ ብቻ ይበቃል ። ነጋድራስ ለአጤ ምኒልክ ወራሽ ስለ አውሮፓ ኃያልነትና እድገት አውስተው ምሳሌነቱን ግን ከጃፓን እንዲከተሉ መጠየቃቸው ያለምክንያት አይደለም ። ቀደም ሲል የተጠቀሰው በጃፓን ለካፒታሊዝም እድገት አመቺ ሁኔታ የተፈጠረው ነገሥታቱ በፖለቲካ ሥልጣን ላይ እያሉ በመሆኑ የኢትዮጵያ ንጉሥ የበለጠ ይህን መንገድ ወደ መቀበል ሊያዘነብሉ ይችላሉ የሚል ግምት የነበራቸው ይመስላል ።

በተረፈ ከላይ በተጠቀሰው የነጋድራስ አባባል ውስጥ የሚገኘው ሌላው ከፍተኛው ቁምነገር ማለትም ስለ ይስሙላ አርነት የሰነዘሩትን በስፋት በሚቀጥለው የዚህ ጽሑፍ ሁለተኛ ክፍል ስለምንመለስበት አሁን በዚሁ እያለፍን ከላይ ያነሳናቸውን ሐሳቦች ለማጠቃለል እንሞክራለን ። ነጋድራስ ባንድ በኩል ፀረ-እድገት የሆኑ ጦርነቶችን ቀስቃሽ የሆኑ ነገሥታት ዓላማ ዘረፋ መሆኑን በጥልቅ አስቀምጠው በሌላ በኩል ለአንዳንድ ነገሥታት አድናቆት ያላቸው መሆኑ የሚቃረን ሳይሆን በመሠረቱ በተያያዘ መልኩ ነጋድራስ ዓላማቸው በጊዜው ተራማጅ የሆነ ግን ዘረፋ የማይቀርበት ካፒታሊዝም ባገራችን እንዲያድግ በመሆኑና ይህንኑ ሥራ ላይ ለማዋል ነገሥታቱን መጠቀም ይቻላል የሚል እምነት ስለነበራቸው ይመስላል ። በዚህ እምነታቸውም ላይ የጃፓን ሁኔታ ከፍተኛ ተጽእኖ ያለው መሆኑም ግልጽ ነው ። ባጭር አነጋገር ጦርነት ቀስቃሽ የሆኑ ነገሥታት ዘራፊነትና ገዳይነትን ያወሱበት የጽሑፋቸው ክፍል ሲታይ፣ ፀረ ፊውዳል አቋማቸውን ሲያሳይ ፤ እነአጼ ቴዎድሮስን ያደነቁበት የጽሑፋቸው ሌላው ክፍል ደግሞ በነዚሁ ነገሥታት ተጠቅመው ለካፒታሊዝም እድገት አመቺ ሁኔታ ለመፍጠር የቆሙ መሆናቸውን ያሳያል ። ደግሞስ ነጋድራስ እንዲዳብር በሚፈልጉት የካፒታሊስት ሥርዓት ውስጥ ዘረፋ የማይቀር መሆኑን ከመገንዘብ ወይም ሐሳባቸውን እንዲቀበሉላቸው የሚፈልጉት ነገሥታት የሳቸውን ሐሳብ ቢቀበሉ ዘረፋ አይቀርብንም ብለው እንዲጽናኑ ፤

«ይህንንም ስላልን እውቀታቸው የሰፋ ነገሥታትም ቢሆኑ መዝረፍን አይተውም ። አዘራረፋቸው ግን የእውቀት አዘራረፍ ነው ፤»[23]
በማለት ተችተዋል ።

እስካሁን ነጋድራስ አንድ ሕዝብ ሊያድግ የሚችልበትን አንድ ብቸኛ መንገድ ለማሳየት ሲሉ ፤ አንድ ካለሚስቱ በስተቀር አጋር የሌለውን ሰው ሁኔታ እንድናስብና እንዴት እየተራባና በኋላም ሀብቱ እየዳበረ እንደሄደ ካወሱን በኋላ በልዩ ልዩ መስናክሎች በተለይም በጦርነት የተነሳ እርሳቸው ስለአጋር የለሹ ሰው ታሪክ እንደተረኩልን ሁኔታዎች ተስተካክለው እንደማይጓዙ ለማሳየት ባደረጉት ጥረት ላይ ያለንን አስተያየት ነው ። ቀጥለው ነጋድራስ ማሳየት የሚፈልጉት የዚህ እድገት መሠረት ምን እንደሆነ ነው ። ይህ ጥያቄ በተለያዩ ወቅቶች በተለያየ የፖለቲካ ኤኮኖሚ አስተሳሰብ ክልል ውስጥ የሚጠቃለሉ ምሁራን በተለያዩ መንገዶች ለመመለስ ጥረት ያደረጉበት መሠረታዊ የፖለቲካዊ ኤኮኖሚ ጥያቄ ሆኖ ቆይቷል ። ነጋድራስ ይህንን ጥያቄ ለመመለስ እንዲያስችላቸው በቅድሚያ የስራ ሚዛንና የዋጋ ትርጉም ምን እንደሆነ ሲያሳዩ ፤

«የማናቸውም ነገር ዋጋ ሲገመት ያ ነገር እስኪገኝ ያለው ድካም ሁሉ እንደመገመት ያህል ነው ፤ ወይንም በሌላ አነጋገር ፤ ዋጋ ማለት የሥራ መለኪያ ማለት ነው ፤»[24]

በማለት ይገልጻሉ ። ይህንኑ ለማብራራትም አያሌ ምሳሌዎችን ያስቀምጣሉ ። ከነኚህም ነጥቡን በደንብ ለማየት እንዲያስችሉን አንዳንዶቹን ብንጠቅስ ፤

«ወዳንድ አገር መንደር ብንሄድ ከዚህም አንድ በርኖስ ሰፊና አንድ ገበሬ ሲገበያዩ ብናይ ባለበርኖሱ ስድስት ቀን የደከመበትን በርኖሱን ለገበሬው ሲሸጥ ስድስት ቀን የተሠራበትን እህል ይፈልጋል ። ማለት የበርኖሱ ሽያጭ የበጉን ጸጉር ቀርጦ ነድፎ ፤ ፈትሎ በርኖሱን ሠርቶ እስኪጨርስ ድረስ ስድስት ቀን የፈጀበት እንደሆነ ገበሬውም ይህንን በርኖስ ለመግዛት ቢፈልግ አርሶ ጉልጉሎ አርሞ አጭዶ ወቅቶ በስድስት ቀን ሊሳብ ያገባውን እህል ለባለበርኖሱ ይሰጣል ።»[25]

እንግዲህ ይህ ነጋድራስ ያስቀመጡት እሴት የሥራ መለኪያ የመሆኑ ጉዳይ በኤኮኖሚያዊ አስተሳሰብ እድገት ታሪክ ውስጥ ሰፋ ያለ ቦታ ያለውና ከብዙ መቶ ዓመታት በፊት በጥንታዊት ግሪክ ውስጥ በነበሩ እንደነአርስቶትልና ፕላቶ በመሳሰሉት ፈላ

INFINIX HOT 8 | 13MP
AI TRIPLE CAMERA

ስፎች ባልተሟላ መልኩ ተሰንዝሮ ፤ በኋላም እስከተወሰነ ደረጃ ድረስ በ14ኛው ምእተ ዓመት አካባቢ እንደነአልበርት ማግኑስና ቶማስ አኩዊናስ ባሉት እንዲሁም በአብዱልራህማን ኢብን ከልዱን በመጠኑ ከተዳሰሰ በኋላ በ17ኛው ክፍለ ዘመን ከካፒታሊዝም እድገት ጋር ፖለቲካዊ ኤኮኖሚ ራሱን የቻለ ሳይንስ በሆነበት ወቅት የቡርዧው ክላሲካል ኤኮኖሚ መስራች በሆነው ሥር ዊሊየም ፒቲ የተነደፈ ንድፈ ሐሳብ ነው ። ምንም እንኳን ይህ የሸቀጦች ልውውጥ የሚወስነው ሸቀጡን ለማምረት በወጣው ጊዜ ነው የሚለው ንድፈ ሐሳብ በነስር ዊሊየም ፔቲና ዴቪድ ሪካርዶ የተነደፈ ቢሆንም የሳይንሳዊ ሶሻሊዝም መሥራች የሆነው አብዮታዊ ምሁር ካርል ማርክስ በ19ኛው ምእተ ዓመት አጋማሽ ላይ ይህን ንድፈ ሐሳብ ከነበረበት ድክመት ሁሉ አጽድቶ እንደገና እስከነደፈው ድረስ በተለያዩ የእድገት ደረጃዎች ውስጥ ሲጓዝ ቆይቷል ። እኛም ይህን መለስ ብለን ለመቃኘት መሞከራችን ነጋድራስ ቀደም ሲል በጠቀስነው አባባላቸውም ሆነ በኋላ በምንጠቅሰው ውስጥ ያነሱዋቸው ነጥቦች በዚህ ንድፈ ሐሳብ እድገት ታሪክ ውስጥ ከየትኛው አካባቢ በምን ነጥብ ላይ እንደሚመሳሰሉና እንደሚለያዩ ለማመልከት ያህል ነው ። ለመጀመር ያህልም ነጋድራስ በግልጽ የዚህ ንድፈ ሐሳብ መሥራች ከሆነው ስርዊሊየም ፔቲ የሚለለዩበት ነጥብ አላቸው ። የእሴት መሠረት የፈሰሰ ጉልበት መሆኑን በግርድፉ እስካየን ድረስ ይህ ነጥብ ሲያመሳስላቸው አዳም ስሚዝና ዴቪድ ሪካርዶን ጨምሮ በዚህ ንድፈ ሐሳብ ላይ እሴትን በሚመለከት ፤ በኅብረተሰቡ ማኅበራዊ የሥራ ክፍፍል መኖርና ከልውውጥ መምጣት ጋር እሴት የሚከሰት በመሆኑ ታሪካዊ ፈርጅ ከመሆን ይልቅ እንደዘለ ዓለማዊ ፈርጅ እንደተመለከቱት ሁሉ ፤ ነጋድራስም ፤

«ሰውየው የዳኒን ፍሬና ሥጋውን ምንም ከሊላ ሰው ባይገዛው ሠርቶ ለፍቶ ነው እንጂ በከንቱ አላገኘውም ። ይህም ሥራው ዋጋው መሆኑ ነው ።»[26] ሲሉ ያስፈሩት ከክላሲካል ኢኮኖሚስቶች ጋር በቅርብ ያመሳስላቸዋል ።

ስር ዊሊየም ፔቲ

«አንድ ሰው አንድ ቡሼል (መስፈሪያ ነው) በቆሎ በለንደን ለማምረት በሚፈጅበት ጊዜ ልክ ከፔሩ አንድ ፓውንድ ብር ቢያመጣ አንድ የሊላው ተፈጥሮያዊ ዋጋነው ።»[27] ሲል

የሰነዘረ ቢሆንም ፤ ስለጊዜ ባጠቃላይ ከማንሳት በስተቀር ማኅበራዊ አስፈላጊ የሥራ ጊዜ መሆኑን ካለማሳየቱም በላይ በመርካንቲሊስቶች ተጽእኖ ሥር በመውደቅ ብርና ወርቅ በጊዜው እንደገንዘብ ሆነው የማገልገላቸውን ምክንያት በትክክል ስላልተረዳ እነዚህን ለማምረት የሚወጣው ጊዜ የተለየ ነው የሚል ስንኩል ምክንያት ነበረው ። በዚህ ረገድ ነጋድራስ የሰር ዊሊየም ፔቲን ኤኮኖሚያዊ ንድፈ ሐሳብ የሚያንጸባርቁ ያለመሆናቸው በግልጽ ይታያል ። ምክንያቱም እሴት የሥራ መለኪያ ነው ስለተባለ ማንኛውም ሥራ ተመጣጣኝ እንዳልሆነና የሥራው ዓይነት በዋጋው ደረጃ ላይ ለውጥ የሚያስከትል መሆኑን ፤ የሚለዋወጡ ሰዎች ለሥራቸው የሚጠቀሙበት እውቀት ተመጣጣኝ መሆን እንዳለበት ፤ እንደዚሁም ወርቅና ብር እንደገንዘብ ቢያገለግሉም እንደማንኛውም ሸቀጥ ሁሉ በተመሳሳይ ድካም (ሥራ) የሚመረቱ መሆናቸውን በማስቀመጣቸው ነው ። እነኝህ ከላይ የተጠቀሱትን ነጥቦች በቀጥታ ነጋድራስን እየጠቀስን ለማየት እንሞክራለን ። ማንኛውም ሥራ ተመጣጣኝ እንዳልሆነ ሲያሳዩ ፤

«ያናጢ ሥራ ከእንጨት ተሸካሚ ሥራ ይልቅ ይወደዳል ፤ እውቀት ከጉልበት ይከበራልና ከቤት ከዳኙ ሥራ ይልቅ የሣር አጫጁ ሥራ ይረክሳል ።»[28] ብለዋል ።

ስለማህበራዊ አስፈላጊ የሥራ ጊዜም ሲያነሱ ፤

«ዋጋ የሥራ መለኪያ ነው ስለተባለ አስቀድሞ ሁለት ነገር ያስፈልጋል ። አንዱ የሠሩትን ሥራ የሚለዋወጡ ሠራተኞች በየሥራቸው የሚሠሩበት እውቀት ሚዛኑ አንድ እንዲሆን ።»[29]

ሲሉ እንዲሁም ወርቅና ብር እንደማንኛውም ለኑሮ እንደሚያስፈልጉ ነገሮች ሁሉ በድካም የሚገኙ መሆናቸውን ሲያሳዩ ፤

«ብርና ወርቅ ምንም የለውጥ መሣሪያ ቢሆኑ እንደ ሌላው ለኑሮ የሚያስፈልገው ነገር ሁሉ ከመሬት የሚወጡት በድካም ነው»[30] ይላሉ ።

እንግዲህ በስነዘሩት የእሴት መለኪያ
ንድፈ ሐሳብ ውስጥ ያሉ የተለያዩ ነጥቦችን
ለማጤን ይቻለን ዘንድ ከስር ዊሊየም ፔቲ
ለማጤን ይቻለን ዘንድ ከስር ዊሊየም ፔቲ
ጋር በማነጻጸር ያላቸውን ልዩነት ለመመ
ልከት ሞክረናል ፡፡ ከላይ በጠቀስነው የነጋ
ድራስ ጽሑፍ ውስጥ የተሰነዘሩት ሐሳቦች ፤
ቀደም ሲል የተጠቀሰውን ንድፈ ሐሳብ
እስከ ተመለከተ ድረስ ባብዛኛው ካአዳም
ስሚዝና ዴቪድ ሪካርዶ ኤኮኖሚያዊ አስተ
ሳሰቦች ጋር የተመሳሰሉ ሲሆኑ ለብሔራዊ
ካፒታሊዝም እድገት የቆሙትን ነጋድራስ
ገ/ሕይወት ከቡርዧዋ ፖለቲካዊ ኤኮኖሚ
ዋና ዋና ምሁራን የሚለዩዋቸው አንዳንድ
ነጥቦችም አሉ ፡፡ እነዚህንም በግልጽ የሚለ
ዩባቸውን ነጥቦች ከማንሳታችን በፊት ሊለ
ዩባቸው የሚችሉ ዳሩ ግን ነጋድራስ በግልጽ
ያልዳሰሱዋቸው በመሆኑ ብቻ የልዩነት
ነጥቡን ለማውጣት አስቸጋሪ ከሆነበት
ቦታዎችም አንዱን ለመጥቀስ እንሞክራ
ለን ፡፡ ይኸውም አዳም ስሚዝ እሴት የሚወ
ስነው በወጣው ማህበራዊ አስፈላጊ የሥራ
ጊዜ ነው በሚለው ንድፈ ሐሳቡ ክልል
ውስጥ የቡርዧው ትርፍ ምንጭ ምን እን
ደሆነ ለማሳየት ባለመቻሉ ይህ ንድፈ ሐሳብ
በቅድመ ካፒታሊዝም ውስጥ ብቻ የሚሠራ
መሆኑን ሲገልጽ ፤ ዴቪድ ሪከርዶ ደግሞ
ጥናቱን በዚሁ ንድፈ ሐሳብ ላይ ብቻ እንዲ
ሞረኮዝ ቢያደርግም ከላይ አዳም ስሚዝ
መመለስ ያቃተውን ጥያቄ እርሱም መመ
ለስ አልቻለም ፡፡ ከዚህ አንጻር ምንም እንኳን
ነጋድራስ በዚያን ጊዜዋ ፊውዳል ኢትዮጵ
ያና በአውሮፓ የካፒታሊስት አገሮች መካ
ከል ያለውን የንግድ ግንኙነት በዚሁ ንድፈ
ሐሳብ ክልል ውስጥ ቢመረመሩም (ይህንን
ዴቪድ ሪካርዶም በአንጻራዊ ወጪ ወይም
በአንጻራዊ ኤኮኖሚ ጥቅም ንድፈ ሐሳቡ
ውስጥ አንስቶታል) ባንድ የካፒታሊስት
አገር ውስጥ ያለውን የልውውጥ ሁኔታ
መሠረት በማድረግ በቀጥታ በማምረት
ተግባር የማይሳተፈው ቡርዧ ትርፍ ምንጭ
ምን እንደሆነ ባለማንሳታቸው በዚህ ረገድ
ልዩነት መኖር አለመኖሩ በግልጽ አይታ
ይም ፡፡ በግልጽ ያላቸው ልዩነትና ለነጋድራስ
የኤኮኖሚያዊ አስተሳሰባቸው (Originality)
የሚሰጠው ወይም በወቅቱ ከኢትዮጵያ
ሁኔታ ጋር ለማዛመድ የግል አስተዋጽኦ
አድርጓል እንድል የሚያስችሉኝ ባብዛኛው
ኤኮኖሚያዊ ንድፈ ሐሳባቸው ከላሲካል
ፖለቲካዊ ኤኮኖሚ በተለይም ከአዳም
ስሚዝና ዴቪድ ሪካርዶ ጋር የተቀራረቡና
በዚሁ ኤኮኖሚያዊ የአስተሳሰብ ክልል
ውስጥ የሚመደቡ ሆኖ ሳለ ፤ በውጪ ንግድ
ረገድ ያላቸው አቋም ግን ጨርሶ የተለየ
መሆኑ ነው ፡፡ አዳም ስሚዝ «ሊዜፌር »
በተሰኘው ኤኮኖሚያዊ ፖሊሲው ከመርካን
ቲሊስቶች ፍጹም በተለየ መንገድ ለ«ነፃ»
የውጪ ንግድ ሲሟገት ፤ ዴቪድ ሪኮርዶም
ከአንጻራዊ ኤኮኖሚያዊ ጥቅም ንድፈ ሐሳቡ
በመነሳት በወቅቱ እንግሊዝ በኢንዱስትሪ
ከፍተኛ የእድገት ደረጃ ላይ የደረሰች መሆኗ
ከፍተኛ ጥቅም ስለሚሰጣት «ነፃ» የውጪ
ንግድ ፖሊሲ እንድትከተል ይሟገት ነበር ፡፡
ኢትዮጵያዊው ነጋድራስ ገብረሕይወት ግን
ይህንን በሚመለከት ረገድ ምንም እንኳን
ራሳቸው እንዳሉት አዲስ የተለየና ቀደም
ሲል ያልተሰነዘረ ሐሳብ አፈለቁ ባይባልም፣
ባብዛኛው ኤኮኖሚያዊ አስተሳሰባቸው ላይ
ተጽእኖ ከጣሉት ከነዴቪድ ሪካርዶ ነፃ
የውጪ ንግድ ፖሊሲ ይልቅ ከ14ኛው እስከ
17ኛው ክፍለ ዘመን ድረስ በኤኮኖሚ አስ
ተሳሰብ ረገድ ጐልቶ ከታየው የመርካንቲ
ሊስቶች የንግድ መከላከል ፖሊሲ (Prote-
ctionist Policy) ለኢትዮጵያ ይጠቅማል
በማለት ማስተጋባታቸው ነው ፡፡ ከዚህ
ንድፈ ሐሳብ ጋር በተያያዘ መንገድ አንድ
መነሳት ያለበት ሌላው ጉልህ ነጥብ ፤

«መሬት እኩል ሆኖ ለሰው ሁሉ እንዲከ
ፋፈል ፤ መሬት ግን በዘመናት ቁጥራቸው
በተወሰነ ሰዎች እጅ ተይዞ እንደሞኖፖሊ
ሆኗል - - -

— ባንድ አገር ውስጥ ያለው መሬት በጥ
ቂቶች ሰዎች እጅ ብቻ የሆነ እንደሆነ ለሕ
ዝቡ ትልቅ ጉዳት ይሆናል ፡፡»[31]

ሲሉ ምናልባትም «መሬት ላራሹ» የተሰ
ኘው ዲሞክራሲያዊ መፈክራችን የመጀመ
ሪያው አንጋቢ ኢትዮጵያዊ ናቸው ቢባል
ማጋነን አይሆንም ፡፡ ነጋድራስ ፤ ቀደም
ሲል እንደተጠቀሰው ፤ ለሰው ፍራቻ ሲባል
እውነት የመሰላቸውን መደበቅ የሚሹ ያለ
መሆናቸውን እንደገለጹት ሁሉ ትክክለኛ
መስሎ የታያቸውን በግልጽ ከማስቀመጥ
ወደኋላ የማይሉ ቁርጠኛ ታጋይ መሆናቸ
ውን ያሳዩበት አባባል ነው ፡፡ ነጋድራስ ቀጥ
ለው በዚህ በጠቀስነው የእሴት ጉልበት

INFINIX HOT 8 | 13MP
AI TRIPLE CAMERA

ንድፈ ሐሳብ ክልል (The Labour Theory of Value) ውስጥ ስለ ሀብት ምንነት ሲያስረዱ ፤

«ሀብትም ማለት የተከማቸ ሥራ እንደሆነ ለእንግዲሁ ተረድተነዋል» ካሉ በኋላ

እነሱም በዛም በድካም ያፈራናቸው ነገሮች ሁሉ ሀብት ሁነው ሳለ ባጠቃላይ ሰው ግን ሀብትን አንጻራዊ በሆነ መልኩ ብቻ በመመልከቱ ስለሀብት ትርጉም ትክክለኛ ግንዛቤ ሊኖረው እንዳልቻለ እንደሚከተለው አስረድተዋል ።

«ሰው ሁሉ ሊላውን ሰው ሀብታም ነው ሲል ግን ይህንን አያስብም ። በሰውም አፍ ሀብታም ነው መባል የሚገባው ያለው ገንዘቡ ሊላው ሰው ከያዘው ገንዘብ ይበልጣል እንደ መባል ያህል ነው ። ይህ ቃል ግን የሀብት ሙሉ ትርጉም አይደለም ። አንዱ ዓይነት ርግጠኛ ሀብት ይባላል ። ሁለተኛውም የብልጫ ሀብት ይባላል ።»[32]

ነጋድራስ ስለ ሀብት ምንነት ትንታኔያቸውን ካቀረቡ በኋላ ይበልጡኑ የሀብት መከማቸት የአንድ አገር እድገት መሠረት መሆኑን በማሳየት ምንም እንኳን ስለካፒታል አንስተው ባያወሩም ይበልጥ ከአዳም ስሚዝ ጋር የሚያቀራርባቸው ሁኔታ አለ ። ይኸው እምነታቸውን ከኢትዮጵያ ሁኔታ ጋር ሲያዛምዱት የሚያጋጥማቸው ነገር የተገላቢጦሽ መሆኑን በመገንዘብ በምሬት ሲያስረዱ ፤

«ባንድ አገር ውስጥ ነጋዴ ሲበዛ ፤ ሹምም ወታደርም ቀማኛም ይበዛል ። የፊት ፊቱም ሥራ በከንቱ እያለቀ በእንደዚህ ያለ አገር ውስጥ ሀብት አይከማችም ። ድህነትና ችጋር በሽታም ሞትም እጅ ለእጅ ተያይዘው ይገቡበታል ።»[33] ይላሉ ።

በዚህ አባባላቸው ነጋድራስ በቀጥታ በቁሳዊ ምርት መስክ በተሰለፉ አምራች ኃይሎችና በሌሎች መካከል ተገቢ መመጣጠን ያለመኖሩ ለአንድ አገር እድገት እንቅፋት መሆኑን ማሳየታቸው በመሆኑ በዚህም ረገድ ያላቸው አመለካከት አሁንም ከፍተኛ ጉልህነት ያለው ነው ። ይህንን ነጥባቸውን እስከተመለከተ ድረስም ይበልጡኑ ከአዳም ስሚዝ የገበዩት ለመሆኑ የሚከተለውን የአዳም ስሚዝን አባባል ማጤኑ በቂ ይሆናል

«አንድን ንጉሥ ከመላው ሠራዊቱ ፤ የሕግ ሰዎቹ ጋር ብንመለከተ አምራቾች አይደሉም እነርሱን ለማኖር የሚያስፈልገው ነገር የሚመጣው በምርት መስክ ከተሰለፉት በሚገኝ የተወሰነ የምርት ክፍል ነው ። በዚሁ ክልል ውስጥ እጅግ ጠቃሚና እምብዛም በማይጠቅም ሥራ ላይ የተሰለፉት እንደ ቤተክርስቲያን ሰዎች ፤ የሕግ ባለሙያተኞች ፤ ሐኪሞች በማንኛውም የፅሕፈት ሥራ የተሰማሩ ሰዎች ዘፋኞችና ዳንኪረኞች ወዘተ --- ይመደባሉ ።»[34]

ይህንን የአዳም ስሚዝ አባባል ካርል ማርክስ ሲተች በጊዜው የነበረውን የወዝ አደሩንም ሆነ የቡርዧውን ጥቅም የሚያንጸባርቅ አባባል ነው ብሎታል ። ነጋድራስም በጊዜው በኢትዮጵያ የሚታየው ችግር የሐኪሞች ፤ በልዩ ልዩ የሥራ መስኮች የሰለጠኑ ኢትዮጵያውያን ያለመኖር መሆኑን መገንዘባቸው ፤ በአቀራረብ ረገድ ፤ ከላይ ከጠቀስነው የአዳም ስሚዝ አባባል ውስጥ ፊውዳሎችን የሚመለከተውን ክፍል ብቻ በመውሰድ ሌላውን ከመተዋቸው በስተቀር ምንም ልዩነት በመካከላቸው እንደሌለ እንመለከታለን ።

ነጋድራስ ቀጥለው በከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ አስተሳሰብ ጥልቀት የሚያወሱት በወቅቱ የነበረውን የኢትዮጵያን የንግድ ሚዛን የሚያሳይ ነቁጥ ወስደው ከመረመሩና የ-ዛባ አቋሙንና ምክንያቱን ካስረዱ በኋላ ፤

«እስቲ አሁን እኛ የኢትዮጵያ ሕዝብ አርነትን አለን ሊባል ነውን ፤ አርነት ያለው ሕዝብ ማለት እውነተኛ ትርጉሙ ለብቻው መንግሥት ያለው ሕዝብ ማለት ብቻ አይደለም ፤ ራሱንም የቻለ ሕዝብ ማለት ነው እንጂ ።»[35]

ወደሚል እጅግ ታሪካዊ ወደሆነው መደምደሚያ ያደረሳቸውን ትንተና ነው ። ይህንን ትንተናቸውንና ሌሎችንም ጠቃሚ የኤኮኖሚ አስተሳሰቦቻቸውን በሚቀጥለው የዚህ ጽሑፍ ሁለተኛ ክፍል እናቀርባለን ።

INFINIX HOT 8 | 13MP
AI TRIPLE CAMERA

የግርጌ ማስታወሻዎች

1 ጥጋቤ አስረስ ፤ የነጋድራስ ገ/ሕይወት ባይከዳኝ አጭር የሕይወት ታሪክ ፤ አዲስ አበባ ግንቦት 1963 (የሕይወት ታሪካቸውን የሚመለከተው በሙሉ የተገኘው ከዚሁ ጽሁፍ ነው)

2. Richard Greenfield, *ETHIOPIA*, 1965 p. 155

3. ገ/ሕይወት ባይከዳኝ ፤ «አጤ ምኒልክና ኢትዮጵያ» በብርሃን ይሁን ፤ አሥመራ ፤ የስዊድን ፕሮቴስታንት ሚሲዮን ማተሚያ ቤት ፤ 1915 ገጽ 353 - 4

4. ገ/ሕይወት ባይከዳኝ ፤ መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር ፤ አዲስ አበባ ሁለተኛ እትም ፤ ንግድ ማተሚያ ቤት ፤ 1953 ገጽ 11

5. በዚሁ መጽሐፍ ገጽ 12

6. ” ” ” 11

7. ” ” ” 11

8. ” ” ” 18

9. ” ” ” 11 - 12

10. ” ” ” 22

11. Quoted in ANIKIN, *Science in its Youth*, progress publishers, Moscow, 1975 p. 120

12. ከ«መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር» ገጽ31

13. ” ” ” 34

14. ” ” ” 33

15. ከ«አጤ ምኒልክና ኢትዮጵያ» ገጽ 343

16. ከ«መንግሥት የሕዝብ አስተዳደር» ” 32

17. ከ«አጤ ምኒልክና ኢትዮጵያ» ” 337

18. ” ” ” 338

19. ” ” ” 338

20. ከ«መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር» ”14

21. ከ«አጤ ምኒልና ኢትዮያ» ” 354

22. ከ«መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር»ገጽ 79

23. ” ” ” 34

24. ” ” ” 44

25. ” ” ” 46

26. ” ” ” 43

27. William petty, *The Economic Writings'* Vol I, Cambridge, 1899, p. 50

28. ከ«መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር»ገጽ 52

29. ” ” ” 54

30. ” ” ” 107

31. ” ” ” 107

32. ” ” ” 57

33. ” ” ” 66

34. A. Smith, *The wealth of Nations, Vol. I*, London, 1924, p. 295

35. ከ«መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር»ገጽ 79

Proudly brought to you by www.binyamhk.wordpress

INFINIX HOT 8 | 13MP
AI TRIPLE CAMERA

ARTISTIC PRINTING PRESS

ዋጋው ብር 1.25